# የአማራ ክልል የመረጃ መጽሐፍ

## የ2014 ዓ.ም ኅትመት



የመንግስት ኮሙዩኒኬሽን ቢሮ በሚዲያ ልማት
የፖሊስ ጥናትና አብዝሃነት ዳይሬክቶሬት
በመንግስት ፓሊሲ አፈፃፀም ትንተና ቡድን
የተዘጋጀ

መጋቢት 2015 ዓ.ም

**የአብክመ የመንግስት ኮሙዩኒኬሽን ቢሮ**

## የኢትዮጵያ ራዕይ

*በህዝብ ተሳትፎና በህዝቦች መፈቃቀድ ላይ የተመሠረተ ዴሞክራሲያዊ ስርዓትና መልካም አስተዳደር የሰፈነባት፣ ማህበራዊ ፍትህ የነገሠባትና ከድህነት ተላቃ መካከለኛ ገቢ ያላት ኢትዮጵያን እውን ማድረግ ነው!*

## የክልሉ ራዕይ

*አስተማማኝ ሠላም፣ ዴሞክራሲና መልካም አስተዳደር የሠፈነበት፣ ማህበራዊ ፍትህ የነገሰበት፣ ከድህነት የተላቀቀና መካከለኛ ገቢ ያለው ክልል እውን ሆኖ ማየት!*

## የ ቢሮው ራዕይ

*በመረጃ የበለፀገ፣ ሁለገብ ተሳትፎ የሚያደርግ፣ በመሠረታዊ ክልላዊና ሀገራዊ ጉዳዮች መግባባት የፈጠረ ህዝብ እውን ሆኖ ማየት!”*

የ2014 አመታዊ የመረጃ መጽሐፍ

የአብክመ የመንግስት ኮሙዩኒኬሽን ቢሮ

# የአማራ ክልል የመረጃ መጽሐፍ

## የ2014 ዓ.ም ህትመት

### በመንግስት ኮሙዩኒኬሽን ቢሮ በሚዲያ ልማት፣ የፖሊስ ጥናትና አብዝሃነት ዳይሬክቶሬት በመንግስት ፖሊሲ አፈጻፀም ትንተና ቡድን የተዘጋጀ

መጋቢት 2015 ዓ.ም

**የአብክመ የመንግስት ኮሙዩኒኬሽን ቢሮ**

የመጀመሪያው ህትመት "ብሔረ አማራ" በሚል መጠሪያ በ1995 ዓ.ም ተዘጋጀ፡፡ ከ2013 ዓ.ም ጀምሮ ደግሞ "የአማራ ክልል የመረጃ መጽሐፍ" በሚል ስያሜ መዘጋጀት ጀመረ፡፡

የአብክመ የመንግስት ኮሙዩኒኬሽን ቢሮ



ዶ/ር ይልቃል ከፋለ

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

ርዕሰ መስተዳደር

የ2014 አመታዊ የመረጃ መጽሐፍ

የአብክመ የመንግስት ኮሙዩኒኬሽን ቢሮ

# የክልል መስተዳድር ምክር ቤት ካቢኔ አባላት



ዶ/ር ይልቃል ከፋለ
ርዕሰ መስተዳድር



ዶ/ር ጌታቸው ጀምበር
ም/ርዕሰ መስተዳድር



ዶ/ር ሰማ ጥሩነህ
የሰላምና ደህንነት ቢሮ ሀላፊ



አቶ ግዛቸው ሙሉነህ
የመንግስት ኮሙኒኬሽን ቢሮ ሀላፊ



አቶ ቢያዝን እንኳሆነ
የቤቶችና መሰረተ ልማት ቢሮ ሀላፊ



ዶ/ር ሃይለማርያም ከፍያለው
የግብርና ቢሮ ሀላፊ



አቶ አብየ ካሳሁን
የጠቅላይ ፍርድቤት ቢሮ ሀላፊ



ዶ/ር ማማሩ አያሌው
ውሃና ኢነርጅ ቢሮ ሀላፊ



ዶ/ር ኢንጅነር ዳኝነት ፈንታ
የመስኖና ቆላማ አካባቢዎች ልማት ቢሮ ሀላፊ



አንሙት በለጠ
የፕላንና ልማት ቢሮ ኃላፊ



ወ/ሮ አስናቁ ድረስ
የሴቶች፣ ህፃናትና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ ኃላፊ



አቶ እርዚቅ ኢሳ
የወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ሀላፊ

**የአብክመ የመንግስት ኮሙዩኒኬሽን ቢሮ**



አቶ ሲሳይ ዳምጤ
የመሬት አስተዳደርና
አጠቃቀም ቢሮ ኃላፊ



አቶ ተስፋሁን አለምነህ
የአካባቢና ደን ጥበቃ
ባለስልጣን



ዶ/ር ማተቤ ታፈረ
የትምህርት ቢሮ ኃላፊ



ዶ/ር ጥላሁን ማህሪ
የገንዘብ ቢሮ ሀላፊ



አቶ ሙሀመድ ያሲን
የመንገድ ቢሮ ሀላፊ



ዶ/ር ፀጋ ጥበቡ
የገቢዎች ቢሮ ሀላፊ



ዶ/ር መልካሙ አብቴ
የጤና ጥበቃ ቢሮ ኃላፊ



አቶ ጣሂር ሙሀመድ
የባህልና ቱሪዝም ቢሮ ኃላፊ



አቶ ገረመው ገብረፃድቅ
የፍትህ ቢሮ ሀላፊ



አቶ አረጋ ከበደ
የስራና ስልጠና ቢሮ ኃላፊ



ወ/ሮ ባንችአምላክ ገ/ማርያም
የሲቪል ሰርቪስና የሰው ሐብት
ልማት ኮምሽነር



የአቶ ሀይሌ አበበ
ማዕድን ሀብት ቢሮ ሀላፊ



አቶ ቀለምወርቅ ምህረቴ
የንግድና ገበያ ልማት ቢሮ ሀላፊ



አቶ እንድሪስ አብዱ
የኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት
ቢሮ ሀላፊ

**የአብክመ የመንግስት ኮሙዩኒኬሽን ቢሮ**

## የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ብሔራዊ ዓርማ

<u>የዓርማው ትርጉም</u>

የስንዴ ዘለላ - የእርሻውን ክፍለ ኢኮኖሚ

ጊሩ - የኢንዱስትሪውን ክፍለ ኢኮኖሚ

እርግቧ - ሠላምን

ሚዛኑ - ፍትህና ዲሞክራሲን

የላሊበላና የፋሲል ግንብ - የክልሉን ታሪክ የቅርስ ሃብት

የጭስ ዓባይ ፏፏቴ - የክልሉን የተፈጥሮ ሃብት ያመላክታል፡፡

**የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የሕዝብ መዝሙር**

የታታሪ ሕዝቦች - - - የታሪክ ማህደር፣
የአኩሪ ባህል አምባ - - - የድንግል ሀብት አፈር፡፡
የሕዝቦችሽ ተስፋ - - - - ለሟ ክልላችን፣
በሠላም በፍትህ - - - በልማት ጉዟችን፣
ተባብረን በሥራ - - - እንገነባሻለን፡፡
የአማራነትን ክብር - - - ደማቅ አርማ ይዘን፣
ከሌሎች ሕዝቦች ጋር - - - እኩል ተከባብረን፣
በፍቅር በአንድነት - - - አብርን እንዘልቃለን፡፡

የ2014 አመታዊ የመረጃ መጽሐፍ

**የአብክመ የመንግስት ኮሙዩኒኬሽን ቢሮ**

**ማውጫ**

**ርዕሰ ጉዳይ** **ገጽ**

**የቢሮ ሀላፊ መልዕክት**

**I. የአማራ ክልል በጥቂቱ---------------------------------------------------1**

**II. ኢኮኖሚ ዘርፍ**

- ግብርና -----------------------------------------------------------5
- ከተሞችና መሰረተ ልማት ----------------------------------------------18
- እንስሳትና አሳ ሀብት ልማት --------------------------------------------35
- ግብርና ምርምር -----------------------------------------------------39
- ህብረት ስራ ማህበራት ማስፋፊያ--------------------------------------------45
- አደጋ መከላከልና ምግብ ዋስትና-----------------------------------------46
- ንግድና ገበያ ልማት -----------------------------------------------48
- የአካባቢና ደን ጥበቃ ልማት---------------------------------------------54
- ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ልማት ------------------------------------57
- ማዕድን ሀብት ልማት----------------------------------------------------63
- ገንዘብና ኢኮኖሚ---------------------------------------------------------66
- መንገድ ልማት------------------------------------------------------------69
- ውሀና ኢነርጅ -------------------------------------------------------------73
- ገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ----------------------------------------75
- ገቢ -------------------------------------------------------------------------78
- ስራና ስልጠና-------------------------------------------------------------81
- መስኖና ቆላማ አካባቢ ልማት-----------------------------------------------87
- የህዳሴ ግድብ ግንባታ----------------------------------------------------------92

ፕላንና ልማት----------------------------------------------------------94

**III. ማህበራዊ ዘርፍ**

- ትምህርትና ስልጠና-------------------------------------------------------98
- ወጣቶችና ስፖርት--------------------------------------------------------111
- ሴቶች፣ ህፃናትና ማህበራዊ ጉዳይ-------------------------------------------119

- ባህልና ቱሪዝም ----------------------------------------------------124
- ሲቪልሰርቪስና የሰው ሀብት አስተዳደር-------------------------------130
- ጤና--------------------------------------------------------------------133
- ሙያ ብቃት ምዘናና ማረጋገጫ ----------------------------------------138
- አማራ ክልል ህዝቦች ሰማዕታት መታሰቢያ ሀውልት ----------------143

IV. **መልካም አስተዳደር ዘርፍ**

- ርዕሰ መስተዳድር -----------------------------------------------------145
- አማራ ሚዲያ ኮርፖሬሽን ---------------------------------------------148
- ዋና ኦዲተር -----------------------------------------------------------153
- ክልል ምክር ቤት--------------------------------------------------------155
- ጠቅላይ ፍርድ ቤት --------------------------------------------------158
- ፍትህ ቢሮ --------------------------------------------------------------163
- የመንግስት ኮሙኒኬሽን------------------------------------------------168
- ስነ-ምግባርና ፀረ - ሙስና ---------------------------------------------174

V. **አጠቃላይ መረጃ**

- በክልል የሚገኙ ልዩ ልዩ መስሪያቤቶች አድራሻ----------------------177
- በክልሉ የሚገኙ የትምህርት፣ የጤና፣ የትምህርት መገናኛ፤ የግብርና ኮሌጆችና ማሰልጠኛ ተቋማት አድራሻ-------------------------------180
- በክልሉ የሚገኙ ዞኖች.................................................................183
- በክልሉ የሚገኙ ዋና ዋና ወንዞች፣ሐይቆችና ተራሮች ----------------184
- በክልሉ የሚገኙ ዋና ዋና የቱሪስት መስብህ ሀብቶች-------------------192
- ባለኮከብ ሆቴሎች----------------------------------------------------198
- በክልሉ የሚገኙ ዞኖችና ወረዳዎች -----------------------------------200

**የአብክመ የመንግስት ኮሙዩኒኬሽን ቢሮ**

## የቢሮ ሀላፊው መልዕክት



የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በአገራችን የፌደራል አወቃቀር ስርዓት ውስጥ የተደራጀ ብሔራዊ የአስተዳደር ክልል ሲሆን ሰላም፣ ዴሞክራሲ እና ልማት እንዲረጋገጥ የድርሻውን ለመወጣት ከፍተኛ ጥረት ሲያደርግ ቆይቷል፡፡

የክልላችን መንግስት በጥበብና አርቆ አስተዋይነት መፈታት ያለባቸው የከረሙ የህዝብ ጥያቄዎች እንዳሉ ይገነዘባል፡፡ በመሆኑም እንደ ሀገር እና እንደ ክልል መፈታት የሚገባቸውን ጥያቄዎች በመለየት ለመፍታት ሰፊ ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡

የአማራ ክልል ህዝብ ለሕግ የበላይነትና ሰላማዊ ግንኙነት መረጋገጥ ከፍተኛ እምነት ያለው ህዝብ በመሆኑ ይህን መልካም እሴት ማስቀጠል ይኖርብናል፡፡ እኩልነትን፣አንድነትን፣ሠላም እና ፍትህን ለማስከበር ሀብቱን ፣ጉልበቱንና ህይወቱን ለመስጠት አመንትቶ የማያውቀውን ሕዝባችንን በማደራጀት እና ከሌሎች ክልሎች ወንድምና እህት ህዝቦች ጋር ማሰናሰልን ያሻል፡፡

በአጥንትና በደማቸው በገነቧት ሀገራቸው ውስጥ በማንነታቸው ሣይገፉ፣በህግ-ወጦች ሳይንገላቱ፣በሀገራቸው በየትኛውም አካባቢ መብታቸው ተከብሮ፣በፍትህ፣ በእኩልነትና በሰላም የመኖር ሕገመንግስታዊ መብታቸው እንዲከበር ማድረግ ይጠበቅብናል፡፡
ላለፉት ግማሽ ምዕተ-ዓመታት አንዳንድ ጠባብ የፖለቲካ ቡድኖች እኩይ ዓላማቸውን ለማስፈፀም የአማራን ህዝብ በጥላቻ ትርዕክት ጨቋኝ እና ተስፋፊ ተደርጎ እንዲታይ በማድረግ ከቀየው እንዲፈናቀል ተደርጓል፡፡ አፈናና ግድያም ተፈፅሞበታል፡፡ ሀብትና ንብረቱንም እንዲያጣ ተደርጓል፡፡

ይህንን እኩይና ፖለቲካዊ ጠባብነት የወለደው የኋላ ቀር የጥፋት ዘመቻዎች በመቃወም፤በሰከነና አደጋን በሚቀንስ መንገድ ለመግታት ከፍተኛ መስዋትነት ተከፍሏል፣ አሁንም እየተከፈለ ይገኛል፡፡ የ60 ዓመታት ፖለቲካዊ አድሮ ቃሪያነት እየፈጠረው የሚገኘውን ችግር በዘላቂነት እንዲፈታ መንግስት በቁርጠኝነት እየሰራ ይገኛል፡፡
ይሁን እንጅ እነዚሁ ፖለቲካዊ አድሮ ቃሪያዎች ለዘመናት የተራጩትና የአማራን ህዝብ በተሣሣተ ትርዕክት በጥርጣሬና በጥላቻ እንዲታይ ያደረጉ ቡድኖችና አመለካከት በህዝብ የለውጥ ትግል ተገደው ወደ ዳር የተገፉ ቢሆንም ዛሬም ድረስ በህዝብ ውስጥ ተወሽቀው እርስ በእርስ ለማባላት ጥላቻን ሲፈለፍሉ ውለው የሚያድሩ ቆሞ ቀሮች በፖለቲካ ገበያው ውስጥ አልታጡም፡፡

**የአብክመ የመንግስት ኮሙዩኒኬሽን ቢሮ**

በተለይ ወጣቶችን በማህበራዊ ሚዲያ አማካይነት ስሜታቸውን በመኮርኮር የብሔር፣ የሐይማኖት ወዘተ ግጭት ውስጥ እንዲገቡ ለማድረግ እኩይ ሴራ ይሸርባሉ፡፡ ሐሰተኛ መረጃዎችን ፍብርኮ በመንዛት በህዝብ መካከል አለመተማመን፤ ጥርጣሬና ጥላቻን ለማንሰራፋት ይራወጣሉ፡፡

በመሆኑም ልማትን ለማፋጠንና ከድህነት ለመውጣት በምናደርገው ጥረት መሳ ለመሳ የፖለቲካ አድሮ ቃሪያዎችን የጥፋት ውጥን ለማምከን ህዝባችንን ማንቃት፤ ማደራጀት እና ማብቃት ይጠበቅብናል፡፡

በሁሉም የተግባቦት ዘዴዎች በምንሰራቸው የሚዲያና ኮሙዩኒኬሽን ስራዎች ሠላምን፤ ልማትን እና መልካም አስተዳደርን ማረጋገጥ አንገብጋቢ እና አጣዳፊ ስራችን ሊሆን ይገባል፣

በተለይ የሕዝብን እና የመንግስትን ስምና ዝና የሚያጠለሹ፤ ሀሰተኛና አፍራሽ የሆኑ ዘገባዎችን ለመመከት የክልላችንንና የሀገራችንን ገፅታ ለመግንባት እንዲቻል፤ የዲጂታል ሚዲያ አቅማችንን ማጠናከር፤ማዘመን በቀጣይ በልዩ ትኩረት የምንፈፅመው ተግባር ይሆናል፡፡

ሎሎች የሚዲያና ተግባቦት ስራ አማራጭ ዘዴዎችንም ሃላፊነትና ተጠያቂነትን ባሰፈነ አግባብ በመጠቀም ፈጣን፤ ትክክለኛ እና ገንቢ መረጃዎችን ተደራሽ የማድረጉ ጉዳይ ከተቋማዊ ስራዎቻችን መካከል አንኳር ተግባራቶቻችን ሆነው ይቀጥላሉ፡፡

በመሆኑም መንግስት በመልካም አስተዳደርና በልማት በየዓመቱ ያከናወናቸውን ዋናዋና ተግባራት የህትመት ውጤቶችን በመጠቀም ወቅታዊ መረጃዎችን በማድረስ ህብረተሰቡ የበኩሉን እንዲወጣ ለማስቻል ስናደርጋቸው የነበሩት ተጋድሎዎች ከተለምነው ከፍታ ላይ እስከንደርስ ድረስ በአዲስ መንፈስና በሩቅ ዓላሚ ልቦና አጠናክረን በማከናወን ወደ ስኬት የምናደርገው ግስጋሴ ይቀጥላል፡፡

ይህ ዓመታዊ የመረጃ መፀሕፍም የተዘጋጀው ይህንኑ ታሳቢ በማድረግ በመሆኑ በየደረጃው የሚገኙ የተቋማችን ቤተሰቦችም ይህንኑ መንፈስ በመውረስ ለቀጣይ የለውጥና የእድገት ጉዟአችን በአንድነት ተደጋግፈን የድርሻችንን ለማበርከት ቃላችንን ልናድስ ይገባል እላለሁ፡፡

"ሠላም ለሁላችን ይሁን"!!!

ግዛቸው ሙሉነህ አበበ
Gizachew Muluneh Abebe
ቢሮ ኃላፊ

**የአብክመ የመንግስት ኮሙዩኒኬሽን ቢሮ**

## I. የአማራ ክልል በጥቂቱ

የክልሉ ግብርና ቢሮ መረጃ እንደሚያሳየው የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ከ9-14 ዲግሪ ሰሜን ኬክሮስና ከ36-40 ዲግሪ ምስራቅ ኬንትሮስ ሃሳባዊ መስመሮች መካከል የሚገኝ ሲሆን 161 ሺህ 828.4 ካሬ ኪሎ ሜትር ስፋት አለው፡፡ ክልሉ ከጠቅላላው የአገሪቱ የቆዳ ስፋት 15 በመቶ የሚሆነውን ይሸፍናል፡፡ ክልሉ በሰሜን ከትግራይ፣ በምስራቅ ከአፋር፣ በደቡብ ከኦሮሚያ፣ በምዕራብ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልልና ከሱዳን ጋር ይዋሰናል፡፡

በአገራችን በከፍታው የሚታወቀውና 4,620 ሜትር ከፍታ ያለው የራስ ደጀን ተራራ የሚገኘው በዚሁ ክልል ሲሆን ለተለያዩ ተግባራት ሊውሉ የሚችሉ የበርካታ ወንዞች (አባይ፣ ተከዜ፣ አንገረብ፣ መገጭ) እና ሐይቆችም (የጣና፣ የዘንገና፣ የሎጎና፣ የአርዲቦ ...) ባለቤት ነው፡፡ የክልሉ የአየር ንብረት 2.35 በመቶ ውርጭ፣ 24.15 በመቶ ደጋ፣ 46.61 በመቶ ወይና ደጋና 26.71 በመቶ ቆላ ነው፡፡ ዓመታዊ የዝናብ መጠኑ ከ598.3-1,692 ሚሊ ሜትር ሲሆን በዓመት በአማካይ ከ12.4-27.8 ዲግሪ ሴንቲ ግሬድ የሙቀት መጠን አለው፡፡

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ገንዘብ ቢሮ የስነ-ህዝብ መረጃዎች እንደሚያመላክቱት የክልሉ የህዝብ ብዛት ከ1999 የህዝብ ቆጠራ በመነሳትና በየዓመቱ በአማካይ የሚጨምረውን የ1.7 በመቶ የህዝብ ዕድገት ምጣኔ መነሻ በማድረግ በ2014 ዓ.ም. የተተነበ የህዝብ ብዛት 22,876,998 ነው፡፡ ይህም በፆታ ሲተነተን 11,400,762 ወንድና 11,476,236 ሴት እንደሆነ ያመላክታል፡፡ የህዝብ ቁጥሩ በአዲስ ተቆጥሮ ያልተረጋገጠ በመሆኑ ከትግራይ ክልል ወደ አማራ ክልል የተመለሱ ወልቃይት ጠገዴ ሴቲት ሁመራና የህዝብ ቁጥር አይጨምርም፡፡

ክልሉ ከአማራ ብሄር በተጨማሪ የአዊ፣ የኦሮሞ፣ የዋግ ኽምራ፣ የአርጎባና የቅማንት ብሄረሰቦች ይኖሩበታል፡፡ በ13 ዞን አስተዳደሮች (ሶስቱ የብሄረሰብ አስተዳደሮች እንዲሁ ከትግራይ ወደ አማራ ክልል የተመለሱ ወልቃይት ጠገዴ ሰቲት ሁመራ ዞኖች ናቸው) እንዲሁም በ8 ሪጆኦ ፖሊታን ከተሞች፣ በ77 የከተማ አስተዳደሮች፣ በ126 መሪ ማዘጋጃ ቤቶች በ99 ንዑስ ማዘጋጃ ቤቶች በ 379 ታዳጊ ከተሞች በአጠቃላይ በ689 ከተሞች የተዋቀረ ነው፡፡

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት አመሰራረት ፓርላሜንታዊ ነው፡፡ በአሁኑ ወቅት ክልል ምክር ቤቱ 294 መቀመጫ ወንበሮች ያሉት ሲሆን በተለያዩ ምክንያቶች በተወሰኑ የምርጫ ክልሎች የምክርቤት አባላት ያልተመረጡ በመሆኑ የምክርቤት አባላት ብዛት 256 ሲሆን ከፆታ አንፃር 163 ወንድና 93 ሴት የምክር ቤት አባላት አሉት፡፡ የምክር ቤቱ አባላት የብልፅግና እና የአብን ተወካዮች ናቸው፡፡

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የክልሉን አኩሪ ባህል ጠብቆ በማቆየት፣ የዱር እንስሳት ሀብት እንዲጠበቁና ለትውልድ እንዲተላለፉ የማድረግ ሚናውን እየተጫወተ ይገኛል፡፡

እንዲሁም ለባለሀብቶችና የቱሪስት አገልግሎት ሰጭ ተቋማት ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ሰላማዊ ስርዓት በማስፈን ፈጣን ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ለማምጣት የሚደረገውን ጥረት በዋናነት እንዲያግዝ የማድረግ አላማ ይዞ እየሠራ ይገኛል፡፡

ለክልላችን ኢኮኖሚ ማደግ አስተዋጽኦ የሚያደርጉና የቱሪስትን ቀልብ ከሚያማልሉ የመስህብ ሀብቶች መካከል በዓለም አቀፍ ደረጃ እውቅና ካላቸው ኪነ-ህንፃዎች፣ ብርቅየ የዱር አራዊ ቶች፣ ታሪካዊ ቦታዎች፣ ልዩ ልዩ ድንቃ ድንቅ ቅርሶች፣ የአባይ ምንጭ ፏፏቴ፣ አስገራሚ ዋሻዎችና ፓርኮች እንዲሁም የጣና ደሴቶችና ገዳማት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ በሀገራችን በዩኔስኮ ከተመዘገቡት የዓለም ቅርሶች መካከል አራቱ በአማራ ክልል ይገኛሉ፡፡ የክልሉ ርዕሰ መዲና ባሕር ዳር ናት፡፡

የባሕር ዳር ከተማ ከተቆረቆረች ረጅም የሚባል ዘመን ብታስቆጥርም በፈጣን የዕድገት ጐዳና ላይ ትገኛለች፡፡ የከተማዋ ነዋሪ ከመንግስት የከተሞች ልማት ፖሊሲ ጋር በመተዋወቅና ልማ ታዊ አስተሳሰብን እያዳበረ በመምጣቱ በባሕር ዳር ከተማ አስገራሚ ፈጣንና ሁለንተናዊ ለውጥ እየተመዘገበ ይገኛል፡፡

በከፊል በጣና ሃይቅ የተከበበችው እና የአባይ ወንዝ አካሎ የሚያልፋት ባሕር ዳር በተፈጥሮ ሃብት የታደለችና የቱሪስቶች መናኸሪያ ከተማ ከመሆኗም በላይ ለንግድ አገልግሎት፣ ለባለ ኮከብ ሆቴሎች መገኛ እና ለተለያዩ አገልግሎት የሚውሉ የኢንቨስትመንት አማራጮች እየተስፋፉ የሚገኙባት ከተማ ሆናለች፡፡

በአማራ ክልል ባሉ ከተሞች ደረጃቸውን የጠበቁ ከ100 በላይ ቱሪስት መጥን ሆቴሎች ሲኖሩ በዋና ከተማዋ በባሕር ዳር ከ23 በላይ ደረጃቸውን የጠበቁ ሆቴሎች ወደ ከተማዋ ለሚገቡ እንግዶች አስፈላጊውን መስተንግዶ በመስጠት ይታወቃሉ፡፡

የአማራ ክልል በአገር ውስጥና በውጭ የሚኖሩ ባለሃብቶችን እንደ ልማት ፍላጐታቸው ማስተናገድ የሚያስችሉ የተለያዩ የኢንቨስትመንት አማራጮችን አቅፎ የያዘና ባለሃብቶች በመረጡት ዘርፍ ቢሠማሩ ትርፋማ ሊሆኑ እንደሚችሉ የሚጠቁሙ መረጃዎችን ለይቶ አደራጅቷል፡፡በዚህ መሠረት ባለሀብቶች ሊሠማሩበት በሚፈልጉት የኢንቨስትመንት መስክ አንፃር መረጃዎችን አገናዝበው መጠቀም እንዲችሉ የተመቸ ዕድል ፈጥሯል፡፡

ክልሉ ለአዝርዕት ተስማሚ የሆነ መሬት፣ የአየር ንብረትና እምቅ የውሃ ሀብት አለው፡፡ ይህም በዝናብም ሆነ በመስኖ የብዕር፣ የጥራጥሬና የቅባት እህሎችን፣ የአትክልትና ፍራፍሬ ሰብሎችን በስፋት ለማልማት ምቹ አድርጐታል፡፡ በክልሉ ከፍተኛ ቁጥር ያለው የእንስሳት ሃብት እንዳለ ቢታወቅም የዘርፉ ልማት የሚካሄደው በተለመደው ኋላቀር አያያዝና የአረባብ ዘዴ በመሆኑ

ሊገኝ የሚገባውን የምርት መጠንና ጥቅም ማግኘት ሳይቻል ቆይቷል፡፡ በመሆኑም የግል ባለሃብቶች በመስኩ በመሰማራት በዘመናዊ መልክ በመጠቀም በእንስሳት እርባታ እና በማድለብ፣ በመኖ ልማት፣ በእንስሳት ተዋፅኦ ገበያ ልማትና የእንስሳት ጤና ጥበቃ አገልግሎት ሊሳተፉ የሚችሉባቸው ዕድሎች ናቸው፡፡

በክልሉ ሰፊ የዓሣ ሀብት ይገኛል፡፡ከጣና ሐይቅ ብቻ በዓመት 15 ሺህ ቶን ዓሳ ማምረት ይቻላል፡፡ በተለይም ከሐይቆች ጣና፣ ሎጐና አርዲቦ፣ ከወንዞች አባይ፣ ተከዜና አንገረብ አስተማማኝ የዓሳ ሃብት ምንጮች መሆናቸውን ጥናቶች ያመለከታሉ፡፡ ባለሃብቶች በዚህ ዘርፍ ቢሰማሩ የዓሳ ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪ በማቋቋም ምርቱን ለሀገር ውስጥና ለውጭ ሀገር ገበያ በማቅረብ፣ እንዲሁም ተረፈ ምርቱን ለእንስሳት መኖ በማቀነባበር ያለውን የሃብት ክምችት ጥቅም ላይ ለማዋል ከማስቻሉም በላይ በከፍተኛ ደረጃ ተጠቃሚ እንደሚያደርግ ይታመናል፡፡

ከክልሉ የተፈጥሮ ደን ውስጥ ሙጫና የዕጣን ዛፍ ይገኙበታል፡፡ ይህን ሃብት ለማልማት 604,382 ሄክታር የሚሸፍን መሬት እንደሚኖር ጥናቶች ይጠቁማሉ፡፡ ይሁን እንጂ እስከ አሁን ይህ ዘርፍ በአግባቡ ጥቅም ላይ ያልዋለ የኢንቨስትመንት መስክ ነው፡፡ በክልሉ የዕጣን ሀብት በስፋት የሚገኙባቸው ቆላማ ቦታዎች አዲአርቃይ፣ ታች አርማጭሆ፣ መተማ፣ ደራ፣ ደብረ ኤልያስ፣ ባሶሊበን፣ ዳንግላና ጓንጓ ሲሆኑ በአጠቃላይ በ9 ዞኖች በሚገኙ 39 ወረዳዎች

በዓመት 200 ሺህ ቶን ዕጣንና የዱር ሙጫ ማምረት ይቻላል፡፡ ይህም በርካታ ባለሃብቶችን ሊያሳትፍ የሚችል አቅም ያለው መሆኑን ያመላክታል፡፡

በክልሉ ያለው የጤናና የትምህርት ሽፋን እየተሻሻለ የመጣ ቢሆንም ክልሉ ካለው የህዝብ ቁጥር አንፃር ሲታይ ገና ብዙ መሠራት እንዳለበት ያመለክታል፡፡ ስለሆነም ባለሃብቶች የሚታየውን የጤናና የትምህርት ሽፋን ለማሳደግ ጉልህ ድርሻ እንደሚኖራቸው ይታመናል፡፡ በትምህርቱ ዘርፍ ከአፀደ ህፃናት እስከ ከፍተኛ ትምህርት፣ በጤና አገልግሎት ደግሞ ከክሊኒክ እስከ ሆስፒታል እንዲሁም የጤናና የቴክኒክ እና ሙያ ማሰልጠኛ ተቋማትን፣ የመድሃኒት ማምረቻና የጅምላ ማከፋፈያዎችን በመክፈት ሰፊ የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ ማካሄድና ተጠቃሚ መሆን ይቻላል፡፡

በአገራችን ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ዕድገት እያሳዩ ከመጡት የኢንቨስትመንት ዘርፎች አንዱ የግንባታ (ኮንስትራክሽን) ኢንዱስትሪ ነው፡፡ ለዚህ ዘርፍ መስፋፋት ምክንያቶች ደግሞ የኢንዱስትሪው ኢንቨስትመንት መጨመርና ለንግድ ሥራ የሚውሉ ግንባታዎች ማስፈለጋቸው ነው፡፡ የህዝብ ብዛት ፈጣን ዕድገት እያሳየ መምጣትና የመኖሪያ ቤት እጥረት ሰፊ በመሆኑ እንዲሁም የመሰረተ ልማት አውታሮች በከተሞች ብቻ ሳይወሰኑ ገጠሩንም ማካለላቸው ለዘርፉ አስፈላጊነት ምክንያቶች ሆነዋል፡፡ ስለዚህ ባለሃብቶች በዚህ መስክ የመኖሪያ ቤቶችን ለቢሮና

**የአብክመ የመንግስት ኮሙዩኒኬሽን ቢሮ**

ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚውሉ ህንፃዎችን ሰርተው ቢያከራዩና በተለያዩ የህንፃ ግንባታና የመንገድ ሥራዎች ላይ ቢሰማሩ ክልሉን ማልማት የሚችሉ ከመሆኑም በላይ አስተማማኝ የገቢ ምንጭ የሚያገኙበት ነው፡፡

ክልሉ ሰፊ የማዕድን ሐብት ባለቤት ነው፡፡ ይሁን እንጂ በአሁኑ ወቅት ያለው የማዕድን ልማት ተግባራዊ እንቅስቃሴ በአብዛኛው ለግንባታ አገልግሎት የሚውል ድንጋይ በማምረትና በመጠቀም ላይ ያተኮረ ነው፡፡ ይህም የሚያመለክተው ክልሉ ያለውን ያልተነካ የማዕድን ሀብት ጥቅም ላይ ለማዋልና ብሎም ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ለማምጣት የማዕድን ፍለጋና ማምረት የግል ባለሃብቶችን ተሳትፎ የሚጋብዝ መሆኑን ነው፡፡ ስለዚህ ባለሀብቶች የተለያዩ የሐይል ግብአቶችን በመጠቀም ለልማቱ አጋዥ መሆን ይችላሉ፡፡

ከዚህ ባሻገር የነፋስና የፀሐይ ሐይል በተለይ በገጠሩ አካባቢ ከፍተኛ አገልግሎት ሊሰጡ የሚችሉ የሐይል ምንጮች መሆናቸውን በመገንዘብ በዘመኑ ቴክኖሎጂ በመታገዝ ጥቅም ላይ ማዋል ይቻላል፡፡

የክልሉ መንግስት ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋት በሰጠው ልዩ ትኩረት መነሻነት የተለያዩ ርምጃዎችን ሲወስድ ቆይቷል፡፡ በፌዴራል መንግስት የተፈቀዱ የኢንቨስትመንት ማበረታቻ ዎችን በመተግበር ለባለሃብቱ ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር ተንቀሳቅሷል፤ ባለሃብቶችን ወደ ክልሉ ለመሳብና ለማበረታታት ለተመረጡ የከተማ ፕሮጀክቶች መሬት በአነስተኛ ክፍያ በማቅረብ ከመስራቱም በላይ ለአርሶ አደር የይዞታ መሬት ካሳ ከፍሎ ከሶስተኛ ወገን ነፃ በማድረግ ለአበባና አትክልት ልማት ኢንቨስትመንት መሬት በነፃ በማቅረብ እያበረታታ ይገኛል፡፡ በጣና ሀይቅ ዙሪያ ሊኖር የሚችለውን የልማት አማራጭ ለማወቅና ጥቅም ላይ እንዲውል ለማድረግ የጣና ሃይቅ አካባቢን በከፍተኛ ባለሙያዎች አስጠንቶ ያለውን ጥቅም የመለየት ስራ ተሰርቷል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም ክልሉ ከጐረቤት ሀገሮች ከሱዳንና ከጅቡቲ ጋር የሚያገናኙ ሀገር አቋራጭ መንገዶች፣ ዓለም-አቀፋዊና የሀገር ውስጥ በረራዎችን የሚያስተናግዱ የአውሮፕላን ማረፊ ያዎች እና የተለያዩ መሠረተ ልማቶች በስፋት የተዘረጉበት ክልል ነው፡፡

በመሆኑም አጋር አካላትና ባሃብቶች በክልሉ በሚገኙ የተለያዩ ዘርፎች ገብተው እንዲሳተፉ ክልሉ አስፈላጊውን ቅድመ ዝግጅት አሟልቶ እየጠበቀ ነው፡፡ ተሳታፊ እንድትሆኑ ጥሪውን ያስተላልፋል፡፡

# II. ኢኮኖሚ ዘርፍ

## ግብርና

የ2014 ዓ.ም የግብርና ልማት ስራችንን ስንጀምር የትግራይ ወራሪ ሃይል ጦርነት በመክፈት የግብርና ልማት ስራችንን በማውደምና በማስተጓጎሉ ምክንያት መገኘት የሚገባው ምርት ቀንሷል፡፡ጉዳቱን ለመቀልበስ የመልሶ ማቋቋም እቅድ በማቀድና ነጻ በወጡ አካባቢዎች ዘር በማቅረብ ወደ ስራ እንዲገቡ በማድረግ ጉዳቱን ሙሉ በሙሉ ባይሆንም መቀነስ ተችሏል፡፡በምርት ላይ የደረሰውን ጉዳት የሚያካክሱ የተለያዩ እቅዶችን በማቀድ በመስኖ አትክልትና ፍራፍሬ፣ በመኸር ሰብል ልማት፣ በተፈጥሮ ሀብት ልማትና የአረንጓዴ አሻራ ልማት ሥራዎችን ማከናወን ተችሏል፡፡

በ2013/2014 የምርት ዘመን የአርሶ አደሩን የቴክኖሎጅና የአዳዲስ አሰራሮችን እውቀትና ክህሎት በማሳደግ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የተለያዩ የግብርና ልማት ሠርቶ ማሳያዎችን በሰብል ልማት፤ በስርዓተ ምግብ፤ በመስኖ፤ በአትክልትና ፍራፍሬ ልማት፤ በተፈጥሮ ሀብት ልማት፤ በአርሶአደር ማሰልጠኛ ማዕከልና በሞዴል አርሶአደሮች ማሳ እንዲካሄድ ክትትል በማድረግ በ2014 ዓ.ም ከታቀደው 139,320 ሰርቶ ማሳያዎች ውስጥ 103,177 የተከናወነ ሲሆን አፈጻጸሙ ከአመቱ ዕቅድ አንጻር ሲታይ 74% ተሰርቷል።

የአርሶ አደሩን ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ ሙሉ ፓኬጅ መጠቀም የላቀ ሚና አለው፡፡በመሆኑም በበጀት አመቱ 2,113,243 አርሶ አደሮችን ሙሉ ፓኬጅ ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ 944,404(45%) ተከናውኗል። በምርት ዘመኑ 5,794,919 የሚሆኑ አርሶአደሮችን የኤክስቴንሽን ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ 5,858,260(101%) አርሶአደሮችን የኤክስቴንሽን ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡

በ2013/2014 ምርት ዘመን 4.5 ሚሊዮን ሄክታር መሬት በማልማት 131 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ለማምረት በተደረገው መሰረት **4,391,276 ሄክታር** መሬት በዘር በመሸፈን ማዕከላዊ ስታትስቲክስ መረጃ ባይደርስም እንደ ግብርና ቢሮ ትንበያ መሰረት 118,057,799 ኩንታል ምርት መሰብሰብ ተችሏል፡፡ የክልሉ ምርታማነትም ከነበረበት 24 ኩንታል በሄክታር 2.8 ኩንታል በሄክታር በመጨመር የክልሉን አጠቃላይ ምርታማነት 26.8 ኩንታል በሄክታር ማድረስ ተችሏል፡፡

### የመኸር የእርሻ ሥራ እንቅስቃሴ

በ2014/2015 ምርት ዘመን የመኸር እርሻ ስራ እንቅስቃሴ በተመለከተ የዝናቡ ሁኔታ የዘገየ

በመሆኑና ለእርሻ ስራ አመች ሁኔታን ባለመፈጠሩ ክንውኑ በጣም ዝቅተኛ ነው፤በመሆኑም 1ኛ እርሻ 4,032,548 ሄክታር (የእቅዱን 83%)፤2ኛ እርሻ 3,246,316 ሄክታር፤3ኛ እርሻ 1,941,980 ሄክታር፤4ኛ እርሻ 503,790 ሄክታር የእርሻ ድግግሞሹን ጠብቆ ታርሷል፡፡ ከባለፈው ተመሳሳይ ወቅት ከታረሰው 3,964,141 ሄክታር መሬት ጋር ሲነጻጸር የምርት ዘመኑ የእርሻ ስራ በ68,407 ሄክታር ብልጫ አለው፡፡

## ማሳን በትራክተር ማረስ

የምርት ዘመኑን የመኽር እርሻ አርሶ አደሩ ያለውን ጉልበት ተጠቅሞ ከማረስ በተጨማሪ ትራክተር ያላቸው በትራክተር፤ትራክተር የሌላቸው በአካባቢው የትራክተር ባለቤት ከሆኑት ጋር ተመጣጣኝ ክፍያ በመክፈል እርሻን የማሳረስ ተግባር በምርት ዘመኑ 762,958 ሄክታር በትራክተር ለማረስ ታቅዶ 219,484 ሄክታር ከእቅዱ 28.77% በ 747 ትራክተር በመጠቀም ታርሷል፡፡ይህ አፈጻጸም በተመሳሳይ ወቅት በትራክተር ከታረሰው ከ141,432 ሄክታር ጋር ሲነጻጸር የዚህ ዓመቱ በ78,052 ሄክታር ብልጫ አለው፡፡



ማሳን በትራክተር ማረስ-ጃቢ ጣህናን ወረዳ

## የዘር ስራ አፈጻጸም

በግንቦትና በሰኔ ወር በአብዛኛዎች የክልሉ ዞኖች የጣለው ዝናብ ከሚጠበቀው በታች በመሆኑ ቀድመው በሚዘሩ ሰብሎች በዘር ወቅት ላይ ተጽኖ ቢያሳድርም እንደ አካባቢው ሁኔታ የነበረውን እርጥበት በመጠቀም 1,470,960 ሄክታር የእቅዱን 30.2% በዘር መሸፈን ተችሏል፡፡



የዘር ስራ-ጃቢጣህናን ወረዳ

## ሰብል በመስመር መዝራት

በምርት ዘመኑ ይለማል ተብል በእቅድ ከተያዘው መሬት ውስጥ 62.2% ወይም 2,605,245 ሄክታር የሚሆነውን በመስመር ለመዝራት ታቅዶ 589,728 ሄክታር ከእቅዱ 22.63% የሚሆነው በመስመር የተዘራ ሲሆን ይህ አፈጻጸም ከአለፈው አመት ተመሳሳይ ወቅት በመስመር ከተዘራው 739,933 ሄክታር ጋር ሲነጻጸር በ515,131 ሄክታር ያንሳል፡፡በመሆኑም በቀጣይ በጀት አመት አርሶ አደሩ በመስመር እንዲዘራ ሁሉም መረባረብ አለበት፡፡

## የበልግ እርሻ እንቅስቃሴ

በ2014 በጀት ዓመት በክልሉ በልግ አብቃይ በሆኑ አካባቢዎች (ሰ/ሸዋ፣ ደ/ወሎ፣ ሰ/ወሎ፣ ኦሮሞ ብሄረሰብ ዞንና ደሴ ከተማ) 218,420 ሄክታር በማልማት 4,007,990 ኩንታል ምርት ለማምረት ታቅዶ የዝናቡ ሁኔታ የተቆራረጠ በመሆኑ እና ለእርሻ ስራ አመች ያልሆነ በመሆኑ 208,772 ሄክታር (95.6%) ታርሶ 136,541 ሄክታር (62.55%) በተለያዩ ሰብሎች በዘር መሸፈን ተችሏል፡፡

## የከሞዲቲ ሰብሎች

በአጠቃላይ በክልሉ ከሚለማው ሰብል ውስጥ በተመረጡ የኮሞዲቲ ሰብሎች (በቆሎ፣ ማሽላ፣ ስንዴ፣ ጤፍ፣ ቢራ ገብስ፤ ሩዝ፣ ሽንብራ፣ ቦሎቄ፣ ሰሊጥ፣ ማሾ፣ አኩሪ አተር እና የፈረንጅ ሱፍ) 353 ወረዳ፤ 3857 ቀበሌ፤ 42116 አርሶ አደሮችን በማደራጀት ከጠቅላላው መሬት 33% የሚሆነውን 1,607,576 ሄክታር መሬት በማልማት 66,282,805 ኩንታል ምርት በማምረት አማካይ ምርታማነትን 41.2 ኩንታል በሄክታር ለማድረስ የታቀደ ሲሆን የተለየ ማሳ **1,428,097 ሄክታር** የእቅዱን 88.84% የተለየ ወረዳ 176 የእቅዱን 49.85%፣ የተለየ ቀበሌ 2,057 የእቅዱን 53.33%፣ የተደራጀ ክላስተር 37,152 የእቅዱን 88.1% እና የተዘራ ማሳ 444,869

ሄክታር የእቅዱን 27.67% ነው፡፡



አመራሩ የጤፍ ሰብል ሲጎበኙ-ምስራቅ ጎጃም ዞን

## የአሲዳማ አፈር ልማት

በ2014/15 ምርት ዘመን የአሲዳማ አፈር ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ 200,000 ኩንታል በመጠቀም 10,000 ሄክታር ለማልማት በተያዘው እቅድ መሰረት በእቅድ የተይዘው ኖራ ለአርሶ አደሩ ለማቅረብ ስራ የተሰራ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪ ኖራ የሚጠቀመውን አርሶ አደር ለመለየት 78,500 የአፈር ናሙና በ16,500 ሄክታር መሬት ላይ ለመሰብሰብ ታቅዶ በ17,209 ሄክታር (104.29%) 58,086 (73.99%) ናሙና ተሰብስቧል፡፡ ከተሰበሰበው ናሙና ውስጥ 56,192 ናሙና ወደ ለላቦራቶሪ ምርመራ ተልኮ የ51,473 ናሙና ውጤት ለወረዳዎች የተላከ ሲሆን ውጤቱን መሰረት በማድረግ 36,663 ኩንታል ኖራ የከረመና በአዲስ ቀርቦ ከዚህ ውስጥ 28,169 ኩንታል ለወረዳዎች ቀርቦ 31,627 ኩንታል ከእቅዱ 9.11% ጥቅም ላይ ውሏል በዚህም 1,321 ሄክታር መሬት በኖራ ማከም ተችሏል፡፡

## ኮምፖስት ዝግጅት

በምርት ዘመኑ ያለውን የማዳበሪያ እጥረት ለመቋቋም በበጀት አመቱ (ከሃምሌ 1/2013 ዓ/ም ጀምሮ) ለማዘጋጀት ከታቀደው 55 ሚሊዮን ሜትር ኩዩብ በተጨማሪ 16,696,366 ሜትር ኩዩብ ከእቅዱ በመጨመር 71,696,368 ሜትር ኩብ እንዲታቀድ በተያዘው መሰረት 37,950,196 ሜትር ኩብ ከእቅዱ 53% ኮምፖስት በማዘጋጀት ጥቅም ላይ እንዲውል ተደርጓል፡፡የቨርሚ ኮምፖስት ዝግጅትና አጠቃቀም በበጀት አመቱ (ከሃምሌ1/2013 ዓ/ም ጀምሮ) ለማዘጋጀት ከታቀደው 279,050 ኩንታል 60,632 ኩንታል የቨርሚን ኮምፖስት

የተዘጋጀ ሲሆን አፈጻጸሙ ከዓመቱ 22% ነው፡፡ በተመሳሳይ **ባዮስለሪ ኮምፖስት ዝግጅት** (ከሃምሌ 1/2013 ዓ/ም ጀምሮ) ለማዘጋጀት ከታቀደው 100,000 ሜትር ኩዩብ ውስጥ 62,815 ሜትር ኩብ ባዮስለሪ ኮምፖስት የተዘጋጀ ሲሆን የእቅዱን 63% ተፈፅሟል፡፡



አመራሩ በአርሶ አደር የተዘጋጀ ኮምፖስትን ሲጎበኙ-ሰከላ ወረዳ

## የተፈጥሮ ፈሳሽ ማዳበሪያ አቅርቦትና ስርጭት

በምርት ዘመኑ የተከሰተውን የማዳበሪያ የአቅርቦት ችግር ለመቀነስ የተፈጥሮ ማዳበሪያን መጠቀሙ አንዱና ዋነኛው መንገድ በመሆኑ ከዚህ ውስጥም ገበያ ላይ ያለውን ፈሳሽ ማዳበሪያ በአርሶ አደሩ ፍላጎት ለመጠቀም በተሰራው ስራ ከ16 ሚሊዮን ሊትር በላይ የተሰበሰበ ቢሆንም 2,268,939 ሊትር ቀርቦ 778,192 ሊትር የተሰራጨ ሲሆን አፈጻጸሙም ከቀረበው 34.3**% ብቻ** ነው**፡፡**

## የዘር ብዜት የፊዚካል ስራዎች አፈጻጸም

በ2013/14 ምርት ዘመን በመኸር ወቅት 21,116 ሄክታር መሬት ላይ በተለያዩ ዘር አባዥ ድርጅቶች (በአማራ ምርጥ ዘር ኢንተርኘራይዝ፣ በኢትዮጵያ ግብርና ስራዎች ኮርፖሬሽን፣ በግል ዘር አባዥ ድርጅቶችና ዩኒዬኖች እንዲሁም በተለያዩ የሰብል ዝርያዎች ቅድመ መስራች፣ መስራችና የተመሠከረለት ዘር ለማባዛት ታቅዶ በዘር የተሸፈነው ማሣ 10,725 ሄክታር /50.8%/ ነው፡፡ ከዚህም ሊሰበሰብ ይችላል ተብሎ ከተገመተው 248,**421** ኩንታል ውስጥ 212,**695** ኩንታል (85.6**%**) ዘር ማሰባሰብ ተችሏል፤ከዚህ በተጨማሪ በመስኖ 10,028 ኩንታል ዘር ማሰባሰብ ተችሏል፡፡

## የሰብል ጥበቃ ስራ

በ2014/2015 ምርት ዘመን መደበኛ ተባዮች አሰሳና መከላከል ተግባራት በተመለከተ 4,856,221 ሄክታር መሬት አሰሳና መከላከል ስራ ለመስራት ታቅዶ 60,915 ሄክታር የአሰሳ ተግባር የተከናወነ ሲሆን የተለያዩ ነፍሳት ተባይ የተከሰተበት 44 ሄክታር ሲሆን በባህላዊ ዘዴ በ10 ሄክታር መሬት ላይ የመከላከል ስራ ተሰርቷል፡፡ በ2014/2015 ምርት ዘመን የእጽዋት በሽታ አሰሳና መከላከል ተግባራት በተመለከተ 4,856,221 ሄክታር መሬት አሰሳና መከላከል ሥራ ለመስራት ታቅዶ የተሠራ ስራ የለም፡፡ በመሆኑም በቀጣይ በጀት አመት ስራውን ትኩረት ሰጥቶ መስራት አስፈላጊ ነው፡፡

በ2014/2015 ምርት ዘመን የመደበኛ አረም አሰሳና መከላከል ተግባራት 4,856,221 ሄክታር መሬት አሰሳና የመከላከል ስራ ለመስራት ታቅዶ በበጀት አመቱ መጨረሻ 1ኛ አረም 16,647 ሄክታር ማሳና 2ኛ አረም 1,935 ሄክታር ማሳ ተከናውኗል፡፡ ከአለፈው ዓመት ተመሰሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር 1ኛ አረም በ7.8% ያንሳል፣ 2ኛ አረም በ71% ብልጫ ያሳያል እንዲሁም 13,322 ሄክታር 25,251 ሊትር ኬሚካል በመጠቀም የመከላከል ስራ ተሰርቷል፡፡

በ2013/2014 ምርት ዘመን የአደገኛና መጤ አረም አሰሳና መከላከል ተግባራት 380,864 ሄክታር መሬት አሰሳና መከላከል ሥራ ለመስራት ታቅዶ 64,044 ሄክታር መሬት በማሰስ 61,547 ሄክታር ማሳ የአደገኛና መጤ አረም ማስወገድ ተችሏል፡፡ ለዚህ ተግባርም ወንድ129,619፣ ሴት 16,701 በድምሩ 146,320 አርሶ አደሮችን ማሳተፍ ተችሏል፡፡

በምርት ዘመኑ በአዊ ብሄረሰብ አስተዳደር ዞን በ5 ወረዳዎች በ25 ቀበሌዎች በሰብል ላይ 1,650.5 ሄክታር በግጦሽ መሬት በ2,145 ሄክታር በድምሩ በ 3,796 ሄክታር ላይ ተምች በመከሰቱ ይህንም መከላከል እንዲቻል ኬሚካል እና መርጫ መሳሪያ እንዲቀርብ በማድረግ እንዲሁም በመስክ ድጋፍ የሚያደርግ ባለሙያ በማሰማራት የመከላከል ስራ ተሰርቷል፡፡

በተደረገው የመከላከል ስራ በኬሚካል 980 ሄክታር ፤በባህላዊ 2,048 ሄክታር በድምሩ በ3,028 ሄክታር ላይ የተከሰተን ተምች መከላከል ተችሏል፡፡

## የምርት ቴክኖሎጅ አጠቃቀም

በበጀት አመቱ 311,941 ሄልማቲክ ጆንያ ለማሰራጨት ታቅዶ 72,521 በማሰራጨት እና ጥቅም ላይ እንዲውል በማድረግ 623,995 ኩንታል ምርት ከብክነት መከላከል ተችሏል፡፡በዚህም ወንድ 72,864 ፤ሴት 11,298 በድምሩ 84,162 አርሶ አደሮች ተሳታፊ ሆነዋል፡፡ዘመናዊ የብረት ጎተራ 1,200 ለማሰራጨት ታቅዶ 282 ጥቅም ላይ እንዲውል በማድረግ ምርትን ከብክነት መከላከል ተችሏል፡፡እንዲሁም የስንዴ ሰብልን ዘመናዊ ቴክኖሎጅ በመጠቀም መሰብሰብ ተችሏል፡፡



የስንዴ ሰብል በኮምባይነር ሲሰበሰብ-ደብረ ኤሊያስ ወረዳ

## የመስኖ ውሃ አጠቃቀም

ሀገራችን የያዘችውን ረጅም የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ጉዞ ለማሳካት የግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ የመሪነት ሚና አለው፡፡ በመጀመሪያው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ አመታት የሰብል ልማት ዘርፍ ለአጠቃላይ የኢኮኖሚ እድገት ጉልህ ሚና የነበረው ሲሆን በተለይ ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር በተያያዘ የሚከሰተውን ችግር ለመቅረፍ በሁለተኛው ዕድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ዘመን የመስኖ ሰብል ልማት ስራዎችን በበለጠ በማስፋፋት ሲሰራ ቆይቷል፡፡

በዚህም መሰረት በሰብል የተሸፈነ በነባር መስኖ 228,229 ሄክታር (99%)፤ በአዲስ መስኖ 9233 ሄክታር (102%) በድምሩ 237,462 ሄክታር (99%) በዘር መሸፈን ተችሏል። የመስኖ ልማት ተሳታፊ በነባር ወንድ 911,659 እና ሴት 99215 በድምሩ 1,010,874 አርሶ አደሮች እንዲሁም በአዲስ ወንድ 31,389 እና ሴት 4,001 በድምሩ 35,390 አርሶ አደሮች ተሳትፈዋል።በአጠቃላይ ወንድ 937,500፤ ሴት 102476 በድምሩ 1,039,976(91.4%) አርሶ አደሮች በመስኖ ልማቱ ተሳታፊ ሆነዋል፡፡

## ምርጥ ዘር አጠቃቀም

አርሶ አደሩ ምርጥ ዘር እንዲጠቀም በተሰራው ስራ አዝርዕት 21,947.5 ኩንታል፣ አትክልት 2,339 ኩንታል እና  ስራ ስር 94,650 ኩንታል በድምሩ 98,774 ኩንታል ዘር ጥቅም ላይ ለማዋል ታቅዶ ከለማው ማሳ ላይ አዝርዕት 40,742.2 ኩንታል፡፡ አትክልት 2,147.1 ኩንታል እና ስራ ስር 58,148.9 ኩንታል በድምሩ 101,038.1 ኩንታል (102.3**%)** ምርጥ ዘር ጥቅም ላይ ውሏል፡፡

**የአብክመ የመንግስት ኮሙዩኒኬሽን ቢሮ**

## ሰርቶ ማሳያዎችን ማካሄድ

በመስኖ ልማት አዳዲስ ቴክኖሎጅዎችና የተሻሻሉ አሰራሮች ላይ ሰርቶ ማሳያዎችን ለማካሄድ በአርሶ አደር ማሳ እና በአርሶ አደር ማሰልጠኛ ተቋም በድምሩ 4,700 ሰርቶ ማሳያዎችን ለማካሄድ ታቅዶ በአርሶ አደር ማሳ እና በአርሶ አደር ማሰልጠኛ ተቋም በድምሩ 4,595 (98%) ሰርቶ ማሳያዎችን በ1701.5 ሄክታር ላይ ለማከናወን ተችሏል፡፡በዚህም ወንድ 5,203 ፤ሴት 1,337 በድምሩ 6,540 አርሶ አደሮች በሰርቶ ማሳያ ተሳትፈዋል።



ሰርቶ ማሳያ-ሰሜን ሜጫ ወረዳ

## መስኖ ልማት

በ1ኛ ዙር መስኖ ልማት 38,508,870 ኩንታል ምርት ለማምረት ታቅዶ 29,317,873 (76.1%) ኩንታል ማከናወን ተችሏል፡፡በተመሳሳይ 2ኛ ዙር መስኖ ልማት 100,750 ሄክታር መሬት ለማልማት ታቅዶ 94,075 ሄክታር (93.4%) መሬት ታርሶ 92,863 ሄክታር (92%) በዘር ተሸፍኗል፡፡በሁለተኛ ዙር መስኖ ልማት 347,588 አርሶ አደሮችን ለማሳተፍ ታቅዶ በአመቱ ወንድ 272,811 እና ሴት 32,119 በድምሩ 304,930 (87.7%) ማሳተፍ ተችሏል።ለመስኖ ኤንፒኤስ 90,675 ኩንታልና ዩሪያ 60450 ኩንታል በድምሩ 151,125 ኩንታል ለመጠቀም ታቅዶ ኤንፒኤስ 34,891 ኩንታል፣ ኤንፒኤስቦሮን 8502 ኩንታል፣ ኤንፒኤስቦሮንዚንክ 9,928 ኩንታልና ዩሪያ 32312 ኩንታል በድምሩ 85,632 ኩንታል (56.6%) ማዳበሪያ ጥቅም ላይ ውሏል፡፡በዚህም 11,514,298 ኩንታል ምርት ማምረት ተችሏል፡፡3ኛ ዙር መስኖ ልማት በሰ/ሸዋ ዞን የታረሰ ማሳ 2,475 ሄክታር ሲሆን 2,449 ሄክታር ማሳ በተለያዩ ሰብሎች ማልማት ችለዋል፡፡ በ3ኛ ዙር መስኖ ወንድ 5,808 እና ሴት 241 በድምሩ 6,049 አርሶ አደሮች ተሳትፈዋል።በምርት ዘመኑ በ3ኛ ዙር መስኖ ልማት ኤንፒኤስ 1,581 ኩንታል እና ዩሪያ 960 ኩንታል በድምሩ 2,541 ኩንታል ማዳበሪያ ጥቅም ላይ ውሏል፡፡በ3ኛ ዙር መስኖ ልማት 264,735 **ኩንታል** ምርት

ለማምረት ተችሏል፡፡በአጠቃላይ በክልሉ በመስኖ ልማት ከ1ኛ እስከ 3ኛ ዙር መስኖ ልማት በድምሩ 41,096,912 ኩንታል ምርት በመስኖ ማምረት ተችሏል፡፡

## የመስኖ የአትክልት ኮሞዲቲ ልማት

በ2014 ምርት ዘመን የተለያዩና የተመረጡ 6 የአትክልት ሰብሎችን (ድንች፣ ቲማቲም፣ የፈረንጅ ቀይ ሽንኩርት፣ ነጭ ሽንኩርት፣ ካሮትና ጥቅል ጎመን) በክላስተር በመስኖ ለማልማትና የተጠናከረ ክትትልና ድጋፍ ለማድረግ ያሙች ዘንድ በክልሉ በተመረጡ 9 ዞኖችና 84 ወረዳዎች 28,759 ሄክታር መሬት በማልማት 6,184,489 ኩንታል ምርት ለማምረት ታቅዶ በአጠቃላይ በስድስቱም የአትክልት ኮሞዲቲ ሰብሎች 28,759 ሄክታር በማልማት 6,184,459 ኩንታል ምርት ለማምረት ታቅዶ የለማ መሬት **22,196 ሄክታር (77.2%)** NPS **18,455 ፤ዩሪያ 8,833 ድምር 27,784 ኩንታል *ማዳበሪያ*** ጥቅም ላይ የዋለ ሲሆን ወንድ- **69,659**፣ ሴት **- 5916** ድምር **74,719(66.8%)**አርሶ አደሮች ተሳታፊ ሆነዋል፡፡



በመስኖ የለማ ካሮት-ደብረ ብርሀን

## የመስኖ ስንዴ ልማት

በተግባር ምዕራፍ ከተከናወኑ ስራዎች መካከል 133 ወረዳዎች፤990 ቀበሌዎች እና 14,437 ክላስተሮች 80,000 ሄክታር በመስኖ ለማልማት ታቅዶ ወደ ስራ በመግባት **41,657 ሄክታር** መሬት ታርሶ **40,005** ሄክታር **መሬት (50%)** በዘር በመሸፈን፤36,144.5 ሄክታር ሰብል በመሰብሰብ 1,266,117.5 ኩንታል መሰብሰብ ተችሏል፡፡ ለዚህም **64,356** ኩንታል ማዳበሪያ (**44,385** ኩንታል ኤንፒኤስቢ እና **19,971** ኩንታል ዩሪያ እና **56,234** ኩንታል ምርጥ ዘር ስንዴ ጥቅም ላይ ውሎ ምርቱን መሰብሰብ ተችሏል፡፡ እንዲሁም ወንድ 97,154 ሴት 7,040

ድምር 104,194 አርሶ አደሮች ተሳታፊ ሆነዋል፡፡



የመስኖ ስንዴ በመስመር ሲዘራ-ፋግታ ለኮማ ወረዳ

## ቡናና ፍራፍሬ

በ2014 ዓ.ም 10,041,000 የቡና ችግኝ በመንግስት፣ በግል፣ በማህበራትና በተቋም /በባለሃብት/ ለማዘጋጀት ታቅዶ በ3,615 ሄክታር ላይ ተከላ በማካሄድ 90,369 (27,111 ሴት) አርሶ አደሮችን ተጠቃሚ ለማድረግ 7,873,288 (78.4%) የቡና ችግኝ ማዘጋጀት ተችሏል፡፡ በቡና ኮሞዲቲ ልማት በተመረጡ ስድስት ዞኖች በ19 ወረዳዎችና 152 ቡና አብቃይ ቀበሌዎች ውስጥ በመንግስት ችግኝ ጣቢያዎች 2,465,259 የተሻሻሉ የቡና ችግኝ ዝርያዎችን በማዘጋጀት 2,455,338 (90%) ችግኝ በ18,077 (5,423 ሴቶች) አርሶ አደሮች እንዲተክሉ በማድረግ በአዲስ 982 ሄክታር መሬት ማልማት ተችሏል፡፡ በመሆኑም ለቡና ኮሞዲቲ ልማት የተዘጋጀ ችግኝ 2,591,003 (105%) ነው፡፡የቡና ምርት አሰባሰብ ዝግጅት በተመለከተ የተለቀመ እሸት የቡና ምርት በኩንታል 16203.50 ከተለቀመው መጋዘን የገባ 8377.05 ኩንታል የቡና ምርት መሰበሰብ ተችሏል፡፡



ቡና ልማት-እየሁ ጓንሳ ወረዳ

## ፍራፍሬ ልማት

የቆላ ፍራፍሬ በተመለከተ 7.087 ሚሊዬን ችግኝ በማዘጋጀት 15,087 ሄክታር መሬት ላይ 6,788,950 ችግኝ ተከላ ለማካሄድ እና 49,438 /14,831 ሴት/ አርሶ አደሮችን ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ በበጀት አመቱ የተዘጋጀ 5,516,360 ሲሆን (78%) የእንክብካቤ ስራ እየተሰራለት ይገኛል፡፡

በ2014 በጀት አመት 900,000 የደጋ ፍራፍሬ ችግኝ በማዘጋጀት 810,000 ችግኝ በ729 ሄክታር ላይ ተከላ በማካሄድ 18,008 (5,403 ሴት) አርሶ አደሮች ተጠቃሚ ለማድረግ 535,553 (60%) ችግኝ የተዘጋጀ ሲሆን ከዚህ ውስጥ 404,225 (47.5%) የተከተበ ነው፡፡

በመደበኛ እና በኮሞዲቲ ልማት 1,662,900 የአቮካዶ ችግኝ ከዚህ ውስጥ 1,082,006 የተከተበ ችግኝ ለማዘጋጀት ታቅዶ የተዘጋጀ አቮካዶ ችግኝ 641,746 (59%) የተከተበ እና 1,216,834 ያልተከተበ በድምሩ 1,854,580 (112%) ችግኝ ለማዘጋጀት ተችሏል፡፡



የአማራና የቤንሻንጉል ክልል ዕርሰ መስተዳደሮች

## በጋራ የፍራፍሬ ችግኝ ሲተክሉ-አማራ ክልል ቻግኒ ከተማ አስተዳደር

## የምርጥ ዘር አሰባሰብ

በምርት ዘመኑ 330,002 ኩንታል ምርጥ ዘር ለማቅረብ ታቅዶ ወደ ስራ የተገባ ሲሆን በክልላችን በተለያዩ አምራቾች ይሰበሰባል ተብሎ ከተገመተው 248,421 ኩንታል ምርጥ ዘር ውስጥ 219,907 ኩንታል ምርጥ ዘር ተሰብስቧል፡፡

## የአፈር ማዳበሪያ አቅርቦትና ስርጭት

በ2014/15 የምርት ዘመን በአዲስ የሚቀርብ የአፈር ማዳበሪያ 8,245,596 ኩንታል፤ የከረመ 674,386 ኩንታል በድምሩ 8,919,982 ኩንታል የታቀደ ሲሆን በተፈጠረው ከፍተኛ የፋይናንስ እጥረት ምክንያት ከእቅዱ የተገዛው 4,851,444 ኩንታል(58%) ሲሆን ከወደብ በአዲስ 4,186,983 ኩንታል ከተገዛው (86%) ከዕቅዱ (50.7%) ቀርቦ ከዚህ ውስጥ በማዕከላዊ መጋዘን የከረመውን ጨምሮ 3,974,612 ኩንታል ወደ ህብረትስራ ማህበራት በማውረድ 3,423,938 ኩንታል ለአርሶ አደሩ ተሰራጭቷል፡፡



የአፈር ማዳበሪያ ስርጭት-ወረታ ከተማ አስተዳደር

## የተፈጥሮ ሃብት ልማት ጥበቃና አጠቃቀም

ለተፈጥሮ ሃብት ልማት ጥበቃ የሰው ሀይል ለመለየትና ለማደራጀት በተሰራው ስራ ወንድ 2,493,668 ሴት 1,722,135 በድምሩ 4.215,803 ሰው ሀይል ለማደራጀት ታቅዶ ወንድ 2,399,996 ሴት 1,602,938 በድምሩ 4.006,934 ተለይተው ወደ ስራ ገብተዋል፡፡

አፈፃፀሙም 95.5 በመቶ ነው፡፡

የተፈጥሮ ሃብት ልማት ጥበቃና አጠቃቀም ስራ ለመስራት የመንግስትና የግል የልማት መሳሪያዎች (አካፋ፣ ዶማ፣ መናኪሎ፣ መዶሻ፤ ዛቢያ፣ ገሶ በዋናነት) 3,726,975 ለማዘጋጀት ታቅዶ 3,352,116 ወይም 89.9 % በላይ መለየት የተቻለ ሲሆን በተጨማሪም 260,671 የተለያዩ የቅየሳ መሳሪያዎች ለማዘጋጀት ታቅዶ 194,868 ወይም 74.8% ተዘጋጅቷል፡፡

## ተፋሰስ ልማት

በተፋሰስ ልማቱ የህብረተሰሰቡን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ በለሙ ተፋሰሶች የተለያዩ የገቢ ማስገኛ ስራዎች በመስራት ህብረተሰቡን ተጠቃሚ ለማድረግ በተደረገው እንቅስቃሴ 6,630 ተፋሰስ ውስጥ 907,278,428 ብር ወንድ 338,843 ሴት 91,224 በድምሩ 333,396 አርሶ አደሮችን ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡

## የአፈርና ውሀ ጥበቃ ስራ

በ2014 ዓ.ም 302,892 ሄክታር መሬት ላይ የአፈርና ውሃ ጥበቃ ስራ ለመስራት ታቅዶ 295,364 ሄክታር መሬት ላይ ማከናወን ተችሏል፡፡ ይህም 97.5 % አፈፃፀም ላይ የደረሰ ሲሆን በአዲስ የሚሰሩ ስራዎች 202,960 ሄክታር መሬት ለመስራት ታቅዶ 197,142 ሄክታር ወይም 97.1 % የተሰራ መሆኑና በነባር በሚሰሩ ስራዎች ላይ 99,932 ሄክታር መሬት ለመስራት ታቅዶ 98,222 ሄክታር ወይም 93.3 % ለመፈጸም ተችሏል፡፡በማሳ ላይ የሚሰሩ የአፈርና ውሃ ጥበቃ ስራዎች 247,670 ሄክታር መሬት ላይ ለመስራት ታቅዶ 238,039 ሄክታር መሬት ላይ ወይም 98.5% መፈጸም ተችሏል፡፡ በማሳ ላይ የሚሰሩ የአፈርና ውሃ ጥበቃ ስራዎች 247,670 ሄክታር መሬት ላይ ለመስራት ታቅዶ 246,910 ሄክታር መሬት ላይ ወይም 99.7 % መፈጸም ተችሏል፡፡

በበጀት አመቱ 148,465 ሄክታር መሬት እርከን ለመስራት ታቅዶ 153,138 ሄክታር ወይም 103%፣ 10,684 ሄክታር መሬት የሳር ሰርጥ ስራ ለመስራት ታቅዶ 8,691 ሄክታር ወይም 83.8% እና 88,522 የማሳ ላይ እርከን ደረጃ ማሳደግ ታቅዶ 84,811 ሄክታር ወይም 95.8% ማከናወን ተችሏል፡፡

በበጀት አመቱ የተራራ ልማት ስራዎች 43,713 ሄክታር ለመስራት ታቅዶ 43,519 ሄክታር መሬት ላይ ወይም 99.6 % መፈጸም ተችሏል፡፡ በዚህም 112,520 ሄክታር ተራራማ መሬት ለመከለልና ለመጠበቅ ታቅዶ 60,809 ሄክታር ወይም 57.8% በመከለል የተለያዩ ስትራክቸሮችን በመስራት ጥቅም ላይ እንዲውል ተደርጓል፡፡2,560 ሄክታር መሬት የጠረጴዛማ እርከን ለመስራት ታቅዶ 1164 ሄክታር ወይም 45.6% መስራት ተችሏል፡፡ 17,590 ሄክታር የጋራ ላይ እርከን ስራ ለመስራት ታቅዶ 16,912 ሄክታር መሬት ወይም 96% መስራት ትችሏል፣

12,558 ሄክታር የጋራ ላይ እርከን ፕላስ ትሬንች ለመስራት ታቅዶ 12,113 ሄክታር ወይም 96.4% መስራት ተችሏል፣ 11,005 ሄክታር የጋራ ላይ እረከን ደረጃ ማሳደግ ታቅዶ 13,411 ሄክታር ወይም 100% መስራት ተችሏል፡፡

በ2014 የምርት ዘመን አነሰተኛ የውሃ ማስረጊያ ስትራክቸሮች የተለያየ ተዳፋት ባላቸው መሬቶች ላይ በቁጥር 5,775,334 ለመስራት ታቅዶ 4,304,236 ስትራክቸር መሬት ላይ ወይም 74.5%፣ 2,577,273 ትሬንች ለመስራት ታቅዶ 2,193,557 ወይም 85%፣ 804,293 አግድም ዝግ ቦይ ለመስራት ታቅዶ 348,456 ወይም 43%፣ 1,547,991 ማይክሮቤዝን ለመስራት ታቀዶ 1,220,093 ወይም 78%፣ 845,777 አይብሮቤዝን ለመስራት ታቅዶ 559,195 ወይም 66% መፈጸም ተችሏል፡፡

በ2014 የትርፍ ውሃ ማስወጫ በመስራት ላይ የሚገኝ ስትራክቸር 3,780,311 ሜትር ኩብ ለመስራት ታቅዶ 3,575,513 ስትራክቸር መሬት ላይ ወይም 94.5%፣ 2,009,498 ሜትር ኩብ የጐርፍ ማፋሰሻ ቦይ ለመስራት ታቀዶ 1,655,765 ሜትር ኩብ ወይም 82.4%፣ 1,770,813 ሜትር ኩብ የውሃ ማፋሰሻ ቦይ ለመስራት ታቅዶ 1,919,748 ሜትር ኩብ ወይም 108.4% መሸፈን ተችሏል፡፡

የ2014 ዓ.ም የተፈጥሮ ሃብት ልማት ጥበቃ ቦረቦር የሚከሰትበትን አካባቢ በመለየት የተለያዩ ስትራክቸሮችን ለመስራት በአካባቢው ያለውን ችግር ከባቢያዊ መፍትሄ ለመስጠት ወደ ስራ ተገብቷል፡፡ በመሆኑም 7,186 ሄክታር በመለየት ወደ ልማት ለማስገባት ታቅዶ የተለያዩ የክትር አይነቶች የተሰራበት 4,935.1 ሄክታር መሬት ላይ ወይም 68.7% መፈጸም ተችሏል፡፡

# ከተማሞችና መሰረተ ልማት

## የከተሞች መልካም አስተዳደር

ባለፉት አመታት ከተሞች ለሰላም እጦት መንስኤ የሆኑ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን ሲያስተናግዱ ቆይተዋል ለዚህ ችግር ዋናው መነሻ ደግሞ በክልላችን ከተሞች መሬትነክና መሬትነክ ባልሆኑ ጉዳዮች ምክንያት ነው፡፡ በመሆኑም በ2014 ዓ.ም በከተሞች ለሰላም እጦት መንስኤ የሆኑ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን በመፍታት መልካም አስተዳደርን ለማስፈን ሁሉም የማዘጋጃ ቤት አገልግሎቶች ደረጃ ወጥቶላቸው ግልፅነት፣ ተጠያቂነትና የተገልጋዩን ዕርካታ በሚያረጋግጥ ሁኔታ እንዲፈፅሙ የተለያዩ ስራዎች ተሰርተዋል፡፡ በከተሞች የሚሰጡ የማዘጋጃ ቤት አገልግሎቶችን ቀልጣፋና ውጤታማ ለማድረግ እንዲቻል 7 የተለያዩ የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት ስታንዳርዶች ተዘጋጅተው የወረዱ ሲሆን በክልሉ በሚገኙ 77 ከተማ አስተዳደሮች እና በሰባት መሪ ማዘጋጃ ቤት ከተሞች የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አሰጣጥ

ስታንዳርዶች እንዲተገበሩ ለማድረግ ታቅዶ በ73 (94.81%) ከተማ አስተዳደሮችና በ6 (85.71%) መሪ ማዘጋጃ ቤት እንዲተገበሩ ተደርጓል፡፡ እንዲሁም የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አሰጣጥ አፈፃፀም ምዘና ለማካሄድ የሚያስችሉ ቁልፍ የምዘና መለኪያዎችን በማዘጋጀት በ77 ከተማ አስተዳደሮች ምዘና በማካሄድ ለከተሞቹ ግብረ መልስ ለመስጠት ታቅዶ በ52 ከተሞች (67.53%) ምዘና ተደርጎ ለከተሞቹ ግብረ-መልስ ተሰጥቷል፡፡ ሌላው የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት ስታንዳርዱ በሚተገበርባቸው 77 ከተሞች የዜጎች ቻርተር እንዲዘጋጅ እና እንዲተገበር ለማድረግ ታቅዶ በ71 (92.21%) ከተሞች ተግባራዊ ማድረግ ተችሏል፡፡

## የሙያ ስታንዳርድ ምዘና

የሙያ ብቃት ምዘና ስርዓት በመዘርጋቱ ከአሁን በፊት ምንም አይነት የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ያልተሰጣቸው እንዲሁም ብዙውን ጊዜ ሙያቸው እንደጠቃሚ ባለመቆጠሩ ዝቅተኛ ግምት ተሰጥቷቸው የኖሩ ነገር ግን የሙያ ባለቤትና ቁልፍ የልማት ሀይል የሆኑ ዜጎች ለማድረግ የሙያ ስታንዳርድ ሥርዓተ ትምህርትና የምዘና መሳሪያ በተዘጋጀላቸው ስድስት የማዘጋጃ ቤት አገልግሎቶችና ሌሎች ሙያዎች በመዋቅሩ ውስጥ ለሚገኙ 4,500 (70% ሴቶች) ፈፃሚዎች/ ሰልጣኞች) በተለያዩ የሙያ ደረጃዎች በማሰልጠን ብቃታቸው በምዘና ተረጋግጦ ወደ ስራ እንዲሰማሩ ለማድረግ ታቅዶ 10 አዳዲስ የምዘና ጣቢያዎችን በማዘጋጀት በ13 ከተሞች 1,760 ወንድ እና 2,551 ሴት በድምሩ 4,311 (95.8%) ባለሙያዎችን በአረንጓዴ ልማት፣ በደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ እንዲሁም በህብረተሰብ ተሳትፎ ሙያዎች በደረጃ I እና II በማሰልጠን ማስመዘን ተችሏል፡፡ ከተመዘኑ ባለሙያዎች መካከልም 3,384 (78.5%) ባለሙያዎች የበቁ ሲሆን 927 ደግሞ ያልበቁ ናቸው፡፡

## የህብረተሰብ ተሳትፎን ማሳደግ

የህብረተሰቡን የልማት ፍላጎት ለማሳካት በመንግስት ውስን በጀት ብቻ መሸፈን አይቻልም በመሆኑም በ2014 ዓ.ም በከተሞች በህብረተሰቡና በመንግስት ቢጋራ በሚከናወኑ የአካባቢ ልማት ስራዎችና ፕሮጀክቶች (የመንገድ ጠረጋና ግንባታ፣ የህዝብ መፀዳጃ ቤት ግንባታ፣ የተፋሰስና የዲች ግንባታ፣ የመብራትና የውሃ መስመር ዝርጋታ፣ የአካባቢ ማስዋብና አረንጓዴ ልማት እንዲሁም የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስራዎች ወዘተ ላይ ህብረተሰቡ 15% በገንዘብ፣ 15% በቁሳቁስ፣ 20% በጉልበትና በእውቀቱ በድምሩ 50% አስተዋጽኦ እንዲኖረው ለማድረግ ታቅዶ በጥሬ ገንዘብ 253,922,283.00 ብር፣ በጉልበት 178,604,566.00 ብር፣ በቁሳቁስ 108,213,380.00 ብር እና በእውቀት 10,836,363.00 ብር በድምሩ 551,576,592.00 ብር የሚገመት ገንዘብ ለልማት ስራዎች አስተዋጾኦ ተደርጓል፡፡ ለእነዚህ የልማት ስራዎች በመንግስት በኩል 969,828,101 ብር ወጪ ተደርጓል፡፡

በጠቅላላው 1,521,404,693 ብር (የመንግስት ወጪ + የህዝብ ተሳትፎ) ለልማት ስራ የዋለ ሲሆን በዚህም የህብረተሰብ ተሳትፎ ድርሻን በአማካይ 36.25% ማድረስ ተችሏል፡፡ በልማት ስራዎች ላይ ወንድ 3,946,171 ሴት 1,843,354 በድምሩ 5,789,525 የህብረተሰብ ክፍል ቀጥታ በጉልበቱ የተሳተፈ ሲሆን በዚህም የሴቶችን ተሳትፎ 31.84% እና የወጣቶችን ተሳትፎ 31.84% ማድረስ ተችሏል፡፡

## የከተማ አገልግሎት ገቢ አሰባሰብና አጠቃቀም

በበጀት አመቱ ለከተማው ያገባኛል የሚል ማንኛውም ማህበረሰብ በከተሞች የተሻለ ገቢ መሰብሰብና ከተሞችን ማልማት ያለበት መሆኑን በመገንዘብ የከተሞች ፋይናንስ አቅርቦት ስትራቴጂ ሰነድ በማዘጋጀት እንዲሁም የአደረጃጀትና የአሠራር ሥርዓት በመዘርጋት በ583 ከተሞች 0.934 ቢሊዮን ብር እንዲሁም ከገቢዎች ጋር በመቀናጀት በ77 ከተማ አስተዳደሮች 3.3 ቢሊዮን ብር በድምሩ 4.234 ቢሊዮን ብር ለመሰብሰብ ታቅዶ ከመሪ መዘጋጃ ቤቶችና ታዳጊ ከተሞች 0.552 (59.08%) ቢሊዮን ብር እና ከከተማ አስተዳደሮች 2.67 (81.04%) ቢሊዮን ብር በድምሩ 3.226 (76.19%) ቢሊዮን ብር መሰብሰብ ተችሏል፡፡እንዲሁም በክልሉ በሚገኙ ከተማ አስተዳደሮች፣ መሪ፣ ንዑስና ታዳጊ ከተሞች መሰብሰብ ካለባቸው 57 የገቢ አርዕስቶች ውስጥ በአማካይ በ40 የገቢ አርዕስቶች ተደራሽ እንዲሆኑ ለማድረግ ታቅዶ በአብዛኛው ከተሞች በአማካይ 36 (90%) የገቢ አርዕስቶች ላይ የአገልግሎት ገቢ መሰብሰብ ተችሏል፡፡

## የፋይናንስ አጠቃቀምን ውጤታማ ማድረግ

የፋይናንስ አጠቃቀምን ውጤታማነት ለማሳደግና ብክነትን ለመከላከል 120 መሪ ማዘጋጃ ቤት ከተሞች ኦዲት ለማድረግ ታቅዶ 110 (91.67%) ከተሞች ኦዲት ያስደረጉ ሲሆን በ87 ከተሞች ብር 67,831,132.54 የገንዘብ ጉድለት የተገኘ ሲሆን ከዚህ መካከል ብር 3,576,727 (5.27%) የተመለሰ ሲሆን ብር 64,254,405.54 ያልተመለሰ በመሆኑ በቀጣይ ትኩረት ሰጥቶ መስራት ያስፈልጋል፡፡ ከባለፉት ዓመታት በኦዲት የተገኘና የተንከባለለ ብር 4,397,489.81 የገንዘብ ጉድለት 100% ተመላሽ ለማድረግ ታቅዶ ብር 2,297,034 የተመለሰ ሲሆን ቀሪው ብር 2,100,455.81 ያልተመለሰ በመሆኑ ዳግም ክትትሉን በማጠናከር ጉድለቱን ማስመለስ ያስፈልጋል፡፡

## ከተሞች በፕላን እንዲመሩ ማድረግ

የከተማ ፕላን ማለት አስቀድሞ ለሚወሰን ዘመን የአንድን ከተማ እና አካባቢውን የወደፊት ዕድገት በልማታዊ ዓላማ መሰረት እንዲመራ የሚዘጋጅ የመሬት አጠቃቀም በመሆኑ በበጀት

አመቱ የክልላችን ከተሞችን በፐላን ለመምራት አሳታፊ፣ ጥራት ያለውና ወጭ ቆጣቢ የሆነ የከተማ ፐላን በማዘጋጀት ሁሉም ከተሞች በፐላን እንዲመሩ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ የተለያዩ ጥረቶች ተደርገዋል፡፡ በመሆኑም ከፐላን ዝግጅት አኳያ ለ60 ከተሞች መሰረታዊ ካርታ ለማዘጋጀት ታቅዶ ለ60 (100%) ከተሞች መሰረታዊ ካርታ ማዘጋጀት ተችሏል፡፡ መዋቅራዊ ፐላን ለሚዘጋጅላቸው 12 ከተሞች መሰረታዊ ካርታ ለማዘጋጀት ታቅዶ የ12 (100%) ከተሞች ተዘጋጅቷል፡፡ ለ60 ከተሞች መሰረታዊ ፐላን ለማዘጋጀት ታቅዶ የ54 (90%) ከተሞች ተዘጋጅቷል፡፡ ለ12 ከተሞች መዋቅራዊ ፐላን ለማዘጋጀት ታቅዶ የ12 ከተሞች (100%) ተዘጋጅቷል፡፡ እንዲሁም መዋቅራዊ ፐላን የሚዘጋጅላቸው 12 ከተሞች ፕላናቸውን ማስተግበር እንዲችሉ 18 የአካባቢ ልማት ፐላን ለማዘጋጀት ታቅዶ 23 (128%) ተዘጋጅቷል፡፡ በተጨማሪም የ48 ከተሞችን መሠረታዊ መረጃ በማሰባሰብና በማደራጀት ለተጠቃሚዎች ዝግጁ ለማድረግ ታቅዶ የ48 (100%) ከተሞች ማዘጋጀት ተችሏል፡፡ በመሆኑም ወንድ 11,700 እና ሴት 6,300 በድምሩ 18,000 የከተማው ነዋሪ ህዝብ በፐላን ዝግጅትና ክለሳ ወቅት ግንዛቤ እንዲያገኝ ለማድረግ ታቅዶ ወንድ 12,926 እና ሴት 6,039 በድምሩ 18,965 (105.36%) ማሳተፍ ተችሏል፡፡ ከፐላን አፈፃፀም አኳያ ፐላን ተዘጋጅቶላቸው ያላጸደቁ ከተሞችን መረጃ በመለየት 28 ያላጸደቁ ከተሞች ፕላናቸውን አጸድቀው ወደ ትግበራ እንዲገቡ ለማድረግ ታቅዶ 28 (100%) ተከናውኗል፡፡ ከዞኖችና ከከተሞች ለሚቀርቡ የፐላን ማስተካከያና የፐላን ምደባ ለውጥ ጥያቄዎች 100% ምላሽ ለመስጠት ታቅዶ ከቀረቡ 116 የፐላን ምደባ ለውጥ ጥያቄዎች መካከል ለ100 (86.21%) ምላሽ ተሰጥቷል፡፡ በከተሞች የሚፈጠሩ ፐላን ጥሰቶች ያለምህረት እንዲስተካከሉ ለማድረግ ታቅዶ በ5 ዞኖች በሚገኙ ከተሞች ከተፈፀሙ 26 የፐላን ጥሰቶች መካከል በ15ቱ (57.69%) የማስተካከያ እርምጃ ተወስዷል፡፡ እንዲሁም በተደጋጋሚ የፐላን ምደባ ለውጥና ጥሰት በሚታይባቸው 12 ከተሞች የፐላን አፈጻጸም ኦዲት በማድረግ ለከተሞቹ ግብረ-መልስ ለመስጠት ታቅዶ በ12 (100%) ከተሞች ኦዲት በማድረግ ለከተሞቹ ግብረ-መልስ ተሰጥቷል፡፡

## የከተማ መሬት ሃብትን ከወረራ መከላከል

አንዳንድ ስግብግብ የህብረተሰብ ክፍሎች በከተማ መሬት ፍላጎት የተነሳ በህገወጥ መንገድ ለመያዝ የማይፈነቅሉት ድንጋይ የለም በመሆኑም በ2014 ዓ.ም የከተማ መሬት ሃብትን ከንጥቂያና ከወረራ በመከላከል በቁጠባ ለላቀ ልማት ማዋል አስፈላጊ በመሆኑ የጠራ የመረጃ ስርዓት በመዘርጋት ሀብቱን ቆጥሮና መዝግቦ ማስተዳደር ይገባል፡፡ ከዚህም አኳያ ከተሞች በግልጽ የሚታወቅ የአስተዳደር ወሰን እንዲኖራቸው በማድረግ የመሬት ሃብታቸውን በሚገባ ቆጥረውና መዝግበው ማስተዳደር እንዲችሉ 332 ከተሞች የአስተዳደር ወሰናቸውን በአዲስ

እንዲያካልሉና መረጃቸውን አደራጅተው እንዲይዙ ለማድረግ ታቅዶ 62 (18.67%) ከተሞች የአስተዳደር ወሰናቸውን በአዲስ የከለሉ ሲሆን 98 (29.52%) ከተሞች ደግሞ መረጃቸውን አደራጅተው ይዘዋል፡፡ 185 ከተሞች ቋሚ የድንበር ወሰን ምልክቶችን እንዲተክሉና የተተከሉ የቅየሳ መቆጣጠሪያ ነጥቦችን መረጃ አደራጅቶ በመያዝ ደህንነታቸው እንዲጠበቅ ለማድረግ ታቅዶ በ86 (46.49%) ከተሞች ቋሚ የወሰን ምልክቶችን የተከሉ ሲሆን 134 (72.43%) ከተሞች በመሬት ላይ የሚገኙ የቅየሳ መቆጣጠሪያ ነጥቦችን በመለየት መረጃቸው ተደራጅቶ እንዲያዝና ደህንነታቸው እንዲጠበቅ ማድረግ ችለዋል፡፡ እንዲሁም ቀደም ሲል የጠፉ 754 የቅየሳ መቆጣጠሪያ ነጥቦችን ለመተካት እቅድ ተይዞ 1058 (140.32%) መተካት ተችሏል፡፡

## የመሬት ሀብት ቆጠራና ምዝገባ

በ2014 ዓ.ም በ126 ከተሞች የፕላን ወሰን ክልል ውስጥ የሚገኝ 18,500 ሄክታር ቁራሽ መሬት ቆጥሮና መዝግቦ ለመያዝ ታቅዶ በ171 ከተሞች 20,752.63 (112.18%) ሄክታር ቁራሽ መሬት መቁጠርና መመዝገብ ተችሏል፡፡ በ152 ከተሞች ለ2,916 የመንግስት ቤቶች፣ የቀበሌና ዝቅተኛ ኗሪ ቤቶች የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ ለመስጠት ታቅዶ ለ11,781 (ከ100% በላይ) የመንግስት ቤቶች፣ የቀበሌና ዝቅተኛ ኗሪዎች ቤቶች የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ ተሰጥቷል፡፡ በ220 ከተሞች 44,712 ይዞታዎች በመመሪያ ቁጥር 3/13 መሰረት ተጣርተው የከተማ ቦታ የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ (ካርታ) እንዲያገኙ ለማድረግ ታቅዶ ለ19,048 (42.60%) ይዞታዎች ሰነድ/ካርታ/ መስጠት ተችሏል፡፡

## የከተማ መሬት ፋይል አደረጃጀትና አያያዝ

በተለያዩ ምክንያቶች የባለቤትነት ማረጋገጫ ፋይል የሌላቸውና የጠፋባቸው ነባር ባለይዞታዎች በስማቸው ግብር የከፈሉበትና ሌላ በእጃቸው የሚገኝ ሰነድ ህጋዊነት እንዲኖረው ማድረግ ተገ ቢ በመሆኑ በ257 ከተሞች 248,332 የይዞታ ፋይሎችን በሃርድና በሶፍት ኮፒ ለማደራጀት ታቅዶ በ265 ከተሞች 433,940 (ከ100% በላይ) ፋይሎች የተደራጁ ሲሆን በ219 ከተሞች 323,211 (130.15%) ፋይሎችን በሶፍት ኮፒ ማደራጀት ተችሏል፡፡ በሁሉም ከተሞች 54,389 ህገ-ወጥ ይዞታዎችንና ግንባታዎችን መረጃ አደራጅቶ በመያዝ 100% ስርዓት ለማስያዝ ታቅዶ 65,734 ህገወጥ ይዞታዎች ተደራጅተው የተያዙ ሲሆን ከነዚህም መካከል 11,543 (17.56%) ህገ-ወጥ ግንባታዎችን የማስወገድ ስራ ተሰርቷል፡፡ በተለይ ባህርዳር ከተማ 5,114 ህገ-ወጥ ግንባታዎችን በማስወገድ በኩል የሄደበት ርቀት ለሌሎች ከተሞች በተሞክሮነት የሚወሰድ ተግባር በመሆኑ ሌሎች ሊማሩበት ይገባል፡፡

**የአብክመ የመንግስት ኮሙዩኒኬሽን ቢሮ**

## የከተማ መሬት ዝግጅት

መሬት የከተሞች ውስን ሀብት በመሆኑ እያንዳንዱ ይዞታ በማን እና በምን አግባብ እንደተያዘ በይዞታው ላይ ያለውን መብት አጣርቶ በማረጋገጥ ባለመብቱ በይዞታው ላይ ያለውን መብት በማወቅ ወደ ኢኮኖሚው አስገብቶ ሊጠቀምበት የሚችልበት አሰራር ማበጀት ተገቢ በመሆኑ በ2014 ዓ.ም በተለያዩ ከተሞች 516 ሄክታር መሬት ለጨረታ ለማዘጋጀት ታቅዶ 412.66 ሄክታር (79.9%) መሬት ማዘጋጀት የተቻለ ሲሆን ለምደባ 2940 ሄክታር መሬት ለማዘጋጀት ታቅዶ 5,068.6 ሄክታር (172.4%) መሬት ማዘጋጀት ተችሏል፡፡ በ94 ከተሞች መሬት ዝግጅት እና ማስተላለፍ አሰራራቸው በመሬት ባንክ የአሰራር ሥርዓት እንዲመራ በማድረግ 2,043 ሄክታር መሬት ወደ መሬት ባንክ እንዲገባ ለማድረግ ታቅዶ በ77 ከተማ አስተዳደሮች የመሬት ባንክ አሰራር ሥርዓት የተዘረጋ ሲሆን 3,380.519 ሄክታር (165.47%) መሬት ወደ መሬት ባንክ እንዲገባ ተደርጓል፡፡ ከተዘጋጀው መሬት ውስጥ ለተለያየ አገልግሎት የሚውል 280 ሄክታር ቦታ በጨረታ ለማስተላለፍ ታቅዶ 95.779 ሄክታር (34.21%) መሬት ለተጠቃሚዎች ተላልፏል፡፡ ከማህበራት ውጪ በምደባ 650 ሄክታር መሬት ለማስተላለፍ ታቅዶ 1173.89 ሄክታር (180.6%) መሬት ለተጠቃሚዎች ተላልፏል፡፡

## የመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበራት

በ2014 ዓ.ም መንግስት በከተሞች የሚኖረውን ህዝብ የቤት ፍላጎት ለማሟላት በህብረት ስራ ማህበራት ተደራጅተው ቤቶችን እንዲገነቡ በሰራው ስራ ለመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበራት 1115.43 ሄክታር ቦታ ለማስተላለፍ ታቅዶ 2196.5 ሄክታር መሬት በ3,133 የቤት ስራ ማህበር ለተደራጁ ወንድ 42,476 ሴት 20,383 በድምሩ ለ62,859 ተጠቃሚዎች ማስተላለፍ የተቻለ ሲሆን አፈጻጸሙም (ከ100% በላይ) ነው፡፡

## የከተማ ቦታ ደረጃ ምደባና ክትትል

በበጀት አመቱ በቦታ ደረጃ ምደባ መሰረት 88 ከተሞች በፕላን ወሰን ክልል ውስጥ የሚገኝ ቦታቸውን የቦታ ደረጃ ምደባ እና የቀጠና ዋጋ ማሻሻያ እንዲያደርጉ እንዲሁም 84 ከተሞች የቀጠና ዋጋ እና የቦታ ደረጃ በአዲስ አዘጋጅተው ወደ ተግባር እንዲገቡ ለማድረግ ታቅዶ 114 (ከ100% በላይ) ከተሞች የቀጠና ዋጋ እና የቦታ ደረጃቸውን ያሻሻሉ ሲሆን 104 (ከ100% በላይ) ከተሞች የቀጠና ዋጋ እና የቦታ ደረጃ በአዲስ በማዘጋጀት አጸድቀው ወደ ተግባር እንዲገቡ ማድረግ ተችሏል፡፡ የልማት ክትትል በማድረግ በጨረታ እና በምደባ ቦታ ለተለያየ አገልግሎት ተወስደው በውላቸው መሰረት ጥቅም ላይ ያልዋሉ (ወደ ልማት ያልገቡ) 151 ቦታዎች (21.44 ሄክታር) እንዲነጠቁ ለማድረግ ታቅዶ ወደ ልማት ያልገቡ 322 ቦታዎች

በመለየትና መረጃ በመውሰድ 18.72 ሄክታር ያለማ መሬት በመንጠቅ ወደ መሬት ባንክ እንዲገባ ተደርጓል፡፡

## የሊዝና የቦታ ኪራይ ክፍያ

በበጀት አመቱ በ208 ከተሞች በሊዝና በኪራይ ለተጠቃሚዎች የተላለፉ ይዞታዎች በውላቸው መሰረት ተገቢውን የሊዝና የቦታ ኪራይ ክፍያ በወቅቱ እንዲከፍሉ በማድረግ
ከሊዝ ይዞታዎች 300.759 ሚሊዮን ብር ለመሰብሰብ ታቅዶ 710.49 ሚሊዮን ብር የተሰበሰበ ሲሆን ከኪራይ ይዞታዎች 56.882 ሚሊዮን ብር ለመሰብሰብ ታቅዶ 154.95 ሚሊዮን ብር በመሰብሰብ ከእቅዱ ከ100% በላይ ማከናወን ተችሏል፡፡

## የስም-ንብረት ዝውውር

በዞኖችና ከተሞች ለ29,124 ተገል,ጋዮች የስመ ንብረት ዝውውር አገልግሎት በመስጠት ብር 377,219,148.86 ገቢ ከአገልግሎቱ መሰብሰብ ተችሏል፡፡ በልማት ምክንያት ከይዞታቸው ለሚነሱ ግለሰቦች ማህበራዊ እንቅስቃሲያቸውን በማያዛባ ሁኔታ ትክና ካሳ ለመስጠት ታቅዶ ለ3,758 የልማት ተነሽዎች 127.1992 ሄክታር ትክ ቦታ እንዲሁም 891,241,629, ብር ካሳ መክፈል ተችሏል፡፡ ከዞኖችና ከተሞች 57 የማስፋፊያ ጥያቄዎች ውሳኔ እንዲሰጥባቸው ለክልል ለከተማና መስረተ ልማት ቢሮ ቀርበው ተሟልተው የተገኙትን 500 ካሬ ሜትር መጠን ያላቸውን 22 የማስፋፊያ ጥያቄዎች ታይተው ውሳኔ የተሰጣቸው ሲሆን 15 ጥያቄዎች ከ500 ካሬ ሜትር በላይ ያላቸውና በመስተዳደር ምክር ቤቱ ውሳኔ የሚሰጥባቸው ሲሆኑ 6ቱ ውሳኔ ተሰጥቶባቸዋል፡፡ ቀሪዎች በሂደት ላይ ናቸው፡፡

ሌላው 6 አዲስ የአምልኮ ቦታ ጥያቄዎች ቀርበው 23,000 ካሬ ሜትር ቦታ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡ 6 ነባር አምልኮ ቦታ የማስፋፊያ ጥያቄ ከባህር ዳር ከተማ ቀርበው ሁሉም ውሳኔ ተሰጥቷቸዋል፡፡ እንዲሁም 70 የምደባ ጥያቄዎች ውሳኔ እንዲሰጥባቸው ለክልል ከተማና መሰረተ ልማት ቢሮ የቀረቡ ሲሆን መረጃዎች ተደራጅተው ውሳኔ እየጠበቁ ይገኛሉ፡፡

## የመኖሪያ ቤት አቅርቦት

በከተሞች እድገትና በተለያዩ ገፊ ምክያቶች ከገጠር ወደ ከተሞች የሚደረግ ፍልሰትን ተከትሎ የመኖሪያ ቤት አቅርቦት ልዩ ትኩረት ማግኘት ያለበት ተግባር ነው፡፡ በመሆኑም በተለያዩ አማራጮች 30,000 መኖሪያ ቤቶችን ለመገንባት ታቅዶ በሪል ስቴት 140፣ በመኖሪያ ቤቶች ሕብረት ሥራ ማኀበራት 15,602፣ በቤቶች ልማት ድርጅት 86፣ በግለሰቦች 11,174፣ እንዲሁም ለዝቅተኛ ነዋሪዎች የቁጠባ ቤቶች 1,202 በድምሩ 28,204 ቤቶች የተገነቡ ሲሆን አፈፃፀሙም

94% ነው፡፡ የመኖሪያ ቤት አቅርቦት ችግርን ለማቃለል በተሰራው ስራ በ3,133 የቤት ስራ ማህበር ለተደራጁ ወንድ 42,476 ሴት 20,383 በድምሩ ለ62,859 ዜጎች የመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ ማስረከብ ተችሏል፡፡



የከተሞችና መሰረተ ልማት ቢሮ የመረጃ አስተዳደር ሶፍትዌር አጀማመር- ባህርዳር

## የቀበሌ ቤት አስተዳደር

በከተሞች ከሚገኙ ቤቶች መካከል በአዋጅ 47/67 የተወረሱና የቀበሌ ካርታ ያልወጣላቸው 5,000 የመንግስት ቤቶችን በመለየት የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ እንዲሰራላቸው ለማድረግ ታቅዶ ለ9,272 (185.44%) የመንግስት ቤቶች የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ተሰርቶላቸዋል፡፡ በሌላ በኩል በመፈራረስ ምክንያት አገልግሎት መስጠት ያቆሙትን የቀበሌ ቤቶች በመለየት ለ600 ቤቶች ጥገና እና ዕድሳት ለማድረግ ታቅዶ ለ979 (163.17%) ቤቶች ጥገና እና ዕድሳት የተደረገ ሲሆን በመንግስት ባለቤትነት የሚከራዩ 5,000 ቤቶች የኪራይ ዋጋ እንዲሻሻል ለማድረግ ታቅዶ 6,594 (131.88%) ቤቶችን ወቅቱን ጠብቀው የኪራይ ዋጋ እንዲያሻሽሉ ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም ያለአግባብ የተያዙ 300 የመንግስት ቤቶችን በመንጠቅ ለሌሎች እንዲተላለፉ ለማድረግ ታቅዶ193 (64.33%) ቤቶችን በመንጠቅ ለሌሎች ተጠቃሚዎች ማስተላለፍ ተችሏል፡፡

በከተሞች የሚገኙ 5,000 የመንግስት ቤቶችን መረጃ በአድራሻ፣ በቤት አይነት፣ በተከራይ አይነት፣ በቤት ደረጃ፣ በኪራይ መጠን፣ እንዲሁም ለመኖሪያ የሚውሉና በጨረታ

**የአብከመ የመንግስት ኮሙዩኒኬሽን ቢሮ**

የሚተላለፉትን በመለየት መረጃ የማሰባሰብና በአንድ የመረጃ ቋት ለማደራጀት ታቅዶ 13,289 ቤቶችን መረጃ ማደራጀት የተቻለ ሲሆን ባህርዳር ከተማ ላይ 198 የመንግስት ቤቶች መረጃ ወደ ቤቶች መረጃ አደረጃጀትና አስተዳደር ሶፍትዌር ማስገባት ተችሏል፡፡ በመሆኑም ይህን አሰራር በሌሎች ከተሞች እንዲሰፋ በማድረግ የቤት አሰተዳደሩን ከብልሹ አሰራር መከላከል ይገባል፡፡

## የከተማ መሰረተ- ልማት

በክልላችን ከከተማ መሰረተ ልማት አቅርቦት ጋር ተያይዞ የሚነሱ የመልካም አስተዳደር ጥያቄዎችን በአግባቡ ለመፍታት በ2014 ዓ.ም በከተሞች የሚገነቡ የመሰረተ-ልማት አውታሮች ለከተሞች ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ መስተጋብር ቁልፍ የልማት

ማዕከል እንዲሆኑና ከተሞች የልማት ማዕከልነታቸውን በብቃት እንዲወጡ ለማስቻል የክልሉ መንግስት ከፍተኛ በጀት መድቦ ዘርፈ-ብዙ የመሰረተ-ልማት አውታሮችን የማስፋፋት ሥራዎችን ሲያከናውን ቆይቷል፡፡ ስራውም UIIDP ፕሮግራም ከአለም ባንክ፣ ከከተሞች፣ ከክልሉ መንግስት እና ከህብረተሰቡ ተሳትፎ በሚገኝ ገንዘብ የሚከናወን ነው፡፡ በክልላችን የፕሮግራሙ ተጠቃሚ በሆኑ 32 ከተሞች በ3.9 ቢሊዮን ብር 785 አዳዲስ ፕሮጀክቶችን በ389.58 ሚሊዮን ብር እንዲሁም 330 የመሰረተ ልማት ጥገና ፕሮጀክቶችን ለመስራት ታቅዶ ወደ ትግበራ የተገባ በመሆኑ በቀጣይ ትኩረት ሰጥቶ መስራት ያስፈልጋል፡፡

በ2014 ዓ.ም ከታቀዱ 785 አዲስ ፕሮጀክቶች ውስጥ 77 የሚሆኑት ለመጠናቀቅ ከ1 ዓመት በላይ ጊዜ እንደሚያስፈልጋቸው በዕቅድ ተለይተው የተቀመጡ በመሆኑ ሙሉ በሙሉ መጠናቀቅ ያለባቸው (ተሻጋሪዎችን በመቀነስ) 708 ፕሮጀክቶች ናቸው፡፡ ከነዚህ 708 ፕረጀክቶች መካከል 679 (95.9%) ፕሮጀክቶች ሙሉ በሙሉ ተጠናቀዋል፡፡ ተሻጋሪ 77 ፕሮጀክቶችን ጨምሮ ቀሪዎቹ 106 ፕሮጀክቶች ደግሞ በተለያዩ የአፈፃፀም ደረጃ ላይ የሚገኙ ሲሆን በጥቅሉ ከ80% በታች አፈጻጸም ያላቸው ናቸው፡፡ በከተሞች አዳዲስ ፕሮጀክቶችን ከመገንባት ጎን ለጎን የተጎዱ መሰረተ ልማቶችን የመጠገን ስራ በፕሮግራሙ ተገቢ ትኩረት ተሰጥቶት እየተከናወነ ይገኛል፡፡በ2014 ዓ.ም ከታቀዱ 330 የጥገና ፕሮጀክቶች መካከል 295 (89.39%) የጥገና ፕሮጀክቶችን ሙሉ በሙሉ ማጠናቀቅ ተችሏል ቀሪዎቹ 35 (10.61%) ፕሮጀክቶች ደግሞ ከ80% በታች አፈጻጸም ያላቸው ናቸው፡፡

### የመንገድ ግንባታ

ደረጃውን የጠበቀ 130 ኪሎ ሜትር ጌጠኛ ድንጋይ ንጣፍ ለመገንባት ታቅዶ 89.93(69.18%)

ኪሎ ሜትር፣ 863.85 ኪሎ ሜትር ጠጠር መንገድ ለመገንባት ታቅዶ 468.51 (54.24%) ኪሎ ሜትር፣ 1,188.3 ኪሎ ሜትር መንገድ ለመክፈት ታቅዶ 550.81 (46.35%) ኪሎ ሜትር፣ 24.66 ኪሎ ሜትር የአስፓልት መንገድ ለመገንባት ታቅዶ 7.24 (29.36%) ኪሎ ሜትር፣ 160 ኪሎ ሜትር የጎርፍ ማስወገጃና መከላከያ ግንብ ለመገንባት ታቅዶ 136.29 (85.18%) ኪሎ ሜትር፣ 25 ደረጃውን የጠበቀ ከፍተኛና መለስተኛ

ድልድይ ለመገንባት ታቅዶ 24.97(100%) ኪሎ ሜትር (100%)፣ 364 ደረጃውን የጠበቀ ስላብ ከልቨርት ለመገንባታ ታቅዶ 316.15 (86.81%) ማከናወን ተችሏል፡፡

## የመንገድ ጥገና

በበጀት አመቱ 37.94 ኪሎ ሜትር የጌጠኛ ድንጋይ መንገድ ጥገና ለማድረግ ታቅዶ 3.88 (10.23%) ኪሎ ሜትር፣ 496.43 ኪሎ ሜትር የጠጠር መንገድ ጥገና ለማድረግ ታቅዶ 246.88 (49.73%) ኪሎ ሜትር እና 15.87 ኪሎ ሜትር አስፓልት መንገድ ለመጠገን ታቅዶ 0.13 (0.82%) ኪሎ ሜትር ጥገና ተደርጓል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም 421.85 ኪሎ ሜትር የከተማ ውስጥ ለውስጥ መንገድ መብራት ለመዘርጋት ታቅዶ 404.12 (95.80%) ኪሎ ሜትር፣ 637.48 ኪሎ ሜትር የውሃ መስመር ለመዘርጋት ታቅዶ 452.22 (70.94%) ኪሎ ሜትር ማከናወን ተችሏል፡፡ በቁጥር 143 የውሃ ቦኖ ለመገንባት ታቅዶ 150 (104.90%) መገንባት ተችሏል፡፡እንዲሁም 137 የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ጊዜያዊ ቦታዎችን ለማዘጋጀት ታቅዶ 144 (105.11%) እና 98 ፍሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃ ጊዜያዊ ቦታዎችን ለማዘጋጀት ታቅዶ 61 (62.24%) ማዘጋጀት ተችሏል፡፡ በሌላ በኩል 1,650 የመስሪያና የመሸጫ ሸድ ለመገንባት ታቅዶ 925.66 (56.10%) የተገነባ ሲሆን 195 የጋራ መፀዳጃ ቤት ለመገንባት ታቅዶ 115 (58.97%) መገንባት ተችሏል፡፡

## የከተሞች ጽዳት፣ አረንጓዴ ልማትና ውበት ሥራ

ኅብረተሰቡ የጽዳት ሥራን የአንድ ወቅት ብቻ ሳይሆን የዕለት ተዕለት ተግባሩ ሊያደርግ ይገባል፡፡ በመሆኑም ከደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስርዓት ማሻሻያ ሥራዎች አንዱ በከተማ ፅዳትና ውበት ስራዎች ዙሪያ የተለያዩ የንቅናቄ ሰነዶችን በማዘጋጀትና የከተማውን ህዝብ በማወያየት በአብዛኛው ከተሞች የጽዳት ቀን ተወስኖ ነዋሪው ሰፈሩንና አካባቢውን እንዲያጸዳ በማድረግ በፅዳት ስራው በላቀ ደረጃ እንዲሳተፍ ማድረግ ነው፡፡ በመሆኑም ለ800,000 (50% ሴቶች) ነዋሪዎች ግንዛቤ በመፍጠር በደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስራ ላይ ለማሳተፍ ታቅዶ ወንድ 453,941፣ ሴት 426,711 በድምሩ ለ880,652 (110%) ነዋሪዎች ግንዛቤ የተፈጠረ ሲሆን

ወንድ 290,389፣ ሴት 282,455 በድምሩ 572,844 (71.61%) የህብረተሰብ ክፍል በደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስራ ላይ ማሳተፍ ተችሏል፡፡ በ207 ከተሞችና ክፍለ ከተሞች የሚገኙ 2,729 ተቋማትና ግለሰቦች ከ20 - 50 ሜትር ርቀት ግቢያቸውንና አካባቢያቸውን እንዲያፀዱ ለማድረግ ታቅዶ በ229 ከተሞችና ክፍለ ከተሞች የሚገኙ 3,149 (115.39%) ተቋማትና ግለሰቦች ተግባራዊ አድርገዋል፡፡

በ2014 ዓ.ም በ77 ከተማ አስተዳደሮች የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስርዓትን ለማሻሻል የተዘጋጁ ህጎች፣ ስታንዳርዶችና የአሰራር ማኑዋሎች በአግባቡ እንዲተገበሩ ለማድረግ ታቅዶ በ84 (109.09%) ከተሞች ላይ ማከናወን ተችሏል፡፡ በ65 ከተሞች በአካባቢ ጽዳትና ውበት ትግበራ ስራው ሞዴል የሆኑ መንደሮችን ለመመስረት ታቅዶ በ70 ከተሞች ላይ 88 (135%) ሞዴል መንደሮችን መስራት ተችሏል፡፡ በ35 ከተሞች ደረቅ ቆሻሻን በዓይነት የመለየት፣ የማጓጓዝና መልሶ የመጠቀም ስርዓት ተግባራዊ ለማድረግ ታቅዶ በ30 (85.71%) ከተሞች እየተተገበረ ያለ ሲሆን በ100 ከተሞች የግንባታ ፍርስራሽ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ እንዲሻሻል ለማድረግ ታቅዶ በ77 (77%) ከተሞች ላይ ማከናወን ተችሏል፡፡ በ86 ከተሞች 703 አዲስ እና 2,790 ነባር የደረቅ ቆሻሻ ማስቀመጫ ቅርጫቶች ተቀምጠው ተገቢውን አገልግሎት እንዲሰጡ ለማድረግ ታቅዶ በ84 ከተሞች 731 (103.98%) አዲስ እና 2,334 (83.66%) ነባር የደረቅ ቆሻሻ ማስቀመጫ ቅርጫቶች ተቀምጠው አገልግሎት እንዲሰጡ ተደርጓል፡፡

የፋይናንስ ስርዓት ያሌላቸው 54 ነባር ከተሞች እንዲጠናከሩ እና 29 አዲስ ከተሞች (ከውሃ ቢልና ከሌሎች አማራጮች ጋር ማስተሳሰር) ቀጣይነት ያለው የተመቻቸ የፋይናንስ ስርዓት እንዲኖራቸው ለማድረግ ታቅዶ 50 ነባር ከተሞችን የማጠናከር ስራ የተሰራ ሲሆን 16 (55.17%) ከተሞች ደግሞ በአዲስ የደረቅ ቆሻሻ ፋይናንስ ስርዓት እንዲዘረጉ ማድረግ ተችሏል፡፡

በከተማ ውበትና አረንጓዴ ልማት ስራዎች በሁሉም ከተሞች ለ800,000 (50% ሴቶች) የከተማ ነዋሪዎች በአረንጓዴ ልማት፣ በችግኝ ተከላ እና እንክብካቤ ዙሪያ ግንዛቤ በመፍጠር በችግኝ ተከላ እና እንክብካቤ በቀጥታ እንዲሳተፍ ለማድረግ ታቅዶ ወንድ 484,230 ሴት 390,311 በድምሩ ለ874,541 (109%) የህብረተሰብ ክፍሎች ግንዛቤ መፍጠር ተችሏል፡፡ በተፈጠረው ግንዛቤ መሰረት 512,951 ወንድ እና 334,500 ሴት በድምሩ 847,451 (105.93%) የህብረተሰብ ክፍሎችን በችግኝ ተከላ እና እንክብካቤ በቀጥታ ማሳተፍ ተችሏል፡፡

በ2014 ዓ.ም በ77 ከተማ አስተዳደሮች እና በ120 መሪ መዘጋጃ ቤቶች የሚገኙ 3,328 ተቋማት ግቢና አካባቢያቸውን በ50 ሜትር ራዲየስ እና በ331 ከተሞች የሚገኙ ነዋሪዎች ደግሞ መኖሪያ

ቤታቸውን በ20 ሜትር ራድየስ በአረንጓዴ እንዲያለሙ ለማድረግ ታቅዶ 2,543 (76.41%) ተቋማት እና በ581 (ከ100% በላይ) ከተሞች የሚገኙ የከተማ ነዋሪዎች አካባቢያቸውንና የመኖሪያ ቤታቸውን ዙሪያ በአረንጓዴ እንዲያለሙ ተደርጓል፡፡ በ164 ከተሞች በፕላን የተመላከቱ 810 አረንጓዴ ቦታዎችን በመለየት የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ለመስጠት ታቅዶ በ161 (98.17%) ከተሞች 897 አረንጓዴ ቦታዎችን በመለየት ለ601 (72.96%) የይዞታ ማረጋገጫ ካርታመስጠት ተችሏል፡፡

ከተሞች ለሰው ልጆች ዘላቂ ማረፊያ እንዲሆኑ በህብረተሰብ ተሳትፎ በክልሉ በሚገኙ 424 ከተሞች 14,699 የተለያዩ የውበት ችግኞችን በመትከል በ1,225 ሄክታር አረንጓዴ ቦታዎችን በአዲስ ለማልማት ታቅዶ በ300 ከተሞች 11,467,488 (78.01%) የውበት ችግኞችን በመትከል 1,028.86 ሄክታር (81.33%) አረንጓዴ ቦታ ማልማት የተቻለ ሲሆን 2,887.86 ሄክታር ነባር አረንጓዴ ቦታዎችን ለመንከባከብ ታቅዶ 2,793 ሄክታር (96.72%) ነባር አረንጓዴ ቦታዎች እንክብካቤ ተደርጎላቸዋል፡፡ የUIIDP ፕሮግራም በሚተገበርባቸው ከተሞች ተግባሮችን አቀናጅቶ ለመፈፀም ጥረት በማድረግ በ27 ከተሞች 27 አዲስ አገልግሎት የሚሰጡ የመዝናኛ ፓርኮችን በስታንዳርድ ዲዛይን ለማልማት ታቅዶ በ26 ከተሞች 26 (96.3%) የመዝናኛ ፓርኮች በአዲስ የለሙ ሲሆን ለ109 ነባር የመዝናኛ ፓርኮች እንክብካቤ ለማድረግ ታቅዶ ለ121 (111%) እንክብካቤ ማድረግ ተችሏል፡፡

በበጀት አመቱ በ47 ከተሞች 47 አዲስ ችግኝ ጣቢያዎች ለማልማት እና ለ142 ነባር ችግኝ ጣቢያዎች እንክብካቤ ለማድረግ ታቅዶ በ27 ከተሞች (ምሥ/ጐጃም 7፣ ጎንደር 1፣ ምዕ/ጎጃም 4፣ ደ/ወሎ 1፣ ባህርዳር 2፣ ሰ/ወሎ 3 እና ማዕ/ጐንደር 1) በድምሩ 30 (63.83%) አዲስ ችግኝ ጣቢያዎችን ማልማት የተቻለ ሲሆን 137 (96.48%) ነባር ችግኝ ጣቢያዎችን መንከባከብ ተችሏል፡፡ በተመሳሳይ በ59 ከተሞችና ክፍለ ከተሞች የመንገድ ዳርቻ፣ አካፋይና አደባባዬች እንዲሁም የውሃ አካላትና ዳርቻ ቦታዎች ውበት በሚያጐናጽፍ መልኩ በስታንዳርድ ዲዛይን እንዲለሙ ለማድረግ ታቅዶ ምዕ/ጐጃም 5፣ ምስ/ጎጃም 13፣ ማዕ/ጎንደር 5፣ ደ/ወሎ 4፣ ሰ/ወሎ 1፣ ኦሮሚያ 4፣ ደ/ጎንደር 5፣ ሰ/ሸዋ 5፣ ጎንደር 6፣

ደ/ብርሀን 4፣ ደ/ማርቆስ 3፣ደሴ 1፣ ምዕ/ጐንደር 3 እና ባህርዳር 4 ክ/ከተሞች በድምሩ በ63 (106.78%) ከተሞች ማልማት ተችሏል፡፡



### አረንጓዴ ልማት-ባህርዳር ከተማ

## የከተማ ምግብ ዋስትና ፕሮግራም ስራ

ከተሞች ያላቸውንም ዕምቅ ሀብት ባለመጠቀማቸውና በአብዛኛው ሊባል በሚችል ደረጃ ከገጠር በሚቀርቡ የግብርና ምርቶች ላይ ጥገኛ በመሆናቸው ምክንያት የምግብ ዋስትና ችግሮችን በመሠረታዊነት ማቃለል አልቻሉም በመሆኑም በከተሞች በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ የሚገኙና ለምግብ እጥረት ተጋላጭ የሆኑ ዜጎችን የምግብ ዋስትና ለማረጋገጥ እንዲቻል የኢፌዴሪ መንግስት የከተሞች የምግብ ዋስትና ስትራቴጂ ቀርጾ ተግባራዊ እያደረገ ይገኛል፡፡ ፕሮግራሙ በዋናነት ከድህነት ወለል በታች የሚገኙ እና ለተለያዩ ማህበራዊ ችግሮች ተጠቂ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎችን ማለትም አነስተኛ ገቢ ያላቸው ቤተሰቦችን፣ የጎዳና ተዳዳሪዎችን፣ ሴተኛ አዳሪዎችን፣ መስራት እየቻሉ ወደ ስራ ያልገቡ ስራ ፈላጊ ዜጎችን፣ አካል ጉዳተኞችን፣ የአደንዛዥ ዕጽ ተጠቃሚዎችን፣ ጠዋሪና ደጋፊ የሌላቸው አረጋውያን እና ህጻናትን ተጠቃሚ የሚያደርግ ነው፡፡ በመሆኑም በ2014 ዓ.ም በክልላችን ባሉ 17 ከተሞች (16 አዲስና በነባሩ በደሴ ከተማ) በኑሮ ደረጃቸው ከድህነት ወለል በታች የሆኑና የመስራት አቅም ያላቸው 40,585 (60% ሴቶችና 75% ወጣቶች) የከተማ ነዋሪዎች በህብረተሰብ ልማት ስራዎች ማለትም በከተማ አረንጓዴ ልማት፣ በተፋሰስ ልማት፣ በደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ፣ በከተማ ማህበራዊ መሰረተ ልማት ግንባታና ጥገና ስራዎች፣ በከተማ ግብርና እና በሌሎችም የቤተሰብ ኑሮ ማሻሻያ ስራዎች በማሳተፍና የስራ እድል በመፍጠር ገቢ እንዲያገኙና ከሚያገኙት ገቢም ቆጥበው ዘላቂነት ያለው የራሳቸውን ስራ እንዲሰሩ ለማስቻል እንዲሁም ደጋፊ

የሌላቸውን 8,744 የማህበረሰብ ክፍሎች ደግሞ የቀጥታ ድጋፍ እንዲያገኙ በማድረግ በጠቅላላው 49,329 ዜጎችን በፕሮግራሙ ተጠቃሚ ለማድረግ እቅድ ተይዞ ተሰርቷል፡፡

## አካባቢ ልማት ስራ

በአካባቢ ልማት ስራ ከታቀፉ 17 ከተሞች በደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ሥራዎች ላይ 7,439 የቤተሰብ ተጠሪዎችን በማሳተፍ 22,409 የቤተሰብ አባላት የምግብ ዋስትናቸው እንዲረጋገጥ ለማድረግ ታቅዶ 17 ከተሞች ወንድ 2,038 ሴት 5,396 በድምሩ 7,434 (99.93%) የቤተሰብ ተጠሪዎችን በማሳተፍ ወንድ 9,565 ሴት 15,027 በድምሩ 24,592 (109.74%) የቤተሰብ አባላትን ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡ በ2014 ዓ.ም በ17 ከተሞች በከተማ ውበትና አረንጓዴ ልማት ሥራዎች ላይ 2,028 የቤተሰብ ተጠሪዎችን በማሳተፍ 6,088 (60% ሴቶችና 75% ወጣቶች) የቤተሰብ አባላትን ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ በ17 ከተሞች ወንድ 888 ሴት 1,811 በድምሩ 2,699 ቤተሰብ ተጠሪዎችን በማሳተፍ ወንድ 3,981 ሴት 4,738 በድምሩ 8,719 የቤተሰብ አባላትን ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡አፈጻጸሙም በሰሪ ኃይል 133% ሲሆን በቤተሰብ አባላት143.2% ነው፡፡በተቀናጀ የተፋሰስ ልማት ሥራዎች ላይ 2,563 የቤተሰብ ተጠሪዎችን በማሳተፍ 7,267 (60% ሴቶችና 75% ወጣቶች) የቤተሰብ አባላትን ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ ወንድ 406 ሴት 621 በድምሩ 1,027 የቤተሰብ ተጠሪዎችን በማሳተፍ ወንድ 1,307 ሴት 1,686 በድምሩ 2,993 የቤተሰብ አባላትን ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡አፈጻጸሙም በሰሪ ኃይል 40% ሲሆን በቤተሰብ አባላት 41.18% ነው፡፡በማህበራዊ የመሠረተ ልማትና አቅርቦት ግንባታና ጥገና ስራዎች ላይ 717 የቤተሰብ ተጠሪዎችን በማሳተፍ 2,151 (60% ሴቶችና 75% ወጣቶች) የቤተሰብ አባላትን ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ ወንድ 113 ሴት 162 በድምሩ 275 ሰሪ ሀይሎችን በማሳተፍ ወንድ 302 ሴት 561 ድምር 863 የቤተሰብ አባላትን ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡ አፈፃፀሙም በሰሪ ሀይል 38.35% ቤተሰብ አባላት 40.12% መሆን ችሏል፡፡

## የከተማ ግብርና

የከተማ ግብርና በከተማ ውስጥና በዙሪያው በአነስተኛ ቦታ ለምግብነትና ለሌሎች ጠቀሜታዎች ሊውሉ የሚችሉ እፅዋትን የማልማት፣ እንስሳትን የማርባት፣ የግብርና ምርት ውጤቶችን የማቀነባበር እና ለተጠቃሚዎች የማቅረብ ስራን የሚያካትት ነው፡፡ በመሆኑም ለከተማ ግብርና ምቹ ሁኔታዎችን ለመፍጠር 890 ሰሪ ኃይሎችን በማሳተፍ ለ2,670 (60% ሴቶችና 75% ወጣቶች) የቤተሰብ አባላትን ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ በ17 ከተሞች ወንድ 414 ሴት 763 በድምሩ 1,177 ሰሪ ኃይሎችን በማሳተፍ ወንድ 1,348 ሴት 1,965 በድምሩ 3,313

የቤተሰብ አባላትን ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡ አፈጻጸሙም በሰሪ ኃይል 132.24% ሲሆን በቤተሰብ አባላት 124% ነው፡፡



የከተማ ግብርና-ፍኖተ ሰላም

## የምግብ ዋስትና

በ2014 ዓ.ም በአስራ ሰባት ከተሞች በኑሮ ደረጃቸው ከድህነት ወለል በታች የሆኑና የመስራት አቅም ያላቸው የከተማ ነዋሪዎች በህብረተሰብ ልማት ስራዎች ማለትም በከተማ አረንጓዴ ልማት፣ በተፋሰስ ልማት፣ በደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ፣ በከተማ ማህበራዊ መሰረተ ልማት ግንባታና ጥገና ስራዎች እና በከተማ ግብርና 13,637 ሰሪ ሀይሎችን በማሳተፍ 40,585 ዜጎችን (የቤተሰብ አባላትን) በምግብ ዋስትና ድጋፍ ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ ወንድ 3,859 ሴት8,753 በድምሩ 12,612 ሰሪ ሀይሎችን በማሳተፍ ወንድ 16,503 ሴት23,977 በድምሩ 40,480 የቤተሰብ አባላትን ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡ አፈፃፀሙም በሰሪ ሀይል 92.48% ሲሆን በቤተሰብ አባላት ደግሞ 99.74 ፐርሰንት ነው፡፡



የከሚሴ ተፋሰስ ልማታ በምግብ ዋስትና ተጠቃሚዎች ሲሰሩ-ከሚሴ ከተማ

**የአብክመ የመንግስት ኮሙዩኒኬሽን ቢሮ**

## የዘላቂ ኑሮ ማሻሻያ

በበጀት አመቱ በ17ቱ ከተሞች 34,870 የአካባቢ ልማት ተጠቃሚዎች በየወሩ ከሚያገኙት ገቢ 20 በመቶ (20,085,120.00 ብር) እንዲቆጥቡ ለማድረግ ታቅዶ በ16 አዲስ ከተሞች 12,517,398 ብርና በነባሩ በደሴ ከተማ 3,228,976.00 ብር በጠቅላላው በ17ቱ ከተሞች 15,746,374.00 (78.39%) መቆጠብ ተችሏል፡፡ ይሁን እንጅ በዋናነት ከድህነት ወለል በታች የሚገኙና ለተለያዩ ማህበራዊ ችግሮች ተጠቂ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎችን ማለትም እጅግ አነስተኛ ገቢ ያላቸው ቤተሰቦችን፣ የጎዳና ተዳዳሪዎችን፣ ሴተኛ አዳሪዎችን፣ መስራት እየቻሉ ወደ ስራ ያልገቡ ስራ ፈላጊ ዜጎችን፣ አካል ጉዳተኞችን፣ የአደንዛዥ ዕጽ ተጠቃሚዎች፣ ጠዋሪና ደጋፊ የሌላቸው አረጋውያንና ህጻናትን በአጠቃላይ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ዜጎችን በአግባቡ በመለየትና በጥራት በመመልመል በኩል ችግሮች ተስተውለዋል፡፡ እንዲሁም በተሸከርካሪ እጥረት ምክንያት በሁሉም ከተሞች በአካባቢ ልማትስራ የተሰበሰበን ቆሻሻ በወቅቱ በማንሳት በኩል ክፍተቶች ተስተውለዋል፡፡ በመሆኑም ከምልመላና መረጣ ጋር ተያይዞ የሚስተዋሉ ችግሮችን አሰራሩን ተከትሎ በወቅቱ በመገምገም ማስተካከል ያስፈልጋል፡፡

## የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ሬጉላቶሪና አቅም ግንባታ ስራ

የኮንስትራክሽን ዘርፉን የሰው ሀይል ልማት በስልጠና አመለካከቱን በማስተካከልና ክህሎቱን በማሳደግ የመፈፀምና የማስፈፀም አቅሙን ለማጎልበት እንዲቻል ከምዘና ማዕከላት ጋር በቅንጅት በመስራት በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው የተሰማሩ ባለሙያዎችን ምዘና የሚያደርጉ 26 መሪ መዛኞችን በማፍራት እና ለ3,600 አነስተኛና መለስተኛ ባለሙያዎች ቅድመ-ምዘና ምዝገባ በማድረግ 2,100 ባለሙያዎችን ለመመዘን ታቅዶ 29 (112%) መሪ መዛኞችን በማፍራት 3,953 (109.81%) ባለሙያዎችን መመዝገብ የተቻለ ሲሆን ከነዚህም መካከል 20,061 (98.14%) ባለሙያዎች ተመዝነው 1,336 (63.62%) ምዘናውን ያለፉ እና 86 ባለሙያዎች ከፍ ወዳለ ደረጃ ማደግ ችለዋል፡፡ እንዲሁም በብቃት ምዘናው ላላለፉ 300 ባለሙያዎች የኩባንያ ትብብር ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ 338 (112.67%) ባለሙያዎች ስልጠና አግኝተዋል፡፡ በሌላ በኩል ለ175 ሥራ ተቋራጮች እና ለ42 አማካሪ ድርጅቶች በሰው ሃይል ማብቃት፣ በግብዓት፣ በአደረጃጀትና በክህሎት ላይ የሚስተዋሉ ችግሮችን ለመቅረፍ የሚያስችል ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ ለ87 (49.71%) ሥራ ተቋራጮች እና ለ31 (74%) አማካሪ ድርጅቶች ድጋፍ ማድረግ ተችሏል፡፡

የክልሉን ተቋራጮችና አማካሪዎች ቁጥር ለማሳደግ እንዲሁም ተወዳዳሪ ስራ ተቋራጮችን እና አማካሪዎችን ከመፍጠር አንፃር (አዲስ 1,300፣ እድሳት 1,500፣ እድገት 120) በድምሩ 2,920

ሥራ ተቋራጮችን ብቃት በማረጋገጥ ለመመዝገብ ታቅዶ ለ3,483 (119.28%) ሥራ ተቋራጮች (አዲስ 1888፣ እድሳት 1,489፣ እድገት 106) ምዝገባ የተደረገ ሲሆን ለ317 አማካሪዎች (አዲስ 50፣ እድሳት 250፣ እድገት 17) ብቃት በማረጋገጥ ምዝገባ ለማድረግ ታቅዶ 258 (81.39%) አማካሪዎች (አዲስ 75፣ እድሳት 165፣ እድገት 18) ምዝገባ ተደርጓል፡፡ በተመሳሳይ ለ1,618 ኮንስትራክሽን ባለሙያዎች የሙያ ፍቃድ ምዝገባ ለማድረግ ታቅዶ ለ2,077 (128.37%) ባለሙያዎች ምዝገባ ተደርጓል፡፡ ለ144 ሥራ ተቋራጮች እና ለ98 አማካሪዎች የመስክ ድጋፍና ኢንስፔክሽን ለማድረግ ታቅዶ ለ108 (75%) ሥራ ተቋራጮች እና ለ90 (91.84%) አማካሪዎች በመስክ ድጋፍና ኢንስፔክሽን ማድረግ ተችሏል፡፡

## የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ አሠራር ሥርዓት ማበልፀግ

የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ፖሊሲ ማስፈጸሚያ፣ የህግና አሠራር ሥርዓት ከማበልፀግ አኳያ የህንጻ አዋጅ አደረጃጀት በተቋቋመባቸው በ206 ከተሞች፣ ክፍለ ከተሞችና መሪ ማዘጋጃ ቤቶች በተፈጠረው አደረጃጀት መሰረት የሰው ሃይል አሟልተው ወደ ስራ እንዲገቡ ክትትልና ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ በ206 (100%) ከተሞች ክትትልና ድጋፍ የተደረገ ሲሆን የህንፃ አዋጅ አደረጃጀት በተፈጠረባቸው ከተሞች ለሚገኙ 40,000 ፕሮጀክቶች የፕላን ስምምነት እና የግንባታ ፈቃድ ለመስጠት ታቅዶ ለ47,886 (119.72%) የፕላን ስምምነት፣ ለ43,902 (109.76%) ፕሮጀክቶች የግንባታ ፈቃድ የተሰጠ ሲሆን ለ30,000 ግንባታዎች ቁጥጥር ለማድረግ ታቅዶ ለ33,744 (112.48%) ግንባታዎች ቁጥጥር ማድረግ ተችሏል፡፡

## የውለታና የዲዛይን ዝግጅት ቁጥጥርና ሙያዊ ድጋፍ ማድረግ

በ2014 ዓ.ም በክልሉ በመንግስት በጀት ለሚሰሩ 84 ሕንፃዎች የውለታና የዲዛይን ዝግጅት ሲጠየቅ እንዲሁም በግንባታ ሂደት የቁጥጥርና ሙያዊ ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ ለ86 (102.38%) ፕሮጀክቶች ድጋፍ ተደርጓል፡፡ በሌሎች የመንግስት ሴክተር መስሪያቤቶች የተዘጋጁ 40 የጨረታ ዶክመንቶችን በግንባታ ህጉ መሰረት መሆኑን በምርመራ ለማረጋገጥ ታቅዶ 38 (95%)፣ 74 የጊዜ ማራዘሚያ ጥያቄዎችን መርምሮ ለማፅደቅ ታቅዶ 58 (78.38%)፣ 40 የአማካሪ ክፍያ መርምሮ ለማፅደቅ ታቅዶ 18 (45%)፣ በመንግስት ተቋማት ለሚከናወኑ 60 የግንባታ ኘሮጀክቶች ተጨማሪ ስራ ለመመርመር ታቅዶ ለ58 (97%) ምርመራ ማድረግ ተችሏል፡፡ እንዲሁም በመንግስት በጀት ለሚገነቡ 35 ግንባታዎች ጊዜያዊ እና የመጨረሻ ርክክብ በሚደረግበት ወቅት ሙያዊ ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ ለ36 (102.8%) የመንግስት ግንባታዎች የመጨረሻ ርክክብ ወቅት ሙያ ድጋፍ ማድረግ ተችሏል፡፡

### የካባ ቦታዎች ማዘጋጀት እና ማልማት

በክልሉ 40 ስትራቴጂያዊ ጠቀሜታ ያላቸው የግንባታ ግብዓት መገኛ ቦታዎችን በማፈላለግ እና ከሶስተኛ ወገን ነፃ በማድረግ ካርታና ፕላን በማዘጋጀ በአዲስ እንዲለሙ ለማድረግ ታቅዶ 162 (405%) ካርታና ፕላን የተዘጋጀላቸው ሲሆን 38(95.0%) በአዲስ እንዲለሙና ጥቅም ላይ እንዲውሉ ተደርጓል፡፡

### የግንባታ ማቴሪያል ጥራት ፍተሻ

ከደንበኞች በሚቀርቡ የፍተሻ ጥያቄዎች መሰረት ለ220 የተለያዩ ዓይነት የኮንስትራክሽን ግብዓቶች ፍተሻ ለማድረግ ታቅዶ 220 (100%) የፍተሻ ስራ በመስራት ውጤቱን ለሚመለከታቸው አካላት በማሳወቅ የግንባታ ጥራትን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

## እንስሳትና ዓሳ ሃብት ልማት

### የወተት ሀብት ልማት

በበጀት አመቱ 1,357,809 ቶን (ከአካባቢ ላሞች 1,063,214፣ከተሻሻሉ ዝርያዎች 292,900 እና ከግመል 1,695) ቶን ወተት ለማምረት ታቅዶ 1,375,443 ቶን (ከአካባቢ ዝርያ ላሞች 1,029,958(96%)፣ ከተሻሻሉ ዝርያዎች 345,388 ቶን (117%) እና ከግመል 97 ቶን ወተት ተመርቷል፡፡ የወተት ምርት ከባለፈው በጀት አመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር በ172,646 ሊትር(14%) ጭማሪ አሳይቷል፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ የወተት ምርታማነትን ለማሻሻል በተሰራው ስራ የአካባቢ ዝርያ ላሞችን የወተት ምርት 1.7 ሊትር እና የተሻሻሉ ዝርያ ላሞችን 12 ሊትር ለማድረስ ታቅዶ የአካባቢ ዝርያ ላሞችን 1.67 ሊትር እና የተሻሻሉ ዝርያ ላሞችን 10.54 ሊትር ማድረስ ተችሏል፡፡



የወተት ሀብት ልማት-ዳንግላ ከተማ

**የአብክመ የመንግስት ኮሙዩኒኬሽን ቢሮ**

## የሥጋ ሀብት ልማት

በበጀት ዓመቱ 1,712,992 ዳል,ጋ ከብት፤ 4,979,832 በጎች እና 2,873,000 ፍየሎችን በድምሩ 9,565,824 እንሰሳትን በማድለብ ለገበያ ለማቅረብ ታቅዶ ዳል,ጋ ከብት 2,066,369 (120%)፣ በጎች 4,924,999 (99%) እና ፍየሎች 2,516,806 (87%) በድምሩ 9,508,174 (99%) እንሰሳትን በማድለብ ለገበያ ማቅረብ ተችሏል፡፡ በመሆኑም በ2014 ዓ.ም ከዳል,ጋ ከብት 219,263 ቶን፣ ከበግ 55,652 ቶን፣ ከፍየል 34,476 ቶን፣ ከዶሮ 11,369 እና ከዓሣ 10125.25 ቶን በድምሩ 330,885 ቶን ሥጋ ለማምረት ታቅዶ ከዳል,ጋ ከብት፣

በግና ፍየል 324,938 ቶን (104%)፣ የዶሮ ስጋ 7,555.37 ቶን(66.5%) እና የዓሣ ስጋ 6,472 ቶን /64%/ በድምሩ 338,956 ቶን (102%) ስጋ ተመርቷል፡፡ በተመሳሳይ በበጀት አመቱ የስጋ ምርታማነትን ለማሻሻል በተሰራው ስራ የዳል,ጋ ከብትን 128 ኪሎ ግራም፣ የበግ 13 ኪሎ ግራም እንዲሁም የፍየልን 12 ኪሎ ግራም ለማድረስ ታቅዶ የዳል,ጋ ከብትን 128.10 ኪሎ ግራም፣ የበግ 12.55 እና የፍየልን ስጋ ምርታማነት 11.43 ኪሎ ግራም ማድረስ ተችሏል፡፡

## የቆዳና ሌጦ ሀብት ልማት

በበጀት ዓመቱ የቆዳና ሌጦ ሀብት ልማት 8,074,361 ሲሆን ከዚህ ውስጥ የዳል,ጋ ከብት 1,220,144፣ የበግ 4,379,923 እና የፍየል 2,474,859 ቆዳና ሌጦ ምርት በማምረት ለገበያ ለማቅረብ ታቅዶ የዳል,ጋ ከብት ቆዳ 1,118,115 (91%) ፣ የበግ ሌጦ 4,039,045 (92%) እና የፍየል ሌጦ 1,901,815 (76%)፣ በድምሩ 7,058,975 (87%) ጥሬ ቆዳና ሌጦ ምርት ለገበያ ማቅረብ ተችሏል፡፡

## የእንስሳት ዝርያ ማሻሻል እና ጥበቃ

በ2013 በጀት ዓመት የነበረውን 621,690 ክልስ የዳል,ጋ ከብት ቁጥር በ2014 ዓ.ም ወደ 747,304 ለማሳደግ ታቅዶ 643,198 /86%/ ማድረስ ተችሏል፡፡ የዝርያ ማሻሻል ሥራውን ለማጎልበት የሚያስችል የእንስት ጥጃ የማስወለድ አቅም ያለው /sexed semen/ 1401 ዶዝ የሴክሲድ ለ17 ወረዳዎች ቀርቦ 989 ላሞች በማዳቀል 384 ላሞች የክብድና ምርመራ ተደርጎላቸው 121 (32%) መከበዳቸው ተረጋግጧል፡፡ በተጨማሪም 1044 ዶዝ ኮሪያ ፍሪዥያን አባላዘር በ4 ወረዳዎች ቀርቦ 1024 ላሞች የተዳቀሉ ሲሆን 258 ላሞች የክብድና ምርመራ ተደርጎ 207 (80%) ላሞች መከበዳቸው ተረጋግጧል፡፡



ሰው ሰራሽ የእንስሳት ማዳቀያ ማዕከል-ባህርዳር

## የማዳቀል አገልግሎት

በበጀት ዓመቱ 354,500 ዳልጋ ከብት ላሞችንና ጊደሮችን ከዚህ ውስጥ በተፈጥሮ ድራት 204,000፣በሆርሞን ድራት 11,000፤ በተሻሻለ ኮርማ 139,500 የማዳቀል አገልግሎት ለመስጠት እቅድ ተይዞ በተፈጥሮ ድራት 93,575 (46/%)፤በሆርሞን ድራት 5,591 (51%) እንዲሁም በተሻሻለ ኮርማ 124,558 (89%) በድምሩ 223,724 (63%) ላሞችና ጊደሮች ማዳቀል ተችሏል፡፡የማዳቀል ስራውን መሰረት አድርጎ የተወለዱ ጥጆች በተፈጥሮ ድራት 49,150 በሆርሞን ድራት 1,245 እና በተሸሻለ ኮርማ ተዳቅለው የተወለዱ 75,220 በድምሩ 125,615 ክልስ ጥጆች ለማስወለድ ታቅዶ በተፈጥሮ ድራት 41484 (84%)፣ በሆርሞን ድራት 460 (37%) እንዲሁም በተሻሻለ ኮርማ 66,970 (89%) በድምሩ 108,914 (87%) ክልስ ጥጆች ማስወለድ ተችሏል፡፡



በእንስሳት ዝርያ ማሻሻል የተወለዱ ጥጆች-ቻግኒ ከተማ

## የደሮ ስጋ እና እንቁላል ምርት

በበጀት አመቱ 2260 የአንድ ቀን ጫጩት ኣሳዳጊዎችን በማደራጀትና በማጠናከር 5,193,736 የአንድ ቀን ጫጩት ለማቅረብ እቅድ ተይዞ 1,760 (78%) አሳዳጊዎችን አሰልጥኖ ወደ ስራ በማስገባት 5,314,497 (102%) የአንድ ቀን ጫጩት ማሳደግ ተችሏል፡፡

## የዓሳ ምርት

በአማራ ክልል በአሳ ሀብት ሠፊ አቅም ቢኖርም ለዘመናት ይህንን ሀብት በሚፈለገው ደረጃ ሳንጠቀምበት ኖረናል፡፡ በመሆኑም በበጀት ዓመቱ የአሳ ምርትን ለማሳደግ በተሰራው ስራ 28,915 ቶን የዓሳ ምርትና 10,125 ቶን የዓሣ ስጋ ለማምረት ታቅዶ 21,378 ቶን/74%/ የዓሳ ምርት እና 6,472 ቶን /64/ የዓሣ ስጋ ማምረት ተችሏል፡፡

## የማር እና ሰም ምርት

በ2014 ዓ.ም 21,854 (ከዘመናዊ 6295፣ ከሽግግር 2,012 እና ከባህላዊ 13,547) ቶን ማር ለማምረት ታቅዶ 18,207 ቶን (83%) የተመረተ ሲሆን ከዚህ ውስጥ ከዘመናዊ ቀፎ 4,040 (64.2%)፣ከሽግግር ቀፎ 1,365.5 ቶን (68%) እና ከባህላዊ ቀፎ 12,801 ቶን (94.5%) ማር ተመርቷል፡፡ከተመረተው መካከል 1,849 ቶን የተጣራ ሰም ለማምረት ታቅዶ 639 ቶን (35%) ማምረት ተችሏል፡፡ ከላይ የተቀመጠውን ግብ ለማሳካት በበጀት ዓመቱ 71,300 (ወደ ዘመናዊ ቀፎ 40,250 እና ወደ ሽግግር ቀፎ 31,050) ህብረ-ንቦችን ለማዛወር ታቅዶ ወደ ዘመናዊ ቀፎ 21,591 (54%) እንዲሁም ወደ ሽግግር ቀፎ 14,511(47%) በድምሩ 36,102 (52%) ህብረ-ንብ ማዛወር ተችሏል፡፡



የንብ ሀብት ልማት-ከሚሴ ከተማ አስተዳደር ቃጫ ቀበሌ

## የእንስሳት በሽታን መከላከልና መቆጣጠር

በበጀት አመቱ ድንበር ዘለል የእንስሳት በሽታዎችና መደበኛ የበሽታ ወረርሽኝን ለመከላከልና ለመቆጣጠር ለ51,321,600 እንስሳት የክትባት አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ ለ46,258,971 እንስሳት ክትባት በመስጠት የእቅዱን (90%) ማከናወን ተችሏል፡፡ ከዚህ መካከል የቅድመ መከላከል ሕክምና አገልግሎት 22,489,118 እንስሳት ለመስጠት ታቅዶ 24,245,003 (108%) የተከናወነ ሲሆን የውጭ ጥገኛ ቁጥጥር በክልሉ ድጋፍ የፍየሎችና በጎች በመጀመሪያ ዙር 424021 በግ እና ፍየሎች መርጨት ተችሏል፡፡ በሌላ በኩል የፈውስ ህክምና አገልግሎት ለመስጠት በተሰራው ስራ ለ12,635,000 እንስሳት የፈውስ ሕክምና አገልግሎት እንዲያገኙ ታቅዶ 10,571,866 (84%) ተከናውኗል፡፡

## ግብርና ምርምር

የአማራ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት በአስር ዓመቱ መሪ ዕቅድ እንዳስቀመጠው የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥና ገበያ መር በሆነ አቅጣጫ በፍጥነት ማሳደግ የሚያስችሉ የግብርና ቴክኖሎጂዎችን በማቅረብ ዘላቂና ፈጣን የሆነ ልማት በክልሉ ለማስመዝገብ እንዲቻል ከፍተኛ አስተዋጽኦ ለማድረግ የተለያዩ ችግር ፈቺ ቴክኖሎጂዎችን በማፍለቅ፣ ውጤታማ የሆኑ ቴክኖሎጂዎችን ከሀገር ውስጥም ሆነ ከሀገር ውጭ ወደ ክልሉ በማሰገባትና በማላመድ በርካታ

ስራዎችን አከናወኗል፡፡ በበጀት ዓመቱ 642 የምርምር ሙከራዎች ታቅደው 457 (71.12%) ማከናወን ተችሏል፡፡ ከዚህ ውስጥ 99 ቴክኖሎጂ/ምክረ-ሃሳቦች/ ይወጣሉ ተብሎ ቢታቀድም 72 ቴክኖሎጂዎች /ምክረ ሃሳቦች/ ቀርበዋል፣ አፈፃፀሙም 72.73% ነው፡፡

## የሰብል ምርምር

በ2014 ዓ.ም ከታቀዱት 316 (271 በመኸር፣ 45 በመስኖ) የምርምር ስራዎች 246 (201 በመኸር፣ 45 በመስኖ) ሙከራዎች በታሰበላቸው ደረጃ የተከናወኑ በመሆኑ አፈፃፀሙ 77.85% ሆኗል። በበጀት አመቱ በአጠቃላይ 41 ቴክኖሎጂዎች ለማውጣት ታቅዶ 28 ቴክኖሎጂ/ምክረ-ሃሳብ/ ወጥተዋል፡፡

## የእንስሳት ምርምር

የእንስሳት ምርምር በዋናነት በእንስሳት ዝርያ ማሻሻል፣ በመኖ ልማት፣ በእንስሳት ጤና፣ ስነ-አመጋገብን ማሻሻል እና የእንስሳት አያያዝ ላይ የሚያተኩሩ ናቸው፡፡ እነዚህም

የምርምር ስራዎች የሚከናወኑት በዳልጋ ከብት፣ በበግና ፍየል፣ በዶሮ፣ በንብ፣ በዓሳና ቢጋማ ከብት ላይ ነው፡፡ በበጀት ዓመቱ 179 ሙከራዎች በማከናዎን በበግና ፍየል 2፣ በመኖና ስነምግብ 3፣ በእንስሳት ጤና 4 እና በአሳ 1 በድምሩ 10 ቴክኖሎጂዎችን ለማውጣት ታቅዶ 91 ሙከራዎችን በማከናወን በዳልጋ ከብት (ወተትና ስጋ) 1፤በመኖና ስነምግብ 3፣ በእንስሳት ጤና1፣ በንብ1፤ በአሳ 3 እና በዶሮ 2 በድምሩ 11 ቴክኖሎጅዎች ወጠተዋል፣ አፈጻፀሙም 110% መሆኑን ያሳያል፡፡ የሙከራዎች አፈጻጸም 50.84% ነው፡፡

## አፈርና ውኃ ምርምር

በ2014 ዓ.ም በተለያዩ ስነ-ምሕዳሮች 61 የምርምር ሥራዎችን ለማካሄድ ታቅዶ 55 የምርምር ሥራዎች ተካሄደዋል፡፡ በአፈር ለምነት 14፣ በግብርና ውሃ አያያዝ 8 እና በአፈርና ውሃ ጥበቃ 2 በድምሩ 24 ቴክኖሎጂዎችን/ ምክረ ሃሳቦችን/ ለማውጣት ታቅዶ በአፈር ለምነት 10፣ በግብርና ውሃ አያያዝ 7 እና በአፈርና ውሃ ጥበቃ 4 በድምሩ 21 ቴክኖሎጂዎች/ ምክረሃሳቦች/ ወጥተዋል፣ አፈጻጸሙም 87.5% ነው፡፡

## የደን ምርምር

በበጀት ዓመቱ በደን ምርምር ዘርፍ 58 ሙከራዎችን ለማከናወን ታቅዶ 37 የተከናወነ ሲሆን አፈጻጸሙም 63.8% ነው፡፡ የምርምር ስራዎች የፊዚካል አፈጻጸም ደግሞ በአማካይ 55.7% ነው፡፡ ለአፈጻጸሙ ዝቅተኛ መሆን ዋነኛ ምክንያት በአሽባሪውና ወራሪው የሕወሃት ቡድን በክልሉ በከፈተው ጦርነት እና የጸጥታ ችግር በሰቆጣ እና ስሪንቃ እየተካሄዱ የነበሩ ሙከራዎች ሙሉ በሙሉ በመቋረጣቸው ነው፡፡ ስለሆነም ይህ መረጃ በሦስት ማዕከላት (አዴት፣

ደብረብርሃን እና ጎንደር) ብቻ የተሰሩትን የሚያካትት ነው፡፡ በክልሉ ከፍተኛ ሀብት የፈሰሰባቸው፣ ከውጭ አገር በውጭ ምንዛሬ የገቡ የዛፍ ዝርያዎች እና ረጅም ጊዜ የወሰዱ ውጤታማ የምርምር ስራዎች በድምሩ 25 ሙከራዎች (በሰቆጣ 12፣ በስሪንቃ 9፣ በጎንደር 2 እና በደብረብርሃን 2 ሙከራዎች) ህ.ወ.ሀ.ት በከፈተው ጦርነት በመውደማቸው በተገቢው መንገድ ሳይተገበሩ ቀርተዋል፡፡

## የዘር ምርምር

በዘር ጥራት ከታቀዱት 7 የምርምር ሙከራዎች ውስጥ 6 ነባር እና 1 አዲስ ሙከራዎች ሲሆኑ ሁሉም ተከናውነዋል፣ አፈጻጸሙም 100 ነው፡፡ ከስራዎች ውስጥ ዋና ዋናዎቹ የበቆሎ ዘር ጥራትን የሚቀንሱ ሁኔታዎችን መፈተሽና ማስተካከያ ምክረ ሃሳብ መስጠት፣ የዘር ምርታማነትንና ጥራትን ሊያሻሽሉ የሚችሉ የአሰራር ስልቶችን በማጥናት የተሻሉ ቴክኖሎጂዎችን ማፍለቅ እንዲሁም የላም ድንች ዘርን በክልሉ ደጋማ ቦታዎች ለማምረት የሚያስችሉ ሁኔታዎችን መፈተሽ የመሰሳሰሉት ይጠቀሳሉ፡፡ ከእነዚህ የምርምር ስራዎች ውስጥ ሁለት የምርምር ስራዎች 1ኛ የተከላ ጊዜና የተከላ ርቀት በማሾ የዘር መጠንና ጥራት ላይ ያለውን ተጽዕኖ ጥናት፣ 2ኛ በተለያዩ የበቆሎ የዘር ደረጃዎች የዘር ጥራትን የሚያጎድፉ ባዕድ ነገሮችን መለየት የሚሉ የምርምር ስራዎች ተጠናቋል፡፡

## አዳዲስ የሰብል ዝርያዎችን ያስለቀቁ ተመራማሪዎች

| ተቁ | የሰብል ዓይነት | የዝርያው ስም | ያስለቀቀው ማዕከል | ዝርያውን ያስለቀቁ 3 ተመራማሪዎች በደረጃ | |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ጤፍ የመኸር | ብር አዳማ | አዴት ግብርና ምርምር ማዕከል | አቶ ምስጋናው ፈረደ |  |
| | | | | አቶ ሠዋገኝ ታሪኩ |  |
| | | | | አቶ አትንኩት ፈንታሁን |  |
| 2 | ጤፍ ለመስኖ | በኩር | አዴት ግብርና ምርምር ማዕከል | አቶ ሠዋገኝ ታሪኩ |  |
| | | | | አቶ ገደፋው ምስጋናው |  |
| | | | | አቶ አትንኩት ፈንታሁን |  |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 3 | የምግብ ገብስ | ዝና | አዴት ግብርና ምርምር ማዕከል | አቶ መሌ ጥላሁን |  |
| | | | | አቶ አቡኑ ማረፊያ |  |
| | | | | ወ/ሪት ዝና ደምሴ |  |
| 4 | የምግበ ሲናር | አጀይ | አዴት ግብርና ምርምር ማዕከል | አቶ መሌ ጥላሁን |  |
| | | | | አቶ ምስጋናው ፈረደ |  |
| | | | | ወ/ሪት ዝና ደምሴ |  |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 5 | ዳጉሳ | AD14-SEL045 | አዴት ግብርና ምርምር ማዕከል | አቶ አንዱዓለም ወሌ |  |
| | | | | አቶ ባለው ፈረደ |  |
| | | | | አቶ ዘላለም አያልነህ |  |
| 6 | ስንዴ | YET-KUL-17#62 | የደብረ ብርሃን ግብርና ምርምር ማዕከል | አቶ ተስፋዬ ሙሉጌታ |  |

# ህብረት ሥራ ማኅበራት ማስፋፊያ

## መሰረታዊ ኅብረት ሥራ ማኅበራትን ማቋቋም

በበጀት ዓመቱ 42 መሰረታዊ ህብረትሥራ ማህበራትን ለማቋቋም ዕቅድ ተይዞ 2,091 የተለያዩ መሰረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራትን በማቋቋም ከእቅድ በላይ ማከናዎን ተችሏል፡፡እነዚህ ማህበራትም በውስጣቸው 224,434 (ሴት 45,605) አባላትን አቅፈዋል እንዲሁም በመነሻ የካፒታል መጠን ብር 214,917,142 ተቋቁመዋል፡፡በተጨማሪም 756 የመኖሪያ ቤቶች እና አካባቢ ልማት መሰረታዊ ኅብረትሥራ ማኅበራትን ማቋቋም ተችሏል፡፡በእነዚህ የመኖሪያ ቤቶች እና አካባቢ ልማት ኅብረት ሥራ ማኅበራት 19,498 ግለሰቦች መካከል 6,380 ሴቶች ሲሆኑ ብር 181,641,220 መነሻ ካፒታል በመያዝ ተቋቁመዋል፡፡



ህብረት ስራ ማህበራትን ማቋቋም-ደቡብ ጎንደር

## ዩኒየን ማቋቋም

በ2014 ዓ.ም አንድ የመስኖ ግብይት ዩኒየን ለማቋቋም ዕቅድ ተይዞ ዩኒየኑ ሲቋቋም 18 መሰረታዊ የመስኖ ልማት ኅብረት ሥራ ማህበራትን ያቀፈ እና ብር 998,000 መነሻ ካፒታል የያዘ 1/አንድ የመስኖ ልማት ግብይት ዩኒየን ማቋቋም የተቻለ ሲሆን፣ አፈጻጸሙም የእቅዱን 100% ማከናዎን ተችሏል፡፡

### ነባር ኅብረት ሥራ ማኅበራትን ማጠናከር

በበጀት አመቱ 4,241 መሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማኅበራትን ለማጠናከር ታቅዶ 3,519 /83%/ መሰረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራትን የማጠናከር ሥራ ተሰርቷል፡፡ በዩንዮን ደረጃ 44

ዩኒዮኖችን ለማጠናከር ታቅዶ 42 /95%/ ዮኒዮኖችን በተለያዩ የማጠናከሪያ ተግባራት በመስራት የማጠናከር ሥራ ተሰርቷል፡፡

## የኅብረት ሥራ ማህበራት ሂሳብ ኦዲት

**በ**2014 ዓ.ም 7,865 መሠረታዊ የኅብረትሥራ ማህበራት ሂሳብ ኦዲት ለማድረግ ዕቅድ ተይዞ፤ 3,468 ኦዲት የተደረገ ሲሆን አፈፃፀሙም 44% መድረሱን ያሳያል፡፡በመሆኑም በበጀት አመቱ የተገኘ ትርፍ የኦዲት አገልግሎት ካገኙት 3,468 መሰረታዊ ማህበራት ውስጥ 3,118 (90%) መሰረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት ባደረጉት የሥራ እንቅስቃሴ ብር 206,856,059 የተጣራ ትርፍ አግኝተዋል፡፡ የኦዲት አገልግሎት ካገኙ 3,468 ውስጥ በ918 (26%) የተገኘው የጉድለት መጠን ብር 56,350,853 ሲሆን በ1,366 ግለሰቦች (414 ሴት) (በ501 አመራር እና 865 ቅጥር ሰራተኞች) ጉድለት ተገኝቷል፣፡ የሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ከተሰጣቸው ውስጥ በ338 መሰረታዊ ማህበራት ላይ ደግሞ ብር 8,346,150 ኪሳራ ተከስቷል፡፡

### ጉድለት ማስመለስ

**በ2014 ዓ.ም** ብር 61,281,427 እና ካለፉት ዓመታት ብር 135,517,953 በድምሩ ብር 196,799,380 ጉድለት የተገኘ ቢሆንም በድርድርና በፍርድ ቤት ውሳኔ ከዘመኑ ጉድለት ብር 19,724,355 (32%) እና ከአለፉት ዓመታት ብር 15,951,694 (12%) በአጠቃላይ ብር 35,676,049 (18%) ጉድለት ተመልሷል፡፡

# አደጋ መከላከልና ምግብ ዋስትና ፕሮግራም

## መረጃ ማሰባሰብና ወቅታዊ መግለጫ መስጠት

በክልሉ ውስጥ የሚታየውን የአደጋ ስጋት ሁኔታ መከታተል ይቻል ዘንድ ከ153 የገጠር ወረዳዎች 52 ሳምንታዊና 1,836 ወርሃዊ የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ መረጃዎችን ለማሰባሰብ ታቅዶ 43 (82%) ሳምንታዊ መረጃ እና 762 (41%) ወርሃዊ መረጃ ተሰብስቦ ወደ ዳታቤዝ ገብቶ ለሚመለከታቸው አካላት በወቅቱ ለማድረስ ተችሏል፡፡

### የአስቸኳይ ጊዜ ምላሽ ማስተባባሪያ ማዕከል

የአስቸኳይ ጊዜ ምላሽ ማስተባበሪያ ማዕከል ከፌደራል ሚኒስትር መስሪያ ቤቶች፣ ከክልል ቢሮዎች፣ መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶችና አለም አቀፍ የሰብአዊ ጉዳዮች ማስተባበሪያ ድርጅቶች በተውጣጣ ቡድን የተቋቋመ አደረጃጀት ነው፡፡ተፈናቃዮችን ለመደገፍ ይቻል ዘንድ ከመስከረም 10/2014 ጀምሮ የሚተገበር እቅድ በማዘጋጀት የተለያዩ ስራዎችን ማከናወን ችሏል፡፡ በዕቅዱ መሰረት ተግባራት በየክላስተሩና አደረጃጀቱ መሰረት በየዕለቱ ይገመገማሉ፣

ክትትል ይደረግባቸዋል፣ በየሳምንቱ በተቋቋሙ የቴክኒክና አብይ ኮሚቴዎች እየተገመገመና አቅጣጫ እየተሰጠበት ሲከናወን ቆይቷል፡፡ ተጎጅዎችን ለመደገፍና ለማቋቋም ይቻል ዘንድ ስራዎችን በበላይነት የሚከታተልና አቅጣጫ የሚሰጥ የክልል አብይ ኮሚቴ የተቋቋመ ሲሆን የአስቸኳይ ጊዜ ምላሽ ማስተባበሪያ ማዕከል በክልሉ አደጋ መከላከል ምግብ ዋስትና ፕሮግራም ማስተባበሪያ ኮሚሽን አስተባባሪነት የሚመራ ሆኖ ተጠሪነቱ ለክልል አብይ ኮሚቴ ሆኖ ጦርነቱ በተካሄደባቸው ዞኖችና ወረዳዎች ያሉትን ተፈናቃዮችና ተጎጅ የህብረተሰብ ክፍሎች ለመደገፍ የተለያዩ ስራዎችን አከናውኗል፡፡

## የጊዜያዊ መጠለያ ዝግጅት-

በክልሉ ውስጥ አሸባሪው የህ.ወ.ሀ.ት ቡድን በከፈተው ጦርነት ሳቢያ ከ7 ዞኖች ከሚገኙ ወረዳዎች ተፈናቅለው ለመጡ ዜጎች 128 መጠለያዎችን (107 ድንኳን፣ 3 ራብሆልና 18 ሸዶች) በተለያዩ ቦታዎች (ደባርቅና ዳባት በትምህርት ቤቶችና በድንኳን፣ ባህር ዳር ዘንዘልማ የገበያ ማዕከል፣ እብናት በትምህርት ቤት እና በድንኳን፣ በሞጣ የኢንዱስትሪ መንደር፣በመካነ ሰላም ት/ቤት፣ በደሴና ኮምቦልቻ በድንኳን፣ ደብረብርሃን ከተማ በትምህርት ቤቶች) በማዘጋጀትና ከ94 በላይ በሚሆኑ ትምህርት ቤቶች ከ 76,522 በላይ ህዝብ እንዲጠለሉ በማድረግ ድጋፍ እየቀረበላቸው የነበረ ሲሆን በመንግስት የተዘጋጁ መጠለያዎች በቂ ባለመሆናቸው ከ1,334,791 በላይ ተፈናቃዮች በዘመድ አዝማድ ተጠልለው ድጋፍ ሲደረግላቸው ነበር፡፡ በመጠለያ ለሚገኙ የህብረተሰብ ክፍሎች ምግብ ነክ ያልሆኑ የቁሳቁስ ድጋፍ በደባርቅ፣ ዳባት፣ ደሴ፣ እብናትና ባህር ዳር፣ ደ/ብርሃን፣ መካነ ሰላም፣ ሞጣ በአጠቃላይ ለ175,342 አባወራ እና እማወራ ለማሰራጨት ተችሏል፡፡



ሰሜን ወሎ ዞን ጃራ ጊዚያዊ መጠለያ

## በተለያዩ አደጋዎች ለተጎዱ የህብረተሰብ ክፍሎች የተደረገ ድጋፍ

በክልሉ መጋዘኖች ከሚገኘው ክምችት ለ128,445 ተጠቃሚዎች እህል 20,552..8 ኩንታል የዕለት ምግብ፣ 3,678.5 ኩንታል የተለያዩ የምግብ አይነቶች ስኳር፣ በሶ ዱቄት፣ መኮረኒ፣ ምስር ክክ፣ በርበሬ፣ ሽሮ፣15,258 ካርቶን የተለያዩ የምግብ አይነቶች ማለትም አንከር ወተት፣ ብስኩትና ጁስ ለተጠቃሚዎች የተሰራጨ ሲሆን የተለያዩ አልባሳትና ቁሳቁሶች (28,281 የቤት ቁሳቁሶች፣ ጀሪካን፣ ባቲ ሳህን፣ ብረት ድስት፣ ባልዲ)፣ ደብተር፣ ፍራሽ፣ ብርድ ልብስ፣ 691 ቦንዳ ልብስ፣ 84,320 ቁጥር የተለያዩ አልባሳትና የመሳሰሉት ድጋፎች ለተጠቃሚዎች ተልኮላቸዋል፡፡ከዚህ በተጨማሪ ከ2013 ዓ.ም የዞረ ለ 28 ወረዳዎች ለ589,176 ተጠቃሚዎች የሚውል ለ1ኛ እና 2ኛ ዙር ለወረዳ አድሚን በጀት 1,482,833 ብር ለተዘዋዋሪ 317,747,630 ብር ተመድቦ በአጠቃላይ 319,230,463 ብር (100%) ለተጠቃሚዎች ማሰራጨት ተችሏል።

## የልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም ደንበኞች ልየታ

የልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም ተጠቃሚዎች ልየታ በአዲስ መልክ ሁሉንም የማህበረሰብ ክፍሎች እኩል ባካተተ መልኩ የድሃ ድሃ የሆኑትን እና ለተለያዩ አደጋዎች የበለጠ ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ለማካተት እንዲያስችል የባለፉት ዓመታት የድንገተኛ አደጋ ምላሽ፤ የተለያዩ የሳተላይት መረጃዎች እና የድህነት መጠን/ስፋት (Extreme poverty index) መሠረት በማድረግ የፕሮግራም ወረዳዎችንና በየወረዳው የተጠቃሚ ቁጥር በፌደራል ደረጃ ተወስኖ ለክልሉ **1,884,378** የቀጣይ አምስት ዓመት ዋና የፕሮግራም ደንበኞች እንዲሆኑ ፀድቆ ተልኳል፡፡

በቅድሚያ የፕሮግራሙን ተቋማዊ አደረጃጀት በነባርና አዲስ ወረዳዎች በማዋቀር በፕሮግራሙ አጠቃላይ ዓላማ፣ አሰራርና መርህ እንዲሁም በልየታ ተግባር ዙሪያ በየደረጃው ላለው የፕሮግራሙ ፈጻሚና ባለድርሻ አካል አጠቃላይ ግንዛቤ ፈጠራ ስራ ተሠጥቷል፡፡ የፕሮግራም ተጠቃሚዎች ልየታ ከክልል እስከ ቀበሌ በሚገኙ ፈፃሚ እና አስፈጻሚ አካላት ስራው ተተግብሯል፡፡ በዚህም መሠረት በአብዛኛዎቹ ወረዳዎች የፕሮግራም ተጠቃሚ ቤተሰቦች ልየታ ስራ ተጠናቋል፡፡

# ንግድና ገበያ ልማት

## ህጋዊ የንግድ ስርዓትን ማጎልበት

በበጀት አመቱ የንግድ እንቅስቃሴ በህግና በስርዓት ተገቢውን የንግድ ምዝገባ፣ ፍቃድ እና እድሳት እንዲያገኝ የንግዱ ማህበረሰብ ወደ ንግድ መረቡ በስፋት እንዲቀላቀል በተደረገው

ጥረት ለ91,710 ነጋዴዎች አዲስ የንግድ ምዝገባ ለመስጠት ታቅዶ ለ61,364 ግለሰብ ነጋዴ፣ ለ4,482 ህብረት ሽርክና፣ ለ896 ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር በድምሩ ለ66,742 (72.78%) የንግድ ማህበረሰብ የንግድ ምዝገባ ማካሄድ ተችሏል፡፡ ለ109,845 ነጋዴዎች ንግድ ስራ ፍቃድ ለመስጠት ታቅዶ ለ76,010 ግለሰብ ነጋዴ፣ ለ4,827 ህብረት ሽርክና እና ለ1,126 ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር በድምሩ ለ83,680 (76.18%) ነጋዴዎች የንግድ ስራ ፈቃድ መስጠት ተችሏል፡፡ ከዚህ መካከል 992 የአስመጭነትና 725 የላኪነት፣ 522 የአክሲዮን እና 84 የመንግስት የልማት ድርጅቶች የስራ ፈቃዶች ይገኙበታል፡፡

ከንግድ ፈቃድ ጋር በተያያዘ በተለያዩ ምክንያቶች የ18,659 ነጋዴዎች ፈቃድ የተሰረዘ ሲሆን ይህም ከተሰጠው የንግድ ፈቃድ አንፃር ሲነፃፀር (24%) ይሸፍናል፡፡432,135 የንግድ ፈቃድ እድሳት ለመስጠት ታቅዶ ለግለሰብ ነጋዴ 330,915፣ ለህብረት ሽርክና ማህበር 13,233 እና 34,492 ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር፣አስመጭነት 2,441 እና የላኪነት 2,002 በድምሩ ለ382,083(88.41%) የንግድ ፈቃድ እድሳት ተከናውኗል፡፡ ከዚህ ውስጥ 132 የአክሲዮን እና 144 የመንግስት የልማት ድርጅቶች ናቸው፡፡በተሰጠው አገልግሎትም ብር 61,236,158 ገቢ ተሰብስቧል፡፡ በክልላችን ህጋዊ የንግድ ፈቃድ አውጥተው የሚንቀሳቀሱ የንግድ ድርጅቶችን የንግድ ህግና አሰራር አክብረው እንዲንቀሳቀሱ እንዲሁም የንግድ ዘርፉ የሚፈልገውን ስነ-ምግባር አሟልተው ስራቸውን እንዲያከናውኑ ተገቢውን የቁጥጥርና የክትትል ስራ ማድረግ ተገቢ በመሆኑ እንዲሁም ያለ ንግድ ፈቃድ የሚደረግን የንግድ እንቅስቃሴ መከላከል ያለመ ስራ በመስራት በኩል በርካታ ተግባራት ተከናውነዋል፡፡



የንግድ ስርዓቱን ለማዘመን የአቅም ግንባታ ስልጠና-ባህርዳር

## የግብይት ስርዓቱን ዘመናዊ ማድረግ

ሸማቹም ሆነ ነጋዴው ህጋዊ የሆነ ደረሰኝ በመጠቀም የግብይት ስርዓቱ ዘመናዊና ህጋዊነትን የተላበሰ እና የሸማቹ ደህንነትና ጤንነት ለማረጋገጥ ይቻል ዘንድ አዲስ 23,007 እና ነባር 121,529 በድምሩ 144,536 ደረሰኝ ጥቅም ላይ እንዲውል እቅድ ተይዞ ክንውን አዲስ 14,194 (61.6%) ጥቅም ላይ ማዋል ተችሏል፡፡በተመሳሳይ ነባር 93,570 (76.9%) በድምሩ 107,764 (74.5%) ደረሰኝ ያላቸው የንግድ ድርጅቶች ለተጠቃሚዎች እንዲሰጡ ተደርጓል፡፡

## የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸውን ምርቶች መከታተል

የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸውን ምርቶች ክትትልና ድጋፍ በማድረግ በኩል በሁሉም የንግድ ድርጅቶች ቁጥጥር ለማድረግ 322,069 እቅድ ተይዞ 233,945(72%) የንግድ ድርጅቶች የቁጥጥር ስራ ተሰርቷል፡፡በዚህም የአገልግሎት ጊዜ ያለፈባቸው በፈሳሽ 26,748.84 ሊትር፤ በጠጣር 32,989.88 ኪሎ ግራም የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸውን ምርቶች ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ማስወገድ ተችሏል፡፡ በገንዘብ ሲገመት 1,523,942 ብር ነው፡፡

## የግብርና ምርት ትስስር

በ2014 ዓ.ም በቅድመና በድህረ የሰብል ምርት ግብይት 3,897,114 ኩንታል ምርት ለማስተሳሰር ታቅዶ 4,189,168 ኩንታል (100% በላይ) ማስተሳሰር የተቻለ ሲሆን በምርት ምድብ / commodity/ በዝርዝር ሲታይም ብዕርና አገዳ ከታቀደው 1,395,502 ኩ/ል (100%) ፣የቅባት እህሎች 52,680 ኩንታል (87.8%)፣ ቅመማ ቅመም 72,384 ኩንታል (90%)፣ ጥራጥሬ 421,620 ኩንታል (90%) እንዲሁም አትክልትና ፍራፍሬ 2,247,018 ኩንታል (100%)፣ አጣና ምርት ከታቀደው 66,200 (81%) ሜትር ኪዩብ፣ የጭረት ምርት(ጥጥ) 22,303 (70%) ኩንታል፣ እጣንና ሙጫ 392 (100%) ኩንታል ማስተሳሰር ተችሏል፡፡

በ2014 ዓ.ም 1,487,311 የቁም እንስሳት ወደ ቀጣዩ መዳረሻቸው በመሸኛ እንዲጓጓዙ ለማድረግ በእቅድ ተይዞ 1,276,644(86%) የተከናወነ ሲሆን በዝርዝር ሲታይ የዳልጋ ከብት 364,219 ለማስተሳሰር ታቅዶ 377,307 (100% በላይ) ተከናውኗል፣ በግና ፍየል 1,011,065 ለማስተሳሰር ታቅዶ 827,856(82%) ተከናውኗል፣ ጋማ ከብት 105,246 ለማስተሳሰር ታቅዶ 64,828 (62%) ተከናውኗል፣ ግመል 6,781 ለማስተሳሰር ታቅዶ 6,653 (98%) ተከናውኗል፣ ስጋ 484 ቶን ለማስተሳሰር ታቅዶ 512 ቶን (100%) ተከናውኗል፡፡ የአሳ ምርት ግብይት 2,688 ዕቅድ ተይዞ ክንውን 1,548 (58%) ቶን ማስተሳሰር ተችሏል፡፡ በተመሳሳይ 3,761,904 ቆዳና ሌጦ ምርትን ከፋብሪካዎች ጋር ለማስተሳሰር ታቅዶ 3,010,112(80%) ቆዳና ሌጦ በመሸኛ እንዲላክ ተደርጓል፡፡ በተናጠል ሲታይ በመሸኛ የተላከ የበግ ሌጦ 2,350,658 (86%)፣ የፍየል ሌጦ

475,407 (54%)፣ የዳልጋ ከብት ቆዳ 184,047 (100%) ነው፡፡ የዳልጋ ከብት ቆዳ ከፍተኛ የሆነበት ምክንያት በፋብሪካዎች እየተፈለገ በመምጣቱ ነው፡፡

በበጀት ዓመቱ የወተት ምርት 177,440 ቶን ታቅዶ ከታቀደው 140,156 ቶን (79%)፣ የማር ምርት 17,869 ታቅዶ 14,123 (79%) ቶን፣ እንስሳት መኖ 11,561 ታቅዶ 2,046 ቶን (100% በላይ)፣ ደሮ በቁጥር 2,726,574 ታቅዶ 2,336,193 (86%)፣ እንቁላል በቁጥር 28,052,172 ታቅዶ 25,166,303 (89%) የምርት ትስስር መፍጠር ተችሏል፡፡



የስንዴ ምርት ትስስር መድረክ-ደብረ ማርቆስ

## የመሰረታዊ ምርቶች አቅርቦትና ስርጭት

በሀገራችን በመሰረታዊ ምርቶች የገበያ ጉድለት በታየባቸው የስኳር፣ የምግብ ዘይት፣ የዳቦ ዱቄት እና ነዳጅ በመንግስት ድጎማ እየተደረገ ለህብረተሰቡ የማድረስ እና ገበያውን የማረጋጋት ስራ የተሰራ ሲሆን ግለሰቦችና ነጋዴዎች በሚፈጽሙት ህገ ወጥ የንግድ ስራ ምርቱን ለህብረተሰቡ በማድረስ በኩል ችግሮች አጋጥመዋል፡፡ችግሩን ለመቅረፍ የእለት ከእለት ክትትል እና ቁጥጥር ስራው ተጠናክሮ ተሰርቷል፡፡ በመሆኑም የስኳር አቅርቦትና ስርጭት ለ 6 ዞኖች በህብረት ስራ ማህበራትና ዩኔኖች፣ ለ7 ዞኖች በኢ.ግልድ፣ ለባህርዳርና ደሴ በአለ በጅምላ በኩል በማቅረብ ለህብረተሰቡ ማሰራጨት ተችሏል፡፡ በበጀት ዓመቱ መቅረብ ያለበት 881,200 ኩንታል የቀረበ 248,106 ኩንታል (28.1%) ከ2013 በጀት ዓመት የዞረ 2,468.9 ኩንታል ከዞረው ጋር ድምር 250,575.2 ከዚህ ውስጥ የተሰራጨ 242,950.7 (96.9%) ኩንታል ሲሆን ቀሪ 7624.5 ኩንታል ስኳር በመጋዘን ላይ ይገኛል፡፡ የስኳር አቅርቦት ማነስ ምክንያቱ ከፊንጫ

ስኳር ፋብሪካ በፀጥታ ምክንያት መቅረብ ባለመቻሉ ነው፡፡ የምግብ ዘይት ኮታ ፍትሃዊ በሆነ መንገድ ለሁሉም ዞኖች እንዲዳረስ በማድረግ የህብረተሰቡን ጥያቄ በተወሰነ ደረጃ ለመመለስ ጥረት ተደርጓል፡፡ በመሆኑም በአምባሰል የንግድ ስራዎች ድርጅት፣ በበላይነህ ክንዴ አስመጭና ላኪ ድርጅት፣ በደብሊውኤ፣ በቤኤካና በወረታ ኢንተርናሽናል አማካኝነት በማቅረብ ማሰራጨት ተችሏል፡፡ በበጀት ዓመቱ መቅረብ ያለበት ኮታ 93,255,060 ሊትር የቀረበ 14,775,804 (15%) ሊትር ነው፡፡ ከ2013 በጀት አመት የዞረ 212,038 ሊትር ጠቅላላ የቀረበ ከዞረው ጋር 14,987,842 ሊትር የተሰራጨ 13,210,034 ሊትር ሲሆን 1,735,270 ሊትር ቀሪ ክምችት በመጋዝን ላይ ይገኛል፡፡ የዘይት አቅርቦት ማነስ ከውጭ ይገባ የነበረው ዘይት ለተወሰነ ጊዜ ባለመግባቱና ለተጠቃሚዎች እንዲደርስ ባለመደረጉ ሲሆን ከ5ኛ ዙር ጀምሮ የተመደበን የዘይት መጠን ከ100% በላይ በማጓጓዝ ለተጠቃሚዎች በማድረስ አቅርቦቱን ለማሻሻል ከፍተኛ ጥረት ተደርጓል፡፡

## የነዳጅ አቅርቦት

በክልሉ ስራ ላይ ያሉ የነዳጅ ማደያዎች የሚሰሩ 225 እና የማይሰሩ ደግሞ 22 በድምሩ 247 ሲሆኑ በየጊዜው የመያዝ አቅማቸውን እና አቅርቦቱን መረጃ በማሰባሰብ የቀረበ የነዳጅ መጠን ቤንዝን 77,757,663 ሊትር፣ ናፍጣ 240,968,035 ሊትር፣ ኬሮሲን 4,309,460 ሊትር ቀርቦ ተሰራጭቷል፡፡ በአጠቃላይ ወደ ክልሉ የሚገባው የነዳጅ አቅርቦት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለ የመጣ ቢሆንም የቤንዚን አቅርቦትና የስርጭት የገበያ አሻጥር ያለበት በመሆኑ በቀጣይ ትኩረት ሰጥቶ መስራት ያስፈልጋል፡፡



የነዳጅ አቅርቦትና ስርጭት መድረክ-ኮምቦልቻ ከተማ

## ምርትን ለውጭ ገበያ ማቅረብ

የውጭ ምንዛሬ ግኝታችን ለማሳደግ የተቀናጀ የግብይት ስርዓት ለመዘርጋት በሀገራችን የውጭ ምንዛሬ ተወዳዳሪ የሚያደርጉ የግብርና ምርት ሰሊጥ፣ ጥራጥሬ፣ የአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶችን ወደ ውጭ በመላክ የውጭ ምንዛሬ ገቢን ለማሳደግ በተሰራው ስራ 359 ሚሊየን ዶላር ለማግኘት ታቅዶ 299.97 ሚሊየን ዶላር ተገኝቷል፡፡ አፈፃፀሙም በዝርዝር ሲታይ ሰሊጥ 1,920,821 ኩንታል ታቅዶ 859,269.1 ኩንታል (44.7%)፣ነጭ ቦለቄ 441,288 ኩንታል ታቅዶ 182,142 ኩንታል (41%)፣ ቀይ ቦለቄ 100,000 ኩንታል ታቅዶ 51,301 ኩንታል (51%)፣ ማሾ 300,000 ኩንታል ታቅዶ 222,402 ኩንታል (74%)፤ አኩሪ አተር 859,480 ኩንታል ታቅዶ 1,112,201 ኩንታል (129%)፣ ከሌሎች የጥራጥሬ ምርቶች ቡላ ቦለቄ 50,000 ታቅዶ 65,505 (100%) ኩንታል፣ ዥንጉርጉር ቦለቄ 20,000 ኩንታል ታቅዶ 11,843 (59%) ኩንታል ማከናወን ተችሏል፡፡ እንዲሁም ቡና 3,864 ኩንታል ታቅዶ 2,889.95 (75%) ኩንታል ለውጭ ገበያ ቀርቧል፣ የእንሰሳት ምርቶችን ወደ ውጭ ከመላክ አንፃር በግና ፍየል በቁጥር 19,935 ወደ ውጭ ለመላክ ታቅዶ 23,514 (100%) ወደ ውጭ እንዲላክ የተደረገ ሲሆን ከዚህም ይገኛል ተብሎ ከታቀደው 1,499,540 ዶላር ውስጥ 1,645,980 (ከ100% በላይ) ዶላር የውጭ ምንዛሬ ማግኘት ተችሏል፡፡ አሳ 63 ቶን ዕቅድ ተይዞ ክንውን 83 ቶን ሲሆን ይገኛል ተብሎ ከታቀደው 16,838 ዶላር ውስጥ 21,200 (ከ100% በላይ) ዶላር የውጭ ምንዛሬ ተገኝቷል፡፡ በድምሩ እንስሳትን ወደ ውጭ ገበያ በመላክ 1,516,378 ዶላር ይገኛል ተብሎ ታቅዶ 1,667,180 ዶላር (ከ100% በላይ) ገቢ ማግኘት ተችሏል፡፡

## የኢንዱስትሪ ምርቶችን ለውጭ ገበያ ማቅረብ

በ2014 ዓ.ም የኢንዱስትሪ ውጤቶችን በመላክ 35.2 ሚሊየን ዶላር ለማግኘት ታቅዶ ከጨርቃ ጨርቅ ውጤቶች 6,578,008.4 ዶላር፣ ከቆዳና ቆዳ ውጤቶች 1,248,223.97 ዶላር፣ ከአግሮ ፕሮሰሲንግ 14,529,494 ዶላር፣ ከኬሚካል 2,300,000 ዶላር በድምሩ 24,655,726.82 ዶላር ማግኘት ተችሏል፡፡ በተጨማሪም ከማዕድን ግብይት ጥሬ አፓል 3,336 ኪሎ ግራም ለመላክ ታቅዶ ክንውን 8,826.353 (100%) ሲሆን በተሰራው ስራም 780,000 ዶላር ለማግኘት ታቅዶ 2,326,487.29 ዶላር፣ እሴት የተጨመረበት አፓል 266.31 ኪሎ ግራም ታቅዶ ክንውን 104.746 ኪሎ ግራም መላክ ተችሏል፡፡በዚህም 3.9 ሚሊየን ዶላር ለማግኘት ታቅዶ1,167,102.5 ዶላር (38%) በድምሩ 4,680,000 ዶላር ታቅዶ 3,493,589.79 ዶላር ተገኝቷል፡፡

በአጠቃላይ በበጀት ዓመቱ ከሰብል ምርቶች 3259 ሚሊየን ዶላር፣ ከእንስሳትና እንስሳት ተዋጽኦ 1,516,378 ዶላር፣ ከኢንዱስትሪ ምርት 35,200,000 ዶላር፣ ከማዕድን ግብይት

4,680,000 ዶላር በድምር 400,396,378 ዶላር ለማግኘት ታቅዶ ከሰብል ምርት 303,883,384 ዶላር፣ ከእንስሳትና እንስሳት ተዋጽኦ 1,667,180 ዶላር፣ ከኢንዱስትሪ ምርት 24,655,726.82 ዶላር፣ ከማዕድን ግብይት 3,493,598.79 ዶላር በድምር 333,699,880.6 ዶላር (83.3%) የውጭ ምንዛሬ ማግኘት ተችሏል፡፡

# አካባቢና ደን ልማት

## የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ

የአካባቢ ይሁንታ ፈቃድ መስጠት የተቋሙ ተግባር በመሆኑ በ2014 ዓ.ም 4,200 አዳዲስ የልማት ፕሮጀክቶች የሚያቀርቡትን የአካባቢ ተፅዕኖ ሰነድ በመገምገም የይሁንታ ፈቃድ ለመስጠት በታቀደው መሠረት መስፈርቱን አሟልተው ለተገኙ 2,074 ፕሮጀክቶች የአካባቢ ይሁንታ ፈቃድ ሰርትፊኬት መስጠት ተችሏል፤አፈጻጸሙ 49.4% ነው፡፡በተመሳሳይ ለ1,500 ነባር ፕሮጀክቶች የይሁንታ ፈቃድ ሰርተፊኬት ዕድሳት አገልግሎት ለመስጠት በታቀደው መሠረት ለ708 ፕሮጀክቶች ሰርተፊኬቱን ማደስ ተችሏል። አፈጻጸሙ 47.2% ሲሆን ከይሁንታ ፈቃድ መስጠትና ከእድሳት አገልግሎት ክፍያ ብር 650,000 ገቢ ለማሰባሰብ ታቅዶ ብር 611,349 (94%) ገቢ መሰብሰብ ተችሏል፡፡ የይሁንታ ፈቃድ ተሰጥቷቸው ወደ ስራ የገቡ 5,500 የተለያዩ ፕሮጀክቶች በገቡት ውለታ መሰረት መተግበራቸውን በመከታተል ግብረ መልስ ለመስጠት በታቀደው መሠረት በ2,168 ፕሮጀክቶች ላይ ክትትል ተደርጓል፡፡ አፈጻጸሙም 39.4% በመሆኑ በቀጣይ ትኩረት ሰጥቶ መስራት ያስፈልጋል፡፡ የአካባቢ ህግ በማያከብሩ 250 ፕሮጀክቶችና ተቋማት ላይ እርምጃ ለመውሰድ በተያዘው ዕቅድ መሠረት በ61 ፕሮጀክቶች ላይ አስተዳደራዊና ህጋዊ እርምጃዎች ተወስደዋል፤አፈጻጸሙ 24.4% ሲሆን ፕሮጀክቶቹ በአካባቢና ማህበረሰብ ላይ ከፍተኛ ጉዳት የሚያደርሱ በመሆናቸው ተደጋጋሚ ቁጥጥር ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡

## እምቦጭ አረምን መከላከል

በጣና ሀይቅና አካባቢው እምቦጭ አረም በተከሰተባቸው 3 ዞኖች፣ 8 ወረዳዎችና 30 ቀበሌዎች ለማስወገድ በተደረገው ዘመቻ በልኬታ የተገኘው የእምቦጭ አረም ሽፋን 2,901.66 ሄክታር የእንቦጭ አረም ከጣና ሀይቅ ላይ በህዝብ ንቅናቄ ለማስወገድ ታቅዶ 2,646.63 ሄክታር በዘመቻ ማስወገድ ተችሏል፤አፈጻጸሙ 91% ነው፡፡ መጤ አረሙን ለማስወገድ 327,500 (142,500) ሰዎች በዘመቻ እንዲሳተፉ ለማድረግ ታቅዶ 192,548 (ሴት 77,693) የህብረተሰብ ክፍሎችን ማሳተፍ ተችሏል፣ አፈጻፀሙም 58.7% ነው፡፡ ከተሳታፊዎች መካከል የወጣቶች ድርሻ 62,118 (ሴት 27,536) ነው፡፡



የእንቦጭ አረምን መከላከል-ጣና ሀይቅ

## የደን ሀብት ልማት

የደን ሀብት ልማት ትልቅ የኢኮኖሚ አቅም እንዲሆን እና ከደን ጭፍጨፋና ውድመት ጋር ተያይዞ የሚከሰተውን የካርቦንዳይ ኦክሳይድ መጠን በከባቢ አየር ላይ መጨመርን ለመቀነስ የደን ሃብትን በስፋት ማልማትና ያሉትን መጠበቅ እንደሚገባ ይታመናል በመሆኑም በመንግስት ደኖች ውስጥ 5,300 ሄክታር የችግኝ ተከላ ቦታ በመለየት የተለያዩ የችግኝ ዝርያዎችን ለመትከል ታቅዶ 7,877 ሄክታር መሬት በመለየት ተከላ ማካሄድ ተችሏል፣ አፈጻጸሙ ከ100% በላይ ነው፡፡ የደኖችን ጥበቃና ማልማት በተመለከተ 133 ነባር የደን ኬላዎችን የማጠናከር፣ 66 ኬላዎች በአዲስ እንዲቋቋሙ የማድረግ፣ በ21 ወረዳዎች የሚገኘውን 91,762.26 ሄክታር የመንግስት ደን በተጠናከረ ሁኔታ የመጠበቅና የማልማት፣ በኃይማኖት ተቋማት እና በአምልኮ ስፍራዎች የሚገኙ 2,696 የደን ቦታዎች፣ 20,661.32 ሄክታር የቀርቀሃ መሬት በመከለል የተጠናከረ ጥበቃ እና አያያዛቸው እንዲሻሻል የማድረግ ስራ ተሰርቷል፡፡ በቆላማ አካባቢዎች የሚገኘውን 74,086 ሄክታር

የተፈጥሮ ደን በተጠናከረ ሁኔታ እንዲጠበቅ በማድረግ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚን ለመገንባት የሚደረገውን ጥረት ለማገዝ ታቅዶ 127,663 ሄክታር ደን በአግባቡ መጠበቅ ተችሏል፤ አፈጻጸሙ ከዕቅድ በላይ ነው፡፡ በተመሳሳይ 145,000 ሄክታር የተራቆተ ተራራማ መሬት ከንክኪ ነጻ ሆኖ እንዲያገግም ለመከለልና ለማልማት ታቅዶ 8,781.65 ሄክታር ወይም 6% ከንክኪ ነጻ ማድረግ ተችሏል፣ በሌላ በኩል በአገራችን ብቻ የሚገኙና ዝርያቸው የተመናመኑ ደኖች መረጃ ብዛት 156 ለማሰባሰብና ለተጠቃሚዎች ተደራሽ ለማድረግ ታቅዶ 156 ሁሉንም ማከናወን ተችሏል፡፡ በ2014 ዓ.ም በ5,358.5 ሄክታር ላይ

አሳታፊ የደን ልማት አያያዝና አጠቃቀም ስርዓት ተግባራዊ በማድረግ ደን በዘላቂነት እንዲጠበቅ፣ እንክብካቤ እንዲደረግለትና ጥቅም ላይ እንዲውል ለመሥራት ታቅዶ 119,101 ሄክታር መሬት በአሳታፊ የደን አያያዝና አስተዳደር ስርዓት ጥበቃና እንክብካቤ እየተደረገለት ይገኛል፣ አፈጻጸሙ ከዕቅድ በላይ ነው፡፡

ህጋዊ የደን ዝውወርን በተመለከተ የደን ምርት ውጤቶች የጅምላና ችርቻሮ ንግድ ፈቃድ ለሚጠይቁ 150 ሰዎች የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ለመስጠት ታቅዶ 218 መስጠት ተችሏል፣ አፈፃፀሙ ከ100% በላይ ነው፡፡55,000 የደን ምርት ማዘዋወሪያ የይለፍ ፈቃድ በመስጠት ህጋዊ የደን ሀብት ግብይት እንዲሰፍን ለማድረግ ታቅዶ ለ37,709 ሰዎች የይለፍ ፈቃድ መስጠት ተችሏል፣ አፈጻጸሙ 69% ነው፡፡ በዚህም አጠና (ወራጅና ቋሚ) 139,385 ሜትር ኪዩብ፣ ማገር (የቆርቆሮና የግድግዳ) 41,432 ሜትር ኪዩብ፣ ግንዲላ 15,860 ሜትር ኪዩብ፣ ፍልጥ 24,355 ሜትር ኪዩብ፣ ማገዶ 66,743 ሜትር ኪዩብ፣ ቀርቀሃ 1,854 ሜትር ኪዩብ በህጋዊ መንገድ ለማንቀሳቀስ ታቅዶ አጠና (ወራጅና ቋሚ) 340,958 ሜትር ኪዩብ፣ ማገር (የቆርቆሮና የግድግዳ) 132,032 ሜትር ኪዩብ፣ ግንዲላ 62,161 ሜትር ኪዩብ፣ ፍልጥ 82,265 ሜትር ኪዩብ፣ ማገዶ 111,631 ሜትር ኪዩብ፣ ቀርቀሃ 3,892 ሜትር ኪዩብ በህጋዊ መንገድ ተንቀሳቅሷል፡፡ይህንን መሰረት በማድረግም ከደን ሮያሊቲና ልማት ብር 150 ሚሊዮን ገቢ ለመሰብሰብ ታቅዶ ብር 135.5 ሚሊዮን ብር ገቢ እንዲሰበሰብ ተደርጓል፣ አፈጻጸሙ 90.33% ነው፡፡ 4,680 ኩንታል ዕጣን (ነጭ 3,042 እና ጥቁር 1,638) በህጋዊ መንገድ ተመርቶ ወደ ገበያ እንዲቀርብ ለማድረግ በታቀደው መሠረት 3,876 ኩንታል ዕጣን (ነጭ 2,431 እና ጥቁር 1,463) ተመርቶ ለገበያ ቀርቧል፤ አፈጻጸሙ 83% ነው፡፡

በህገ ወጥ መንገድ ተመርተው የተገኙ ምርቶችን ለመውረስ በታቀደው መሠረት ዕጣን 61 ኩንታል (ነጭ 56 እና ጥቁር 5)፣ ሙጫ 56 ኩንታል፣ አጠና (ወራጅና ቋሚ) 4,601 ሜትር ኪዩብ፣ ማገር (የቆርቆሮና የግድግዳ) 212 ሜትር ኪዩብ፣ ግንዲላ 149 ሜትር ኪዩብ፣ ፍልጥ 155 ሜትር ኪዩብ፣ ማገዶ 435 ሜትር ኪዩብ፣ ከሰል 6,222 ሜትር ኪዩብ ውርስ ተደርጓል፡፡

## የደን ሀብት ገቢ መሰብሰብ

ከተለያዩ የደን ምርት ውጤቶች የልማትና ሮያሊቲ ክፍያ ብር 150 ሚሊዮን ገቢ ለመሰብሰብ ታቅዶ ብር 176.42 ሚሊዮን ብር ገቢ ተሰብስቧል፤አፈጻጸሙ 118% ሲሆን ከደን ምርት ውጤቶች ብቻ በክልሉ ውስጥ 1,357,084,245.15 ብር ግብይት ተካሂዷል፡፡ በተጨማሪም 8,960 ሜትር ኩብ የአጣናና ግንዲላ ምርት ወደ ውጭ በመላክ ምንዛሬ ለማግኘት ታቅዶ 3,931 (43.87%) ሜትር ኩብ ወደ ውጭ የተላከ ሲሆን ከተላከው ምርት 630,748 ዶላር የውጭ ምንዛሬ ማግኘት ተችሏል፡፡ በህገ ወጥ መንገድ ተከማችቶና ሲዘዋወር የተገኘ የደን

ምርት ውጤት ክትትልና ቁጥጥር በማድረግና በመውረስ ብር 2 ሚሊዮን ገቢ ለማሰባሰብ ታቅዶ 1.44 ሚሊዮን ብር ለመንግስት ገቢ ተደርጓል፤ አፈፃፀሙ 72% ነው፡፡

## የደን የኢኮኖሚ አስተዋጽኦ

በደን ዘርፍ ቋሚ የስራ ዕድል ለ15,000 (ሴት 5,000) እንዲሁም ጊዜያዊ የሥራ ዕድል ለ135,000 (ሴት 15,000) በድምሩ ለ150,000 (ሴት 75,000) ሰዎች የሥራ ዕድል ለመፍጠር ታቅዶ በቋሚነት ለ16,419 (ሴት 2,481) እና በጊዜያዊ ለ101,919 (ሴት 32,401) ሰዎች በድምሩ ለ118,338 (ሴት 34,882) ሰዎች የሥራ ዕድል በመፍጠር ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፤አፈጻጸሙ 79% ሲሆን በደን ዘርፍ ልዩ ልዩ የህብረተሰብ ክፍሎች አጣናና ግንዲላ በመጫን፣ በማውረድና በማዘዋወር፣ ከሰል ማክሰልና ማዘዋወር፣ ችግኝ በማፍላትና መሸጥ፣ ዕጣንና ሙጫ ማምረትና መሸጥ፣ በቀርቀሃ ማምረት፣ ወዘተ... ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡

በ2014 ዓ.ም የዱር እንስሳት ጥብቅ ስፍራዎችን በመንከባከብና የማልማት ስራ በመስራት በጥብቅ ስፍራው የሚኖሩ የዱር እንስሳቶችን ጤንነት የመጠበቅ ስራ ተሰርቷል፡፡ በጥብቅ ስፍራዎች የጎብኝዎችን ቁጥር ወንድ 50,000 ፤ሴት 20,000 በድምሩ ወደ 70,000 ከፍ ለማድረግ ታቅዶ ወንድ 21,614 ሴት 5,341 በድምሩ 26,955 ጎብኝዎች በክልሉ በተለያዩ ቦታዎች ጉብኝት አድርገዋል፤አፈጻጸሙ 38.5% ነው፡፡በመሆኑም በጥብቅ ስፍራዎች ከኢኮ ቱሪዝም፣ ከፊልምና ሌሎች አገልግሎቶች 1.1 ሚሊዮን ብር ገቢ ለመሰብሰብ ታቅዶ 120,638 ብር የተሰበሰበ ሲሆን አፈጻጸሙ 11% ብቻ በመሆኑ በቀጣይ በጀት አመት ከኢኮ ቱሪዝም የሚገኘውን ገቢ ማሳደግ ያስፈልጋል፡፡

# ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ልማት

## የኢንቨስትመንት ፕሮሞሽን መስራት

የኢንቨስትመንት ፕሮሞሽን ለመስራት በቅድሚያ በክልሉ ኢንቨስት ሊያደርጉ ይችላሉ ተብለው የሚገመቱ አቅምና ክህሎት ያላቸው ባለሃብቶችን መለየት አስፈላጊ ነው፡፡

በዚህም መሰረት በ2014 ዓ.ም 693 ነባር ኢንቨስተሮችን፣ 28 የውጭ ዲያስፖራዎችንና 4501 አዳዲስ ባለሃብቶችን በአጠቃላይ 5222 አቅምና ክህሎት ያላቸውን ባለሃብቶች ለመለየት ታቅዶ 719 ነባር እና 4943 አዳዲስ ባለሃብቶችን እንዲሁም 87 ዲያስፖራዎችን በድምሩ 5749 አቅም ያላቸውን ባለሃብቶች መለየት ተችሏል፡፡ከተለዩት ባለሀብቶች መካከል 58ቱ ሞዴል አርሶ አደሮች ናቸው፡፡ነገር ግን ሁሉም ዞኖች የለዩአቸውን ባለሃብቶች በዝርዝር በመያዝ ተከታትሎ ፍቃድ እንዲያወጡ ከማድረግ አኳያ ሰፊ ክፍተት የታየ በመሆኑ በቀጣይ ትኩረት ሰጥቶ መስራት ያስፈልጋል፡፡

የክልሉን ፀጋዎች መሰረት በማድረግ 416 የተለያዩ ኩነቶችን፣ 35 የፓናል ውይይቶችን እና 82

ፎረሞችን በመጠቀም 7,844 ለሚሆኑ አቅም ያላቸው ባለሃብቶች እና ሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች ስለክልሉ የኢንቨስትመንት አማራጮችና ምቹ ሁኔታዎች ግንዛቤ ለመፍጠር ታቅዶ 485 የተለያዩ ኩነቶችን፣ 20 የፓናል ውይይት እና 95 ፎረም በመጠቀም ለ12,239 ባለሃብቶችና ሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች ግንዛቤ ተፈጥሯል፡፡ በተጨማሪም ግንዛቤ ከተፈጠረላቸው ባለሃብቶችና አቅም ካላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ውስጥ 3,884 ባለሃብቶችን ለመመልመል ታቅዶ 3,904 ባለሃብቶችን መመልመል ተችሏል፡፡

በበጀት አመቱ ከተመለመሉት ባለሃብቶች መካከል 2,722 ባለሃብቶች የኢንቨስትመንት ፈቃድ እንዲያወጡ ብር 166 ቢሊዮን ካፒታል እንዲያስመዘግቡና ለ410,218 (ወንድ 252,309 እና ሴት 157,909) ዜጎች የስራ እድል እንዲፈጥሩ ለማድረግ ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር ታቅዶ 175.82 ቢሊዮን ብር ካፒታል ያስመዘገቡ እና ወደ ስራ ሲገቡ ለ506,703 (ወንድ 297,880 እና ሴት 208,823) ዜጎች የስራ እድል ሊፈጥሩ ለሚችሉ 3,077 ባለሃብቶች የኢንቨስትመንት ፈቃድ እንዲያወጡ ምቹ ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡



የኢንቨስትመንት ፎረም መክፈቻ-አቫንቲ ሪዞርት (ባህርዳር)

## የኢንቨስትመንት ፈቃድ መስጠት

የኢንቨስትመንት ፈቃድና ተዛማጅ አገልግሎቶችን ለማግኘት የሚመጡ ባለሀብቶችን 100% አገልግሎቶችን ለመስጠት በታቀደዉ መሰረት በፕሮሞሽን ክፍል በገጽ ለገጽ በሚሰራው የፕሮሞሽን ስራና ከዚያ ውጭ ለመጡ 2,872 ባለሃብቶች የኢንቨስትመንት ፈቃድ ተሰጥቷል፡፡ በተጨማሪም 3,343 የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ፈቃድ በስታንዳርዱ መሰረት እንዲያድሱ ለማድረግ ታቅዶ 2,580 የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ፈቃዳቸውን እንዲያድሱ በማድረግ የእቅዱን 77% መፈጸም ተችሏል፡፡

የለውጥ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ለሚፈልጉ ባለሃብቶች 100% አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ ጥያቄ ላቀረቡ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች የለውጥ የኢንቨስትመንት ፈቃድ አገልግሎት ተሰጥቷቸዋል፡፡በተጨማሪም ትክ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ለሚፈልጉ ባለሃብቶች 100% አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ጥያቄ ላቀረቡ 49 የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ትክ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ተሰጥቷል፡፡

## ለኢንቨስትመንት የሚውል መሬት መለየት

ለኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች የሚውል በሁሉም ኢንዱስትሪ ቀጠናዎች በሳይት ፕላን የተመላከተ ለተለያየ አገልግሎት የሚውል 3,809 ሄክታር መሬት በ191 ከተሞች ለማመላከት ታቅዶ 3208.9 ሄክታር መሬት በ47 ከተሞች በሳይት ፕላን ማመላከት ተችሏል፣ አፈፃፀሙ በሳይት ፕላን ማመላከት 84.2% እንዲሁም በከተሞች ቁጥር 23.7% ነው፡፡ በመሆኑም በከተሞች ቁጥጥር የተሰራው ስራ ዝቅተኛ በመሆኑ በቀጣይ በጀት አመት ትኩረት ሰጥቶ መስራት ያስፈልጋል፡፡

በሁሉም ኢንዱስትሪ ቀጠናዎች በሳይት ፕላን የተመላከተ ለተለያዩ ፕሮጀክቶች አገልግሎት የሚውል 3,014 ሄክታር መሬት በ108 ከተሞች ከ3ኛ ወገን ነጻ ለማድረግ ታቅዶ 481.877 ሄክታር መሬት በ37 ከተሞች ከ3ኛ ወገን ማፅዳት ተችሏል፣ አፈፃፀሙ ከ3ኛ ወገን ማፅዳት 15.9% እና በከተሞች ቁጥር 34.2% ነው፡፡በአጠቃላይ ለአምራች ኢንዱስትሪ ፕሮጀክቶች፣ ለግብርና፣ ለአገልግሎት ሰጭ እና ለአበባ፣አጸጣእም አትክልት እና ፍራ ፍሬ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች 23,267.5 ሄክታር መሬት ከሦስተኛ ወገን ነፃ የማድረግ ስራ ተሰርቷል፡፡

## አምራች ኢንዱስትሪ ፕሮጀክቶችን በመገምገም ወደ ስራ ማስገባት

በበጀት ዓመቱ በአዲስ የሚጀምሩ 1,360 የአምራች ኢንዱስትሪ ፕሮጀክቶችን ገምግሞ ለማሳለፍ ታቅዶ 1438 ፕሮጀክቶች ተገምግመው ያለፉ ሲሆን አፈጻጸሙም 105.7 ነው፡፡ ተገምግመው ካለፉ ፕሮጀክቶች መካከል 1056 ፕሮጀክቶች መሬት እንዲያገኙ ታቅዶ 515(49%) ፕሮጀክቶች መሬት እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡

በተጨማሪም ከአምራች ኢንዱስትሪዎች ውጭ ባሉ የኢንቨስትመንት ዘርፎች ለግምገማ የቀረቡ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ብዛት 948 ሲሆን ሁሉም ፕሮጀክቶች ተገምግመው 663 ፕሮጀክቶች ያለፉ ሲሆን 253 ፕሮጀክቶች 19881.5 ሄክታር መሬት ማግኘት ችለዋል፡፡

በአጠቃላይ በአምራች ኢንዱስትሪ እና ከአምራች ኢንዱስትሪ ውጭ 2,386 የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ለግምገማ ቀርበው 2,101 ፕሮጀክቶች ግምገማውን ያለፉ ሲሆን ከዚህ መካከል 768 ፕሮጀክቶች በድምሩ 20347.3834 ሄክታር መሬት አግኝተዋል።

## የመሰረተ ልማት ችግሮች እንዲፈቱ ማድረግ

ለኢንዱስትሪ አገልግሎት እንዲውል ለተዘጋጀው መሬት 100% የመሰረተ ልማት ችግር እንዲፈታ ለማድረግ ለጠጠር መንገድ 278.55 ኪሎ ሜትር፣ ለዲች/ማፋሰሻ/ 29.9 ኪሎ ሜትር፣ ለድልድይ 0.276 ኪሎ ሜትር፣ለመብራት መስመር 90 ኪሎ ሜትር እና ለውሃ 274.73 ኪሎ ሜትር በድምሩ 671.456 ኪሎ ሜትር መሰረተ ልማት በብር 3.49 ቢሊዮን ለአዲስ እና ነባር ኢንዱስትሪ ፓርክ ለማሟላት ታቅዶ የጠጠር መንገድ 11.5 ኪሎ ሜትር፣ ዲች/ማፋሰሻ/ 1.76 ኪሎ ሜትር፣ ለድልድይ 0.1 ኪሎ ሜትር፣ የመብራት መስመር 96.17 ኪሎ ሜትር እና የውሃ 7.5 ኪሎ ሜትር እና ለስልክ 0.1 ኪሎ ሜትር በድምሩ 117.13 ኪሎ ሜትር በብር መጠን 0.138 ቢሊዮን የተሰራ ሲሆን አፈፃፀሙም በኪሎ ሜትር 15% እና በብር መጠን 4% ነው፡፡ መሰረተ ልማት ማሟላት በኪሎ ሜትር አፈፃፀሙ ዝቅተኛ የሆነበት ምክንያት ለኢንዱስትሪ ፓርኮች መሰረተ ልማት ለማሟላት የሚያስፈልገው በጀት ባለመመደቡ እና በበጀት አመቱ በተፈጠረው ሃገራዊና ክልላዊ የጸጥታ ችግር ምክንያት ነው፡፡

የአምራች ኢንዱስትሪ ፕሮጀክቶችን መሰረተ ልማት ችግር በጥናት በመለየት ለመፍታት በታቀደው መሰረት በርካታ ኢንዱስትሪዎች የመንገድ፣ የውሃ፣ የመብራት እና የቴሌ ችግር እንዳለባቸው በጥናት ቢለይም ችግሮችን በመፍታት በኩል ያለው አፈፃጸም በጣም ዝቅተኛ ነው፡ይህም በዝርዝር ሲታይ የ421 ኢዱስትሪዎችን የመንገድ ችግር በመለየት 211 ለመፍታት እቅድ ተይዞ 460 ኢንዱስትሪዎች ችግር እንዳለባቸው ተለይቶ የ61 ፕሮጀክቶች ችግር ተፈቷል፡፡ በተመሳሳይ የ670 ኢንዱስትሪዎችን የመብራት ችግር በመለየት 335 ለመፍታት እቅድ ተይዞ 639 ኢንዱስትሪዎች ችግር እንዳለባቸው ተለይተው የ224 ኢንዱስትሪዎች ችግር ተፈቷል፡፡ የ201 ኢንዱስትሪዎችን የውሃ ችግር በመለየት የሁሉንም ለመፍታት እቅድ ተይዞ ችግር እንዳለባቸው ከተለዩ 285 ኢንዱስትሪዎች የ72 ኢንዱስትሪዎች ችግር ተፈቷል፡፡ በተመሳሳይ የስልክ ችግር እንዳለባቸው የተለዩትን አምራች ኢንዱስትሪዎች የሁሉንም ችግር ለመፍታት ታቅዶ 39 ኢንዱስትሪዎች ችግር እንዳለባቸው የተለየ ሲሆን የ13 ፕሮጀክቶችን ችግር መፍታት ተችሏል፡፡

## የአምራች ኢንዱስትሪዎችን ችግር በጥናት መለየትና መፍታት

በምርት ላይ ያሉ የሁሉንም አምራች ኢንዱስትሪዎችን ሁለተናዊ ችግር በጥናት ለይቶ ለመፍታት በተደረገው ጥረት ለ2,484 አምራች ኢንዱስትሪዎች የቴክኒካል ክህሎት፣ ለ2,573 አምራች ኢንዱስትሪዎች የኢንተርፕርነርሽፕ፣ለ2,918 አምራች ኢንዱስትሪዎች የጥራትና ምርታማነት፣ ለ1,436 አምራች ኢንዱስትሪዎች የቴክኖሎጅ አቅም ግንባታ ተጠቃሚ በማድረግ ችግራቸውን ለመፍታት ታቅዶ ችግር እንዳለባቸው ከተለዩት ውስጥ 1009 አምራች

ኢንዱስትሪዎች የቴክኒካል ክህሎት፣ 1268 አምራች ኢንዱስትሪዎች የኢንተርፕርነርሽፕ፣ ለ1267 አምራች ኢንዱስትሪዎች የጥራትና ምርታማነት እንዲሁም ለ638 አምራች ኢንዱስትሪዎች የቴክኖሎጅ አቅም ግንባታ ድጋፍ ተጠቃሚ በማድረግ ችግሮቻቸውን በኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን መፍታት ተችሏል፡፡

አምራች ኢንዱስትሪዎችን በድጋፍ ማዕቀፎች በመደገፍና በማገዝ በቴክኒካል ክህሎት፣ በኢንተርፕርነርሽፕ፣ በምርት ጥራት እንዲሁም በቴክኖሎጅ አጠቃቀም የተሻሉ በመሆን የማምረት አቅማቸውን በማሳደግ ሰፊ የስራ እድል መፍጠር እንዳይችሉ የሚያደርጉ ተግዳሮቶችን ማስተካከል አስፈላጊ ነው፡፡ከዚህ ጋር በተያያዘ አምራች ኢንዱስትሪዎች ከቴክኒክና ሙያ ልማት ተቋምና ከዩኒቨርሲቲዎች ጋር ያላቸው ቅንጅታዊ አሰራር ዝቅተኛ መሆኑ፣ወርክሾፖችና የቴክኖሎጅ ኢንኩቤሽን ሴንተር በክልል አለመኖሩ እና የመሳሰሉት የሚታዩ ተግዳሮቶች በመሆናቸው እነዚህን ተግዳሮቶች ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን ማስተካከል አስፈላጊ በመሆኑ ትኩረት ሰጥቶ መስራት ያስፈልጋል፡፡

## ለኢንዱስትሪዎች የጥሬ ዕቃ ግብዓት ችግር በጥናት መለየትና መፍታት

በበጀት አመቱ 1,370 ኢንዱስትሪዎችን የግብዓት ትስስር ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ የ431 ኢንዱስትሪዎችን የግብዓት ትስስር ችግር መለየት የተቻለ ሲሆን ከተለየላቸው ውስጥ 226 ኢንዱስትሪዎችን የ461.657 ሚሊዮን ብር የጥሬ ዕቃ ዋጋ የግብዓት ትስስር ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡የዚህ ተግባር አፈጻጸም ማነስ ምክንያት አብዛኛው ጥሬ ዕቃ ሀገር ውስጥ በስፋት አለመመረታቸውና የምንዛሬ ችግሮች ዋናዎቹ ናቸው፡፡

## የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችን የፋይናንስ ተጠቃሚ ማድረግ

የግብርናና አገልግሎት ሰጭ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች፣ የአምራች ኢንዱስትሪ ፕሮጀክቶችና በምርት ላይ ያሉ አምራች ኢንዱስትሪዎች 100% የፋይናንስ አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆኑ በመደገፍ በኩል በኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ቢሮ በተቀመጡ የብድር ሞዳሊቲዎች የኢንዱስትሪ እና ኢንቨስትመንት ዘርፍ ተጠቃሚነት በጥቅል ሲታይ በፕሮጀክት ፋይናንስ በፕሮጀክት ደረጃ ያሉ 100 አምራች ኢንዱስትሪ ፕሮጀክቶችን የብድር ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ 128 ፕሮጀክቶች የብደር ጥያቄ ያቀረቡ ሲሆን 104 ፕሮጀክቶች ተጠቃሚ ሆነዋል በብር ሲታይ ብር 11.178 ቢሊዮን ነው፡፡

በግብርና ፕሮጀክቶች 179፣ በአበባና አትክልት 5 ፕሮጀክቶች፣ በአገልግሎት ሰጭ ተቋማት 554 ፕሮጀክቶች በምርት ላይ ላሉ አምራች ኢንዱስትሪዎች 407 በድምሩ በስራ ማስኬጃ 1145 ፕሮጀክቶች ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ 443 ፕሮጀክቶች የስራ ማስኬጃ ብድር ተጠቃሚ ለመሆን የጠየቁ ሲሆን 119 ፕሮጀክቶች የስራ ማስኬጃ ብድር ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡ በገንዘብ

ሲታይ 10,907,810,000. ብር ለስራ ማስኬጃ አገልግሎት ውሏል፡፡

በፕሮጀክት ደረጃ ያሉ አምራች ኢንዱስትሪ ፕሮጀክቶች የሊዝ ፋይናንስ የብደር ተጠቃሚ ለማድረግ በእቅድ 50 ተይዞ 98 ፕሮጀክቶች የብደር ጥያቄ ያቀረቡ ሲሆን 39 ፕሮጀክቶች 396.04 ሚሊዮን ብር የሊዝ ፋይናንስ ብድር ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ በማምረት ላይ ላሉ 416 አምራች ኢንዱስትሪዎች የሊዝ ፋይናንስ ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ 230 አምራች ኢንዱስትሪዎች የብድር ተጠቃሚ ለመሆን ጥያቄ አቅርበው 98ቱ አምራች ኢንዱስትሪዎች 537.049 ሚሊዮን ብር የብድር ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡በድምሩ በሊዝ ፋይናንስ 466 ፕሮጀክቶች ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ 328 ፕሮጀክቶች የሊዝ ፋይናንስ ብድር ተጠቃሚ ለመሆን ጠይቀው 137 ፕሮጀክቶች ብር 933.089 ሚሊዮን የሊዝ ፋይናንስ ብድር ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡

## አምራች ኢንዱስትሪ ፕሮጀክቶችን ማበረታታት

በበጀት አመቱ የአገልግሎት ሰጭ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች እና የአምራች ኢንዱስትሪ ፕሮጀክቶችን የማበረታቻ አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆኑ 100% ለመደገፍ እና ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ 289 ደንበኞች የጉሙሩክ ቀረጥ ነጻ ተጠቃሚ ለመሆን ጠይቀው ቅድመ ሁኔታዎችን /መሟላት ያለባቸውን መረጃዎች/ አሟልተው የመጡ 248 ፕሮጀክቶች የጉሙሩክ ቀረጥ ነጻ ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡በተመሳሳይ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች 100% የገቢ ግብር ነጻ ማበረታቻ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ ታቅዶ ቅድመ ሁኔታዎችን በማሟላት ለጠየቁ 37 የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች የገቢ ግብር ነጻ ማበረታቻ ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡

## የአምራች ኢንዱስትሪዎችን ምርጥ ተሞክሮ መቀመር

በበጀት ዓመቱ የ51 አምራች ኢንዱስትሪዎችን ምርጥ ተሞክሮ ለመቀመር ታቅዶ የ33 አምራች ኢንዱስትሪ ምርጥ ተሞክሮ መቀመር ተችሏል፡፡በሰፋው ተሞክሮ ተጠቃሚ የሆኑ አምራች ኢንዱስትሪ ዕቅድ አነስተኛ 501፣ መካከለኛ 144፣ ከፍተኛ 44 በድምሩ 659 ሲሆኑ ክንውን አነስተኛ 96፣ መካከለኛ 15፣ ከፍተኛ 5 በድምሩ የ116 አምራች ኢንዱስትሪዎች ተሞክሮዎችን ማስፋት ተችሏል፡፡

## የአምራች ኢንዱስትሪዎች የደረጃ ሽግግር

አምራች ኢንዱስትሪዎች የደረጃ ሽግግር እንዲያደርጉ ለመደገፍ በተሰራው ስራ ከአነስተኛ ወደ መካከለኛ ደረጃ 81፣ ከመካከለኛ ወደ ከፍተኛ 22 በድምሩ 103 ኢንዱስትሪዎች የደረጃ ሽግግር ለመስራት ታቅዶ ከአነስተኛ ወደ መካከለኛ ደረጃ 25 ኢንዱስትሪዎችን ማሸጋገር የተቻለ ሲሆን ከመካከለኛ ወደ ከፍተኛ ደረጃ የተሸጋገሩ ደግሞ 3 በድምሩ 28 አምራች ኢንዱስትሪዎች የደረጃ ሽግግር አድርገዋል፡፡

**የአብክመ የመንግስት ኮሙዩኒኬሽን ቢሮ**

## በአምራች ኢንዱስትሪዎች የስራ እድል ፈጠራ

በኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ቢሮ (በግብርና፣ በአገልግሎት ሰጭ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችና በአምራች ኢንዱስትሪዎች) ወንድ 19,256 እና ሴት 19,234 በድምሩ 38,490 ለሚሆኑ ዜጎች የስራ እድል ለመፍጠር ታቅዶ ወንድ 22,928 እና ሴት 16,234 በድምሩ 39,162 የስራ ዕድል መፍጠር ተችሏል፡፡ከዚህ መካከል ለወጣቶች የተፈጠረ የስራ እድል ወንድ 1165 እና ሴት 474 በድምሩ 1589 ሲሆን ለአካል ጉዳተኞች ደግሞ ወንድ 11 እና ሴት 10 በድምሩ ለ21 አካል ጉዳተኞች የስራ እድል መፍጠር ተችሏል፡፡



በመርሀ ጋርመንት የተፈጠረ የስራ እድል-ባህርዳር

# የማዕድን ሃብት ልማት

## የስነ-ምድር ጥናት

በ2014 ዓ.ም የክልሉን የስነ-ምድር ጥናት በሚመለከት ባለ 1፡50,000 መስፈርት የስነምድር ካርታ (1:50,000 scale geological mapping) መረጃ ሽፋንን ከ 20,419.56 ካሬ ኪሎ ሜትር ወደ 33,635.82 ካሬ ኪሎ ሜትር ለማሳደግ ታቅዶ ነባር ፕሮጀክቶች የጃዊና የቋራ ወረዳዎች ፕሮጀክት የ11,458.26 ካሬ ኪሎ ሜትር 1፡50,000 መስፈርት የሥነ-ምድር ጥናትና ካርታ ስራ ተጠናቆ ከጎንደር ዩኒቨርሲቲ ጋር ርክክብ በተደረገበት ወቅት አፈጻፀሙ100% ሆኗል፡፡ በጥናቱም የብረት ማዕድን፣ የግራናይት ማዕድን፣ የእብነ በረድ ማዕድን፣ የሳንድ ስቶን ማዕድን፣ የወርቅ ማእድንና የሲልካ ሳንድ ማዕድን ተገኝቷል፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ እየተጠና ያለው አየሁ ጓጉሣ ወረዳ የኢናባራ - ጎምር

የ750 ካሬ ኪሎ ሜትር የስነ-ምድር ጥናትና ካርታ ስራ በመጠናቀቅ ላይ ሲሆን የተገኙ ማዕድናትም ፊልድስታር፣ ካኦሊን ማዕድናት ናቸው፡፡ጠቀሜታቸውም ካኦሊን ለሴራሚክ ግብዓት እና ለወረቀት ማንጫነት እንዲሁም ፊልድስፐር ማዕድን ደግሞ ለጌጣጌጥ ማዕድናት እና ለሴራሚክ ግብዓትነት የሚያገለግል መሆኑን ጥናቱ ያመላክታል፡፡ ባለ1፡50,000 መስፈርት የማዕድን ፍለጋና ክምችት ግመታ መረጃ ሽፋንን ከ3,135.435 ካሬ ኪሎ ሜትር ወደ 3,466.085 ካሬ ኪሎ ሜትር ለማሣደግ ታቅዶ ነባር ፕሮጀክቶች በውጭ አቅም በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ እየተጠና ያለው በደቡብ ወሎ ዞን በቦረና ወረዳ እና በምስራቅ ጎጃም ዞን እነብሴ ሳር ምድር፣ እናርጅና እናዉጋ ወረዳዎች በ750 ካሬ ኪሎ ሜትር ላይ እየተጠና ያለው የኖራ ድንጋይ፣ ጀሶ ድንጋይ እና ተዛማጅ ማዕድናት ክምችት ግምታ፣ ስርጭትና ጥናትና ምርመራ ጥናት ተጠናቋል፡፡ በጥናቱም የብረት ማዕድን፣ የላይምስቶን ማዕድን፣ የጅፕሰም ማዕድን፣ የሳንድ ስቶን ማዕድንና የጌጣጌጥ ማዕድን ተገኝቷል፤ አፈጻጸሙም 100 ፐርሰንት ሲሆን ለብረት እና ሲሚንቶ ፋብሪካ ግብዓትነት ያገለግላሉ፡፡ በራስ አቅም በሰሜን ሸዋ ዞን አንኮበር ወረዳ የ 25 ካሬ ኪሎ ሜትር የካኦሊን ማዕድን ፍለጋና ክምችት ግመታ ጥናት ለምርመራ ተልኮ በ4 ካሬ ኪሎ ሜትር ላይ የካኦሊን ማእድን የተገኘ ሲሆን የክምችት መጠኑም 879,552 ቶን መሆኑ ታውቋል፤አፈጻጸሙ 100% ነው፡፡ በክልሉ ውስጥ ባሉ በ7 ወረዳዎች ማለትም (ደላንታ፣ ኩታበር፣ ሃብሩ፣ ወረኢሉ፣ መቅደላ፣ ሸበል በረንታ እና አዋበል) የድንጋይ ከሰል ፍለጋና ክምችት ግመታ የዳሰሳ ጥናት ተጠናቋል፡፡ በጥናቱም መሰረት በሁሉም ወረዳዎች በጥቆማ ደረጃ የተገኘ ሲሆን በሀብሩ፣ በኩታበር እና በደላንታ ወረዳ ሊግናይት ተብሎ የሚጠራ የድንጋይ ከሰል ክምችት እንዳለ ታውቋል፤ አፈፃፀሙም 100% ነው፡፡

በአዲስ ፕሮጀክቶች በሰሜን ሸዋ ዞን በአንጎለላና ጠራ ወረዳ 15 ካሬ ኪሎ ሜትር የቤንቶናይት ማዕድን ክምችት ግመታ ጥናት፣ በአዊ ዞን ዚገም ወረዳ 25.65 ካሬ ኪሎ ሜትር የግራናይት ማዕድን ፍለጋና ክምችት ግመታ ጥናት እና ሰሜን ወሎ ዞን ግዳን ወረዳ 10 ካሬ ኪሎ ሜትር የናትሮላይት-ዚኦላይት ማዕድናት (Precious Minerals) ፍለጋና ክምችት ግመታ ጥናት የተጠናቀቀ ሲሆን በፍለጋውም ለሴራሚክና ውኃ ጉድጓድ ቁፋሮ፣ መርዛማ ኬሚካል ውኃ ለማጣራት፣ ለኮንስትራክሽን ግብዓትነት፣ለመጠጥ ውሃ ማጣሪያነት እና ለማዳበሪያ ግብዓትነት ሊያገለግል የሚችል ከላይ የተጠቀሱት ማዕድናትን ማግኘት ተችሏል፡፡

## የማዕድን ስራ ፈቃድ መስጠት

የማዕድን ምርት ግብይት ብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት እንዲሀም ነዳጅና የነዳጅ ውጤቶች ችርቻሮ ብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት የመስጠት አቅምን በ2013 በጀት ዓመት መጨረሻ ከነበረበት ከ2,512 ወደ 3,778 ለማሳደግ የታቀደ ሲሆን በአጠቃላይ በክልል ደረጃ 824

የማዕድን ማምረት ስራ ፈቃድ፣ 79 የማዕድን ምርመራ ፈቃድ እና 60 የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ለመስጠት ታቅዶ 1,359 የማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድ (አፈፃፀም ከ100% በላይ) ፤305 የማዕድን ምርመራ ፈቃድ (አፈፃፀም ከ100% በላይ)፣ 76 የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት (አፈፃፀም 100%) ተከናውኗን፡፡ ስለሆነም ለ963 ኢንተርፕራይዞች፣ ባለሀብቶችና ኩባንያዎች ፈቃድ ለመስጠት ዕቅድ ተይዞ ለ1,740 ኢንተርፕራይዞች፣ ባለሀብቶችና ኩባንያዎች ፈቃድ በመስጠት የክልሉን የኢንቨስትመንት ደረጃ ከፍ በማድረግ ላይ ይገኛል (አፈፃፀም ከ100% በላይ ነው)፡፡

በአጠቃላይ በክልል ደረጃ 7,880 (ወንድ 5,551፤ ሴት 2,329) በማዕድን ማምረት ስራ ፈቃድ፣ ለ500 (ወንድ 300 ሴት 200) የማዕድን ምርመራ ፈቃድ እና ለ360 (ወንድ 253፤ ሴት 107) የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት የሥራ ዕድል ለመፈጠር ዕቅድ ተይዞ ለ21,165 (ወንድ 15,509 ፤ሴት 5,656) የማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድ (አፈፃፀም>100%)፣ ለ1,756 (ወንድ 886 ፤ሴት 870) የማዕድን ምርመራ ፈቃድ (አፈፃፀም >100%)፣ እና ለ1,673 (ወንድ 1089 ፤ሴት 584) የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት (አፈፃፀም >100%) ስራ ዕድል ተፈጥሯል፣በዘርፉ የተፈጠረ የስራ ዕድል ፈጠራ ዕቅድ ወንድ 13,901 ፤ሴት 5,958 ድምር 19,859 ታቅዶ ከንውን ወንድ 17,488፤ ሴት 7,106 በድምሩ 24,594 ማድረስ ተችሏል፡፡ከዚህ መካከል 18,913 (ወንድ 14,135፤ ሴት 4,778 ) ወጣቶች ናቸው፡፡

## ከማዕድን የስራ እንቅስቃሴ የተሰበሰበ ገቢ

በበጀት አመቱ ከሮያሊቲ፣ ከመሬት ኪራይ፣ ከፈቃድ አገልግሎት እና ሌሎች ተዛማጅ አገልግሎት ክፍያዎች ብር 42 ሚሊዮን ለመሰብሰብ በተሰራው ስራ በአጠቃላይ በበጀት ዓመቱ ከዘርፉ ማዕድን ሚኒስቴር፣ ከቢሮው፣ ከዞኖች እና ከሜትሮፖሊታንት ከተሞች ከማዕድን ሥራዎች ፈቃድ መስጠትና ማስተዳደር የሮያሊቲ፣ የመሬት ኪራይ፣ የማዕድን ፈቃድ አገልግሎትና ሌሎች ተዛማጅ ክፍያዎች ብር 42,000,000 ለመሰብሰብ ታቅዶ ብር 55,214,422 ገቢ ተሰብስቧል፤ አፈፃፀሙም 134.5% ነው፡፡

## የውጭ ምንዛሬ ግኝት

የዘርፉን ዓመታዊ የውጭ ምንዛሬ ግኝት በ2013 በጀት ዓመት መጨረሻ ከነበረበት 3.6086 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ወደ 10.4 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ለማሳደግ ታቅዶ በአጠቃላይ በበጀት ዓመቱ 8,000 ኪሎ ግራም ኦፓል ለውጭ ገበያ በማቅረብ 1.5 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር የውጭ ምንዛሬ ለማግኘት ዕቅድ ተይዞ 14,368.15 ኪሎ ግራም ጥሬ ኦፓል ለውጭ ገበያ በማቅረብ 3.654 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር የውጭ ምንዛሬ ተገኝቷል፡፡በመሆኑም 100 ኪሎ ግራም እሴት የተጨመረበት ኦፓል ለውጭ ገበያ በማቅረብ 3.12 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር

ለመሰብሰብ ዕቅድ ተይዞ 190.973 ኪሎ ግራም እሴት የተጨመረበት ኦፖል በማቅረብ 1.9497 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ተሰብስቧል (አፈፃፀሙ 52.8%) ሆኗል፡፡

## ገንዘብና ኢኮኖሚ

### የበጀት ድልድል

በ2014 ዓ.ም የክልሉን በጀት ፍትሀዊ በሆነ መንገድ ለክልሉ ልማት ለማዋል እና ከብክነት በፀዳና ተጠያቂነት በሰፈነበት አግባብ ለልማት ማስፈፀሚያነት እንዲውል ለማድረግ በበጀት ዓመቱ የበጀት ድልድል በማካሄድ እቅዱን ውጤታማ ሊያደርጉ የሚችሉ ስራዎችን ለመስራት ታቅዶ ወደ ሥራ ተገብቷል፡፡ በዚህ መሰረት በ2014 በጀት ዓመት በክልሉ እንዲመጣ የሚፈለገውን ልማት እውን ለማድረግ የክልሉ በጀት ብር 80.1 ቢሊዮን በክልል ምክር ቤት የፀደቀ ሲሆን የክልሉ በጀት ዋነኛ የገቢ ምንጮች ደግሞ ከክልል የሚሰበሰብ ገቢ ብር 34,180,538,000 (42.6%)፣ የፌደራል መንግሥት ድጎማ ብር 47,696,123,348 (59.5%)እና የውጭ አገር ዕርዳታ ብር 228,008,049(0.28%) በድምሩ ብር 80,104,669,397 ለክልሉ የልማት ሥራዎች ማስፈፀሚያ በጀት ሁኖ ፀድቋል፤በጀቱም ከ2013 ዓ.ም ጋር ሲነጻጸር በ27.8% አጠቃላይ እድገት አሳይቷል፡፡

### የወጭ አፈፃፀም

በበጀት ዓመቱ ከፌደራል መንግስት የተላከ ድጎማና የተሰበሰበ ገቢ ጨምሮ ከመንግስት ግምጃ ቤት (ትሬዠሪ) በ2014 በጀት ዓመት ከተመደበው በጀት የወጣ ወጭ የመደበኛ በጀት ብር 54.53 ቢሊዮን እንዲሁም የካፒታል በጀት ብር 5.68 ቢሊዮን ጠቅላላ ድምር ብር 60.21 ቢሊዮን ወጭ በIBEX ተመዝግቧል፡፡ሆኖም ከተመደበው በጀት አንፃር አፈፃፀሙ ዝቅ የሆነበት ምክንያት ሁሉም ቢሮዎች፣ዞኖችና ከተማ አስተዳደሮች ወቅታዊ የሂሳብ ምዝገባ በIBEX አጠቃለው ባለመመዝገባቸው ነው፡፡ የተሰብሳቢና ተከፋይ ሂሳብ በክልሉ ውስጥ ባሉ ሁሉም ቢሮዎች፣ ዞኖች፣ ወረዳዎችና ከተማ አስተዳደሮች ለማሰባሰብ ጥረት ሲደረግ የቆየ ሲሆን በአጠቃለይ በክልሉ ሂሳብ ከሚታየው ውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 521,333,141.88 እና ተከፋይ ሂሳብ ብር 910,934,298.79 ማወራረድ ተችሏል፡፡

በቻናል አንድ እንቅስቃሴ ያላቸው ፕሮግራሞች 8 ሲሆኑ በዚህ ፕሮግራም ለ2014 በጀት ዓመት በቻናል አንድ ፕሮግራሞች የታወጀው የበጀት መጠን ብር 11.2 ቢሊዮን ነው፡፡ ከዚህ በጀት ውስጥ ብር 9.6 ቢሊዮን ከባለፈው ዓመት ከዞረውና በበጀት ዓመቱ ከገንዘብ ሚኒስቴር የተገኘ ሲሆን ብር 8.9 ቢሊዮን ለፈፃሚ ወረዳዎች፣ ከተማ አስተዳደሮች፣ ዞኖችና ክልል ቢሮዎች ተልኳል፡፡ አጠቃላይ የፕሮግራሞች ወጪ ደግሞ ብር 6.6 ቢሊዮን ነው፡፡

## የአብክመ የመንግስት ኮሙዩኒኬሽን ቢሮ

## የውጭ ሃብት ግኝትና አስተዳደር

በክልሉ ውስጥ በለጋሽና አበዳሪ ድርጅቶች የገንዘብ ድጋፍ ወደ ክልሉ የሚመጡ የእርዳታና ብድር በጀቶች በአግባቡ በቢሮዎች በማስተዳደር በርካታ ተግባራት ተከናውነዋል፡፡ በዚህም መሰረት፡-UNSDCF /United Nations Sustainable Development Co-operation Frame work/ ፕሮጀክቶች እና ፕሮግራሞች ከባለፈው አመት የዞረ ብር 78.6 ሚሊዮን፣በዚህ አመት የተለቀቀ ብር 740 ሚሊዮን በድምሩ ብር 819 ሚሊየን የነበረ ሲሆን ከዚህ ውስጥ 275.8 ሚሊዮን ብር በእቅድ ያልተያዘ ተጨማሪ ገንዘብ በህ.ወ.ሀ.ት ወራሪ ቡድን ወረራ በክልሉ በተወረሩ አካባቢዎች ለአደጋ ጊዜ ምላሽ ፕሮግራም የመጣና በወረራ ለተያዙ ወረዳዎች እንዲተላለፍና ስራ ላይ እንዲውል ተደርጓል፡፡ ከተመደበው ብር 819 ሚሊዮን ውስጥ 492.3 ሚሊየን (60%) ስራ ላይ ውሏል ቀሪው ብር 325 ሚሊየን ስራ ላይ ያልዋለ ሲሆን ትምህርት ቢሮ በወቅቱ ባለመጠቀሙ ምክንያት ብር 1,224,990 ወደ ኤጀንሲዉ ተመልሷል፡፡ ካልተወራረደዉ ብር 357.29 ሚሊየን ብር ውስጥ ጤና ቢሮ 135.37 ሚሊዮን፣ሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ 89.43 ሚሊዮን ሴቶችና ህፃናት ጉዳይ ቢሮ 58.35 ሚሊዮን፤ ትምህርት ቢሮ 24.44 ሚሊዮን እና ውሃና ኢነርጂ ልማት ቢሮ ብር 12.8 ሚሊዮን ድርሻ ያላቸው ሲሆን የተሻለ አፈፃጸም ያላቸዉ ወሳኝ ኩነት ምዝገባ ኤጀንሲ፣ፕላን ኮሚሽን፣ ገንዘብ ቢሮ እና ምግብ ዋስትና ናቸው፡፡ በUNDP/ በተባበሩት መንግስታት የልማት ፕሮግራም/ በትህነግ ወረራ እና በሰሜን ሸዋና በኦሮሞ ብሄረሰብ አስተዳደር አጎራባች ወረዳዎች ግጭት የደረሰውን ጉዳት መልሶ ማቋቋሚያ የ 6.2 ሚሊዮን ዶላር ድጋፍ ፤14 ተሽከርካሪ፤ 165 ላብቶፕ፤ 42 ፕሪንተር እና 11 ስካነር ጉዳት ለደረሰባቸው ዞንና ወረዳዎች ተልኳል፡፡በተጨማሪም ከተያዘው የድጋፍ በጀት ውስጥ በUNDP አማካኝነት የ14,877,007.4 ሚሊዮን 169 ዲስክቶፕ ኮምፒዩተር፤ 5 ስካነር ፤ 84 ፕሪንተር እና 12 ኤክስተርናል ሃርድ ዲስክ ግዥ እንዲፈጸም, ውክልና ተሰጥቷል፡፡

## የፕሮጀክት ግምገማ

በታቀደው ዕቅድ መሰረት ፈጻሚ ሴክተሮች፣ ዞኖችና ወረዳዎች በተገኙበት አጠቃላይ የአፈጻጸም ግምገማ ተካሂዷል፣ በዚህም የሁለቱም ፕሮጀክቶች የፊዚካልና የገንዘብ አጠቃቀም ሪፖርት ቀርቦ ተገምግሟል፣ በCRGE (Climate Resilient Green Economy) ፕሮጀክቶች ከባለፈዉ አመት የዞረ ብር 128.6 ሚሊዮን እና በዚህ አመት የተላከ ብር 201.052 ሚሊዮን በድምሩ 329.6 ሚሊዮን ሲሆን በበጀት አመቱ ውስጥ ብር 240.11 ሚሊዮን (73.7%) ስራ ላይ ውሏል፣ የ2014 በጀት አመት በእርዳታና ብድር

**የአብክመ የመንግስት ኮሙዩኒኬሽን ቢሮ**

በፕሮጀክቶችና ፕሮግራሞች የቻናል አንድን ሳይጨምር የተገኘ ጠቅላላ ሀብት ብር 4,303,820,271 ነው፡፡ የበጀት አጠቃቀሙ 1,774,226,039 ብር ሲሆን አፈፃፀሙም 41% ነው፡፡በሌላ በኩል ከጊዜ ወደ ጊዜ የሚመጣውን የውጭ ሃብት አጠቃቀምን የመከታተልና የመደገፍ ሁኔታው እየተሻሻለ ቢመጣም አሁንም የመጣውን ሃብት በአግባቡ ከማስተዳደር አንጻር የሚስተዋሉ ችግሮች ማለትም ለእርዳታና ብድር ሃብት የሚሰጠው ትኩረት አነስተኛ መሆን ምክንያቱ ወቅቱን የጠበቀ የአፈጻጸም ግምገማ አለማድረግ፤ ተግባሩን ለባለሙያ እና ዘርፉን ለሚመሩና ለሚደግፉ የስራ ክፍሎች መተው አፈጻጸሙ ዝቅ እንዲል አድርጎታል፡፡

## የበጎ አድራጎት እና ማህበራት ድርጅቶች በጀት አጠቃቀም

በ2014 በጀት ዓመት መንግስት ቀጣይነት ያለው ልማት ለማረጋገጥ ከአጋር አካላት ማለትም ከተለያዩ ረጅና በጎ አድራጎት ድርጅቶች ወደ ክልላችን የሚመጣውን ሀብት አጠቃቀምና የፕሮጀክቶችን አፈጻጸም የመከታተል እና በተናጠልም ሆነ በተቀናጀ መንገድ የሚደረጉ የድጋፍ ስራዎችን በበላይነት የማስተባበር ሃላፊነት አለበት፡፡ በመሆኑም በ2014 ዓ.ም በወረዳ፣ በዞንና በክልል በአጠቃላይ 220 አዲስ ፕሮጀክቶች ጋር ስምምነት በመፈራረም ብር 3..5 ቢሊዮን ለማግኘት ታቅዶ 21 በወረዳ፣ 44 በዞንና 148 በክልል በድምሩ ከ 213 አዲስ ፕሮጀክቶች ጋር ስምምነት በመፈራረም ብር16.364 ቢሊዮን በማግኘት የዕቅዱን (96.81%) እና (ከመቶ ፐርሰንት በላይ) በቅደም ተከተል መፈጸም ተችሏል፡፡ የፐሮጅክት ፋይናንሽያል አፈጻጸሙ ከዕቅድ በላይ የሆነው ለሴፍቲኔት ፕሮግራም 11 ቢሊዮን ብር  ከ ኤፍ.ኤች እና ከኦርዳ ኢትዮጵያ ጋር ስምምነት በመደረጉ ነው፡፡ከፕሮጀክት ስምምነቱ 10 ቢሊዮን ህዝብ ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ 9 ሚሊዮን ህዝብ ተጠቃሚ በማድረግ የዕቅዱን (90%) መፈፀም ተችሏል፡፡



የሲቭል ማህበረሰብ ድርጅቶች ባለስልጣን ከፌደራል ባለ ድርሻ አካላት ጋር ውይይት ሲያደርጉ-ባህርዳር

# መንገድ ልማት

## የኮንትራት አስተዳደር

በነባር የመንገድ ዲዛይን ስራ በ2013 ዓ.ም ይጠናቀቃሉ ተብለው በእቅድ ከተያዙት የመንገድ ዲዛይን ፕሮጀክቶ መካከል መርጦለማርያም -ቆረሽ-የጠፋት-ኢዛና-ገሰስ የ40 ኪሎ ሜትር የመንገድ ዲዛይን ስራ 60% ተሰርቶ ቀሪው 40% በ2014 በጀት አመት ለመስራት ታቅዶ የፊዚካል እና የበጀት እቅዱ 100% ተጠናቋል፡፡ በተመሳሳይ አቡነአሮን -ሰርኮ የ10 ኪሎ ሜትር የመንገድ ዲዛይን የፊዚካል እና የበጀት እቅዱ 100% ተጠናቋል፡፡ እንዲሁም ሸበልበረንታ-ወግዲ የ 50 ኪሎ ሜትር እስከ 2013 በጀት አመት በተለያዩ ችግሮች ምክንያት ተጓቶ 60% ላይ ቆሞ የነበረ ቢሆንም በ2014 በጀትአመት ቀሪውን 40% ለመስራት ታቅዶ ወደ ስራ ተገብቶ የመንገድ ጥናትና ዲዛይን ስራው የሁለቱን ወረዳዎች ጥቅምና ፍላጎት ባረጋገጠ ሁኔታ እንደገና የማስተካከል ስራ እንዲሰራ በተሰጠው የቢሮ አቅጣጫ መሰረት የመንገድ ምርጫ ስራ ተጠናቆ የሁለቱ ወረዳዎችና የዞን ተወካዮች/አመራሮች/ በተገኙበት ተገምግሟል፣ በዚህም መሰረት የመንገዱ ርዝመት ከ 50 ኪሎ ሜትር ከፍ የሚል ሲሆን አሁን ላይ የጥናትና ዲዛይን ስራው 33 % አፈጻጸም ደርሷል፡፡ የቢኮሎ አባይድልድይ እና አንዳሳ ድልድይ ውሉ አልቆ ቅድመ ክፍያ ተከፍሏል፡፡ በሌላ በኩል በበጀት ዓመቱ የ11 የተንጠልጣይ ድልድዮች ስራ 80% በመንግስት፤20% ከሄልቬታስ ስዊዝኢንተር ኮኦፐሬሽን-ኢትዮጲያ ጋር ለመስራት ወደ እንቅስቃሴ ተገብቶ የ8ቱ ተንጠልጣይ ድልድዮች የዲዛይን ስራ ቀደም ሲል ሙሉ በሙሉ 100 % የተጠናቀቀ ሲሆን፣ የቀሪዎቹ የ3ቱም ተንጠልጣይ ድልድዮች የጥናትና ዲዛይን ስራ ሙሉ በሙሉ 100% ተጠናቋዋል፡፡

## መንገድና ድልድይ ግንባታ

በ2014 ዓ.ም 11 ተንጠልጣይ ድልድይ ውስጥ 8ቱን ለመገንባትና 3ቱን የዲዛይን ስራ ለመስራት በተከለሰው እቅድ የተያዘ ሲሆን በበጀት ማነስ ምክንያት ከ8ቱ ድልድይ 4ቱን ለተደራጁ ማህበራት እንዲሰጡ በማድረግ ለ4ቱ ማለትም ዱራ፤ ጀማ፤ ተሜ እና ማላ ወንዝ የሳይት ርክክብ ተደርጎ በቅደም ተከተል 10%፤15%፤11% እና 20% የግንባታ አፈጻጸም ላይ ማድረስ ተችሏል፤ የግንባታ ሂደቱ ለወጣቶች የስራ ዕድል የሚፈጥር እና ለቴክኖሎጂ ሽግግር ጉልህ አስተዋጽኦ አበርክቷል፡፡

በክልሉ መንግስት ለድንገተኛ ጥገና እና ለስትራክቸር ጥገና ከተያዘው 57,284,241(ሃምሳ ሰባት ሚሊዮን ሁለት መቶ ሰማንያ አራት ሽህ ሁለት መቶ አርባ አንድ) ብር ውስጥ 46 መንገዶች ጥገና (780 ኪሎ ሜትር) እና 19 ስትራክቸር ጥገና ለመስራት ታቅዶ 16 መንገዶች (394 ኪሎ ሜትር) እና 2 ስትራክቸር በብር 22,382,818.60/ ሃያ ሁለት ሚሊየን ሦስት መቶ ሰማንያ

ሁለት ሽህ ስምንት መቶ አስራ ስምንት ብር ከ60 ሳንቲም/ በካፒታል በጀት የተሰራ ሲሆን 373 ኪሎ ሜትር መንገድ እና 17 ስትራክቸሮች በመደበኛው የመንገድ ፈንድ በጀት ጥገና ተሰርቷል፡፡ 12 ኪሎ ሜትር ቀሪ ሶስት መንገዶች ወደ ኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን እንዲሰሩ የተላለፉ ሲሆን የካፒታል በጀቱን 48% መጠቀም ተችሏል፡፡ ለአፈፃፀሙ ማነስ ዋናው መንስኤ በትህነግ ወረራ ምክንያት የወሎ ጥገና ጽ/ቤት ሙሉ በሙሉ የሸዋና የጎንደር ጥገና ጽ/ቤት በከፊል ወደ ስራ አለመግባታቸው፣ በወሎ ጥገና ጽ/ቤት ስር የሚገኙ ማሽነሪዎች ከነሙሉ መለዋወጫዎቹ በትህነግ ወራሪ ቡድን በመዘረፉና በመውደሙ የተነሳ ሲሆን ከሌሎች የጥገና ጽ/ቤቶች ማሽነሪዎችና ተጨማሪ ግብአቶች በትውስት በማቅረብ ወደ ስራ እንዲገቡ በመደረጉ በቀጣይ እቅዱን አሟልቶ ለመፈፀም ጥብቅ ስምሪት ተሰጥቷል።

በጎጃም እና በጎንደር ክላስተር ርክክብ እንዲደረግላቸው የተጠየቁ መንገዶች ብዛታቸው 11 ሲሆን (በጎጃም ክላስተር 4 መንገዶች 106.31 ኪሎ ሜትር ሲሆኑ በጎንደር ክላስተር 7 መንገዶች 189 ኪሎ ሜትር) ቢሆኑም ከእነዚህ መንገዶች ውስጥ ለርክክብ ብቁ የሆኑ መንገዶች ጎጃም ክላስተር 2 መንገድ 42.31 ኪሎ ሜትር እንዲሁም ጎንደር ክላስተር 3 መንገዶች 93.3 ኪሎ ሜትር እንዲሁም በወሎ እና በሰሜን ሸዋ ክላስተር ርክክብ እንዲደረግላቸው የተጠየቁ መንገዶች ብዛታቸው 11 ሲሆኑ (በወሎ ክላስተር 8 መንገዶች 300 ኪሎ ሜትር ሲሆኑ በሰሜን ሸዋ ክላስተር 3 መንገዶች 67 ኪሎ ሜትር) ቢሆኑም ከእነዚህ መንገዶች ውስጥ ለርክክብ ብቁ የሆኑ መንገዶች ወሎ ክላስተር 3 መንገድ 54 ኪሎ ሜትር እንዲሁም ጎንደር ክላስተር 3 መንገዶች 67 ኪሎ ሜትር ሲሆኑ በአጠቃላይ 11 መንገዶች 256.61 ኪሎ ሜትር መንገድ መረከብ ተችሏል፡፡

በመንግስት የልማት ድርጅቶችና በገጠር መንገዶች ኮንስትራክሽን ኤጀንሲ የሚገነቡ መንገዶች ዕቅድ አፈጻጸም ሲታይ በመደበኛ መንገድ ግንባታ ዘርፍ በዕቅድ ለማሰራት የተያዙ ፕሮጀክቶች በአማራ ገጠር መንገድ ኮንስትራክሽን ኤጀንሲ እና በክልሉ የልማት ድርጅቶች የሚገነቡት በዋነኝነት ተጠቃሽ ናቸው። ስለሆነም በኤጀንሲው የሚሰሩ ነባር መንገዶች ከ2004 ዓ.ም ጀምሮ ወደ ግንባታ የገቡና ያልተጠናቀቁ 45 የመንገድ ፕሮጀክቶች 964.02 ኪሎ ሜትር ርዝመት ያላቸው ሲሆን በገጠር መንገድ ኮንስትራክሽን ኤጀንሲ በነባር የመንገድ ፕሮጀክቶች በበጀት ዓመቱ 255 ኪሎ ሜትር መንገድ ለመገንባት ታቅዶ አሸባሪውና ወራሪዉ የትህነግ ቡድን በከፈተብን ወረራና ጦርነት ምክንያት የመንገድ ግንባታ ስራው የዕቅዱን 12.90 ኪሎ ሜትር (5%) ብቻ ማከናወን ተችሏል፣ አፈጻጸሙ ዝቅተኛ የሆነበት ዋነኛው ምክንያት ጦርነቱን ለመቀልበስ በተደረገዉ ጥሪት ለህልውና ማስከበር ዘመቻ ግንባር የሄዱ የኤጀንሲው ዳምትራኮች፣ ሻወር ትራኮች፣የሰርቪስ መኪኖችና ማሽነሪዎች ሙሉ በሙሉ ባለመመለሳቸው

ወደ ስራ መግባት አልተቻለም፤ ነገር ግን በእቅድ ያልተያዙና የህልውና ዘመቻውን ለማሳለጥ በበጀት አመቱ በርካታ የመንገድ ከፈታና ጥገና ስራ በኤጀንሲው በኩል ተሰርቷል፡፡ ከህልውናው ዘመቻ መልስ የማሽነሪ ኪራይ አለመገኘት፣ የሲሚንቶና ነዳጅ አቅርቦት ችግር መኖር ምክንያት አፈጻጸሙ ዝቅተኛ እንዲሆን አድርጎታል፤ በመሆኑም ቢሮዉ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመነጋገር በቀሪ 90 ቀናት በዕቅድ የተያዙትን 45 ፕሮጀክቶችን ወደ ስራ ማስገባት እንደማይቻል ታሳቢ በማድረግ ከተጀመሩ በርካታ አመታትን ያስቆጠሩትን (ከ2004 ዓ.ም ጀምሮ ያሉትን) ለፀጥታ እና ለሰላም ማስከበር ተግባር አጋዥ የሚሆኑትን እንዲሁም ከክረምቱ በፊት ካልተሰሩ በሰውና በንብረት ላይ አደጋ ሊያደርሱ የሚችሉትን መነሻ ተደርጎ እቅዱን በመከለስ 10 ፕሮጀክቶችን ማለትም 60.29 ኪሎ ሜትር በኤጀንሲው ለማስገንባት ስምምነት ተደርሶ አስሩም ፕሮጀክቶች ወደ ስራ የገቡ ሲሆኑ እነሱም አምባ ጊዮርጊስ-ስላሬ-ሀሙሲት 0.81 ኪሎ ሜትር፤ማጀቴ–ወዠድ 1.3 ኪሎ ሜትር፤አጅባር-ተድባበማርያም፤ አላውሃ–ቃሊም–ሮቢት 1.51 ኪሎ ሜትር፤መሻህ-በስቂያ-መረው-አገጣ 1.71 ኪሎ ሜትር፤አርባፅጓር–መሸሃ፤ቁይ–ይቅበሀና 1.08 ኪሎ ሜትር፤ጊናገር–ስጦን–መተህብላ 0.7 ኪሎ ሜትር፤ ጉልት–አቤራ–ጠለምት 14 ኪሎ ሜትር፤ ክምር ድንጋይ-አጃ-መቀጠዋ 0.25 ኪሎ ሜትር ፕሮጀክቶች ሲሆኑ በተያዘው ዕቅድ መሰረት እንዲፈፀም ጥብቅ ክትትልና ድጋፍ ተደርጓል፡፡




*የወንቃ ወንዝ ድልድይ-ጎዛምን ወረዳ*

**የአብክመ የመንግስት ኮሙዩኒኬሽን ቢሮ**

## በልማት ድርጅቶች የተገነቡ ድልድዮች

በ2014 ዓ.ም በልማት ድርጅቶች የተገነቡ አዳሪ ድልድይ ግንባታ ብዛት 3 (መሎ፣ በምቢያና ዛሪማ)፤መሎ ድልድይ 40 ሜትር ርዝመት ያለው እብናት ወረዳ የሚገኝ በ2008 ዓ.ም የተጀመረና አፈፃፀሙም 100% የተጠናቀቀ፤በምቢያ ድልድይ 140 ሜትር ርዝመት ያለውና በ2013 ዓ.ም የተጀመረ ፍየል ውሃ አካባቢ የሚገኝ በፀጥታ ችግር የቆመ፤ዛሪማ ድልድይ 54 ሜትር ርዝመት ያለውና በ2013 ዓ.ም የተጀመረ አዲርቃይ አካባቢ የሚገኝ እንዲሁም አዲስ ድልድይ ግንባታ ብዛት 3 ገርጣ፣ ቢኮሎ አባይ እና አንዳሳ፤ገርጣ ድልድይ እቅድ 10% ሲሆን አፈፃፀሙም አሸናፊው ተለይቶ እና ሳይት ርክክብ ተደርጎ የስራ ማስጀመሪያ ቅድሚያ ክፍያ ተከፍሎ ወደ ስራ እንዲገባ ተደርጓል፤ቢኮሎ አባይ ድልድይ እቅድ 20% ሲሆን አፈፃፀሙም በመቅደላ ኮንስትራክሽን ወደ ቅድመ ግንባታ ለመግባት የሳይት ርክክብ ተደርጎ እና የስራ ማስጀመሪያ ቅድሚያ ክፍያ ተከፍሎ ወደ ስራ እንዲገባ ተደርጓል፤አንዳንሳ ድልድይ እቅድ 20% ሲሆን አፈፃፀሙም አሸናፊው ተለይቶ ውሉ ተይዞ እና ቅድመ ክፍያ ተከፍሎ ወደ ስራ ገብቷል፤በአጠቃላይ የመንገድ ግንባታ፣ጥገና እንዲሁም የድልድይ ግንባታ ስራዎችን የተሻለ አፈፃፀም ለማስመዝገብ የመስክ ድጋፍና ክትትል የሚያደርግ የሱፐርቪዥን ቡድን በማዋቀር ወደ ዞኖች በተደራጀ ቼክሊስት መደገፍ ተችሏል። በተጨማሪም ችግር ያለባቸውን ፕሮጀክቶች አመራሩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት በአካል በመገኘት የመስክ ድጋፍ ማድረግ የተቻለ ሲሆን በተጨማሪም ከፕሮጀክት ተቋራጮች ጋር የሶስትዮች የስራ ግምገማ በማድረግ እና በችግር ውስጥ ለሚገኙ ተቋራጮችም የግንባታ ውሉን መሰረት ተደርጎ እርምጃ በመውሰድ ወደ ተግባር ለማስገባት ጥረት ተደርጓል።

## በወረዳ ገጠር መንገድ ልማት አስተዳደር የተሰሩ ስራዎች

በወረዳ ገጠር መንገድ ልማት አስተዳደር ዘርፍ በወረዳ ምክር ቤት በጀትና በህብረተሰቡ ተሳትፎ 5986.75 ኪሎ ሜትር መንገድ ለመጠገን ታቅዶ 7002.42 ኪሎ ሜትር ከዕቅድ በላይ መፈጸም ተችሏል፡፡በስራው የተሣተፈ ህዝብ ወንድ 672,969 ሴት 263,866 ድምር 936,835 ሲሆን የህዝቡ ጉልበት በገንዘብ ሲተመን 128,610,155.22 ብር ነው፡፡በወረዳ በጀትና በህብረተሰብ ተሳትፎ የመንገድ ግንባታ ስራ 100 ኪሎ ሜትር አዲስ መንገድ ለመገንባት ታቅዶ በዌትድ አቬሪጅ 263.14 ኪሎ ሜትር ከዕቅድ በላይ መፈጸም የተቻለ ሲሆን ከዚህ ውስጥ የጠረጋ ስራ 934.91 ኪሎ ሜትር፤ አፈር ድልዳሎ ስራ 602.21 ኪሎ ሜትር ፤ጠጠር ልባስ ስራ 365.94 ኪሎ ሜትር፤ እስትራክቸር ከ12 ሜትር በታች 140 እስትራክቸር መገንባት ተችሏል፡፡

# ውሃና ኢነርጂ

## የንጹህ መጠጥ ውሃ ተደራሽነት

የክልሉን ህዝብ የንጹህ መጠጥ ውሃ ተጠቃሚና ተደራሽ ለማድረግ በተቀመጠው መስፈርት መሰረት ከቅድመ ዝግጅት ሰራ ጀምሮ ወደ ተግባር በመግባት የታቀደውን ግብ ለማሳካት የሚያስችሉሰፊ ሰራዎች ተከናውነዋል፡፡ በመሆኑም በገጠር 11 የገጠር ባለመስመር አገናኝ ተቋማት 243 የመጠጥ ጉድጓዶች፤ እና 1705 አነስተኛ የውሃ ተቋማት ግንባታ በማከናወን 429,273 (206,052 ወንድ እና 223,221 ሴት) ህዝብ ተጠቃሚ በማድረግ በ2013 በጀት ዓመት መጀመሪያ በገጠር ከተደረሰበት 69.84 የንጹህ መጠጥ ውሃ ሽፋን ላይ በ2.37% በመጨመር ወደ 72.21% ማድረስ ተችሏል፡፡ በተመሳሳይ በከተማ 8 በተጠናቀቁ የንጹህ መጠጥ ውሀ ፕሮጀክቶች 104,230 (52,115 ወንድ እና 52,115 ሴት) ህዝብ ተጠቃሚ በማድረግ የከተማ የንጹህ መጠጥ ውሃ ሽፋን በ2013 በጀት ዓመት መጀመሪያ ከተደረሰበት ከ67.05% ላይ 2.19% የሽፋን እድገት በማምጣት የከተማ የንጹህ መጠጥ ውሃ ሽፋንን 69.24% ማድረስ ተችሏል፡፡

በአጠቃላይ በ2014 በጀት ዓመት በገጠርና በከተማ በተጠናቀቁ ፕሮጀክቶች 533,503 (256,081 ወንድ እና 277,422 ሴት) የህብረተሰብ ክፍል ተጠቃሚ በማድረግ የክልሉን የንጹህ መጠጥ ውሃ ሽፋን በ2013 መጀመሪያ ከተደረሰበት 69.44% ላይ በ2.33% በመጨመር ወደ 71.77% ማድረስ ተችሏል፡፡

የውሃ ተቋማትን መገንባት ብቻ ሳይሆን የተበላሹትን ጠግኖ ወደ ስራ በማስገባትና በዘላቂነት አገልግሎት ለመስጠት በሚያስችል መልኩ ተንከባክቦ እና የእኔ ባይነት ስሜትን ማሳደግ ተገቢ ነው፡፡ በመሆኑማ የመጠጥ ውሃ ተቋማት በተጠቃሚው ህብረተሰብ ዘንድ የበለጠ የባለቤትነት ሙብት እንዲኖራቸው ለማድረግ የሚያመቹ 5,707 አባላት ያላቸው 61 የገጠር መጠጠጥ ውሃ ተጠቃሚዎች ማህበራትን እና 18 የገጠር መጠጥ ውሃ አገልግሎት ማህበራትን ማቋቋም ተችሏል፡፡ የመጠጥ ውሃ ተቋማትን የብልሽት ምጣኔም በ2013 ዓ.ም ከደረሰበት 12.11% ወደ 11.76% የደረሰ ሲሆን ይህም በጦርነት ምክንያት የተበላሹ የውሃ ተቋማት ቁጥር በመጨመሩ መሆኑን የተሰበሰበው መረጃ ያመላክታል፡፡ ከከተሞች ዕድገት ጋር እያደገ የመጣውን የከተሞች የውሃ አቅርቦት በዘላቂነት ይዞ ለማስተዳደር በከተሞች ለውሃ ግንባታ የሚወጣውን የኢንቨስትመንት ወጪ ታሳቢ ያደረገ ታሪፍ በማዘጋጀት የኢንቨስትመንት ወጪን መመለስ ተገቢና በትኩረት ተይዞ ወደ ተግባር የተገባበት ስራ ነው፡፡ በመሆኑም ከከተማ ውሃ አገልግሎቶች 7,670,000/ ሰባት ሚሊዮን ስድስት መቶ ሰባ ሺ ብር/ የኢነቨስትመንት ወጪ በማስመለስ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ገቢ ሆኗል፡፡



ንፁህ መጠጥ ውሀ-አይከል ከተማ

## አማራጭ የኢነርጂ ምንጮችን መጠቀም

በየጊዜው እየተራቆተ የመጣውን የደን ሀብት ጠብቆ በቁጠባ ለመጠቀም እንዲሁም በአየር ንብረት መዛባት ላይ የሚያስከትለውን አሉታዊ ተጽዕኖ ለመከላከል አማራጭ የኢነርጂ ምንጮችን መጠቀም ተገቢ ነው፡፡ በመሆኑም በክልላችን አማራጭና ታዳሽ የኢነርጂ ቴክኒሎጂዎች በስፋት እየተሰራጩ ሲሆን ለሙብራት ከምንጠቀምባቸው አማራጭ የኢነርጂ ቴክኖሎጂዎች በተጨማሪ ብዙ ኃይል የሚጠይቁ የምግብ ማብሰያ ምድጃዎችን በተሻሻሉ ኃይል ቆጣቢ ምድጃዎች በመተካት በክልሉ ያለውን የተሸሻሉ የኃይል ቆጣቢ ምድጃዎችን ስርጭት ሽፋን በ2013 መጀመሪያ ከተደረሰበት 59.14% ላይ በ3.8% በመጨመር ወደ 62.97% ማሳደግ ተችሏል፡፡

በ2014 ዓ.ም የክልሉን ህብረተሰብ የባዮ ጋዝ ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ ለማድረግ በስፋት የተሰራ ሲሆን በዚህም መሰረት 2375 ባዮ ጋዞች ተገንብተው ለ11,875 ህብረተሰብ አገልግሎት መስጠጥ ጀምረዋል፡፡ የክልሉን የገጠር ህብረተሰብ የኤሌክትሪክ ኃይል ተጠቃሚ ለማድረግ በፀሐይና በንፋስ ኃይል እንዲሁም አነስተኛ ሀይድሮ ኤልክትሪክ ለማመንጨት የሚያስችል ስራ እየተሰራ ይገኛል፡፡ በመሆኑም 71,325 የሶላር ማሾችን እና 21,184 የቤተሰብ ሶላር እንዲሁም 10 የቲቪ ሶላር በድምሩ 92,519 የሶላር ቴክኖሎጂዎችን በማሰራጨት 0.5897 ሜጋ ዋት ኃይል ማቅረብ የተቻለ ሲሆን በዚህም 92,519 ከኤሌክትሪክ ዋና መስመር ርቀው የሚገኙ የክልሉን የገጠር አባወራና እማወራዎችን ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡



**ባዮ ጋዝን በመጠቀም ምግብ ማብሰል-ጎዛምን ወረዳ**

# ገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም

## የማሳ ድንበር ማዘጋጀት

በክልላችን በተለያዩ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች ድጋፍ 54 በወረዳዎች ባሉ 209 262,714 ባለይዞታ ቀበሌዎች ለ1,068,483 የማሳ ካርታ አዘጋጅቶ የ2ኛ ደረጃ ይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ለመስጠት፤ የማሳ ድንበር ለመለካትና የምዝገባ መረጃ ለመሰብሰብ ታቅዶ 2,222,375 ማሳ መለካት ተችሏል፤ አፈፃፀሙም 98.26 % ደርሷል፡፡

## የማሳ ካርታ ማዘጋጀት

በተለያዩ ምክንያቶች የመስክ ባለሙያዎች በወቅቱ አለመሟላት ስራውን ወደኋላ ቢያስቀረውም ከተለካው ማሳ *ውስጥ* 1,958,224 የማሳ ካርታ ዲጅታይዝ ለማድረግ ታቅዶ 1,958,224 ማሳ ድጂታይዝ ማድረግ ተችሏል፤ አፈጻፀሙም ከተለካው ማሳ 88.11% ሆኗል፡፡

የአብከም የመንግስት ኮሙዩኒኬሽን ቢሮ




የማሳ ካርታ ማዘጋጀት

## የመሬት መረጃን በመረጃ ቋት መመዝገብ

በበጀት አመቱ 338,190 የባለይዞታዎችን 3,564,956 ማሳ መረጃ ወደ መረጃ ቋት ለማስገባት ታቅዶ የ179,817 (53.17%) ባለይዞታዎችን፣ 817,242 (22.92%) ማሳዎች መረጃ ወደ መረጃ ቋት የመመዝገብ ሥራ ተሰርቷል፡፡

## የመሬት ይዞታ ማስመለስ

በበጀት አመቱ አላግባብ ይዞታቸውን ያጡ ተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎችን መረጃ በማጥራት ይዞታቸው እንዲመለስላቸው ለማድረግ የ1,850 ባለይዞታዎችን ለማስመለስ ታቅዶ በአመቱ ውስጥ የ2,893 (327.35%) (ወንድ 1,589፣ ሴት 1,304) ከዚህ መካከል (ወላጆቻቸውን ያጡ ህፃናት 892፣ አረጋውያን 1727፣ አካል ጉዳተኞች 274)1584.2 ሄክታር መሬት እንዲመለስላቸው ተደርጓል፤ አፈፃፀሙ ከአመቱ 20% ነው፡፡ ይሁን እንጅ የተሰራው ስራ አፈፃፀም ዝቅተኛ በመሆኑ በቀጣይ በጀት አመት በቁርጠኝነት መሰራት ያስፈልጋል፡፡

## ለመሬት ቅሬታዎች ምላሽ መስጠት

በ2014 ዓ.ም 33,400 ከመሬት ይዞታ ጋር በተያያዘ ከተለያየ ወረዳዎችና ቀበሌዎች የሚመጡ አቤቱታዎችን ለመፍታት ታቅዶ የ41,128 (276.01%) (ወንድ 24,693 ሴት 16,435) አቤቱታ አቅራቢዎችን ችግር በማጣራት መፍትሄ መስጠት ተችሏል፤ አፈፃፀም 276.01% ሆኗል፡፡

## በህገ-ወጦች የተያዘ የወል መሬት ማስመለስ

በ2014 ዓ.ም በህገወጥ መንገድ የተወረረን የወል መሬት ወደ ህብረተሰቡ የጋራ መጠቀሚያነት ማስመለስ እየተጠናከረ የመጣ ተግባር ሲሆን በአመቱ በህገ-ወጥ መንገድ የተያዙ መሬቶችን በህዝብ የነቃ ተሳትፎ በመለየትና በማስተቸት ከህገ-ወጦች የማስመለስ ስራ ተሰርቷል፡፡ በመሆኑም ከ2,500 ግለሰቦች 15,000 ሄክታር በህገ-ወጥ መንገድ የተያዘውን የወል መሬት ለማስመለስ ታቅዶ ከ36,499 (ወ-30,036 ሴ 6,455) ግለሰቦች 15,844 ሄክታር (105.2%) መሬት ማስመለስ ተችሏል፡፡

## አርሶ አደሩን በቀበሌ ማዕከል ማሰባሰብ

በ2014 ዓ.ም የ178 ቀበሌ ማእከላትን አዲስ ፕላን ለማዘጋጀት ታቅዶ ለ131 (73.8%) ቀበሌዎች አዲስ ፕላን ማዘጋጀት ተችሏል፡፡ የተዘጋጀውን የቀበሌ ማእከል ፕላን ወደ መሬት በማውረድ 165 ብሎክ ለመከፈት ታቅዶ 123(74.8%) ብሎክ ተከፍቷል፡፡ በመሆኑም በ144 ቀበሌዎች 23,787 ቦታዎችን ለመሸንሸን ታቅዶ በ99 ቀበሌዎች 12,347(52%) ቦታዎች መሸንሸን ተችሏል እንዲሁም 39,698 ተጠቃሚዎችን ግንባታ ለማስጀመር ታቅዶ 12,464(31.4%) ተጠቃሚዎች ግንባታ እንዲጀምሩ ተደርጓል፡፡ 25,357 ተጠቃሚዎች ግንባታ ለማጠናቀቅ ታቅዶ 9,224 (36.4%) ግለሰቦች ግንባታቸውን አጠናቀዋል፡፡ ግንባታ ካጠናቀቁት ውስጥ ለ5,690 (15%) ቋሚ ካርታ ተሰጥቷል፡፡ ለ885 ግለሰቦች የስመ ንብረት አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ ለ552 (62%) ግለሰቦች አገልግሎት የተሰጠ ሲሆን ከግንባታ ፈቃድና ከስመ ንብረት ዝውውር ብር 5,524,371 ገቢ መሰብሰብ ተችሏል፡፡ በበጀት አመቱ 40,002 ሳይት ፕላን ለመስጠት ታቅዶ 10,022 (25%) ሳይት ፕላን ተሰርቷል፡፡ 30,218 የግንባታ ፕላን ለማዘጋጀት ታቅዶ 7,614 (25%) የግንባታ ፕላን ማዘጋጀት ተችሏል፡፡ ከመሰረተ ልማት ስራዎች አንፃር በ97 ቀበሌዎች መንገድ ለመስራት  ታቅዶ በ22 (23%) ቀበሌዎች 49 ኪሎ ሜትር መንገድ መስራት ተችሏል፡፡ በ134 ቀበሌዎች የውሀ መስመር ለመዘርጋታ ታቅዶ በ46 ቀበሌዎች ለ11,877 (20%) ተጠቃሚዎች እንዲዘረጋ ተደርጓል፡፡ በ50 ቀበሌዎች የመብራት መስመር ለመዘርጋታ ታቅዶ በ43 (107.9%) ቀበሌዎች ለ2,858 (13%) ተጠቃሚዎች እንዲዘረጋ ተደርጓል፡፡ በባህርዳር ከተማ ባሉ ስድስት ክፍለ ከተሞች የቅየሳ ስራ ለመስራት በታቀደው መሰረት 4,705 ማሳዎች 906.31 ሄክታር መሬት የመለካት ስራ በመስራት ካርታ እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ ከገጠር ቀበሌ

ማእከላት የአገልግሎት ክፍያዎች 920,417 ብር ገቢ ለማሰባሰብ ታቅዶ 5,524,371 ብር በመሰብሰብ ከ100% በላይ መፈፀም ተችሏል፡፡

## የካሳ ግመታና ክፍያ

በበጀት ዓመቱ በልማት ምክንያት ከይዞታቸው የሚነሱ 51,587 ባለይዞታዎች 6.44 ቢሊዮን ብር ካሳ ገምቶ እንዲከፈላቸው ለማድረግ ታቅዶ ለ 38,086 (73.8%) ባለይዞታዎች ለ6,384 ሄክታር መሬት ብር 6.661 ቢሊዮን (ከ100% በላይ) የካሳ ክፍያው ተፈፅሟል፡፡ ለ285 አርሶ አደሮች ትክ የእርሻ መሬት እንዲያገኙ ታቅዶ 609(199%) አርሶ አደሮች ትክ የእርሻ መሬት እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡

## ለኢንቨስትመንት መሬት መለየት

በ2014 ዓ.ም 7,500 ሄክታር በኢንቨስትመንት ለሚሰማሩ ባለሃብቶች የሚሰጥ መሬት ለመለየትና ለማዘጋጀት በታቀደው መሰረት 15,177.56 ሄክታር (በላይ 100%) መሬት የመለየት ስራ ተሰርቷል፡፡

## የቅየሳና ካርታ ዝግጅት ስራ

በ2014 ዓ.ም በ14ቱ ከተሞች 66,000 ይዞታዎችን የይዞታ ወሰን ለማካለል ታቅዶ በ10 ከተሞች 18,691 (28.32%) ይዞታዎችን የማካለል ስራ ተሰርቷል፡፡ በ14ቱ ከተሞች 66,000 ይዞታዎችን የወሰን ልኬት ቅየሳ ሥራ ለመስራት ታቅዶ በ6 ከተሞች የ15,668 (23.74%) ይዞታዎች የወሰን ልኬት ቅየሳ ሥራ ተሰርቷል፡፡ በተመሳሳይ 4,500 የ3ኛ ደረጃ የቅየሳ መቆጣጠሪያ ነጥቦች ጥራቱንና ደረጃውን ጠብቆ ንባብ ለመውሰድ ታቅዶ 1,120 (24.89%) የቅየሳ መቆጣጠሪያ ነጥቦች ንባብ የመውሰድ ስራ ተሰርቷል፡፡

# ገቢ

## ዘመናዊ የግብር አስተዳደር ስርዓት መዘርጋት

በክልሉ የሚደረገውን የፀረ ድህነት ትግል አጠናክሮ ለማስቀጠል የክልሉ ኢኮኖሚ የሚያመነጨውን ገቢ አሟጦ ለመሰብሰብና የክልሉን የልማት ፋይናንስ ፍላጎት ለማሳደግ ዘመናዊ የግብር አስተዳደር ስርዓት ተዘርግቶ በየደረጃው ሰፊ ጥረት ተደርጓል፡፡ የገቢ አሰባሰቡንም በታክስ ሰራዊት ግንባታና በተደራጀ መዋቅር በመፈጸም ውጤቶችን ለማምጣት ሰፊ ስራ ተሰርቷል፡፡

**የአብክመ የመንግስት ኮሙዩኒኬሽን ቢሮ**

## ገቢ መሰብሰብ

በ2014 ዓ.ም የኪራይ ሰብሳቢነት ትግልን በቁርጠኝነት በማጠናከር ኢኮኖሚው የሚያመነጨውን ገቢ በብቃት ለመሰብሰብ በተሰራው ስራ ከመደበኛ ገቢ ብር 26.75 ቢሊዮን እና ከከተማ አገልግሎት ብር 3.30 ቢሊዮን በድምሩ ብር 30.05 ቢሊዮን ገቢ ለመሰብሰብ ታቅዶ ወደ ተግባር በመግባት ብር 26,992,578,627 የተሰበሰበ ሲሆን አፈፃፀሙም 89.8% ሆኗል፡፡ ካለፈው በጀት ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ከተሰበሰበው ገቢ ብር 20,210,917,728 ጋር ሲነጻጸር 6,781,660,899 (33.6%) ዕድገት አሳይቷል፡፡ ይሁን አንጅ የገቢ አፈፃፀሙ እንደ ክልል ሲታይ ክልሉ አሁን ካለበት አስቸጋሪ ነባራዊ ሁኔታ አኳያ ገቢውን ለመሰብሰብ የተደረገው ጥረት አበረታች ቢሆንም ዕቅዱን ማሳካት ግን አልቻለም፡፡

ለእቅዱ አለመሳካት ዋና ዋና ምክንያቶች እንደ ክልል በተከፈተብን ጦርነት በሰ/ወሎ፣ በዋግኽምራ፣ በሰ/ጎንደር፣ በደ/ወሎ፣ በደሴ እና በደ/ጎንደር በግብር ከፋዩ ሃብት ላይ ከፍተኛ ውድመትና ዘረፋ እንዲሁም መፈናቀል የተፈጠረ መሆኑ፣ ጦርነቱ ከፍተኛ የሆነ የንግድ መቀዛቀዝ የፈጠረ መሆኑ፣በየደረጃው ያለው አመራር፣ ሙያተኛ፣ አጋርና ባለድርሻ አካላት ትኩረታቸው ሙሉ በሙሉ ህልውና ዘመቻው ላይ የነበረበ መሆኑ፣ በትልልቅ ከተሞች ሌሎች መወሰን የሚገባቸውን ገቢዎች በወቅቱ ወስኖ ማስከፈል ባለመቻሉ፣ የቀረቡ ይግባኞችን በፍጥነት አይቶ ገቢው እንዲሰበሰብ አለመደረጉ፣ የኪራይ ገቢን፣ የደረጃ "ለ" ግብርን በሚፈለገው ልክ ማስከፈል ባለመቻሉ፣ ደረሰኝ ክትትሉ በጣም የተቀዛቀዘ በመሆኑ፣ የሃሰተኛ ደረሰኞች መበራከት ገቢ እያሳጣ በመሆኑ፣ የውስጥና የውጭ ሌብነቱን በሚፈለገው መልኩ መታገል አለመቻል፣ የህገ-ወጥ አየር በአየር ንግድን መቆጣጠር አለመቻል፣ የውዝፍ ሊዝና የቦታ ኪራይን በተገቢው አለማስከፈል፣ በትልልቅ ከተሞች ስመ ንብረት ዝውውር የቆመ በመሆኑ የሚጠቀሱ ችግሮች ናቸው፡፡ ስለሆነም በቀጣይ መታረም የሚችሉትን ችግሮች ገምግሞ በማረም ውጤታማ ስራ መስራት ተገቢ ነው፡፡

የገቢ አሰባሰቡን ውጤታማ ለማድረግ ከአጋርና ባለድርሻ አካላት ጋር መግባባት ላይ በመደረሱ በበጀት አመቱ አጋርና ባለድርሻ አካላት ለገቢ ተቋሙ የዕቅድ መሳካት ሚናቸው ከፍተኛ ነበር፡፡ በዚህም መሰረት በ2014 ዓ.ም የደረጃ "ሐ" ግብር ከፋዮችን ግብር በወቅቱ ለመሰብሰብ እንዲቻል በ100 መድረኮች ለወንድ 3,114 ሴት 1,168 በድምሩ 4,282 አጋርና ባለድርሻ አካላትን የማሳተፍ ስራ ተሰርቷል፡፡ በዚህም አጋርና ባለድርሻ አካላት በ2014 በጀት ዓመት የደረጃ "ሐ"፣ "ለ" እና "ሀ" ግብር ከፋዮች ግብራቸውን በወቅቱ እንዲከፍሉ ቅስቀሳ በማድረግ፣ በህገ-ወጥ ንግድ የተሰማሩትን ወደ ንግድ መረቡ እንዲገቡ በማድረግ፣ በከተማ ገቢ አሰባሰብ ዙሪያ በቅንጅት በመስራት፣ መመሪያዎችን በማውጣትና በማሻሻል፣ ህግ በማስከበር የነበረው ጅምር

ስራ አበረታች የነበረ ሲሆን በአንፃሩ ደግሞ ይግባኞችን በወቅቱ አለማየትና አላግባብ መናድ፣ ህገ- ወጥነትን በሚገባ አለመከላከል፣ ቅንጅታዊ ስራው የላላ መሆን፣ ሂሳብ አዋቂዎች ሚዛናዊ አለመሆንና ለግብር ከፋዩ ማድላት፣ አመራሩ ለገቢ ተቋሙ ግብአት አለማሟላት ችግሮች እንደነበሩ እና በቀጣይ መስተካከል እንዳለባቸው መግባባት ላይ ተደርሷል።

## የመልካም አስተዳደር ማስፈን

የገቢ ተቋሙ ተገልጋዩ አገልግሎት ፈልጎ የሚመጣበት ከመሆኑ ጋር በተያያዘ የሚፈጠሩ የመልካም አስተዳደር ችግሮች በግብር ከፋዩ ከግብር በዛብኝ ጋር በተያያዘ የቀረቡ ቅሬታዎችን **99.66%** የሚሆኑትን ምላሽ እንዲያገኙ መደረጉ፣ ከሂሳብ መዝገብ ምርመራ አኳያ ውዝፍ መዝገቦች ላይ በማተኮር ከተመረመሩ **18,747** የሂሳብ መዝገቦች መካከል **7,633**(40.72%) ውዝፍ መዝገቦችን ኦዲት በማድረግ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን መቀነስ መቻሉ፣ ከሂሳብ መዝገብ ምርመራ ጋር በተያያዘ ከቀረቡ 78 ቅሬታዎች መካከል ለ68 ወይም (87.18%) ግብር ከፋዮች ምላሽ የተሰጠ መሆኑ፣ በበጀት አመቱ አግባብነት ያለው ተመላሽ ካቀረቡ 111 ግብር ከፋዮች መካከል ለ39(35.13%) ምላሽ የተሰጣቸው መሆኑ፤ የሰራተኞች ፈቃድ አሰጣጥ እና ሌሎች አገልግሎቶች በአግባቡ እየተከናወኑ መሆናቸው፤ በጥንካሬ የሚታዩ ሲሆን በአንፃሩ ደግሞ የግብር ይግባኝ ካቀረቡ 6,517 ግብር ከፋዮች መካከል 423/6.49%/ቱ ገና ምላሽ ያላገኑ መሆኑ፤ በየደረጃው የሚሰጡ አገልግሎቶች በግብር ከፋዩ ዘንድ በተሟላ ሁኔታ እርካታን ያልፈጠሩ መሆኑ በድክመት የሚታዩና በቀጣይ መፈታት የሚገባቸው የመልካም አስተዳደር ችግሮች በመሆናቸው በትኩረት ይዞ መፍታትና አገልግሎት አሰጣጡን ቀልጣፋና ዘመናዊ በማድረግ የተገልጋዩን እርካታ ማሻሻል ይገባል፡፡

## የፀረ-ሌብነት ትግል

የግብር አስተዳደር ስርዓቱ ለሌብነት በቀላሉ ተጋላጭ በመሆኑ ራሱን የቻለ የፀረ-ሌብነት መታገያ ዕቅድ ተዘጋጅቶለት ችግሮችን ለመፍታት ጥረት እየተደረገ መሆኑ፤የአመራሩንና የሰራተኛውን መልካም ስነ-ምግባር ለማሳደግ ለወንድ 4,764 ሴት 3,869 ድምር 8,633 የገፅ ለገፅ ስልጠና በመስጠት ግንዛቤ የተፈጠረ ሲሆን ለወንድ 291 ሴት 261 ድምር 552 ደግሞ የምክር አገልግሎት ለመስጠት ጥረት የተደረገ መሆኑ፤የውስጥ ሌብነቱን ከመታገል አኳያ በተለያየ አግባብ የስነ-ምግባር ጉድለት የታየባቸው ወንድ 92 ሴት 48 ድምር 140 ሠራተኞች ላይ ትግል በማድረግ የዲስፕሊን እርምጃ የተወሰደ መሆኑ፡፡

## የውጭ ሌብነትን መታገል

በ2014 ዓ.ም 1,492 ግብር ከፋዮች ያቀረቧቸው 3,159 ሃሰተኛ ደረሰኞች ተይዘው

የ643,279,197.54 ግኝ ውድቅ መደረጉ፤ በግል ድርጅቶች የሥራ ግብር ክትትል ከተደረገባቸው 717 ድርጅቶች 131,058,085.07 ብር ሳይከፈል ማግኘት የተቻለ መሆኑ በጥንካሬ የሚታዩ ሲሆን የውስጥ ሌብነቱን በመታገል በኩል ጅምር ቢኖርም አሁንም ውስንነት ያለ መሆኑ፡፡ በተለይም ታክስ የሚሰውሩትንና የሚያጭበረብሩትን ግብር ከፋዮች ሙያን ተጠቅሞ ማምከን አለመቻል፤ ኦዲተሮች ግብር ከፋዩ ያቀረበውን እንዳለ ማሳለፍና ተገቢነት የሌለው ወጭ መያዝ፤ ለደንበኞች የአገልግሎት እዳ እያለበት ክሊራንስ መስጠትና አግባብነት የሌለው የቅሬታ መልስ መስጠት፤ ገንዘብ ያዦች ደረሰኝ በማበላለጥ ማጭበርበር እና የክትትል ባለሙያዎች ፍትሃዊነትን ማዛባት፤ የግብር ውሳኔ በወቅቱ አለመወሰንና ተገቢ ያልሆነ ተመላሽ መፍቀድ፤ እዳ ክትትሉ ውዝፍ መረጃን በአግባቡ አለመያዝ የሚታዩ ዝንባሌዎች መኖራቸውና በቀጣይ ትግል የሚያስፈልጋቸው ናቸው፡፡ የውጭ ሌብነቱ መልኩን እየቀያየረ ግብር ለመሰወርና ለማጭበርበር የሚደረገው ጥረት ከፍተኛ መሆኑ፡፡ በተለይም ሃሰተኛ ደረሰኞችን በመጠቀም የተጋነነ ወጭ ማቅረብ፤ ፈቃድ በመቀያየር ግብር መሰወር፤ ዋና ድርጅት ሳይኖረው ቅርንጫ በመክፈት ግብር መሰወር፤ተገቢ ያልሆነ ተመላሽ መጠየቅ፤ ደረሰኝ ለተጠቃሚ አለመስጠት፤ ከመሸጫ ዋጋ በታችና የዕቃ ቁጥር በመቀነስ ማጭበርበር፤መጋዝንን በመደበቅና በጨለማ ያለደረሰኝ በመሸጥ ማጭበርበር፤በስም ሃብትና ንብረት እንዳይኖር በማድረግ ውዝፍ ግብር አለመክፈል፤የግል ድርጅቶች የስራ ግብር የሚሰበስቡትን ቆርጠው ማስቀረት፤ከገቢ ተቋሙ አመራርና ሙያተኞች ጋር ተገቢ ያልሆነ ግንኙነት በመፍጠር የመንግስትን ገቢ ማሳጣት የሚጠቀሱና በቀጣይ በትግል መፈታት ያለባቸው ናቸው፡፡

### የንግድ ግብር ከፋዮችን ቁጥር ማሳደግ

በ2014 ዓ.ም የንግድ ግብር ከፋዮችን ቁጥር ከ340,925 ወደ 383,417 ለማሳደግ በዕቅድ ተይዞ በተሰራው ስራ መሰረት በአስራ ሁለት ወራት 40,307 ግብር ከፋዮችን ወደ ንግድ መረቡ በማስገባት የንግድ ግብር ከፋዮችን ቁጥር ወደ 358,555/93.52%/ ማሳደግ ተችሏል፡፡

## ስራና ስልጠና

### የኢንተርፕራይዝ ምሥረታና ስራ ዕድል ፈጠራ

በከተማና በገጠር የስራ እድል ለመፍጠር በተሰራው ስራ 52,693 አዲስ ኢንተርፕራይዝ በማቋቋም 936,180 (ቋሚ 757,301 ጊዜያዊ 178,879) የሥራ ዕድል ለመፍጠር ታቅዶ 42,824 ኢንተርፕራይዞች በመመስረት 965,203 የስራ ዕድል መፍጠር ተችሏል፣ አፈፃፀሙም በኢንተርፕራይዝ 81.27% በስራ ዕድል ፈጠራ 103% ማድረስ ተችሏል፣ በቋሚና ጊዜያዊ የስራ እድል ፈጠራ በዝርዝር ሲታይ፣ ቋሚ- ወንድ - 399,483 ሴት- 205,365 ድምር- 604,848

(80.5%)፣ ጊዜያዊ ወንድ-238,685 ሴት- 121,670 ድምር - 360,355 (ከ100%በላይ) መሆን ችሏል፡፡

በአጠቃላይ ሲታይ በበጀት አመቱ ወንድ- 638,168 ሴት- 327,035 ድምር - 965,203 (103%) በቋሚና ጊዜያዊ የሥራ ዕድል ተፈጥሯል፡፡ ከተፈጠረው የሥራ ዕድል ውስጥ በከተማና በገጠር የወጣቶችን ተጠቃሚነት 80% ለማድረስ ታቅዶ፣ ወንድ 548,065 ሴት 270,504 ድምር 818,569 ወጣቶች ተጠቃሚ የሆኑ ሲሆን አፈፃፀሙ ከተፈጠረው ሥራ ዕድል አንጻር **84.81%** ማድረስ ተችሏል፡፡ በከተማና በገጠር የሴቶችን ተጠቃሚነት **50%** ለማድረስ ታቅዶ፣ አጠቃላይ ከተፈጠረው ሥራ ዕድል **33.88%** ማድረስ ተችሏል፡፡ በከተማና በገጠር ለወንድ 508 ለሴት 316 ድምር ለ824 የአካል ጉዳተኛ ዜጎች የሥራ ዕድል ተፈጥሯል፡፡ በከተማና በገጠር ለወንድ 1,674 ለሴት 1,746 ድምር ለ3,420 ከስደት ተመላሽ ዜጎች የሥራ ዕድል ተፈጥሯል፡፡እንዲሁም በከተማና በገጠር ለ3,118 የቤት እመቤቶች የስራ ዕድል መፍጠር ተችሏል፡፡

## ለምሩቃን የተፈጠረ የሥራ ዕድል

በአጠቃላይ በበጀት አመቱ በስራ ፈላጊነት ከተመዘገቡ 39,091 ዩኒቨርስቲ ተመራቂዎች መካከል 26,489 የሥራ ዕድል ያገኙ ሲሆን አፈፃፀሙ 67.7% እንዲሁም የቴክኒክ ምሩቃን ከተመዘገበው 79,702 መካከል 64,580 የተከናወነ ሲሆን አፈፃፀሙ 81% የሥራ ዕድል መፍጠር ተችሏል፡፡ ጠቅላላ ከተመዘገቡት 118,793 ተመራቂዎች መካከል ለ91,029 ስራ ዕድል የተፈጠረ ሲሆን አፈፃፀሙም 76.6% ነው፡፡ ይሁን እንጅ በከተማ እና በገጠር መተግበር ካለበት ስራ እድል ፈጠራ አኳያ የተሻለ የስራ እድል መፈጠሩን ቢያመለክትም በኢንተርፕራይዝ ምስረታ ረገድ የተፈለገውን ውጤት ማምጣት አለመቻሉን አመልካች ሲሆን ከተፈጠረው የስራ እድል መካከል በጊዜያዊነት የተፈጠረው የስራ እድል ቀላል የማይባለውን ቁጥር የሚሸፍን መሆኑን ያሳያል፡፡ ለዚህም ችግር የሚጠቀሱት ምክንያቶች የተዘዋዋሪ ብድር መቆሙ፣የነበረው ጦርነት፣ የግብረ-ሀይሉ መምራት አለመቻል፣ የብድር ማስመለስ ስራው መፋዘዙ..ወዘተ ናቸው፡፡ በመሆኑም ካለው አንገብጋቢ የወቅቱ የስራ አጥነት ችግርና ከሚጠበቅብን ግብ አኳያ ሲታይ በከተማም ይሁን በገጠር እየተፈጠረ ያለው የስራ እድል የበለጠ መጠናከር እንዳለበት የሚያመለክት ሲሆን በተለይ የስራ ፈላጊዎችን ችግር በዘላቂነትና በወሳኝነት ከመፍታት አንጻር የታቀደውን ወደ ተግባር ለመለወጥና ከታለመው ግብ ለመድረስ አሁን የሚታየውን የአፈጻጸም ችግር ማሻሻል የሚያስችል አመራርን በመከተልና በቅርበት ክትትልና ድጋፍ በማድረግ በቀጣይ እቅድ ዘመን ትኩረት ተሰጥቶት የስራ እድል ፈጠራ ስራውን አሻሽሎ የዜጎችን የስራ እድል ፈጠራና ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ ልዩ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡

## ለኢንተርፕራይዞች የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ድጋፍ መስጠት

በ2014 ዓ.ም በዕድገት ተኮር ዘርፎች ክፍተትንና የእድገት ደረጃን መሠረት ያደረገ ለ22,055 (ከተማ 20,452, ገጠር 1,603) ነባርና አዲስ ኢንተርፕራይዞች (66,922 አንቀሳቃሾች) የተሟላ የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ ለ18,977 (በከተማ 16,778፣ በገጠር 2,199) ነባርና አዲስ ኢንተርፕራይዞች፣ ለ71,285 (ወንድ 47,846 ሴት 23,439) አንቀሳቃሾች የተሟላ የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት የተሰጠ ሲሆን አፈፃፀሙ በኢንተርፕራይዝ 86% በአንቀሳቃሽ ከ100% በላይ ተፈፅሟል፡፡




በኤሌክትሪክ ቻርጅ የሚሰራ ባጃጅ-ደብረ ብርሀን ከተማ አስተዳደር

## የኢንተርፕራይዞች የዕድገት ደረጃ ሽግግር

በ2014 ዓ.ም የእድገት ደረጃንና ክፍተትን መሠረት ያደረገ የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ድጋፍ በመስጠት በትኩረት ዘርፍ የተሰማሩ በሁሉም ደረጃዎች 10,566 (በከተማ 9,719 በገጠር 847) ኢንተርፕራይዞችን ከደረጃ ደረጃ ለማሸጋገር ታቅዶ 9,196 (በከተማ 8,706 በገጠር 490 ኢንተርፕራይዞችን ማሸጋገር ተችሏል፤ አፈፃፀሙም 87% ሆኗል፡፡

## የተቋማት የሰልጣኝ ቅበላና ስልጠና

የሰልጣኝ ቅበላ በግል መንግስታዊ ባልሆኑ ኮሌጆች በመደበኛው ስልጠና ነባር 18,455፣ አዲስ 15,996 በድምሩ 34,451 ሰልጣኞችን ተቀብሎ ለማሰልጠን ታቅዶ ነባር ወንድ 4,868 ሴት 10,421 በድምሩ 15,289 (82.84%) እና አዲስ ወንድ 3,729ሴት 9,474 ድምር 13,203 (82.5%) በጠቅላላው ወንድ 8,597 ሴት 19,895 ድምር 28,492 (82.7%) ሰልጣኞችን በመቀበል በማሰልጠን ላይ ይገኛሉ፡፡

## የአብክመ የመንግስት ኮሙዩኒኬሽን ቢሮ

## በገበያ ትስስሩ የተገኘ ገቢ

በማኒፋክቸሪንግ ዘርፍ በከተማ ብር 880,527,709 (22.2%) በገጠር ብር 40,824,030 (6.07%) በድምሩ ብር 921,351,739 (19.86%) በኮንስትራክሽ ዘርፍ በከተማ ብር 2,867,196,673(72.31%)በገጠር ብር 542,052,409(80.69%)በድምሩ ብር 3,409,249,082 (73.5% ) እንዲሁም በከተማ ግብርና ዘርፍ ብር 217,155,984 (5.47%) በገጠር ግብርና ዘርፍ ብር 88,852,265 (13.22%) በድምሩ ብር 306,008,249 (6.59%) ድርሻ አላቸው፡፡ በአጠቃላይ በከተማና በገጠር ብር 4,636,609,070 የገበያ ትስሰር መፍጠር ተችሏል፡፡

## የውጭ ሀገር ገበያ ትስስር

በበጀት ዓመቱ በኤክስፖርት ስታንዳርድ የማምረትና ወደ ውጭ ሀገር ኤክስፖርት ለማድረግ አቅምና ፍላጐት ያላቸውን 54 ነባር እና 30 አዲስ በድምሩ 84 ኢንተርፕራይዞችን (251 አንቀሳቃሾችን) 696,450 የአሜሪካን ዶላር የውጭ ሀገር የገበያ ትስስር ለመፍጠር ታቅዶ 69 ነባር አዲስ 15 በድምሩ 84 ኢንተርፕራይዞች (ወንድ 415 ሴት 120 በድምሩ 535 አንቀሳቃሾች) ከምርት ሽያጭ 1,562,507 የአሜሪካ ዶላር ገቢ ማግኘት ተችሏል፤ አፈፃጸሙ በኢንተርፕራይዝ፣ በአንቀሳቃሽ እና በብር ከ100% ተከናውኗል፡፡

## ቁጠባና ብድር ማመቻቸት

በ2014 ዓ.ም የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን ችግር ለመፍታት እንዲያመችና የቁጠባ ባህል እንዲጐለብት ለማድረግ ብር 2,604,731,206 ቁጠባ ለማሰባሰብ ታቅዶ ከ298,402 ቆጣቢዎች ብር 3,118,780,307 ከቁጠባ ማሰባሰብ የተቻለ ሲሆን አፈፃፀሙ በብር ከ100% በላይ ማከናወን ተችሏል።

## የብድር አቅርቦት

በበጀት አመቱ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን የፋይናንስ ችግር ለመፍታት በመደበኛ ብድር ብር 2,111,400,000 ለ28,152 ኢንተርፕራይዞች (ለ84,456 አንቀሳቃሾች)፣ በተዘዋዋሪ ብድር ብር 1,144,450,575 ለ7,775 ኢንተርፕራይዞች (ለ23,325 አንቀሳቃሾች) በድምሩ ብር 3,255,857,184፣ ለ35,927 ኢንተርፕራይዞች (107,781 አንቀሳቃሾች) ብድር ለመስጠት ታቅዶ መደበኛ ብድር ለ28,351 ኢንተርፕራይዞች እንዲሁም ለ65,600 አንቀሳቃሾች (ወንድ 37,150 ሴት 28,450) ብር 1,956,590,685 ተሰራጭቷል፡፡ አፈፃፀሙም በኢንተርፕራይዝ 100.7%፣ በአንቀሳቃሽ 77.67%፣ በብር 92.66% ተፈፅሟል፡፡ በተዘዋዋሪ ብድር ደግሞ ለ664 ኢንተርፕራይዞች እንዲሁም ለ973 አንቀሳቃሾች(ወንድ 695 ሴት 278) ብር 108,505,387

የተሰራጨ ሲሆን አፈፃፀሙ በኢንተርፕራይዝ 8.54%፣ በአንቀሳቃሽ 4.17% እና በብር 9.48% ሆኗል፡፡

በአጠቃላይ ለ29,015 ኢንተርፕራይዞች (ወንድ 37,845 ሴት 28,728 ድምር 66,573 አንቀሳቃሾች) ብር 2,065,096,072 የተሰጠ ሲሆን፣ አፈፃፀሙም በኢንተርፕራይዝ 80.76%፣ በአንቀሳቃሽ 61.76% በብር 63.42% ማከናወን ተችሏል።

## ብድር ማስመለስ

በ2014 ዓ.ም መደበኛ ብድር ከዋና 874,913,667 ከወለድ 113,446,112 ድምር 988,359,779፣ ከ18,010 ኢንተርፕራይዞች ወንድ 29,118 ሴት 21,631 ድምር 50,749 ተጠቃሚዎች ማስመለስ ተችሏል፡፡ የተዘዋዋሪ ብድር አመላለስ ምጣኔ 69% ነው፡፡

## የቦታ አቅርቦትን በተመለከተ

በ2014 ዓ.ም ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች 58,020,000 ካሬ ሜትር ቦታ ለ39,468 ኢንተርፕራይዞች (78,935 አንቀሳቃሾች) የመስሪያና መሸጫ ቦታ በማዘጋጀትና ጥቅም ላይ በማዋል ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ የተዘጋጀ መሬት ለሼድ ግንባታ 1,371,609 ካሬ ሜትር ለግብርና 175,597,582 ካሬ ሜትር ሌሎች (አሸዋ፣ ድንጋይ፣ የወንዝ ጠጠር፣ ወዘተ...) 21,517.219 ካሬ ሜትር በድምሩ 198,486,410 ካሬ ሜትር ቦታ የተዘጋጀ ሲሆን አፈጻጸሙ በቦታ ከ100% በላይ ነው፡፡ እንዲሁም 11,308 ኢንተርፕራይዞች (ወንድ 90,184 ሴት 34,431 በድምሩ 124,615 አንቀሳቃሾች በተዘጋጀው መሬት ተጠቃሚ ማድረግ የተቻለ ሲሆን አፈጻጸሙ በኢንተርፕራይዝ 28.7% እና በአንቀሳቃሽ ከ100% በላይ ተከናውኗል፡፡

ከተዘጋጀው ቦታ ውስጥ ሥራ ላይ የዋለው ለሼድ ግንባታ 564,822 ካሬ ሜትር (ከተዘጋጀው ቦታ አንጻር 41.17%)፣ ለግብርና 169,699,004 ካሬ ሜትር (ከተዘጋጀው ቦታ አንጻር 96.64%)፣ ሌሎች (አሸዋ፣ ድንጋይ፣ የወንዝ ጠጠር፣ ወዘተ) 13,229.346 ካሬ ሜትር (ከተዘጋጀው ቦታ አንጻር 61.48%) በድምሩ 183,493,172 ካሬ ሜትር (ከተዘጋጀው ቦታ አንጻር 92.44%) ይሸፍናል፡፡

በከተማና በገጠር 3,838 ሼዶችን በመገንባት 7,675 ኢንተርፕራይዞችን (15,351 አንቀሳቃሾችን) ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ 1,334 ሼዶች ተጠናቀው 1,476 ሼዶች ለ6,474 ኢንተርፕራይዞችና፣ 14,324 (ወንድ 8,281 ሴት 6,043 አንቀሳቃሾች) ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡ አፈጻጸሙ በተገነቡ ሼዶች 22.25%፣ በኢንተርፕራይዝ 84.35%፣ በአንቀሳቃሽ 57.97% ማከናወን ተችሏል፡፡

## የምዘና ተደራሽነትን ማስፋት

በ2014 ዓ.ም ከመካከለኛና ከፍተኛ ኢንዱስትሪ 27፣ ከጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች 139 በድምሩ 166 የምዘና ማዕከላትን አዲስ ዕውቅና ለመስጠት ታቅዶ ከመካከለኛ እና ከከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች 15(55.56%) እና ከጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች 51 (36.69%) በድምሩ ለ66(39.76%) የምዘና ማእከላት እወቅና ተሰጥቶአቸዋል፡፡ እንዲሁም ለ67 ነባር የምዘና ማእከላት በ274 ሙያወች ተጨማሪ ፈቃድ ተሰጥቶአቸዋል፡፡ የምዘና ማእከላት አዲስ ፈቃድም ሆነ የእድሳት ጥያቄ ሲያቀርቡ የተቀመጠውን መስፈርት ማሟላታቸው በአካል እየተረጋገጠ እንዲሰጥ ተደርጓል፡፡

## የኢንዱስትሪ መዛኞችን ማፍራት

በበጀት አመቱ ከመካከለኛ እና ከከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች 184፣ ከጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች 33 በድምሩ 217 የኢዱስትሪ መዛኞችን ለማፍራት ታቅዶ ከመካከለኛ እና ከከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች 277 አፈፃፀም 150.54%፤ከጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች 67 አፈፃፀም 203.03% በድምሩ 344 የኢንዱስትሪ መዛኞችን ማፍራት የተቻለ ሲሆን አፈፃፀሙም 158.53% ሆኗል፡፡

## መደበኛ ስልጠና ብቃት ማረጋገጥ

በበጀት አመቱ መደበኛ ስልጠና አጠናቃቂዎችን ብቃት በምዘና ለማረጋገጥ 69,796 ታቅዶ ለምዘና የተቀመጡ ወንድ **16,781** ሴት **28,657** ድምር **45,438** ሲሆኑ አፈፃፀሙም 65.1% ነው ፡፡ ከነዚህ መካከል ተመዝነው ብቁ የሆኑ ስልጠና አጠናቃቂወች ወንድ **8,413** ሴት**11,031** ድምር **19,444** አፈፃፀሙም 42.8% ነው፡፡

## የመደበኛ ሰልጣኞች ከደረጃ ደረጃ ሽግግር

በበጀት አመቱ በክልሉ ውስጥ ብቃታቸዉ በምዘና የተረጋገጠ መደበኛ የደረጃ ሽግግር ሰልጣኞችን በሚመለከት 112,173 ለማከናወን ታቅዶ፣ ለምዘና የተቀመጡ ወንድ **46,693** ሴት **89,238** ድምር **135,931** ሲሆኑ አፈፃፀሙም **121.2%** ነው፡፡ ከነዚህ መካከል ተመዝነው ብቁ የሆኑ ወንድ **27,048** ሴት **37,597** ድምር **64,645** ሲሆኑ አፈፃፀሙም **47.6%** ነው፡፡

### በብቃት ምዘና ወቅት የተወሰዱ እርምጃዎች

በመዛኝ፣ በተመዛኝ፣ በሶፐ ረዳት፣ በምዘና ማዕከላትና በሱፐርቫይዘሮች ላይ የሚስተዋሉ የኪራይ ሰብሳቢነት አመለካከቶችና ተግባር በተመለከተ ከምዘና መልስ በሁሉም ምዘና በተሰጠባቸው የምዘና ማዕከላትን መሠረት ተደርጎ በተደረገው የሱፐርቪዝን እና

የሱፐርቫይዘሮች ሪፖርትን መሠረት በማድረግ ከምዘና መልስ ምዘናውን በመገምገም ችግር በተስተዋለባቸው አካላት ላይ አስተዳደራዊ እርምጃ በመውሰድ በምዘና ስርዓቱ የሌብነት አስተሳሰብና ተግባር ላይ የሚስተዋሉ ችግሮችን ለመቀነስ ጥረት ተደርጓል፡፡ በዚህም መሠረት፤ ወንድ 135 ሴት91 ድምር 226 ተመዛኞች ከፁሁፍ ማስጠንቀቃያ እስከ ሙሉ በሙሉ ከምዘና እንዲታገዱ ተደርጓል፤ ወንድ 81 ሴት 11ድምር 92 መዛኞች ከጽሁፍ ማስጠንቀቂያ እስከ ሙሉ በሙሉ ከመዛኝነት እንዲሰረዙ ተደርጓል፣ ሱፐርቫይዘር ወንድ3 ሴት- ድምር 3 ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷል፤ ሾፕ ረዳት/ባለሙያ/ ወንድ 5 ሴት- ድምር 5 ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷል፤ 12 የምዘና ማዕከላት ላይ ከጹሁፍ ማስጠንቀቂያ እስከ የምዘና ማዕከል ፈቃድ ጊዚያዊ እገዳ ድረስ የእርምት እርምጃ ተወስዷል፡፡ መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር ትስስር በመፍጠር ከስርዓቱ ጋር ተያይዘው ያሉ የሌብነት ድርጊቶችን ከመታገል አንፃር ሁሉም ተቋም ከመስሪያቤቱ ዌብ ሳይት የሙያ ብቃት ማስረጃዎችን ከተጭበረበረው እንዲለዩ ሁኔታ የተመቻቸ ሲሆን በጥርጣሬ ወደ ተቋሙ እንዲጣሩ የቀረቡ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ማስረጃዎችን በማጣራት በተለያየ ጊዜ ለጠየቁ መንግስታዊ ተቋማትና መስሪያቤቶች ግብረመልስ ተሰጥቷል፡፡ በዚህም መሠረት በ12 ወራት ውስጥ 1382 ማስረጃዎች እንዲጣሩ ጥያቄ ቀርቦ 86(6.2%) ትክክለኛ ያልሆኑ የሐሰተኛ ማስረጃዎች ሆነው ተገኝተዋል፡፡ ከእነዚህም መካከል በግለሰቦች እጅ የቀረቡትን በህግ ተጠያቂ ለማድረግ እንዲቻል ክትትል እየተደረገ ይገኛል፡፡

## መስኖና ቆላማ አካባቢ ልማት

### ጥናትና ዲዛይን

በዘላቂ ልማት ግብ በጀት 710 ሄክታር ማልማት አቅም ያለው የበሰኒት አፈር ግድብ ከነበረበት 95% አፈጻጸም በመነሳት 95.25% ለማድረስ ታቅዶ አማካሪ ድርጅቱ አማራ ዲዛይንና ቁጥጥር ስራዎች ድርጅት በመሳሪያ እጥረት ሳይሰራ ከ2 ዓመት በላይ ያስቆጠረ ቢሆንም በዚህ በጀት ዓመት የውሃ ማሳለፍ ፍተሻ (ፓከር ቴስት) ስራ ተሰርቷል፡፡ በተመሳሳይ 5,587 ሄክታር የሚያለሙ የ16 ነባር ፕሮጀክቶች ጥናትና ዲዛይን ስራን ከ76.56% በመነሳት ለማጠናቀቅ ታቅዶ 96.56 በመቶ ማድረስ የተቻለ ሲሆን የ7 ፕሮጀክቶች ጥናትና ዲዛይን ስራ 100% ተጠናቋዋል፡፡ የ16 ነባር ፕሮጀክቶች አፈፃፀሙ መቀነስ ዋነኛው ምክንያት በርካታ ፕሮጀክቶች በምስራቅ አማራ የሚገኙ በመሆናቸውና የምስራቅ አማራ ዲዛይን እና ቁጥጥር ስራዎች ድርጅት ወራሪው የትግራይ ሀይል ባካሄደው ወረራ ምክንይት ቢሮው ተዘግቶ የነበረ በመሆኑና ስራን

ተረጋግቶ መስራት ባለመቻሉ የተፈጠረ ነው። የሰባት ፕሮጀክቶች (ጀደብ-5፣ መና-2፣ ጥራሬ -3፣ ተከዜ -2፣ ተላ፣ ጃራ እና ጉማራ ማርሚ) ዲዛይን ግምገማ እና ክለሳ ተከናውኗል።

በ2014 ዓ.ም የማልማት አቅማቸው 13,395 ሄክታር የሚጠጋ የ53 አዲስ መስኖ ልማት ፕሮጀክቶችን የጥናት እና ዲዛይን አፈፃፀም በአማካኝ 50 በመቶ ለማድረስ ታቅዶ 73% መፈጸም የተቻለ ሲሆን የ3 ፕሮጀክቶች (ጫን፣ ፋጣ እና ተጥማ-2) የጥናትና ዲዛይን ስራ 100% ማጠናቀቅ ተችሏል።ጉደር ፋግታ ጥናቱ የተጀመረና በውሃ እጥረት ችግር ምክንያት ጥናቱ የማይቀጥል ሲሆን በዋግ ህምራ ዞን ውስጥ የሚገኙ በጦርነት ምክንያት ጥናታቸው ተቋርጧል፡፡

በበጀት አመቱ በአነስተኛ መስኖ መሠረተ ልማት የማልማት አቅማቸው 10,754 ሄክታር የሆኑ 129 የመስኖ ልማት ፕሮጀክቶችን የጥናትና ዲዛይን ስራ በመስራት እንዲሁም ለ75 ፕሮጀክቶች የጥናት ሰነድ ሙሉነት ግምገማ በማድረግና በማጽደቅ ወደስራ ለማስገባት ታቅዶ 62 ፕሮጀክቶች በበጀት ተደግፈው ወደ ግንባታ ማስገባት ተችሏል፡፡

የሳላያት ሳይት ዲዛይን ስራ ተጠናቆ የጥናት ሰነድ ሙሉነት ግምገማ ብቻ የቀረ ሲሆን የበራ ሳይት የኢንጅነሪንግ ስራ ተጠናቆ የኤሌክትሪካል እና ጅኦሎጅካል ኢንቨስቲጌሽን ስራ ይቀረዋል፡፡ እንዲሁም በሰቆጣ ቃል ኪዳን ፕሮግራም ከፌደራል በተገኘ በጀት የአስር መስኖ ልማት ፕሮጀክቶችን የጥገና ጥናት እና ዲዛይን ለማከናወን በእቅድ የተያዘ ሲሆን ደቡብ ወሎ 5 ፕሮጀክቶች እና ሰሜን ወሎ 3 ፕሮጀክቶች በድምር 8 ፕሮጀክቶች የዲዛይን ማሻሻያው ተጠናቆ የጥገና ስራን እንዲሰሩ በጀት ተለቆ በመሰራት ላይ ይገኛሉ። ከዚህ በተጨማሪ በአዳፕቴሽን ፈንድ 17 ሄክታር ማልማት የሚችል የችህና የጥልቅ ጉድጓድ መስኖ ጥናት እና ዲዛይን ስራውን 100% ለማድረስ ታቅዶ በአሁኑ ስዓት ጥናቱ ተጠናቆ ወደ ግንባታ መግባት ተችሏል፡፡

## የመስኖ ልማት ፕሮጀክቶችን ሰርቶ ማጠናቀቅ

በ2013 በጀት ዓመት የአደሩ 99 ፕሮጀክቶች (በዘላቂ ልማት ግቦች የበጀት ድጋፍ 54፣ በግብርና ዕድገት ፕሮግራም 30፣ በሽዲፕ በጀት ድጋፍ 15) በአማካኝ ከነበሩበት 37.6% በመነሳት በ2014 በጀት ዓመት ለማጠናቀቅ ታቅዶ 81.32% ማድረስ የተቻለ ሲሆን በዘላቂ ልማት ግቦች 20፤ ሽዲፕ 9፤ ኤጅፒ 21 ድምር 50 ፕሮጀክቶችን ማጠናቀቅ ተችሏል፡፡ በሽዲፕ የበጀት ድጋፍ የሚከናወኑ 762.35 ሄክታር የሚያለሙ የአደሩ 15 ፕሮጀክቶች ከነበሩበት 49% በመነሳት ለማጠናቀቅ ታቅዶ 90% ማድረስ ተችሏል፡፡ በግብርና ዕድገት የበጀት ድጋፍ የሚከናወኑ 1884.67 ሄክታር የሚያለሙ 30 ፕሮጀክቶች ከነበሩበት 37.28% በመነሳት ለማጠናቀቅ ታቅዶ 89.66% ማድረስ ተችሏል፤ ሌላው በሰቆጣ ቃል ኪዳን ፕሮግራም የማልማት አቅማቸው 180

ሄክታር የሆኑ የሁለት (02) ነባር መስኖ ልማት ፕሮጀክትን (ላስታ ወረዳ ሳላይት ፕሮጀክት 70 ሄክታር እና ዳባት ወረዳ በራ ፕሮጀክት 110 ሄክታር) ከነበሩበት 40 በመቶ አፈፃፀም በመነሳት ለማጠናቀቅ  እቅድ የተያዘ ሲሆን በበጀት ዓመቱ 40 በመቶ በማከናወን አጠቃላይ አፈፃፀሙን 80 በመቶ ማድረስ ተችሏል።

በበጀት አመቱ በዘላቂ ልማት ግብ በጀት 5,499 ሄክታር ማልማት የሚችሉ 13 ፕሮጀክቶች ግንባታ ከደረሱበት 58.4 በመቶ አማካኝ አፈፃፀም በመነሳት 98 በመቶ ለማድረስ ታቅዶ 67.1% ማድረስ ተችሏል። 200 ሄክታር መልማት የሚችል አጓት ውሃ ሳይንት አፈር ግድብ ግንባታን በማጠናቀቅ ወደ ልማት ማስገባት የተቻለ ቢሆንም የግንባታ ግብዓት ዋጋ በከፍተኛ ሁኔታ መናር እና ከገበያ መጥፋት፣ የተቋራጭ አፈፃፀም ደካማ መሆን እና በተደጋጋሚ የሚያጋጥሙ የማህበራዊ ችግሮች ምክንያት የቀሪ  ፕሮጀክቶች አፈፃፀም (ሚሌ ኮትቻ፣ ግልገል አባይ፣ ጉማራ እና አበያ ማስፋፊያ)  እጅግ አነስተኛ ነው። ሚሌ ኮትቻ መስኖ ልማት ፕሮጀክት ከተጀመረ በርካታ ዓመታትን ያስቆጠረ ቢሆንም በተቋራጩ ችግር፤ የተወሰኑ የማህበረሰብ ክፍሎች የመግቢያ መንገድ በመከልከላቸው የግንባታ ስራው በከፍተኛ ሁኔታ እንዲጓተት ሆኗል።ይህን ችግር ለመፍታት ከዞን አስተዳደር እስከ ቀበሌ አመራር እና ህብረተሰብ ውይይት ተቋራጩን ኪሳራ ውስጥ ከመክተት ያለፈ መፍትሄ መስጠት አልተቻለም፡፡ ግልገል አባይ መስኖ ልማት ፕሮጀክት አባይ ወንዝ ላይ የተሰራው የውሃ መቀልበሻ የአባይን ወንዝ ውሃ ሲሞላ አቅጣጫ በማስቀየሱ ከፍተኛ የአርሶ አደር መሬት በውሃ እንዲጠለቀለቅ በማድረግ ጉዳት ደርሶብናል በማለት የሰሜን ሜጫ አርሶ አደሮች የአናት ስራው ማጠናቀቂያ ስራ እንዳይሰራ በመከልከላቸው የአናት ስራውን በማጠናቀቅ የተወሰነ የእርሻ መሬት ለማልማት የተያዘውን እቅድ እንዳይሳካ አድርጎት ቆይቷል።እንዲሁም 4,051.5 ሄክታር ማልማት የሚችሉ 18 ፕሮጀክቶች ግንባታ ከደረሱበት 24.8 በመቶ አማካኝ አፈፃፀም በመነሳት 62.02 በመቶ ለማድረስ 42.94% ብቻ ማድረስ ተችሏል። ለአፈፃፀሙ መቀነስ ምክንያቶች የግንባታ ግብዓት ዋጋ በከፍተኛ ሁኔታ መናርና ከገበያ መጥፋት፣ የተቋራጭ መፈጸም አቅም ችግር፣ የካሳ ግምት ክፍያ መዘግየት፣ የዲዛይንና ዋጋ ማሻሻያ ጥያቄ ምላሽ አለማግኘት እና የዞን መዋቅር አለመኖር የሚጠቀሱ ናቸው።

በበጀት አመቱ 2,969.32 ሄክታር ማልማት የሚችሉ 51 አዲስ አነስተኛ መስኖ ግንባታ ፕሮጀክቶች ግንባታ ለማጠናቀቅ ታቅዶ 30.52% ብቻ መፈጸም ተችሏል፡፡ ለአፈፃፀሙ ማነስ ዋናው ምክንያት አደረጃጀቱ በፍጥነት ዞን እና ወረዳ ባለመውረዱ፣ ከፌደራል የተገኘው ገንዘብ ዘግይቶ መለቀቁ፣ በወረዳ በኩል የጨረታ ሂደት ሰፊ ጊዜ መውሰድ እና በፑል አገልግሎቱ ምክንያት የክፍያ መዘግየት ዋና ዋና ምክንያቶች ናቸው። በዘላቂ ልማት ግብ በጀት 2760

ሄክታር ማልማት የሚችሉ ነባር 54 ፕሮጀክቶች ግንባታ ባለፈው ዓመት ከደረሰበት 26.5% በመነሳት ለማጠናቀቅ ታቅዶ የዕቅዱን 64.3% መፈጸም ተችሏል፡፡

ባለአነስተኛ ይዞታ ልማት ፕሮጀክት (ሽዲፕ) በጀት 762.4 ሄክታር ማልማት የሚችሉ 15 ፕሮጀክቶች ግንባታ ባለፈው ዓመት ከደረሰበት 49% በመነሳት ለማጠናቀቅ ታቅዶ 90% ማድረስ ተችሏል፡፡ በተጨማሪ በግብርና ዕድገት ፕሮግራም (ኤጂፒ) በጀት 1884.7 ሄክታር ማልማት የሚችል 30 ፕሮጀክቶች ግንባታ ባፈው በጀት ዓመት ከደረሰበት 37.3% በመነሳት ለማጠናቀቅ ታቅዶ የዕቅዱን 89.66% መፈጸም ተችሏል፡፡

በአጠቃላይ በበጀት ዓመቱ በተከናወኑ ተግባራት 50 አነስተኛ የመስኖ ፕሮጀክቶች የተጠናቀቁ ሲሆን በድምር 2882 ሄክታር መሬት ወደ ልማት ማስገባት ተችሏል፡፡

በግብርና እድገት ፕሮግራም (ኤጅፒ) በጀት ድጋፍ የግንባታ ስራቸው የሚከናወኑ ስራወችን ስናይ በተለያየ በጀት ዓመት የተጀመሩ 3,253.5 ሄክታር የሚያለሙ 22 ነባር የመስኖ ፕሮጀክቶች ግንባታ በ2013 ከደረሱበት 51.6 በመቶ አማካኝ አፈጻጸም በመነሳት በበጀት ዓመቱ ለማጠናቀቅ ታቅዶ 73.15% ማድረስ ተችሏል፡፡ የማልማት አቅማቸው 483 ሄክታር የሆኑ አምስት መስኖ ልማት ፕሮጀክቶች (አዳጊ ቦይ፣ ዝንግኒ ማፋፊያ፣ ዘያ፣ ብልቅ ውሃ እና ላህ ሽምበቂማ) ማጠናቀቅ የተቻለ ቢሆንም የቀሪ ፕሮጀክቶች ግምባታ የተጓተተ ሲሆን ለግንባታ መጓተት ምክንያቶች የግንባታ ዋጋ መናርና ከገበያ መጥፋት፣ የግንባታ ቦታዎች ከሶስተኛ ወገን ነጻ አለመሆንና የተቋራጭ የመፈጸም አቅም ችግር መኖር ናቸው፡፡ በተሳትፎአዊ አነስተኛ (ኢፋድ) መስኖ ልማት በጀት ድጋፍ ደግሞ በተለያየ በጀት ዓመት የተጀመሩ 1,703 ሄክታር የሚያለሙ 7 ነባር የመስኖ ፕሮጀክቶች ግንባታ በ2013 ከደረሱበት 56.35 በመቶ አማካይ አፈጻጸም በመነሳት በበጀት ዓመቱ ለማጠናቀቅ ታቅዶ 71.98 በመቶ ማድረስ ተችሏል።

በዚህ በጀት ዓመት ወደ ግንባታ መግባት እና ስራ መጀመር የተቻለው በአራት (ሆጣ፣ ጤና፣ ጨረቲ-2 እና ቦርከና ተረፎ) ፕሮጀክቶች ላይ ብቻ ሲሆን በተጠናቀቁ እና በግንባታ ላይ እያሉ ወደ ልማት በገቡ ፕሮጀክቶች 496.5 ሄክታር መሬት ወደ ልማት እንዲገባ ማድረግ ተችሏል። የአዟሪ-1ን የመጀመሪያ ርክክብ ከማድረግ በተጨማሪ የበርካታ መስኖ ልማት ፕሮጀክቶችን የመጨረሻ ጥገና በማከናወን ርክክብ ማድረግ ተችሏል። ርክክብ ከተደረገባቸው ፕሮጀክቶች መካከል ሰውር-3፡ አዋጆ፣ ጨለቃ፣ ሲደኒ፣ አዟሪ-2፣ ታችኛው አሚቱ፣ ማይስ-1 እና ማይስ-2 እና ጫሊ መስኖ ልማት ፕሮጀክቶች ይገኙበታል። አጠባ-1 እና አጠባ-2 መስኖ ልማት ፕሮጀክቶች አሁንም በጦርነት ቀጠና በተያዙ አካባቢዎች የሚገኙ ፕሮጀክቶች በመሆናቸው እስከ አሁን ድረስ ግንባታ መጀመር አልተቻለም። ወርቄ የመስኖ ልማት ፕሮጀክት በጸጥታ

ችግር ምክንያት የዘገየ ቢሆንም በአሁኑ ሰዓት ተቋራጩ ወደ ስራ ገብቶ ቀሪ ስራውን ለማጠናቀቅ ፈቃደኛ ባለመሆኑ ስራው ተቋርጦ ይገኛል።



በኢንተርፕራይዞች የተገነባ መስኖ ፕሮጀክት-ጓንጓ ወረዳ

## በፌደራል መንግስት በጀት ግንባታቸው የሚከናወኑ ከፍተኛ የመስኖ ፕሮጀክቶች

በክልላችን በፌደራል መንግስት በጀት ግንባታቸው የሚከናወኑ ከፍተኛ የመስኖ ፕሮጀክቶች (በመገጭ ግድብ ሊለማ የሚችለውን 10,980 ሄክታር) ሳይጨምር በአጠቃላይ 22,450 ሄክታር መሬት ሊያለሙ የሚችሉ 4 ፕሮጀክቶች ሲሆኑ ለአሰራር እንዲመች በ7 ውል ተከፍለዋል፡፡ እስካሁን ባለው መረጃ መሰረት ፕሮጀክቶችን ለማጠናቀቅ በአጠቃላይ 16.9 ቢሊዮን ብር በጀት እንደሚያስፈልግ ይገመታል፡፡አብዛኛወቹ ፕሮጀክቶች ተጀምረው ሳይጠናቀቁ ረዥም ጊዜ በመውሰዳቸው የክልሉ መንግስት እና ህዝብ ከፕሮጀክቶች ማግኘት ያለበትን ጥቅም ብቻ ማሳጣት ሳይሆን ህዝብ በመንግስት ላይ እምነት እንዳይኖረው በማድረግ ከፍተኛ የሆነ የመልካም አስተዳደር ጥያቄ ከመሆናቸውም በላይ የክልሉ መንግስት ከፌደራል መንግስት ማግኘት ያለበትን ጥቅም ጭምር ያሳጡ ፕሮጀክቶች ናቸው፡፡

በመሆኑም የመስኖ ፕሮጀክቶች ያሉበትን ሁኔታ መገምገም፣ ችግሮችን መለየት እና የመፍትሄ አቅጣጫወችን ለማስቀመጥ ከሚኒስቴር መስሪያቤቱ የበላይ ሀላፊዎች፣ ከክልሉ መንግስት የበላይ ሃላፊዎች፣ ተቋራጮችና አማካሪ ድርጅቶች ጋር በጋራ ተደጋጋሚ የመስክ ምልከታ (መገጭ እና ርብ ግድቦች፣ መገጭ ሰራባ መስኖ፣ ላይኛው እና ታችኛው ርብ፣ አጅማ

ጫጫ፤ቆጋ እና ጣና በለስ ፕሮጀክቶች) እና የባለድርሻ አካላት ውይይቶችን በማድረግ አፈፃፀማቸውን በመገምገም ችግሮችን ለመፍታት ጥረት ተደርጓል፡፡

### የስራ ዕድል መፍጠር

በበጀት አመቱ በመስኖና ቆላማ አካባቢዎች ልማት ለወንድ-249 ለሴት-14 ድ-263 ቋሚ፣ ለወንድ-4,551 ለሴት-3,785 ድ-8,336 ጊዜያዊ እንዲሁም ለወንድ-711 ለሴት-122 ድ-833 ኢንተርፕራይዞች የስራ ዕድል መፍጠር ችሏል፡፡

## ህዳሴ ግድብ

### የሕዝብ ግንኙነት ሥራዎች

በግድቡ ዙሪያ የተጀመረውን መነሣሣት በሕዝብ ሞቢላይዜሽን በማጀብና ውጤት ላይ በማተኮር በየደረጃው የሚገኙ የኅብረተሰብ ክፍሎች ለሥራው መሳለጥ የበኩላቸውን ሚና እንዲወጡ ተደርጓል፡፡ በዚህም መሠረት የግድቡን የስራ፤ ደረጃና ወቅታዊ ሁኔታዎች ላይ ያተኩሩ መረጃዎች ከተለያዩ ሀገር ውሰጥ ሚዲያዎች በህትመትና በኤሌክትሮኒክስ የተላለፉትን ዘገባዎች በጽ/ቤቱ ፌስ ቡክ አድራሻ በመልቀቅ ለህዝብ መረጃ የማቅርብ ስራ ተሰርቷል፡፡

ለተለያዩ ለሀገር ውስጥ እና ለውጭ ሀገር ብዙኀን መገናኛዎች የተለያዩ መረጃዎችን በመስጠት ለኅብረተሰቡ መረጃዎችን ተደራሽ የማድረግ ስራ ተሠርቷል፡፡ በተለይም የአማራ ብዙኃን መገናኛ ድርጅት በአማራ ቲቪ በቀጥታ ስረጭት ሙያው የሚመለከታቸውን በመጋበዝ በዓለም አቀፍ የውሀ ህጎች በውሀ ፖለቲካ ዙሪያ የተለያዩ የውይይት መድርኮችን በተከታታይ በማዘጋጅት መረጃ ለህዝቡ ማድርስ ተችሏል፡፡ በተመሳሳይ በአማራ ብዙሀን መገናኛ ድርጅት (በክልሉ በሚገኙ በተለያዩ ሚዲ ኤሞች፣ በቴሌቪዥን ጣቢያ፣ በጋዜጣ) የተለያዩ መረጃዎችን ተደራሽ ማድረግ ተችሏል፡፡

### የጉብኝት ፕሮግራሞችን ማመቻቸት

ግድቡን ከቦታው በአካል ሄዶ ማየት የሚፈጥረው መነሣሣትና ለቀጣይ ድጋፍና ተሳትፎ የሚያበረከተው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው፡፡ ስለሆነም ይህን ተግባር አጠናክሮ ለመቀጠል በዕቅድ ተይዞ በየደረጃው ኅብረተሰቡ ግድቡ የደረሰበትን ደረጃ በአካል እንዲያይ የተጠናከረ የቅስቀሳ ሥራ ተሰርቷል፡፡ በመሆኑም በበጀት ዓመቱ እስከ ሚያዚያ ወር 2014 ዓ.ም ወንድ 51,651፣ ሴት 2,799፣ ድምር 54,450 ሰዎች ታላቁን የህዳሴ ግድብ በአካል ሄደው ጉብኝተዋል፡፡

### ሀብት ማሰባሰብ

ታላቁ የህዳሴ ግድብ በሕዝብና በመንግሥት የፋይናንስ አቅም ግንባታው ከተጀመረ አስራ

አንደኛ ዓመቱን ይዟል፡፡ በእነዚህ ዓመታት ግድቡ ከመሰረተ ግንባታው ጀምሮ አሁን እስካለበት ደረጃ እስኪደርስ ድረስ ሀብትን በማሰባሰብ በኩል ጥሩ ስራ ተሰርቷል፡፡ በእነዚህ ዓመታት የመንግስት ሰራተኛው እና መንግስታዊ ያልሆኑ መሰሪያቤቶች ስራተኞች፤ የንግዱ ህብረተሰብ፤አርሶ አደሩ፤ ባለሀብቱ፤ የተለያዩ ተቋማት ወዘተ...የመሳሰሉት የበኩላቸውን ድጋፍ በማድረግ ተሳትፈዋል፡፡ከፊሎች የድጋፍ መዋጮውን ያላቋረጡ የመንግሥት ሠራተኞች እንዳሉም ከተለያዩ አካላት የሚደርሱን መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡

## በቦንድ ግዥ እና በልገሳ የተሰበሰበ ገንዘብ

| ተ.ቁ | የገንዘብ ምንጭ | የተሰበሰበ ገንዘብ በብር |
|---|---|---|
| 1 | ከመንግሥት ሠራተኞች | 212,575.92 |
| 2 | ከባለሀብቱና ከንግዱ ኅብረተሰብ | 191,500.00 |
| 3 | ከተቋማት፣ ከድርጅቶች ከመያድ እና ከልዩ ልዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች | 1,641,063.89 |
| 4 | በልገሳ ከተለያዩ የኅብረተስብ ክፍሎች የተሰጠ- | 10,157.20 |
| | ድምር | 2,055,297.01 |



የህዳሴ ግድብ 3ኛ የውሀ ሙሌት-ጉባ

### የአብክመ የመንግስት ኮሙዩኒኬሽን ቢሮ

## የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ሥራ

በበጀት ዓመቱ እስከ ሰኔ ወር 2014 ዓ.ም ድረስ የህዳሴ ግድቡን ዓላማ መሠረት ባደረገ መልኩ በተለያዩ ቦታዎች ላይ 344,812 ሔክታር መሬት ላይ 1.41 ቢሊዮን ችግኝ ተተክሏል፡፡ የህዝቡ ተሳትፎ የጉልበት አስተዋጽኦ በገንዘብ ሲተመን ብር 2,981,938,144.00 የሚገመት ሥራ ማከናወን ተችሏል፡፡ አጠቃላይ የህዳሴ ግድብ የስራ እንቅስቃሴ በገንዘብ ሲተመን የቦንድ ግዥና ልገሳ ብር 2,055,297.01 እንዲሁም የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ሥራ ብር 2,981,938,144.00 ጠቅላላ ድምር ብር 2,983,993,441.01 ደርሷል፡፡

# ፕላንና ልማት

## እቅድና ልማት

በ2014 ዓ.ም በዕቅድ ተይዘው ሲሰሩ ከነበሩ ሥራዎች መካከል የ2014 በጀት ዓመት የልማትና የመልካም አስተዳደር ዕቅድ የማጠናቀቅ ሥራ ሲሆን የ2014 በጀት ዓመት የልማትና የመልካም አስተዳደር የሴክተሮች ዕቅድ በወቅቱ ታቅዶ ወደ ስራ ተገብቷል፡፡ በተመሳሳይ ሁሉም ዞኖችና ወረዳዎች የየራሳቸውን የአስር ዓመትና ዓመታዊ ዕቅድ እንዲያዘጋጁ ክትትልና ድጋፍ ለማድረግ በእቅድ ተይዞ ክትትልና ድጋፍ ተደርጓል፡፡

በዩኒሴፍ የገንዘብና የቴክኒክ ድጋፍ በ2014 ዓም የሕዝብ ፋይናንስ ለልጆች (Public finance for children) በተሰኘ ፕሮግራም ህጻናት ተኮር በሆኑ ሴክተሮች አጭር የበጀት መግለጫ ሰነድ ማዘጋጀትና ማሳተም፤ የህጻናትን ጉዳይ ተቋማት ትኩረት ሰጥተው እንዲሰሩ ለማስቻል የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ በ2014 ዓ.ም በተመረጡ ህጻናት ተኮር የሆኑ የክልል ሴክተር መስሪያ ቤቶች ህጻናትን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ የበጀት አመዳደባቸው ምን እንደሚመስል ያለፉ አመታትን መረጃ በመተንተን ከውጤቱ በመነሳት ለበጀት መዳቢ፤ ስራ አስፈጻሚ እና ፖሊሲ አውጭዎች የህጻናትን ጉዳይ ትኩረት እንዲያገኝ ለማስቻል ስራ ተሰርቷል፡፡ በመሆኑም የሶስት ሴክተሮች ማለትም የትምህርት፣ ጤና እና ውሃና ኢነርጅ ቢሮዎች ከ2000 ዓ.ም እስከ 2011 ዓ/ም ድረስ ያለውን መረጃ በእንግሊዘኛ ቋንቋ ተተንትኖ በ2013 ዓ.ም የተዘጋጀውን በ2014 ዓ.ም ወደ አማርኛ ቋንቋ የመተርጎም ስራ የተከናወነ ሲሆን የትርጉም ሰነዱም ለዩኒሴፍ ተልኮ ለሚፈለገው አላማ ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ እንዲሁም የህጻናትን መብት ከለላና ጥበቃ ከሚሰሩ ተቋማት ጋር ሰላምና ደህንነት፣ ፍትህ ቢሮ እና ጠቅላይ ፍርድ ቤት እንዲሁም ከወሳኝ ኩነት ኤጀንሲ ጋር በመተባበር አጭር የበጀት መግለጫ ተዘጋጅቷል፡፡

**የአብክመ የመንግስት ኮሙዩኒኬሽን ቢሮ**

በ2014 ዓ.ም የቀጣይ አስር ዓመት መሪ የልማት ዕቅድን መከለስ አንዱ ትኩረት የተሰጠው ጉዳይ ነው፡፡በመሆኑም ባለፉት ሁለት ዓመታት የነበረውን ሁኔታ በመገምገምና አሁን ያለውን ነባራዊ ሁኔታ ያገናዘበ እንዲሆን ለማድረግ ለመስሪያቤቶች ደብዳቤ ተጽፎና ኦሬንቴሽን ተሰጥቶ ወደ ሥራ ተገብቷል፡፡ በተመሳሳይ የ2015 በጀት ዓመት የልማትና መልካም አስተዳደር ዕቅድ ማዘጋጀት የበጀት ዓመቱ አንዱ ተግባር ነው፡፡ በመሆኑም ዕቅድ የማዘጋጀት ሥራውን ማጠናቀቅ ተችሏል፡፡

## የክልል ማክሮ ኢኮኖሚ

የ2013 በጀት ዓመት የክልሉን ጥቅል ምርት ለመገመት በዞንና በወረዳ ደረጃ መረጃዎችን ለሚሰበስቡ ባለሙያዎች ስልጠና ለመስጠት የሚያስችል የስልጠና ሠነድና የመረጃ መሰብሰቢያ ፎርማቶችን የማዘጋጀትና ነባሮችን የመከለስ ስራ ተሰርቷል፡፡ በዞንና በወረዳ ደረጃ መረጃ ለሚሰበስቡ ባለሙያዎች (በ6 ዞኖች የሚገኙ ወረዳዎች እና በ2 ከተማ አስተዳደሮች) ወንድ 81 ሴት 30 በድምሩ ለ111 ባለሙያዎች ስልጠና ተሰጥቶ ወደ ስራ ተገብቷል፡፡ በመሆኑም የ2013 በጀት ዓመት ጥቅል ምርት ለመገመት የሚያስችል መረጃ በክልል ባለሙያዎች አማካኝነት በባህርዳር ከተማና በአዲስ አበባ ከተሞች ተሰብስቦ ወደ ኮምፒዩተር በማስገባት የመረጃ ማጥራትና የመረጃ ማደራጀት ሥራ ተሠርቷል፡፡ ክልላዊ ጥቅል ምርት ግመታ ሂደት በእቅዱ መሰረት 100% ማከናወን ተችሏል፡፡

ተሰብስቦ በተተነተነው መረጃ መሰረት የ2013 በጀት ዓመት የክልሉ ጥቅል ምርት የ3.8% እድገት የተመዘገበ ሲሆን ከባለፈው በጀት ዓመት (2012) ከነበረው የ3.6% እድገት የ0.2% ብቻ ጭማሪ አሳይቷል፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት የማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ መረጃ እንደሚያሳየው ከ50% በላይ የክልሉ ኢኮኖሚ ድርሻ ያለው የግብርናው ሴክተር በተለይ የመኸር ወቅት ዋና ዋና የሚባሉት የሰብል ምርቶች ጤፍ፣ ገብስ፣ ማሽላ እንዲሁም ከጥራጥሬ እህሎች አተር፣ ሽምብራ፣ ምስር፣ ጓያ የመሳሰሉት የምርት ዓይነቶች እሴት ጭማሪ ከዓመት ወደ ዓመት እየቀነሰ መምጣት፤ የምርትና የአገልግሎት ዋጋ ጭማሪ ያስከተለው ተፅዕኖ እንዲሁም ከኢንዱስትሪው ዘርፍ ትልቅ ድርሻ የነበረው የኮንስትራክሽን ዘርፉ ከ0% በታች እድገት ማስመዝገቡ በዋናነት የሚጠቀሱ ምክንያቶች ናቸው፡፡

## የስታትሰቲክስ፣ ሶሽዩኢኮኖሚ፣ ኢንፎርሜሽን እና ጅ. አይ .ኤስ

በክልላችን አንድ መረጃ ቋት ለመመስረት በታቀደው መሰረት በ2012 ዓ.ም ከ2005 እስከ 2009 ዓም ድረስ በተመረጡ አመልካቾች የ42 ተቋማት መረጃ ቋት ተመርቆ አገልግሎት እንዲሰጥ ተደርጓል፡፡ ዳታ ቤዙን በመረጃ ለማበልፅግ በ2014ዓ.ም የሶስት ዓመት መረጃ በመሰብሰብ የ23 ተቋማትን መረጃ ወደ ዳታ ቤዙ ለማሰገባት ታቅዶ የተወሰኑ ተቋማትን መረጃ ማስገባት

የተቻለ ሲሆን ሁሉንም ተቋማት መረጃ ለማስገባት እንዲቻል በአዲሱ የመስሪያቤቶች አደረጃጀት መሠረት ሶፍት ዌሩን የማስተካከል ስራ ተሰርቷል፡፡ በተጨማሪም አስተዳደራዊ ለውጥ በተደረገባቸው በክልሉ የሚገኙ ከተሞችን አስተዳደራዊ ወሰን የ13 የከተማ አስተዳደሮችን የአስተዳደራዊ ወሰን ባቀረቡት መረጃ መሰረት የመረጃውን ትክክለኝነት በማረጋገጥ የአስተዳደራዊ ወሰን ተሰርቷል፡፡

ለክልሉ የበጀት ቀመር የሚያስፈልጉ የመልካ ምድራዊ መረጃዎችን የየወረዳው የቆዳ ስፋት፤ወረዳው ከክልሉ መቀመጫና ከዞኑ መቀመጫ ከተሞች ያለውን ርቀት እንዲሁም 210 የከተማና ገጠር ቀበሌዎች ለመስራት ታቅዶ ክንውን 210 አፈፃፀም 100% ሆኗል፡፡

በክልል የሚገኙ ሴክተሮችን፤ ዞኖችና ወረዳዎች መረጃ በማሰባሰብና ወደ ዳታ ቤዙ በማስገባት የክልሉን ዳታ ቤዝ ወቅታዊ እንዲሆን ለማድረግ ታቅዶ የክልሉን ክትትልና ግምገማ ለማገዝ የሚያስችል ዳታ ቤዝ ለማልማት በፌደራል ፕላንና ልማት ሚኒስቴር የለማውን ተናባቢ የሆነና ክልላዊ ሶፍትዌር ስራ ማጠናቀቅ ተችሏል፡፡

## ስነ-ህዝብ እና ልማት

በእድሜ ክፍፍል እና በነጠላ እድሜ የክልሉን የህዝብ ቁጥር በመተንበይ በተለያዩ ዘዴዎች ለተጠቃሚዎች ተደራሽ እንዲሆን ማድረግ፤ በክልል ደረጃ የ2015 ዓ.ም የክልሉን ህዝብ ብዛት መረጃ በወረዳ ደረጃ በ5 ዓመት የእድሜ ክፍፍል እና በነጠላ እድሜ የመተንበይ ስራ በመስራት መረጃው ለዞኖች፤ለገንዘብ ቢሮ ለበጀት ቀመር ድልድል፤ጥያቄ ላቀረቡ የክልል ተቋማት የተሰጣቸው ሲሆን በቀጣይ ለሁሉም ተቋማት የሚሰራጭ ይሆናል፡፡

የ2014 ዓ.ም የክልሉን ህዝብ ብዛት መረጃ በወረዳ/በከተማ ደረጃ ሽግግር ያደረጉ 33 ከተሞች ጨምሮ በነጠላ እድሜ እና በ5 ዓመት የእድሜ ክፍፍል በመተንበይ ለክልል ሴክተር መስሪያቤቶች እና ለሁሉም ዞንና ከተማ አስተዳደሮች መረጃው እንዲደርስ ተደርጓል፡፡በዓመቱ መጀመሪያ ለከተማና መሰረተ ልማት ቢሮ በ2013 ዓ.ም የደረጃ ሽግግር የጠየቁ 91 ከተሞችን በዞኖች በኩል መረጃ እንዲያሟሉ በማድረግ ወቅታዊ የሆነ የከተሞችን የህዝብ ብዛት መረጃ በቢሮ ደረጃ በማደራጀት መረጃውን መስጠት ተችሏል፡፡

ለ2014 ዓ.ም ለደረጃ ሽግግር የ203 ከተሞችን ህዝብ መረጃ በመተንበይ እና የደረጃ ሽግግር የጠየቁ 91 ከተሞችን መረጃ በማደራጀት ለከተማና መሰረተ ልማት ቢሮ የተላከ ሲሆን የአዲስ ከተሞችን እና አስተዳደራዊ ለውጥ ያላቸውን ከ31 በላይ ከተሞችን የህዝብ ብዛት መረጃ በመስከና በዴስክ ወቅታዊ የማድረግ ስራ በመስራትና በማደራጀት ለከተማና መሰረተ ልማት ቢሮ መላክ ተችሏል፡፡

**የአብከመ የመንግስት ኮሙዩኒኬሽን ቢሮ**

## የልማት ፕሮጀክቶች ፕላን

የክልል ባለበጀት መስሪያቤቶች በፎርማቱ መሰረት አዘጋጅተው የላኩት የ2014 በጀት ዓመት የካፒታል ፕሮጀክት ዕቅድ ክልላዊ የማድረግ ስራ ተሰርቷል፡፡በተመሳሳይ የካፒታል ፕሮጀክት ዕቅድ በክልል ደረጃ ወጥ ለማድረግ የዕቅድ ፎርማት በማዘጋጀትና የባለበጀት መስሪያቤቶች ቢሮ ኃላፊዎች፤ም/ቢሮ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች እንዲገመገምና እንዲዳብር በማድረግ አብዛኞቹ መስሪያቤቶች በፎርማቱ መሰረት ዕቅዳቸውን እያዘጋጁ የላኩ ሲሆን በቢሮዎች የሚቀርቡ የፕሮጀክት ዕቅዶችን በመለየት ቅደም ተከተል ለማስያዝ የሚያገለግሉ መስፈርቶችን በማዘጋጀት ስራ ላይ እንዲውል ማድረግ ተችሏል፡፡

ሴክተር መስሪያ ቤቶች የፕሮጀክት ዕቅድ ፕሮፖዛል በወቅቱ እንዲያቀርቡ በማድረግ ትኩረት የተሰጣቸው የልማት ፕሮጀክቶች በእቅዱ እንዲካተቱ፤ አዘጋጅተው እንዲልኩና የክልል ባለበጀት መስሪያቤቶች የ2014 በጀት ዓመት የካፒታል ፕሮጀክት ዕቅድ ክልላዊ ሆኖ እንዲዘጋጅ በማድረግ ለሚመለከተው አካል ተልኳል፡፡

በመንግስት መስሪያ ቤቶች እና የልማት ድርጅቶች ውስጥ ወጥ የሆነ የልማት ፕሮጀክቶች ዕቅድ አዘገጃጀት ስርዓት እንዲዘረጋ ለማድረግ በተያዘው ዕቅድ መሰረት የአዲስና ነባር የካፒታል ፕሮጀክት ዕቅድ ወጥ ለማድረ የዕቅድ ፎርማት በማዘጋጀት በመስሪያቤቶች የሚቀርቡ አዲስና ነባር የካፒታል የፕሮጀክት ዕቅዶችን በመለየት ቅደም ተከተል ለማስያዝ የሚያስችል መስፈርቶችን በማዘጋጀት ፕሮጀክቶች በክልላዊ ዕቅድ ውስጥ እንዲካተቱ የማድረግ ስራ ተሰርቷል፡፡

ፈጣን የኢኮኖሚና ማህበራዊ ልማት ዕድገት ለማምጣት የሚረዱ ፕሮጀክቶችን ለማመንጨት፣ ለማጥናት፣ ለመተግበርና ለመገምገም የሚረዱ የፖሊሲ/ስትራቴጂ /ሃሳቦችን ማመንጨት፤ በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ መስሪያቤቶች የተሻሉ የፕሮጀክት ሃሳቦች እንዲያፈልቁ በማድረግ እና በአግባቡ ተጠንተው ውጤታማነታቸው ሲረጋገጥ በፎርማቱ መሰረት ተዘጋጅተው እንዲቀርቡ ተደርጓል፡፡

## የልማት ፕሮጀክት አፈፃፀም ክትትልና ግምገማ

የፕሮጀክት አፈፃፀም መረጃዎችን ማሰባሰብ በእቅድ የተያዘ ተግባር ሲሆን በ2014 ዓ.ም ከፕሮጀክት ባለቤት መስሪያ ቤቶች ጋር በደብዳቤ፤ በስልክና በአካል በመነጋገር የፕሮጀክት አፈጻጸም መረጃ ለመሰብሰብ ተችሏል፡፡ በመሆኑም መስሪያ ቤቶች ከላኩት ሪፖርት በመነሳት በመስክ ሊታዩና ሊደገፍ የሚገባቸውን ፕሮጀክቶች መለየት ተችሏል፡፡ በዚህም የበጀት ዓመቱን 9ኛ ወር ሪፖርት መሰረት በማድረግ በክልሉ 1,357 የሚሆኑ ፕሮጀክቶች እየተከናወኑ የሚገኙ ሲሆን ከእነዚህ ውስጥ 89.7 በመቶ ወደ ኋላ የቀሩ መሆናቸውን ለመረዳት ተችሏል፡፡

አብዛኛው ፕሮጀክቶች እንደተጓተቱ የሚያመላክት ቢሆንም ጥቅል አፈጻጸማቸውን ስንመለከት በ3ኛው ሩብ ዓመት ሪፖርት መሰረት የተሻለ አፈጻጸም ያላቸው ፕሮጀክቶች 23.4 በመቶ፣ መካከለኛ አፈጻጸም ያላቸው ፕሮጀክቶች 14.2 በመቶ፣ ዝቅተኛ አፈጻጸም ያላቸው ፕሮጀክቶች 22.8 በመቶ እና አፈጻጸማቸው የማይታወቅ ደግሞ 39.7 በመቶ መሆናቸውን ለማወቅ ተችሏል፡፡

# III ማህበራዊ ዘርፍ

## ትምህርት እና ስልጠና

### የትምህርት ቅድመ ዝግጅትና ትግበራ

በ2014 ዓ.ም ትምህርት የአንድ ዓመት እቅድ አፈፃፀም ከቅድመ ዝግጅት ተግባራት በተጨማሪ በርካታ ግብአትን የማሟላትና መሰረተ ልማት የማስፋፋት የእቅድ ዝግጅት እና ትውውቅ፤ፈጻሚን የማዘጋጀት ስራዎች ተሰርተዋል፡፡በመሆኑም ትምህርት ቤቶች በግብአት፣ በሂደት እና በውጤት የተመዘገበ መሻሻል እንዲያሳዩና ደረጃቸው ከፍ እንዲል ግቦች ተቀምጠው እንቅስቃሴ ተደርጓል፡፡

የትምህርት ስራ ውጤታማ ሊሆን የሚችለው በአመለካከት በእውቀትና በክህሎት ብቃት ያላቸው የትምህርት ቤት አመራሮችንና መምህራንን ማሟላት ሲቻል ነው፡፡ በዝግጅት ምዕራፍ ትኩረት ከተሰጣቸው ተግባራት መካከል የትምህርት ተቋማት ብቃት ባላቸው አመራሮች እንዲመሩ ማድረግ፤ እንዲሁም በየደረጃው የሚያስፈልገውን መምህርና ባለሙያዎችን የማሟላት ስራ ተሰርቷል፡፡

በአመቱ መጀመሪያ የጉድኝት ሱፐርቫይዘሮችን የማሟላት ተግባር አፈጻጸም በአንደኛና መካከከለኛ ደረጃ 2,224 የጉድኝት ማዕከላት የሚገኙ ሲሆን 2,125 (ወንድ 2,072፣ ሴት 52) ነባር እና አዲስ ሱፐርቫይዘሮችን በማሰማራት 95.5% የተሟላ እንዲሆን ማድረግ ተችሏል፡፡ በተመሳሳይ በሁለተኛ ደረጃ 231 የጉድኝት ማዕከላት የሚገኙ ሲሆን 205 (ወንድ 201፣ ሴት 4) ነባር እና አዲስ ሱፐርቫይዘሮችን በማሰማራት 88.7% ማሟላት ተችሏል፡፡

ርዕሰ መምህራንን ለሚሟላት በተሰራው ስራ ለ497 አፀደ ህፃናት 377 (ወንድ 166፣ ሴት 211) ርዕሰ መምህራን ወይም 75.9%፤ ለ3,335 የአንደኛ ደረጃ (1ኛ - 6ኛ ክፍል) ትምህርት ቤቶች 3,253 (ወንድ 3,018፣ ሴት 235) ወይም 97.5%፣ ለ5,859 የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ (1ኛ - 8ኛ ክፍል) ትምህርት ቤቶች 5,595 (ወንድ 5,317፣ ሴት 278) ወይም 95.5% እና ለ641 ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች 611 (ወንድ 600፣ ሴት 11) ወይም 95.3% ርዕሰ መምህራንን ማሰማራት ተችሏል፡፡

በተመሳሳይ በመምህራን ትምህርት ኮሌጆች በነባር እና አዳዲስ ስምሪት አመራሮችን ለማሟላት በተደረገው እንቅስቃሴ 25 (ወንድ 24፣ ሴት 1) ወይም 83.3% ዲኖች እና ምክትል ዲኖች አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛሉ፡፡ በኮሌጆች በሚገኙ በጥቅሉ 61 ዲፓርትመንቶችን 61 (ወንድ 57፣ ሴት 4) ተጠሪዎች በማገልገል ላይ የሚገኙ በመሆኑ 100.0% ዲፓርትመንቶች ተጠሪ እንዲኖራቸው ማድረግ ተችሏል፡፡

## የመምህራን ስምሪት

በነባር ስምሪት እና በቅጥር ለቅድመ አንደኛ ደረጃ በአጸደ ህፃናት 2,738 (ወንድ 187፣ ሴት 2,551) እና በ "ኦ ክፍል" 9,197 (ወንድ 1,263 ፣ ሴት 7,934)፣ ለአንደኛና መካከለኛ ደረጃ 143,835 (ወንድ 76,560፣ ሴት 67,275) እንዲሁም ለሁለተኛ ደረጃ 45,325 (ወንድ 33,504፣ ሴት 11,821) መምህራን በማስተማር ላይ ናቸው፡፡ከኦ ክፍል ቅድመ አንደኛ ደረጃ በስተቀር በሌሎች ክልላዊ ጥቅል የመምህራን ብዛት በታቀደው መሰረት የተሟላ መሆኑን የተሰበሰበው መረጃ ያሳያል፡፡ ይህ ሲባል በአጠቃላይ ያለውን የመምህራንን ቁጥር ሲሆን በእነዚህ ደረጃዎችም የመምህራን እጥረት በየ ትምህርት አይነቱ ሲተነተን እጥረቶች ተስተውለዋል፡፡ በተመሳሳይ በብዙ ትምህርት ቤቶች የሚታይ እጥረት እንዳልተቀረፈ በተደረጉ ውይይቶችና በመስክ ምልከታዎች ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ የመምህራን እጥረት ካልተቀረፈ የትምህርት ጥራትን ማረጋገጥ ስለማይቻል እጥረቱን ለመፍታት ጥረት ተደርጓል፡፡ በመሆኑም ይህን እጥረት ለመቅረፍም በተደረገው እንቅስቃሴ በአጸደ ህፃናት 325 (ወንድ 9፣ ሴት 316)፣ በኦ ክፍል ቅድመ አንደኛ ደረጃ 2,515 (ወንድ 436፣ ሴት 2,079)፣ በአንደኛና መካከለኛ ደረጃ 4,392 (ወንድ 2,934፣ ሴት 1,458) እና በሁለተኛ ደረጃ 909 (ወንድ 643፣ ሴት 266) መምህራንን በአዲስ መቅጠር ተችሏል፡፡ በድምሩ በሁሉም ደረጃ ቅጥር የተፈፀመላቸው አዲስ መምህራን 6,536 (ወንድ 3,667፣ ሴት 2,869) መሆኑን መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ በተመሳሳይ የመምህራን ትምህርት ኮሌጆች አሰልጣኝ መምህራንን እና ቴክኒካል ረዳቶችን ለማሟላት እንቅስቃሴ የተደረገ ሲሆን የተጓደሉ አመራሮችን የመተካት ስራ ተሰርቷል፡፡

የዞን/ከተማ/ ትምህርት መምሪያዎችን እና የወረዳ ባለሙያዎችን ስምሪት በስርዓተ ትምህርት ዝግጅትና ትግበራ 1,173 (ወንድ 790፣ ሴት 383)፣ በመምህራን እና ትምህርት አመራሮች ልማት 964 (ወንድ 576፣ ሴት 388)፣ በአጠቃላይ ትምህርት ኢንስፔክሽን 886 (ወንድ 630፣ ሴት 256)፣ በተቋማት ማስፋፋት 220 (ወንድ 165፣ ሴት 55)፣ በትምህርት ልማት ስታትስቲክስ ትንተና፣ እቅድ ዝግጅት እና ሀብት ማፈላለግ 568 (ወንድ 354፣ ሴት 214)፣ በኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ 182 (ወንድ 103፣ ሴት 79)፣እና በሌሎች ሙያዎች

294 (ወንድ 145፣ ሴት 149) ባለሙያዎች በስራ ላይ ናቸው፡፡ የትምህርት መምሪያና ጽ/ቤት ሃላፊዎች ብዛትም 343 (ወንድ 325፣ ሴት 18) ነው፡፡

## መማሪያ ክፍል ግንባታ

በበጀት አመቱ አዲስ በተከፈቱ ትምህርት ቤቶች ውስጥ 160 መማሪያ ክፍሎችን ለመገንባት ታቅዶ 144 (90.0%) ክፍሎች ተገንብተዋል፡፡ በተመሳሳይ በነባር ትምህርት ቤቶች መጨናነቅ ለመቀነስ እና ያረጁትን አፍርሶ በአዲስ ለመተካት መማሪያ ክፍል ግንባታ ይሰራል፡፡ በመሆኑም መጨናነቅ በመፈጠሩ ምክንያት በተጨማሪ የተገነቡ ክፍሎች 368 ታቅዶ 202 (54.9%) እና በመልሶ መተካት 241 ታቅዶ 181 (75.1%) ማከናወን ተችሏል፡፡

የክልሉን ትምህርት ከክፍል እጥረት ለማላቀቅ በተደረገ ተከታታይ ጥረት በአለፉት አምስት አመታት 951 የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ሙሉ በሙሉ ከዳስ ወደ ቆርቆሮ የተቀየሩ ሲሆን በሌሎች ትምህርት ቤቶች ደግሞ 1,390 መማሪያ ክፍሎች ወደ ቆርቆሮ እንደተቀየሩ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ይህን መሻሻል ለማስቀጠል በበጀት አመቱ መጀመሪያ የነበሩ 33 ትምህርት ቤቶች (406 መማሪያ ክፍሎች) በሙሉ ወደ ቆርቆሮ መቀየር ተችሏል፡፡ በአንደኛና መካከለኛ ደረጃ በእርጅና እጅግ የተጎሳቆሉና የፈራረሱ ትምህርት ቤቶችን ብዛት 795 ሲሆን ከእነዚህ መካከል በበጀት አመቱ 310 (39.0%) ትምህርት ቤቶች እና 1,631 መማሪያ ክፍሎችን መልሶ መገንባት ስራ ተሰርቷል፡፡ በተጨማሪም በአንደኛና መካከለኛ ደረጃ አዲስ በተከፈቱ ትምህርት ቤቶች ውስጥ 489 መማሪያ ክፍሎችን ለመገንባት ታቅዶ 261 (53.4%) ክፍሎች ተገንብተዋል፡፡ በሌላ በኩል በነባር ትምህርት ቤቶች መጨናነቅ ለመቀነስ፣ የትምህርት ቤቶችን ደረጃ ለማሳደግ እና ያረጁትን አፍርሶ በአዲስ ለመተካት የመማሪያ ክፍል ግንባታ ለመስራት በተደረገው ጥረት የነባር ትምህርት ቤቶችን ደረጃ ለማሻሻል ተጨማሪ ክፍሎች 1,829 ለመገንባት ታቅዶ 1,085 (59.3%)፣ መጨናነቅ በመፈጠሩ ምክንያት በተጨማሪ የተገነቡ ክፍሎች 3,431 ታቅዶ 2,135 (62.2%) እና በመልሶ መተካት 2,649 ታቅዶ 2,024 (76.4%) ክፍሎች ግንባታ ማካሄድ ተችሏል፡፡



መማሪያ ክፍል ግንባታ-ሰሜን ሸዋ ዞን

## የተማሪዎች የነፍስ ወከፍ በጀት

የተማሪዎች የነፍስ ወከፍ በጀት ወረዳዎች ትምህርት ቤቶችን ለመለወጥና ለማሻሻል ከወረዳው ጠቅላላ በጀት ለመጀመሪያና ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በተማሪ ቁጥር ተሰልቶ የሚመደብ ነው፡፡ በአለፉት አመታት በተማሪ የሚመደበው በጀት መጠን ከወቅቱ የብር የመግዛት አቅም ጋር ሲነጻጸር እጅግ አነስተኛ በመሆኑ ለትምህርት ቤቶች የሚደርሰው ጥቅል ድጎማ ለውጥ የሚያመጣ ነው ባይባልም መሰረታዊ ችግሮችን ለማቃለል ችሏል፡፡ በዚህ መሠረት ለ1,844,976 ከ1ኛ-4ኛ ክፍል ተማሪዎች ብር 15,957,685 (ይህም በአማካይ ብር 8.65 ለአንድ ተማሪ ማለት ነው)፣ ለ1,502,605 የ5ኛ-8ኛ ክፍል ተማሪዎች ብር 16,377,136 (በአማካይ ብር 10.90 በተማሪ)፣ ለ574,044 የ9ኛ-10ኛ ክፍል ተማሪዎች ብር 8,968,319 (በአማካይ ብር 15.62 በተማሪ) እና ለ344,845 የ11ኛ-12ኛ ክፍል ተማሪዎች ብር 9,746,312 (በአማካይ ብር 28.26 በተማሪ) በጠቅላላው ለ4,266,470 ተማሪዎች ብር 51,049,451.75 (በአማካይ ብር 11.42 በተማሪ) ተመድቧል፡፡ በመሆኑም በአጠቃላይ ተማሪ ቁጥር መመደብ ከሚገባው ብር 69,711,965.00 መካከል የተመደበው ብር 51,049,451.75 ሲሆን አፈጻፀሙ 73.2% ነው፡፡

## የትምህርት ቤት የድጎማ በጀት ማሟላት

በ2014 በጀት ዓመት ከፌዴራል ትምህርት ሚኒስቴር ለሁሉም የመንግስት ት/ቤቶች (የአንደኛ፤ መካከለኛ እና ሁለተኛ ደረጃ) ለሚገኙ ተማሪዎች እና የልዩ ፍላጎት ድጋፍ መስጫ ማዕከላት በድምሩ ብር 323,935,186.00 የድጎማ በጀት የተላከ ሲሆን በየደረጃው በሚገኙ ተማሪዎች እና ድጋፍ መስጫ ማዕከላት ተሰልቶ ለትምህርት ቤቶች ተላልፏል፡፡

## የመምህራን እና ትምህርት አመራሩን ሙያ ማሻሻል

የመምህራን እና ትምህርት አመራሩ ልማት ስራዎች ውስጥ ሌላው ትኩረት ተሰጥቶት እየተሰራ ያለው መምህራን በስራ ላይ ተከታታይ የሙያ ማሻሻያ ፕሮግራሞችን ማካሄድ ነው፡፡ በመሆኑም በተከታታይ ሙያ ማሻሻያ የተሳተፉ የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ መምህራን ድርሻ በ2013ዓ.ም ከነበረበት 88.8% በ2014 ዓ.ም ወደ 92.7% ከፍ ለማድረግ ታቅዶ በማስተማር ላይ ከሚገኙ 126,815 (ወንድ 66,850፣ ሴት 59,965) ነባር መምህራን መካከል የፕሮግራሙ ተሳታፊዎችን 119,286 (ወንድ 62,723፣ ሴት 56,563) ወይም 94.1% (ወንድ 93.8%፣ ሴት 94.3%) በማድረስ ከእቅዱ 101.5% መፈጸም ተችሏል፡፡ በፕሮግራሙ የሚሳተፉ የሁለተኛ ደረጃ መምህራንን ድርሻ በ2013 ዓ.ም ከነበረበት 88.6% በ2014 ዓ.ም 100.0% ለማድረስ ታቅዶ በማስተማር ላይ ከሚገኙ 41,967 (ወንድ 31,275፣ ሴት 10,692) ነባር መምህራን መካከል ተሳታፊዎችን 31,531 (ወንድ 23,314፣ ሴት 8,217) ወይም 75.1% (ወንድ 74.5%፣

ሴት 76.9%) በማድረስ ከእቅዱ 75.1% መፈጸም ተችሏል፡፡

የርዕሰ መምህራንን ሙያ ለማጎልበት የሙያ ማሻሻያ ፕሮግራሙ ታቅዶ በመፈጸም ላይ ነው፡፡ በመሆኑም በተከታታይ ሙያ ማሻሻያ የተሳተፉ የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ርዕሰ መምህራን ድርሻ በ2013 ዓ.ም ከነበረበት 72.2% በ2014 ዓ.ም 100.0% ለማድረስ ታቅዶ በስራ ላይ ከሚገኙ ርዕሰ መምህራን መካከል የፕሮግራሙ ተሳታፊዎችን 8,330 (ወንድ 7,860፣ ሴት 470) ወይም 94.1% (ወንድ 94.3%፣ ሴት 91.6%) በማድረስ ከእቅዱም 94.1% መፈጸም ተችሏል፡፡ በፕሮግራሙ የሚሳተፉ የሁለተኛ ደረጃ ርዕሰ መምህራንን ድርሻ በ2013ዓ.ም ከነበረበት 99.6% እስከ በዘመኑ 100 % ለማድረስ ታቅዶ በስራ ላይ ከሚገኙ ርዕሰመምህራን መካከል የፕሮግራሙ ተሳታፊዎችን 544 (ወንድ 533፣ ሴት 11) ወይም 89.0% (ወንድ 88.8% ፣ ሴት 100.0%) በማድረስ ከእቅዱ 89.0% መፈጸም ተችሏል፡፡ፕሮግራሙም ለጉድኝት ሱፐርቫይዘሮች እንዲደርስ ከትትትልና ድጋፍ የተደረገ ሲሆን በተከታታይ ሙያ ማሻሻያ የተሳተፉ የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ጉድኝት ሱፐርቫይዘሮችን ድርሻ በ2013 ዓ.ም ከነበረበት 99.9% በ2014 ዓ.ም መጨረሻ 100.0% ለማድረስ ታቅዶ በስራ ላይ ከሚገኙ የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ሱፐርቫይዘሮች መካከል የፕሮግራሙ ተሳታፊዎችን 1,999 (ወንድ 1,951፣ ሴት 48) ወይም 94.1% (ወንድ 94.2%፣ ሴት 92.3%) በማድረስ ከእቅዱም 94.1% መፈጸም ተችሏል፡፡ በፕሮግራሙ የሚሳተፉ የሁለተኛ ደረጃ ሱፐርቫይዘሮችን ድርሻ በ2013ዓ.ም ከነበረበት 98.3% በዘመኑ 100.0% ለማድረስ ታቅዶ በስራ ላይ ከሚገኙ የሁለተኛ ደረጃ ሱፐርቫይዘሮች መካከል ተሳታፊዎችን 186 (ወንድ 182፣ ሴት 4) ወይም 90.7% (ወንድ 90.5%፣ ሴት 100.0%) በማድረስ ከእቅዱ 90.7% መፈጸም ተችሏል፡፡

## ለትምህርት ቤቶች መሰረተ ልማት ማሟላት

ንጹህ የመጠጥ ውሀ ያላቸው የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች 56.0% ለማድረስ ታቅዶ በክልሉ ከሚገኙ አንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል 4,173 ወይም 45.4% ትምህርት ቤቶች ንፁህ መጠጥ ውሃ ያላቸው ሲሆን ከታቀደው አፈፃፀሙ 81.1% ሆኗል፡፡ በተመሳሳይ ንጹህ የመጠጥ ውሀ ያላቸው ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ብዛት 79.1% ለማድረስ ታቅዶ በክልሉ ከሚገኙ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል 490 ወይም 76.4% ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውሃ ያላቸው ሲሆን ከታቀደው አፈፃፀሙ 96.7% ሆኗል፡፡

የመፀዳጃ ቤት ያላቸው የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ት/ቤቶች ብዛት 87.7% ለማድረስ ታቅዶ በክልሉ ከሚገኙ አንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል 2,575 ወይም 28.0% ትምህርት ቤቶች ደረጃውን የጠበቀ መጸዳጃ ቤት ያላቸው ሲሆን ከታቀደው አፈፃፀሙ 31.9%

ሆኗል፡፡ በሁለተኛ ደረጃ የመፅዳጃ ቤት ያላቸውን ት/ቤቶች ብዛት 98.1% ለማድረስ ታቅዶ በክልሉ ከሚገኙ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል 413 ወይም 64.4% ትምህርት ቤቶች ደረጃውን የጠበቀ መጸዳጃ ቤት ያላቸው ሲሆን ከታቀደው አፈፃፀሙ 65.7% ሆኗል፡፡

የሴቶች የንጽህና መጠበቂያ አገልግሎት መስጫ ክፍል ያላቸው ት/ቤቶች ብዛት 45.0% ለማድረስ ታቅዶ በክልሉ ከሚገኙ የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል 792 ወይም 8.1% ትምህርት ቤቶች ደረጃውን የጠበቀ የሴቶች የንጽህና መጠበቂያ አገልግሎት መስጫ ክፍል ያላቸው ሲሆን ከታቀደው አፈፃፀሙ 17.9% ሆኗል፡፡

የኤሌክትሪክ አገልግሎት ያላቸው የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ት/ቤቶች ብዛት በዘመኑ 20.0% ለማድረስ ታቅዶ በክልሉ ከሚገኙ አንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል 1,840 ወይም 20.02% ትምህርት ቤቶች የኤሌክትሪክ አገልግሎት ያላቸው ሲሆን ከታቀደው አፈፃፀሙ 100.1% ሆኗል፡፡ በሁለተኛ ደረጃ የኤሌክትሪክ አገልግሎት ያላቸውን ት/ቤቶች ብዛት 75.0% ለማድረስ ታቅዶ በክልሉ ከሚገኙ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል 458 ወይም 71.5% ትምህርት ቤቶች የኤልክትሪክ አገልግሎት ያላቸው ሲሆን ከታቀደው አፈፃፀሙ 95.3% ሆኗል፡፡

በትምህርት ቤት ኤሌክትሪክ ሃይል እንዲዳረስ ከማድረግ ባሻገር የኤሌክትሪክ አገልግሎት በሌለባቸው አካባቢዎች ተማሪዎች በምሽት ማንበብ እንዲችሉ እና የተማሪዎች የንባብ ክህሎት እንዲሻሻል በየደረጃው ጥረት ተደርጓል፡፡ በመሆኑም ከመንግስት ጋር በትብብር ከሚሰራ ፕሮጀክት ድጋፍ የተገኘውን 11,880 ጥራታቸውን የጠበቁ የሶላር አምፖሎች የ2ኛ እና 3ኛ ክፍል ተማሪዎችን ቁጥር መሰረት በማድረግ ማሰራጨት ተችሏል፡፡



ንፁህ መጠጥ ውሀ-ባህርዳር

## በትምህርት ቤቶች የቤተሙከራ አገልግሎት ማሻሻል

በ2014 ዓ.ም የሣይንስ ቤተ-ሙከራ ክፍል ያላቸው የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ት/ቤቶች ብዛት 67.0% ለማድረስ ታቅዶ በክልሉ ከሚገኙ አንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል 3,957 ወይም 43.0% ትምህርት ቤቶች የሣይንስ ቤተ-ሙከራ ክፍል ያላቸው ሲሆን ከታቀደው አፈፃፀሙ 64.2% ሆኗል፡፡ በሁለተኛ ደረጃ በሶስት ወይም ሁለት የሳይንስ ትምህርት አይነቶች ቤተ-ሙከራ ክፍል ያላቸውን ት/ቤቶች ብዛት 90.0% ለማድረስ ታቅዶ በክልሉ ከሚገኙ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል 511 ወይም 79.7% ትምህርት ቤቶች በሶስት ወይም ሁለት የሳይንስ ትምህርት አይነቶች ቤተ-ሙከራ ያላቸው ሲሆን ከታቀደው አፈፃፀሙ 88.6% ሆኗል፡፡



ቤተ-ሙከራ--ዳንግላ ከተማ

## የትምህርት ቤት ምገባ መርሀግብር

የትምህርት ቤት ምገባ መርሀ ግብር ተጠቃሚ የሆኑ የቅድመ አንደኛ እና አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ብዛት 10.0% ለማድረስ ታቅዶ በቅድመ አንደኛ እና አንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በመማር ላይ ከሚገኙ 4,228,629 (ወንድ 2,108,725፣ ሴት 2,119,904) ተማሪዎች መካከል የምገባ መርሃግብር ተጠቃሚ የሆኑት 72,291 (ወንድ 35,859፣ ሴት 36,432) ወይም 1.71% (ወንድ 1.70%፣ ሴት 1.72%) በማድረስ ከእቅዱ 17.1% መፈጸም ተችሏል፡፡ ይህ አፈፃፀም አነስተኛ በመሆኑ የተማሪዎችን መማር ለማሻሻል ከክልሉ መንግስት እና አጋር አካላት ጋር በመሆን በትኩረት መስራት አለበት፡፡



የትምህርት ቤት ምገባ-ደብረ ማርቆስ ከተማ

## የስርዓተ-ትምህርት ማበልጸጊያ ማእከል

የስርዓተ-ትምህርት ማበልጸጊያ ማእከል ያላቸው የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን ብዛት 75.0% ለማድረስ ታቅዶ በክልሉ ከሚገኙ አንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል 5,911 ወይም 64.3% ትምህርት ቤቶች ማዕከል ያላቸው ሲሆን ከታቀደው አፈፃፀሙ 85.7% ሆኗል፡፡ በሁለተኛ ደረጃ የስርዓተ-ትምህርት ማበልጸጊያ ማእከል ያላቸውን ት/ቤቶች ብዛት 69.0% ለማድረስ ታቅዶ በክልሉ ከሚገኙ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል 438 ወይም 68.3% ትምህርት ቤቶች ማዕከል ያላቸው ሲሆን ከታቀደው አፈፃፀሙ 99.0% ሆኗል፡፡

## የተማሪ ሴክሽን ጥምርታ

በአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት የተማሪ ሴክሽን ጥምርታ 50 ለማድረስ ታቅዶ በአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚማሩ ተማሪዎች 3,496,884 እና የሴክሽን ብዛት 94,261 በመሆኑ ጥምርታው 37 ሲሆን ከታቀደው አፈፃፀሙ 134.8% ሆኗል፡፡ በሁለተኛ ደረጃ ጥምርታውን 40 ለማድረስ ታቅዶ በክልሉ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በ17,022 ሴክሽኖች የሚማሩ 972,173 ተማሪዎች በመሆናቸው ጥምርታው 57 ሲሆን ከታቀደው አፈፃፀሙ 70.% ሆኗል፡፡

## የልዩ ፍላጎት ድጋፍ መስጫ ማዕከላት ማቋቋም

በትምህርት ቤቶች የተደራጁ የልዩ ፍላጎት ድጋፍ መስጫ ማዕከላት ብዛት 202 ለማድረስ ታቅዶ በክልሉ ከሚገኙ የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል 285 ወይም 2.9% ትምህርት ቤቶች ድጋፍ የልዩ ፍላጎት መስጫ ማዕከል ያደራጁ ሲሆን ከታቀደው አፈፃፀሙ 141.3% ሆኗል፡፡

**የአብክመ የመንግስት ኮሙዩኒኬሽን ቢሮ**

## ጥቅል ቅበላ ምጣኔ

ጥቅል የቅድመ አንደኛ ደረጃ ቅበላ ምጣኔን 39.0% ለማድረስ ታቅዶ በደረጃው በ4 አመት እድሜ በቅድመ አንደኛ ደረጃ ለመጀመሪያ ጊዜ የተመዘገቡት 219,632 (ወንድ 107,739፣ ሴት 111,893) ህጻናት ናቸው፡፡ በመሆኑም በዚህ ምዝገባ አፈፃፀም ንጥር ቅበላው 33.5% (ወንድ 32.5%፣ ሴት 34.7%) ሲሆን ከታቀደው 86.0% (ወንድ 83.2%፣ ሴት 88.9%) ሆኗል፡፡

ጥቅል የቅድመ አንደኛ ደረጃ ቅበላ ምጣኔን 59.36% ለማድረስ ታቅዶ በደረጃው በሁሉም እድሜ በቅድመ አንደኛ ደረጃ ለመጀመሪያ ግዜ የተመዘገቡት 409,924 (ወንድ 204,244፣ ሴት 205,680) ህጻናት ናቸው፡፡ በመሆኑም በዚህ ምዝገባ አፈፃፀም ጥቅል ቅበላው 62.6% (ወንድ 61.5%፣ ሴት 63.7%) ሲሆን ከታቀደው 125.8% (ወንድ 123.6%፣ ሴት 128.1%) ሆኗል፡፡

## ቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት

በክልላችን በቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት 961,851 (ወንድ 984,454፣ ሴት 948,137) ነባርና አዲስ ገቢ የቅድመ አንደኛ ደረጃ ተማሪዎችን በማሳተፍ ጥቅል ተሳትፎውን 49.8% (49.7% ወንድ፣ 49.8% ሴት) ለማድረስ ታቅዶ የተመዘገቡት 409,924 (ወንድ 204,244፣ ሴት 205,680) ህፃናት ሲሆኑ በዚህ መሠረት ጥቅል ተሳትፎው 39.2% (ወንድ 39.5%፣ ሴት 38.8%) ሲሆን የእቅድ አፈፃፀሙ 78.7% (79.3% ወንድ፣ 78.% ሴት) ሆኗል፡፡

## የተማሪ ንጥርና ጥቅል ቅበላ

በክልላችን የአንደኛ ክፍል ንጥር ቅበላ 701,338 (ወንድ 357,217፣ ሴት 344,121)፣ የአንደኛ ደረጃ በ7 ዓመት እድሜ ለመጀመሪያ ግዜ ገቢ ተማሪዎችን በመመዝገብ ንጥር ቅበላ ምጣኔውን 100% (ወንድ 100%፣ ሴት 100%) ለማድረስ ታቅዶ 502,000 (ወንድ 264,225፣ ሴት 237,775) ተማሪዎችን ምዝገባ በማከናወን የምዝገባና ንጥር ቅበላ አፈፃፀሙ 71.6% (ወንድ 74.0%፣ ሴት 69.1%) ሆኗል፡፡

የአንደኛ ክፍል ጥቅል ቅበላን በተመለከተ በሁሉም እድሜ ለመጀመሪያ ግዜ ገቢ ተማሪዎችን በመመዝገብ የጥቅል ቅበላ ምጣኔውን 103.8% ለማድረስ ታቅዶ 516,472 (ወንድ 269,611፣ሴት246,861) ተማሪዎችን ምዝገባ በማከናወን የምዝገባ አፈፃፀሙ 70.9% (ወንድ 72.7%፣ ሴት 69.1%) እና የጥቅል ቅበላ አፈፃፀሙ 73.6% (ወንድ 75.5%፣ ሴት 71.7%) ሆኗል፡፡

በክልላችን 3,333,469 (ወንድ 1,719,561፣ ሴት 1,613,908) ነባርና አዲስ ገቢ የአንደኛ ደረጃ ተማሪዎችን በመመዝገብ ጥቅል ተሳትፎውን 81.02% (81.04% ወንድ፣ 80.99% ሴት) ለማድረስ ታቅዶ የተመዘገቡት 2,730,980 (ወንድ 1,378,810፣ ሴት 1,352,170) ሲሆኑ በዚህ መሠረት ጥቅል ተሳትፎው 68.6% (ወንድ 68.6%፣ ሴት 68.6%) ሲሆን የእቅድ አፈፃፀሙ

81.93% (ወንድ 81.93%፣ ሴት 81.92%) ሆኗል፡፡

በ2014 ዓ.ም በክልላችን 955,016 (ወንድ 466,837፣ ሴት 488,179) ነባርና አዲስ ገቢ የመካከለኛ ደረጃ ተማሪዎችን በመመዝገብ ጥቅል ተሳትፎውን 79.26% (ወንድ 75.58% ፣ ሴት 83.13%) ለማድረስ ታቅዶ የተመዘገቡት 765,904 (ወንድ 357,298፣ ሴት 408,606) ሲሆኑ በዚህ መሠረት ጥቅል ተሳትፎው 63.6% (ወንድ 57.8%፣ ሴት 69.6%) ሲሆን የእቅድ አፈፃፀሙ 80.2% (72.98% ወንድ፣ 87.79% ሴት) ሆኗል፡፡

በክልላችን 1,220,181 (ወንድ 578,568፣ ሴት 641,613) የሚሆኑ ነባርና አዲስ ገቢ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎችን በመመዝገብ ጥቅል ተሳትፎውን 48.35% (45.06% ወንድ፣ 51.75% ሴት) ለማድረስ ታቅዶ 972,173 (ወንድ 445,687፣ ሴት 526,486) በመመዝገብ ጥቅል ተሳትፎው 38.5% (ወንድ 34.7%፣ ሴት 42.5%) ሲሆን የእቅድ አፈፃፀሙ 79.7% (71.80% ወንድ፣ 87.83% ሴት) ሆኗል፡፡

## መጠነ ማቋረጥ

በአንደኛ ደረጃ በአመቱ መጀመሪያ ከተመዘገቡ ተማሪዎች መካከል በ2014 ዓ.ም መጨረሻ ድረስ በተሰበሰበ መረጃ 127,325 (ወንድ5 74,391፣ ሴት 52,934) ወይም ከተመዘገቡት 4.7% (5.4% ወንድ፣ 3.9% ሴት) ከትምህርት ቤት ቀርተዋል፡፡ በመሆኑም በአመቱ ለንቅናቄ ከተያዘው 2.0% እቅድ ጋር ሲነፃፀር የእቅድ አፈፃፀሙ 42.9% (ወንድ 37.1%፣ ሴት 51.1%) ሆኗል፡፡

በመካከለኛ ደረጃ በአመቱ መጀመሪያ ከተመዘገቡ ተማሪዎች መካከል በ2014 ዓ.ም መጨረሻ በተሰበሰበ መረጃ 39,172 (ወንድ 22,159፣ ሴት 17,013) ወይም ከተመዘገቡት 1.4% (ወንድ 1.6%፣ ሴት 1.3%) ከትምህርት ቤት ቀርተዋል፡፡ በመሆኑም በአመቱ ለንቅናቄ ከተያዘው 2.0% እቅድ ጋር ሲነፃፀር የእቅድ አፈፃፀሙ 139.4% (ወንድ 124.4%፣ ሴት 159%) ሆኗል፡፡

በሁለተኛ ደረጃ በአመቱ መጀመሪያ ከተመዘገቡ ተማሪዎች መካከል በበጀት አመቱ መጨረሻ በተሰበሰበ መረጃ 65,621 (ወንድ5 38,417፣ ሴት 27,204) ወይም ከተመዘገቡት 6.7% (8.6% ወንድ፣ 5.2% ሴት) ከትምህርት ቤት ቀርተዋል፡፡ በመሆኑም በአመቱ ለንቅናቄ ከተያዘው 2.0% እቅድ ጋር ሲነፃፀር የእቅድ አፈፃፀሙ 29.6% (ወንድ 23.2%፣ ሴት 38.7%) ሆኗል፡፡

## ትምህርት ጥቅል ተሳትፎ ፆታዊ ምጥጥን

በተመሳሳይ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት (ከ1ኛ - 6ኛ ክፍል) ጥቅል ተሳትፎ ፆታዊ ምጥጥንን በ2013 ዓ.ም ከነበረበት 0.97 በ2014 ዓ.ም 0.98 ለማድረግ ታቅዶ የሴቶች ጥቅል ተሳትፎ 68.61% የደረሰ ሲሆን የወንዶች 68.62% በመሆኑ ጾታዊ ምጥጥኑ 1.00 በመሆኑ የእቅድ አፈፃፀሙ 102.0% ሆኗል፡፡ የመካከለኛ ደረጃ (ከ7 - 8ኛ ክፍል) ትምህርት ጥቅል ተሳትፎ

ፆታዊ ምጥጥንን በ2013 ዓ.ም ከነበረበት 1.17 በ2014 ዓ.ም 1.07 ለማድረግ ታቅዶ  የሴቶች ጥቅል ተሳትፎ 69.58%  የደረሰ ሲሆን የወንዶች 57.84%  በመሆኑ ጾታዊ ምጥጥኑ 1.20 በመሆኑ የእቅድ አፈፃፀሙ 89% ሆኗል፡፡

በሁለተኛ ደረጃ (ከ9ኛ - 12ኛ ክፍል) ትምህርት ጥቅል ተሳትፎ ፆታዊ ምጥጥንን በ2013 ዓ.ም ከነበረበት 1.16 በዘመኑ ወደ 0.98 ዝቅ ለማድረግ ታቅዶ  በሁለተኛ ደረጃ የሴቶች ጥቅል ተሳትፎ 42.46%  የደረሰ ሲሆን የወንዶች 34.71%  በመሆኑ ጾታዊ ምጥጥኑ 1.22 በመሆኑ የእቅድ አፈፃፀሙ 80.1% ሆኗል፡፡

## በትምህርት ስርዓቱ የሴቶች ድርሻ

የቅድመ አንደኛ ደረጃ የሴት መምህራን ድርሻ በ2013 ዓ.ም ከነበረበት 81.0% በ2014 ዓ.ም 94.4% ለማድረስ የታቀደ ሲሆን  በክልሉ በማስተማር ላይ ከሚገኙ 11,935 የቅደመ አንደኛ ደረጃ መምህራን መካከል 10,485 ወይም 87.9% ሴቶች በመሆናቸው የእቅድ አፈፃፀሙ 93.0% ሆኗል፡፡ በተመሳሳይ በአንደኛና መካከለኛ ደረጃ የሴት መምህራን ድርሻ በ2013 ዓ.ም ከነበረበት 46.7% በ2014 ዓ.ም 46.8% ለማድረስ ታቅዶ በክልሉ በማስተማር ላይ ከሚገኙ 141,190 የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ መምህራን መካከል 66,180 ወይም 46.9% ሴቶች በመሆናቸው የእቅድ አፈፃፀሙ 100.3% ሆኗል፡፡ በሁለተኛ ደረጃ የሴት መምህራን ድርሻ በ2013ዓ.ም ከነበረበት 24.8% በ2014 ዓ.ም 26.7% ለማድረስ ታቅዶ በክልሉ በማስተማር ላይ ከሚገኙ 45,325 የሁለተኛ ደረጃ መምህራን መካከል 11,821 ወይም 26.1% ሴቶች በመሆናቸው የእቅድ አፈፃፀሙ 97.6% ሆኗል፡፡

በትምህርት አመራሩ የሴቶችን ድርሻ ከፍ ለማድረግ እቅድ ተይዞ እንቅስቃሴ ተደርጓል፡፡ የአንደኛ እና መካከለኛ ደረጃ የሴት ርዕሰመምህራን ድርሻ በ2013 ዓ.ም ከነበረበት 6.6% በ2014 ዓ.ም 10.2% ለማድረስ ታቅዶ በክልሉ በማገልገል ላይ ከሚገኙ 8,848 የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ርዕሰ መምህራን መካከል 513 ወይም 5.8% ሴቶች በመሆናቸው የእቅድአፈፃፀሙ 56.7% ሆኗል፡፡ በተመሳሳይ የሁለተኛ ደረጃ የሴት ርዕሰመምህራን ድርሻ በ2013 ዓ.ም ከነበረበት 2.5% በ2014 ዓ.ም 4.1% ለማድረስ ታቅዶ በክልሉ በማገልገል ላይ ከሚገኙ 611 የሁለተኛ ደረጃ ርዕሰ መምህራን መካከል 11 ወይም 1.8% ሴቶች በመሆናቸው የእቅድ አፈፃፀሙ 43.9% ሆኗል፡፡

የአንደኛ እና መካከለኛ ደረጃ የሴት ጉድኝት ሱፐርቫይዘሮችን ድርሻ በ2013 ዓ.ም ከነበረበት 4.4% በ2014 ዓ.ም 11.0% ለማድረስ የታቀደ ሲሆን በክልሉ በማገልገል ላይ ከሚገኙ 2,125 የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ሱፐርቫይዘሮች መካከል 52 ወይም 2.4% ሴቶች በመሆናቸው የእቅድ አፈፃፀሙ 22.2% ሆኗል፡፡ በተመሳሳይ የሁለተኛ ደረጃ የሴት ጉድኝት ሱፐርቫይዘሮችን

ድርሻ በ2013ዓ.ም ከነበረበት 1.9% በዘመኑ 5.7% ለማድረስ የታቀደ ሲሆን በዘመኑ በክልሉ በማገልገል ላይ ከሚገኙ 205 የሁለተኛ ደረጃ ሱፐርቫይዘሮች መካከል 4 ወይም 2.0% ሴቶች በመሆናቸው የእቅድ አፈፃፀሙ 34.1% ሆኗል፡፡

በመጨረሻም በትምህርት ባለሙያዎች የሴቶችን ድርሻ ከፍ ለማድረግ እቅድ ተይዞ እንቅስቃሴ በመደረግ ላይ ነው፡፡ የሴት የትምህርት ባለሙያዎች ድርሻ በ2013 ዓ.ም ከነበረበት 32.2% በ2014 ዓ.ም 33.7% ለማድረስ የታቀደ ሲሆን በክልሉ በማገልገል ላይ ከሚገኙ 4,931 የዞን እና ወረዳ ትምህርት ባለሙያዎች መካከል 1,637 ወይም 33.2% ሴቶች በመሆናቸው የእቅድ አፈፃፀሙ 98.5% ሆኗል፡፡

## የልዩ ፍላጎት ትምህርት

በክልሉ በቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት 1,996 (ወንድ 1,019፣ ሴት 978) የልዩ ፍላጎት ያላቸው የቅድመ አንደኛ ደረጃ ተማሪዎችን በማሳተፍ ጥቅል ተሳትፎውን 0.61% (ወንድ 0.61%፣ ሴት 0.60%) ለማድረስ ታቅዶ የተመዘገቡት 801 (ወንድ 409፣ ሴት 392) ልዩ ፍላጎት ያላቸው ህፃናት ሲሆኑ ጥቅል ተሳትፎው 0.24% (ወንድ 0.25%፣ ሴት 0.24%) ሲሆን የእቅድ አፈፃፀሙ 40.13% (ወንድ 40.15%፣ ሴት 40.10%) ሆኗል፡፡

በአንደኛ ደረጃ (ከ1ኛ - 6ኛ ክፍል) ትምህርት 32,677 (ወንድ 17,532 ፣ ሴት 15,146) የልዩ ፍላጎት ያላቸው የአንደኛ ደረጃ ተማሪዎችን በማሳተፍ ጥቅል ተሳትፎውን 4.66% (ወንድ 4.96% ፣ ሴት 4.37%) ለማድረስ ታቅዶ የተመዘገቡት 12,416 (ወንድ 6,717፣ ሴት 5,699) ልዩ ፍላጎት ያላቸው ህፃናት ሲሆኑ ጥቅል ተሳትፎው 1.8% (ወንድ 1.9%፣ ሴት 1.6%) ሲሆን የእቅድ አፈፃፀሙ 38.0% (ወንድ 38.3%፣ ሴት 37.6%) ነው፡፡

በመካከለኛ ደረጃ (ከ7ኛ - 8ኛ ክፍል) ትምህርት 4,437 (ወንድ 2,395፣ ሴት 2,042) የልዩ ፍላጎት ያላቸው የመካከለኛ ደረጃ ተማሪዎችን በማሳተፍ ጥቅል ተሳትፎውን 2.09% (2.20% ወንድ፣ 1.98% ሴት) ለማድረስ ታቅዶ የተመዘገቡት 2,565 (ወንድ 1,415፣ ሴት 1,150) ልዩ ፍላጎት ያላቸው ህፃናት ሲሆኑ ጥቅል ተሳትፎው 1.2% (ወንድ1.3%፣ ሴት 1.1%) ሲሆን የእቅድ አፈፃፀሙ 57.9% (59.2% ወንድ፣ 56.2% ሴት) ማድረስ ተችሏል፡፡

በሁለተኛ ደረጃ (ከ9ኛ - 12ኛ ክፍል) ትምህርት 3,584 (ወንድ 2,090 ፣ ሴት 1,494) የልዩ ፍላጎት ያላቸው የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎችን በማሳተፍ ጥቅል ተሳትፎውን 0.83% (ወንድ 0.95%፣ ሴት 0.71%) ለማድረስ ታቅዶ የተመዘገቡት 2,052 (ወንድ 1,150፣ ሴት 902) ልዩ ፍላጎት ያላቸው ታዳጊዎች ሲሆኑ ጥቅል ተሳትፎው 0.5% (ወንድ 0.5%፣ ሴት 0.4%) ሲሆን የእቅድ አፈፃፀሙ 55.7% (43.5% ወንድ፣ 65.1% ሴት) ነው፡፡

**የአብከመ የመንግስት ኮሙዩኒኬሽን ቢሮ**



ልዩ ፍላጎት ትምህርት-ሰሜን ጎንደር ዞን

## የጎልማሶች እና መደበኛ ያልሆነ ትምህርት

ከሥራ ጋር የተሳሰረ የጎልማሶች እና መደበኛ ያልሆነ ትምህርት በእቅድ ተካቶ እየተሰራ ይገኛል በመሆኑም የተቋቋሙ መማማሪያ ጣቢያዎች ብዛት በቁጥር 20,000 ለማድረስ ታቅዶ በበጀት አመቱ መጨረሻ 4,759 ጣቢያዎች የተቋቋሙ በመሆኑ እቅድ አፈፃፀሙ 23.8% ሆኗል፡፡ ቅጥር የተፈጸመላቸው አመቻቾች ብዛት 13,748 ለማድረስ ታቅዶ 2,998 (ወንድ 1,199፣ ሴት 1,799) ተቀጥረው አገልግሎት በመስጠት ላይ በመሆናቸው እቅድ አፈፃፀሙ 21.8% ሆኗል፡፡

የትምህርት ብርሀን ምዘና የወሰዱ ጎልማሶች እና ታዳጊዎች ብዛት በቁጥር በ2014 ዓ.ም 50,000 (ወንድ 35,000፣ ሴት 15,000) ሲሆን ይህን ተግባር ለመፈጸም የምዘና ጥያቄዎችን አዘጋጅቶ ለዞኖች በመላክ በሁለት ዙር ምዘና ተከናውኗል፡፡ በመጀመሪያው ዙር በሚያዝያ ወር ሰሜን ሸዋን ጨምሮ በመዕራብ አማራ የተካሄደ ሲሆን በዚህ ዙር 90,249( ወ.56,877፣ ሴ.33,372 ) ለመመዘን ታቅዶ 110,969 (ወ.81,219፣ ሴ.29,750) ጎልማሶች ተመዝግበው 86,187 (ወ. 66,424፣ ሴ.19,763 ) ጎልማሶች ተመዝነዋል፡፡ ከተመዘኑት ጎልማሶች መካከል 72,718( ወ 56,861፣ ሴ15,857)84.37% የሽግግር መስፈርቱን ማሟላታቸውን የተላከው መረጃ ያመላክታል፡፡

በሁለተኛው ዙር ምዘና የተካሄደው በሰኔ ወር የጸጥታ ችግር በነበረባቸው በምስራቅ አማራ ባሉ ዞኖች እና በመጀመሪያ ዙር ምዘና ባልሰጡ አንዳንድ የምዕራብ አማር ወረዳዎች ነው፡፡ በዚህ ዙር ለመመዘን ከተመዘገቡት 46,802 (ወ 34,139፣ ሴ-12,663) ጎልማሶች የተመዘኑት 35,125 (ወ- 26,469፣ ሴ-8646) ሲሆኑ የሽግግር መስፈርቱን ያሟሉት ጎልማሶች 28,918 (ወ-22,057፣ ሴ- 6,861) 82.35% መሆናቸውን መረጃው ያሳያል፡፡ በአጠቃላይ በክልሉ በሁለቱም

ዙር ለምዘና የተመዘገቡ ጎልማሶች 157,771 (ወ- 115,358፣ ሴ- 42,413) ሲሆኑ የተመዘኑት 121,312 (ወ- 92,893፣ ሴ- 28,409) ሲሆኑ የሽግግር መስፈርቱን ያሟሉት 101,636(ወ-78,918፣ ሴ-22,718) 83.78% ናቸው፡፡



የጎልማሶች ትምህርት-ደብረ ማርቆስ ከተማ

# ወጣቶችና ስፖርት

## ወጣቶችን ማደራጀት

በበጀት አመቱ ወጣቶችን በሚፈልጉት አደረጃጀት በመደራጀት መብትና ጥቅማቸውን በማስጠበቅ ተሳታፊና ተጠቃሚ ለማድረግ በተሰራው ስራ ለ1,497,644 (ወንድ 748,822፣ሴት 748,822) ወጣቶችን በማደራጀት ጥቅምና አስፈላጊነት ግንዛቤ ለመፍጠር ታቅዶ ለ902,052 (ወንድ 4547,266፣ ሴት 354,786) ወጣቶች ግንዛቤ የተፈጠረላቸው ሲሆን አፈጻጸሙ 62.2% ነው፡፡ ግንዛቤ ከተፈጠረላቸው ወጣቶች መካከል 978,109 (ወንድ 489,055፣ ሴት 489,054) ወጣቶችን በተለያዩ አደረጃጀቶች እንዲደራጁ ታቅዶ 456,577 (ወንድ 307,340፣ ሴት 149,160) ወጣቶችን ለማደራጀት የተቻለ ሲሆን አፈጻጸሙም 46.6% ነው፡፡ በተለያዩ አደረጃጀቶች ከተደራጁት ወጣቶች መካከል በወጣት ማህበርና ሊግ 548,066 (ወንድ 274,033፣ ሴት 274,033)፤ በወጣት ልማት ቡድን 345,200 (ወንድ 172,600፣ ሴት 172,600)፤ በበጎፈቃድ ክበባትና ማህበራት 109,022 (ወንድ 54,511፣ ሴት 54,511)፤ በኪነ ጥበባት ክበባትና ማህበራት 52,127 (ወንድ 26,064፣ ሴት 26,063) እንዲደራጁ ለማድረግ ታቅዶ በወጣት ማህበርና ሊግ 238,636 (ወንድ 165,456 ሴት 73,103)፤ በወጣት ልማት ቡድን 155,229 (ወንድ 106,853 ሴት 48,376)፤ በበጎፈቃድ ክበባትና ማህበራት 49,697

(ወንድ 27,971 ሴት 21,726)፤ በኪነጥበባት ክበባትና ማህበራት 13,015 (ወንድ 7,060 ሴት 5,955) ወጣቶችን እንዲደራጁ ለማድረግ የተቻለ ሲሆን አፈጻጸሙ በቅደም ተከተላቸው መሰረት 43.5%፤ 44.9%፤ 45.5% እና 24.9% ነው፡፡

## ለወጣቶች ድጋፍ ማድረግ

በበጀት አመቱ ለወጣት አደረጃጀቶች ድጋፍ ለማድረግ በተሰራው ስራ 20,570 የሙያ፣ 11,474 ቁሳቁስ እና 5,286 የገንዘብ ድጋፍ በማድረግ አደረጃጀቶችን ለማጠናከር ታቅዶ 9,006 የሙያ፣ 1846 ቁሳቁስ እና 3000 አደረጃጀቶችን የገንዘብ ድጋፍ በማድረግ ማጠናከር የተቻለ ሲሆን አፈጻጸሙም በቅደም ተከተላቸው መሰረት 43.7%፣ 16% እና 56.7% ነው፡፡

## የወጣቶችን ተሳትፎና ውክልና ማረጋገጥ

በበጀት አመቱ ወጣቶች በየደረጃው ባሉ የህዝብ ምክር ቤቶች የአደረጃጀቶች ውክልና በመያዝ በምክር ቤቶች ሚናና አሰራር ግንዛቤአቸውን ማሳደግ እንዲችሉ ተሳታፊና ተጠቃሚ የሚያደርጉ ውሳኔዎች እንዲወሰኑ ለማድረግ በተሰራው ስራ በየደረጃው ባሉ የህዝብ ምክር ቤቶች 87,318 (ወንድ 43,663፣ ሴት 43,655) የወጣት አደረጃጀት አመራሮችን ለማሳተፍ ታቅዶ 67,208 (ወንድ 35529፣ ሴት 31,679) የወጣት አደረጃጀት አመራሮችን ማሳተፍ ተችሏል፣ አፈጻጸሙም 77% ነው፡፡

በንቅናቄ ተሳትፎ ኮንፈረንስ 1,206,378 (ወንድ 603,189፣ ሴት 603,189) ወጣቶችን ለማሳተፍ ታቅዶ ወንድ 986,252 ሴት 452,770 ድምር 1,439,022 ወጣቶች በተሳተፉበት መድረኩ ተካሂዷል፡፡ አፈጻጸሙ ከ100% በላይ ሲሆን ይህም አፈጻጸም ከተሳታፊ አኳያ አጠቃላይ የእቅዱን ከ100% በላይ፣ በዞን ከ100% በላይ፣ በወረዳ ስንመለከት ወ 83428ሴ 38188ድ 121616 ወጣቶች /ከ100% በላይ / እንዲሁም በቀበሌ ወንድ 892,873 ሴት 409,925ድ 1,302,798 /ከ100% በላይ/ ወጣቶች በወቅታዊ ሁኔታ በተፈጠረው ንቅናቄ እንዲሳተፉ ተደርጓል፡፡

## ስብዕና ልማትና አስተሳሰብ ግንባታ

በ2014 ዓ.ም በሰብዕና ልማትና በአስተሳሰብ ግንባታ ለ962,805(ወንድ 481,403 ሴት 481,402) ወጣቶችን ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ 347,774 (ወንድ 205,424 ሴት 142,350) ስልጠና እንዲያገኙ ተደርጓል፣ አፈጻጸሙ 36.1% ነው፡፡ ለ644,459 (ወንድ 322,230 ሴት 322,229) ወጣቶችን የህይወት ክህሎት ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ 244,522 (ወንድ 141,924 ሴት 102,598) ስልጠና እንዲያገኙ ተደርጓል፣ አፈጻጸሙ 37.9% ነው፡፡ ለ664,707 (ወንድ 332,354 ሴት 332,353) ወጣቶችን በአቻ ለአቻ ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ 248,861 (ወንድ 140,646 ሴት 108,215) የአቻ ለአቻ ስልጠና እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ በተመሳሳይ በወጣቶች

የስብዕና ልማት ማዕከላት አሰራርና አስተዳደር ለባለድርሻ አካላት ለ2,830 (ወንድ 1,415 ሴት 1,405) የስብዕና ልማት ማዕከላት ስራ አስኪያጆችና ቦርድ አመራሮች ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ 3731 (ወንድ 2606 ሴት 1126) ስራ አስኪያጆችንና የቦርድ አመራሮች ተሰጥቷል፣ አፈጻጸሙ100% ነው፡፡ ለ19,321 (ወንድ 9,661 ሴት 9,660) የወጣት አደረጃጀት አመራሮችን ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ 5,600 (ወንድ 4,559 ሴት 1041) የወጣት አደረጃጀት አመራሮችን ማሰልጠን የተቻለ ሲሆን አፈጻጸሙ29% ነው፡፡ የወጣቶችን ተሳትፎ ለማጎልበት እና አሉታዊ የሆኑ አመለካከቶችን በመስበር ሰብዕናቸውን በመገንባት ረገድ የተከናወኑ ተግባራት በጥቅሉ ሲታይ በሁሉም ዞኖችና ከተማ አስተዳደሮች አፈጻጸሙ ዝቅተኛ በመሆኑ በቀጣይ በጀት አመት ትኩረት ሰጥቶ መስራት ያስፈልጋል፡፡

## የወጣቶችን የስራ አጥነት ችግር መቅረፍ

በበጀት አመቱ የወጣቶችን የስራ አጥነት ችግር ለመቅረፍ በስራ ዕድል ፈጠራ ወይም በጥቃቅንና አነስተኛ ዘርፎች እንዲሰማሩ ስራ ፈላጊ ወጣቶችን የመመዝገብ፣ የመለየትና ግንዛቤ የመፍጠር፣ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ወጣቶች የስራ ዕድል እንዲፈጠርላቸውና ኢንተርፕራይዞች ውጤታማ እንዲሆኑ የመከታተል እና ተጠቃሚ የማድረግ ስራዎችን ማከናወን ተገቢ ነው፡፡ በመሆኑም በገጠርና በከተማ 1,456,071(ወንድ 728,036 ሴት 728,035) ስራ ፈላጊ ወጣቶችን በመለየት የስራ ፈላጊ መረጃ ለማደራጀት ታቅዶ 871,755 (ወንድ 556,699 ሴት 315,076) ስራ ፈላጊ ወጣቶች መለየት ተችሏል፣ አፈጻጸሙም 59.8% ነው፡፡ በመሆኑም በገጠር 530,900፣ በከተማ 340,875 ወጣቶች ተመዝግበዋል፡፡ በተመሳሳይ የወጣቶችን የጠባቂነት አመለካከት መስበር የሚያስችል በኢንተርፕርነርሺፕ ለ1,366,959 (ወንድ 683,480 ሴት 683,479) ወጣቶች የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎችን ለመስራት ታቅዶ 906,219 (ወንድ 555,881 ሴት 350,338) ወጣቶችን ግንዛቤ ማስጨበጥ የተቻለ ሲሆን አፈጻጸሙም 66.2% ነው፡፡

ለስራ ፈላጊ ወጣቶች የስራ ዕድል እንዲፈጠርላቸው ለማድረግ ቅንጅታዊ ስራዎችን በማጎልበት እና አስፈላጊውን ክትትል በማድረግ ለ1,456,071 (ወንድ 728,037 ሴት 728,034) ወጣቶች የስራ እድል እንዲፈጠርላቸው ለማድረግ ታቅዶ 721,701 (ወንድ 479,617 ሴት 242,084) ወጣቶችን የኢኮኖሚ ተጠቃሚ ማድረግ የተቻለ ሲሆን አፈጻጸሙም 49.5% ነው፡፡ የተፈጠረው የስራ እድል ሲታይ ከአካባቢ አኳያ በገጠር ለ463,244 (ወንድ 329,661 ሴት 133,583) በከተማ ደግሞ ለ277,584 (ወንድ 163,991 ሴት 113,593) ወጣቶች የስራ እድል የተፈጠረላቸው ሲሆን አፈጻጸሙም በቅደም ተከተል 53.02% እና 47.6% ነው፡፡

ከስራ ስምሪት አንጻር ሲታይ ደግሞ በቋሚ 439,822 (ወንድ 297,459 ሴት 142,363)

በጊዜያዊ የስራ እድል 281,879 (ወንድ 182,158 ሴት 99,721) ሲሆን አፈጻጸሙም የቋሚ ስራ እድል 60.9% የጊዜያዊ ስራ እድል ፈጠራ ደግሞ 39.06% ነው፡፡ ይህም ከተቀመጠው የመንግስት አቅጣጫ አኳያ የ80/20 የቋሚ/ጊዜያዊ የስራ እድል ድርሻ ሲታይ በቋሚ የስራ ዕድል ከመፍጠር አንፃር ውስንነት እንዳለበት ያመለክታል፡፡በሌላ በኩል የሴት ወጣቶች የተጠቃሚነት ድርሻ ሲታይ ደግሞ 33.2% ነው፡፡

## የወጣቱን ስብዕና መጠበቅ

በአሉታዊ መጤ ባህሎችና አደንዛዥ ዕፆች ዙሪያ ለ1,983,000 (ወንድ 991,500 ሴት 991,500) ወጣቶች እና ለ7,932 (ወንድ 3,966 ሴት 3,966) የሃይማኖት መሪዎች፣ የተቋማት አመራሮች፣ የአሉታዊ መጤ ባህሎችና አደንዛዥ እጾች ተከላካይ ግብረ-ሃይል አባላትና አመራሮች ግንዛቤ ለመፍጠር ታቅዶ ለ602,145 (ወንድ 320,871 ሴት 281,273) ወጣቶች እና ለ17,920 (ወንድ 11712 ሴት 6208) የሃይማኖት መሪዎች፣ የተቋማት አመራሮች፣ የአሉታዊ መጤ ባህሎችና አደንዛዥ እጾች ተከላካይ ግብረ-ሃይል አባላትና አመራሮች ግንዛቤ መፍጠር ተችሏል፡፡ አፈጻጸሙም እንደ ቅደም ተከተላቸዉ 30.7% እና ከ100% ተከናውኗል፡፡ በተመሳሳይ በማህበራዊ ጠንቅ ተጋላጭነት ዙሪያ ለ991,500 (ወንድ 495,750 ሴት 495,750) ወጣቶች ግንዛቤ ለመፍጠር ታቅዶ 804,091(ወንድ447,991 ሴት 356,100) ወጣቶች ግንዛቤ መፍጠር ተችሏል፡፡ አፈፃፀሙም 81.1% ነው፡፡ እንዲሁም ለ594,900 (ወንድ297,450 ሴት 297,450) ሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች ግንዛቤ ለመፍጠር ታቅዶ ለ437,797 (ወንድ 224,364 ሴት193,433) ሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች ግንዛቤ ተፈጥሮሯል፣ አፈፃፀሙም 73.6% ነው፡፡

## የህልውና ዘመቻ

ወጣቶች የመከላከያንና የልዩ ኃይሉን በመቀላቀል የህልውና ዘመቻውን እንዲቀለብሱ ለማድረግ በየደረጃው በተፈጠሩ 122 መድረኮች 97,163 (ወንድ 71,404 ሴት 25,759) ወጣቶች ግንዛቤ እንዲኖራቸው በማድረግ በርካታ ወጣቶች መከላከያንና ልዩ ኃይሉን ተቀላቅለዋል፣ በሚሊሻና ሌሎች አደረጃጀቶች ገብተው በህልውና ዘመቻው ላይ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክተዋል፡፡ በዚህም 20,726 (ወንድ 19,479፣ ሴት 1,247) ወጣቶች ወደ መከላከያ፤ 10,601(ወንድ 10,395፤ ሴት 206) ወጣቶች ወደ አማራ ልዩ ኃይል ተቀላቀለዋል፡፡ በስንቅ ዝግጅትና ሎጀስቲክ አቅረቦት ላይ 90,676(ወንድ 44,065፤ሴት 46,611) ወጣቶች በመሳተፍ 27,996.83 ኩንታል እህል በማዘጋጀት 18,292.8 ኩንታል ወደ ግንባር እንዲላክ የተደረገ ሲሆን ወንድ 24,411 ሴት 1,138 ድምር 25,549 በጎ ፈቃደኛ ወጣቶች ወደ ግንባር የሄዱ የ9,655 ዘማቾችን ሰብል በመሰብሰብ፤ በመውቃትና መሬታቸውን በማረስ፤ 27,541(ወንድ 12,779፤

ሴት 14,762) የዘማች ቤተሰቦችን በመደገፍና በመንከባከብ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ ተችሏል፡፡

ቁስለኞችን መንከባከብ 11,813(ወንድ 6,856፤ ሴት 4,957) በጎ ፈቃደኛ ወጣቶች በአካባቢያቸው በሚገኙ ሆስፒታሎችና ጤና ጣቢያዎች ቁስለኞችና በመንከባከብ አገልግሎት በመስጠት ለ11,013(ወንድ 5,925 ሴት 5,040) ለተፈናቀሉ ወገኖች በጥሬ ገንዘብ 3,599,963 ብር፤እህል 4,377,137 ኩንታል፤ አልባሳትና ጫማ 504 ኩንታል እንዲሁም ሌሎች ምግብ ነክና ምግብ ነክ ያልሆኑ በረካታ ድጋፎች ተደርገዋል፡፡ 528 ተጠርጣሪ ጸጉረ ልውጦችን በህግ ቁጥጥር ስር እንዲውሉ ማድረግ ተችሏል፡፡

በግንባር ለሚገኘው መከላከያ ሰራዊት፣ልዩ ሀይልና ሚላሻ እንዲሁም በየሆስፒታሎች ደም ለሚያስፈልጋቸው የህብረተሰብ ክፍሎች አገልግሎት የሚውልና ህይወትን በአዲስ መልክ ነፍስ እንዲዘራ ለማድረግ የሚያስችለውን ደም በመለገስ በኩል / ወንድ 5,081 ሴት 3193 ድምር 8,274 ወጣቶችን ተሳታፊ በማድረግ 8,274 ዩኒት ደም በመለገስ የቁስለኛ ሰራዊታችንን ህይወት መታደግ ተችሏል፡፡

የህልውና ዘመቻው ስኬታማ እንዲሆን በአጭር ጊዜ እንዲጠናቀቅ እንዲሁም ዘማቾች በትግል ወቅት ወደ ቤተሰቦቻቸው ሳያስቡ በሙሉ አቅማቸውና ትኩረታቸው ወደ ጦርነቱ እንዲሆን በማሰብ በየአካባቢው የዘማች ቤተሰቦችን/ የመከላከያ፣ የልዩሃይል፣ የሚሊሻና የፋኖ ቤተሰቦችን/፣ መንከባከብና ድጋፍ ማድረግ ይገባል፡፡ በዚህም ወንድ 49736 /ወ 48899 ሴ 837/ ዘማቾችን በመለየት 95027 /ወ 61140 ሴ 33887 /የዘማች ቤተሰቦችን ፍላጎትና አካባቢዎችን በመለየት 7795680 የገንዘብና 7081.8 ኩንታል እህል ድጋፍ ማድረግ ተችሏል፡፡ በዚህም ሰብል መሰብሰቡን/ የእርሻ ተግባራትን ጨምሮ 200921 በጎ ፈቃደኛ ወጣቶች ተሳትፈዋል፡፡ የሰብል ስብሰባ ስራዎች ለአብነት 69386 /ወ 47761 ሴ 21625/ በጎፈቃደኛ ወጣቶች በመሰማራት13232/ ወ 8030 ሴ 5202/ የዘማች ቤተሰቦችን ማሳ በግምት ከ1000 ሄክታር በላይ የሚሸፍን ማሳ ሰብል መሰብሰብ ተችሏል፡፡

በክልልና በየደረጃው ባሉ መንግስታዊ አስተዳደር እርከን 243,171.3 ኩንታል እህል ለማሰባሰብ ታቅዶ 86,569.33 ኩንታል እህል በበጎ ፈቃደኛ ወጣቶችና የወጣት አደረጃጀቶች ማሰባሰብ ተችሏል፡፡ በዚህም የእቅዱን 36 በመቶ ማከናወን ተችሏል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም 25,356 ዘይት በሊትር፣ 48,860 ውሃ በደርዘን፣ 48,860 ብስኩት በካርቶን፣ 14,278 የእርድ እንስሳ ፣ 8,531 ፓስታ በፍሬ እሽግ፣ 3,560 ጁስ በደርዘን፣ 3560 ሳሙና በፍሬ በማሰባሰብ ለግንባር ውጊያ ላይ ላለው ሃይላችን፣ ለሰልጣኞች፣ በሆስፒታል ለሚገኙ ለቁስለኛ ሰራዊታችን እና ለተፈናቃይ ወገኖቻችን ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ ይህ ተግባር እውን የሆነው በየደረጃው የሚገኙ

የተቋሙና የሂደቱ አመራሮች፣ ባለሙያተኞች ተግባሩን በባለቤትነት በመስራት የህልውና ዘመቻው ስኬታማና ውጤታማ እንዲሆን የነበራቸው ሚና ከፍተኛ ነበር፡፡

## የበጎ ፈቃድ አገልግሎት

በበጋ ወራት የወጣቶች የበጎ ፈቃድ አገልግሎት እንዲሰጡ ወንድ 1,781,313 ሴት 1,581,313 በድምሩ 3,362,631 ወጣቶችን በተለያዩ ዘርፎች ለማሳተፍ ታቅዶ ወንድ 774,321 ሴት 631,328 በድምሩ 1,405,649 ወጣቶችን ማሳተፍ ተችሏል፡፡ አፈጻጸሙም 41.8% ነው፡፡ በዋናነትም ሰብል ስብሰባ፣ ተፈጥሮ ሃብት ልማትና ጥበቃ፣ ችግኝ መንከባከብ፣ የህልውና ዘመቻ /ወቅታዊ ስራዎች/፣ ተፈናቃይ ወገኖችን መንከባከብና መደገፍ፣ ደም ልገሳ፣ ዘማች ቤተሰቦችን መንከባከብ፣ ቁስለኛ መንከባከብ፣ የአካባቢ ሰላም መጠበቅ፣ ከተማ ጽዳትና ውበት፣መንገድጥገና፣ አረጋዊያንና አቅመ ደካማ ድጋፍ፣ ተማሪ ቅስቀሳና ምዝገባ ተግባራትን ማከናወን ተችሏል፡፡

## የወጣት ስብዕና ልማት ማዕከላትን ማጠናከር

የወጣት ስብዕና ልማት ማዕከላትን በቁሳቁስና በሰው ሃይል በማጠናከርና የማዕከላት አገልግሎት አሰጣጡን በማሻሻል ለ5,673,664 (ወንድ 2,836,832 ሴት 2,836,832) ወጣቶች በስብዕና ልማት ማዕከላት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ በእቅድ ተይዞ 1038,235 (ወንድ 615,651 ሴት 422,584) ወጣቶችን በስብዕና ማዕከላት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ የተቻለ ሲሆን አፈጻጸሙም 18.3% ነው፡፡ አፈጻጸሙ ዝቅተኛ የሆነበት ምክንያት የስብዕና ልማት ማዕከላትን በቁሳቁስና በሰው ሃይል በማጠናከርና የማዕከላት አገልግሎት አሰጣጡን በማሻሻል በኩል የሚደረገው ጥረት አነስተኛ በመሆኑ ነው፡፡ በተመሳሳይ 78 የወጣቶችን የስብዕና ልማት ማዕከላትን ለአካል ጉዳተኛና ለሴት ወጣቶች ምቹ እንዲሆኑ ለማድረግ በዕቅድ ቢያዝም ያልተከናወነ ተግባር ነው፡፡

## የስፖርት አደረጃጀቶችን ማጠናከር

በበጀት አመቱ ከክልል እስከ ወረዳ 217 መንግስታዊ ስፖርት ተቋማትን ለማደራጀት ታቅዶ 211 መንግስታዊ ስፖርት ተቋማትን ተደራጅተዋል፣ አፈጻጸሙም 97% ነው፡፡በተጨማሪም የተደራጁ ህዝባዊ የስፖርት አደረጃጀቶች በክልል 50፣ በዞን 750፣ በወረዳ 8,600 እና በቀበሌ 15,600 በድምሩ 25,000 አደረጃጀቶችን ለማጠናከር ታቅዶ በክልል 23፤ በዞን 687፣ በወረዳ 2,986 እና በቀበሌ 5,718 በድምሩ 9,414 ማከናወን ተችሏል፣ አፈፃፀሙም በክልል 46% ፤በዞን 92%፤ በወረዳ 34.7% እና በቀበሌ 36.6% ሲሆን በጥቅል 38% ነው፡፡

## የስፖርት ክለቦችን ማጠናከር

በ2014 ዓ.ም በተለያዩ የስፖርት መስኮች ክለቦችን ማጠናከርና በአዲስ በማቋቋም (በማደራጀት) ረገድ 90 ክለቦችን ለማጠናከርና ለማደራጀት ታቅዶ 196 ክለቾች ለማጠናከርና ለማደራጀት የተቻለ ሲሆን አፈፃፀሙ ከ100% በላይ ነው፡፡ በተመሳሳይ 798 ልዩ ልዩ የስፖርት ቡድኖችን ለማጠናከር ታቅዶ 2,909 ቡድኖች የተጠናከሩ ሲሆን አፈፃፀሙም ከ100% በላይ ሆኗል፡፡

በየደረጃው በክልል 23፤ በዞን 255፤በወረዳ 1,805፣ በቀበሌ 3,475 በድምሩ 5,558 ፌዴሬሽንና ኮሚቴዎችን ለማጠናከር ታቅዶ በክልል 23፣ በዞን 229፣ በወረዳ 1,837 እና በቀበሌ 2,829 በድምር4,918 ማከናወን ተችሏል፣ አፈፃፀሙም 88.4%ነው፡፡ በክልል 23፤ በዞን 75 እና በወረዳ 224 በድምሩ 322 የዳኞች ማህበር ማቋቋምና ማጠናከር ታቅዶ በክልል 14፣ በዞን 39፣ በወረዳ 150 በጥቅሉ 203 ማጠናከር ተችሏል፣ አፈጻጸሙም በቅደም ተከተላቸው 61%፤ 52%እና 67% ሲሆን በጥቅል 63% ነው፡፡ በተጨማሪም በክልል 23፤ በዞን 90፣ በወረዳ 239 በድምሩ 352 የአሰልጣኞች ማህበር ማቋቋምና ማጠናከር ታቅዶ በክልል 19፣ በዞን 41፣ በወረዳ 122 በጥቅሉ 182 ማጠናከር ተችሏል፣ አፈጻጸሙም በቅደም ተከተላቸው 83%፤ 46% እና 51% ሲሆን በጥቅል አፈጻጸሙም 52% ነው፡፡

በበጀት አመቱ 215 (በክልል1፤ በዞን 15፤ በወረዳ 199) የስፖርት ሳይንስ የሙያ ማህበራትን በየደረጃው ለማጠናከርና ለማደራጀት ታቅዶ በክልል 1፤ በዞን 9 እና በወረዳ 112 በድምሩ 122 ማከናወን ተችሏል፣ አፈፃፀሙ በክልል 100%፣ በዞን 60% እና በወረዳ ደረጃ 56.2% ነው፣ በጥቅልም 57% ነው፣ በክልል 20፣ በዞን 75፣ በወረዳ 221 በድምሩ 316 የቴክኒክ ኮሚቴ ማቋቋምና ማጠናከር ታቅዶ በክልል 23፣ በዞን 73 እና በወረዳ 54 በድምሩ 150 የቴክኒክ ኮሚቴ ተጠናክሯል፣ አፈጻጸሙም 47.4% ነው፡፡

## የስፖርት የፋይናንስ አቅምን ማሳደግን

ከስፖርት ፖሊሲ የትኩረት አቅጣጫዎች መካከል አንዱ ስፖርት ከመንግስት የበጀት ድጎማ ደረጃ በደረጃ የሚላቀቅበትና ራሱን የሚችልበት ምቹ ሁኔታ መፍጠር መሆኑ ይታወቃል፡፡በመሆኑም በየደረጃዉ ከህብረተሰቡ ብር 80,000,000 ለመሰብሰብ ታቅዶ ብር **69,246,233** ተሰብሰቧል፤ አፈፃጸሙ 87% ነው፡፡ ፕሮጀክት በመቅረፅ ብር 40,000,000 ለማሰባሰብ ታቅዶ ብር 21,277,266 የተገኘ ሲሆን አፈፃፀሙም 53.1% ሆኗል፡፡ በህዝባዊ አደረጃጀቶች ፕሮጀክት በመቅረጽ ከስፖንሰርሽፕ 1,500.000 ብር ለማሰባሰብ ታቅዶ 1,767,800.00 ማሰባሰብ ተችሏል፤ አፈፃፀሙ100% ሲሆን ከመንግስት ድጋፍ ለማግኘት

180,000,000 ታቅዶ 62,327,477 ተከናውኗል፤አፈፃፀሙም 34.6% ሆኖ ታይቷል፡፡ ከስቴዲየም መግቢያ ቲኬት ገቢ ብር 2,500,000 ለማሰባሰብ ታቅዶ 569,960 ተሰብስቧል፡፡ አፈፃፀሙም 23% ነው፡፡ በተጨማሪ ከሜዳ ልዩ ልዩ ገቢዎች ብር 3,635,000 ለማሰባሰብ ታቅዶ ብር 6,338,028 ለመሰብሰብ ተችሏል፤ አፈፃፀሙም ከ100% በላይ ነው፡፡ስፖርትን በባለቤትነት ይዘው ከሚመሩ መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ብር 180,000,000 ለማሰባሰብ ታቅዶ ብር 100,112,655 ተሰብስቧል፡፡ አፈፃፀሙም 56%ነው፡፡ እንዲሁም ከክለቦች ለውድድር መመዝገቢያ 800,000 ለማሰባሰብ ታቅዶ 953,758.00 መሰብሰብ ተችሏል፤አፈፃፀሙም ከ100% በላይ ነው፡፡ በተጨማሪም ከዲያስፖራ ማህበረሰብ 400,000 ብር ለማሰባሰብ ታቅዶ 266,480 ብር መሰብሰብ ተችሏል፡፡ አፈፃጸሙም 66% ነው፡፡

## የስፖርት ማሰልጠኛ ተቋማትን ማሳደግ

በበጀት አመቱ ሁለት ለተገነቡ የስልጠና ማዕከላት በመዋቅሩ መሰረት የሰው ሀይል እንዲሟላላቸው ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ፣ ተከናውኗል፡፡ 6 የመ ደረጃ፤ 5 የሐ ደረጃ፤1 የለ ደረጃ እንዲሁም 1 የሀ ደረጃ ያላቸዉ የስፖርት ማስልጠኛ ማዕከላት ለመገንባት ታቅዶ 4 የመ ደረጃ እንዲሁም 1የሀ ደረጃ ያላቸዉ የስፖርት ማሰልጠኛ ማዕከላት ተገንብተዋል፡፡ አፈፃፀማቸው በቅደም ተከተል 67%፤ 80%ና 100% ነው፡፡

## በስፖርት አበረታች ቅመሞች ዙሪያ ግንዛቤ መፍጠር

በበጀት አመቱ በፀረ-ዶፒንግ ዙሪያ ለተለያዩ የህብረተሠብ ክፍሎች ወንድ 150፣ ሴት 150 ድምር 300 ግንዛቤ ለመፍጠር ታቅዶ ወንድ 4,957፣ ሴት 2,512 ድምር 7,469 ግንዛቤ ተፈጥሯል፣ አፈፃፀሙም ከ100% በላይ ነው፡፡ በስፖርት ህክምና ለባለሙያዎች ስልጠና ወንድ 35፣ ሴት 35 ድምር 70 ታቅዶ ወንድ 15፣ ሴት 9 ድምር 24 ባለሙያዎች ስልጠና ተሰጥቷል፣ አፈፃፀሙም ከ 34.2% ነው፡፡

## የስፖርት ኢንዱስተሪውን ማስፋፋት

በበጀት አመቱ በስፖርት ኢንዱስትሪው ዙሪያ ወንድ 1,000፣ ሴት 1,000 ድምር 2,000 ባለሃብቶች እንዲሳተፉ ታቅዶ ወንድ 842፣ ሴት 521፣ ድምር 1363 ግንዛቤ ተፈጥሯል፣ አፈፃፀሙም 68.1% ነው፡፡ በስፖርት ኢንቨስትመንት ዙሪያ ወንድ 2,500፣ ሴት2,500 ድምር 5000 የህብረተሰብ ክፍሎች ግንዛቤ ለመፍጠር ታቅዶ ወንድ 2,218፣ ሴት 1286 ድምር 3,504 ግንዛቤ መፍጠር ተችሏል፣ አፈፃፀሙ 70%ነው፡፡ በስፖርት ኢንቨስትመንት ለባለሃብቶች የብቃት ማረጋገጫ በመስጠት ለማሰማራት ወንድ 75፣ ሴት 75 ድምር 150 ታቅዶ ወንድ 200፣ ሴት 89 ድምር 289 መስጠት ተችሏል፣ አፈፃፀሙ ከ100% በላይ ነው፡፡

በስፖርት ኢንቨስትመንት ወንድ 3,500፣ ሴት 3,500 ድምር 7,000 ወጣቶች የስራ ዕድል

ለመፍጠር  ታቅዶ ወንድ 2,671፣ ሴት 1,509 ድምር 4,180 ዜጎች የስራ ዕድል መፍጠር ተችሏል፡፡ አፈፃፀሙ 60% ነው፡፡

ባለሃብቶችን በስፖርት ትጥቅ አስመጭነት ለማሰማራት  ወንድ 60፣ ሴት 60 ድምር 120 ታቅዶ ወንድ 42፣ ሴት 3 ድምር 45 ተከናውኗል፣ አፈፃፀሙም 38%ነው፡፡  ባለሃብቶች በስፖርት ኢንቨስትመንት 879,000,000 ብር ካፒታል እንዲያስመዘግቡ ታቅዶ 120,150,000.00 ተከናውኗል፤ አፈፃፀሙም 14%ነው፡፡ እንዲሁም  215 ወጣቶች በማርሻል አርት ስፖርት ወደ ኢንቨስትመንት እንዲሰማሩ ታቅዶ 82 ወጣቶች እንዲሰማሩ ተደርጓል፡፡ አፈፃፀሙም 38.1% ነው፡፡ በተጨማሪም የስፖርት ጅምናዝየም ለማስፋፋት 50 ታቅዶ 31 ተከናውኗል፣ አፈፃፀሙም 62% ነው፡፡

በስፖርት ኢንቨስትመንት ወንድ 3,500፣ ሴት 3,500 ድምር 7,000 ወጣቶች የስራ ዕድል ለመፍጠር  ታቅዶ ወንድ 2,671፣ ሴት 1,509 ድምር 4,180 ዜጎች የስራ ዕድል መፍጠር ተችሏል፣ አፈፃፀሙ 60% ነው፡፡ ባለሃብቶችን በስፖርት ትጥቅ አስመጭነት ለማሰማራት ወንድ 60፣ ሴት 60 ድምር 120  ታቅዶ ወንድ 42፣ ሴት 3 ድምር 45 ተከናውኗል፣ አፈፃፀሙም 38%ነው፡፡

## ሴቶች፤ ህፃናትና ማህበራዊ ጉዳይ

ሴቶች፣ ህፃናትና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ የተለያዩ ፖሊሲዎችንና ስትራቴጂዎችን በመንደፍ ሴቶች፣ ህጻናት፣ አካል ጉዳተኞች፣ አረጋዊያን እና ሌሎች ለችግር ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎችን ተጠቃሚና ተሳታፊ እያደረገ ይገኛል፡፡ በዚህም በኢኮኖሚያዊ፣ በማህበራዊና ለፖለቲካዊ ችግሮች ግንባር ቀደም ተጋላጭና ተጎጂ የሆኑትን ሴቶች፣ ህጻናት፣ አካልጉዳተኞች፣ አረጋዊያን እና ሌሎች ለችግር ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎችን ችግር ለመፍታትና ጥያቄዎቻቸውንም ለመመለስ ተቋማትን መልሶ በማደራጀት እና የአስር ዓመት መሪ ዕቅድ በመከለስ ወደ ተግባር ገብቷል፡፡

### የሴቶች፣ ህፃናት፣ የአካል ጉዳተኞችንና አረጋዊያን መብት ማስጠበቅ

በበጀት ዓመቱ በሴቶች፣ ህፃናት፣ አካል ጉዳተኞችና አረጋዊያን ላይ አካላዊ፤ አእምሮአዊ፣ ስነልባናዊና ማህበራዊ ተጽዕኖ የሚያሳድሩና ለዘላቂ ችግርና አካል ጉዳት የሚዳርጉ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች እንዲወገዱ ለ3,792,368 (ወንድ1,896,184 ሴት11,896,184) የህብረተሰብ ክፍሎች ትምህርት ለመስጠት ታቅዶ ለ3,158,627 (ወንድ1,784,857 ሴት1,373,7700)ለሚሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ግንዛቤ ተፈጥሯል፡፡

ከዚህ ጋር በተያያዘ በየደረጃው ለሚገኙ 4167 የጎጂ ልማዳዊ ድርጊት ጥምረቶችን ለማጠናከር ታቅዶ 2884 ጥምረቶች ላይ ክትትልና ጥረት ተደርጓል፣ አፈፃፀሙም 69% ነው፡፡ በተሰራው

ስራ 959 ቀበሌዎችን ከልጅነት ጋብቻ ነጻ ለማድረግ ታቅዶ 371 ቀበሌዎች ዝግጁ ሆነዋል፣ አፈፃፀሙም 39% ነው፡፡ በመሆኑም አፈፃፀሙ ዝቅተኛ በመሆኑ በቀጣይ በጀት አመት ትኩረት ሰጥቶ መስራት ያስፈልጋል፡፡



በመገንባት ላይ የሚገኝ የአረጋውያን ማዕከል-ታች አርማጭሆ(ሳንጃ)

## የሴቶችን ደህንነት ማስጠበቅ

በበጀት ዓመቱ ጾታዊ ጥቃት የሚያደርሰውን ጉዳት የሚያስገነዝቡ ድርብ ግፍ ያልተጸፈባቸው ወረቀቶች በሚሉ ርዕሰ ጉዳዮች በአሚኮ ዶክመንተሪ ፊልሞች በአየር ላይ በማዋል ህብረተሰቡ ትምህርት እንዲያገኝ ተደርጓል፡፡ የልጅነት ጋብቻ ይቁም ፕሮግራሙ በሚተገበርባቸው ወረዳዎች ዳሰሳዊ ጥናት በማስጠናትና በፕሮግራሙ የተሻለ ውጤት እና ተሞክሮ ያላቸው ወረዳዎች ያስመዘገቡ ወረዳዎች የተሻለ ተሞክሮቻቸውን ከተቋሙ ፖሊስና ፍትህ ለተውጣጡ 55 (ወንድ 40 ሴት 15) አመራሮችና ባለሙያዎች አቅርበው የልምድ ልውውጥ ተካሂዷ፡፡የጎጅ ልማዳዊ ድርጊቶች የቴክኒክ ኮሚቴ አባላትን የስድስት ወራት አፈጻጸም በመገምገም የቀጣይ ስድስት ወራት ዕቅድ እንዲከለስና የተጠናከረ ስራ እንዲሰራ ተደርጓል፡፡ በመድረኩም 23 (ወንድ 20 ሴት 3) ተሳትፈዋል፡፡ እንዲሁም 4741 የልጅነት ጋብቻ ጥቆማዎች የደረሱ ሲሆን 1246ቱን ደግሞ በድርድር ማቋረጥ ተችሏል፡፡ 825 ደግሞ ለጋብቻ የእድሜ ምርመራ አድርገው ያላለፉ ልጃገረዶች ናቸው፡፡

በሌላ በኩል በአሸባሪው ቡድን አስገድዶ መደፈር የተፈፀመባቸው የ1799 ሴቶችና የ140 ህፃናት መረጃ ተሰብስቧል፡፡ በመረጃ ከተያዙት ውስጥ 1521 የስነ ልቦና፣ 1061 የህክምና፣ 90 የህግ

አገልግሎት እና 1939 የገንዘብ ድጋፍ አግኝተዋል፡፡ በዚህም 11,370,600 ብር ድጋፍ እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ የህክምና አገልግሎት ካገኙት መካከል 16 ሴቶች የኤች.አይ.ቪ ኤድስ የምርመራ ውጤታቸው ፖዘቲቭ፣ 40 እርግዝና ተፈጥሮ የጽንስ ማቋረጥ ያደረጉ እና 25 ለአባላዘር በሽታ የተጋለጡ መሆናቸው የህክምና ውጤታቸው አሳይቷል፡፡

በተመሳሳይ በደሴ የአንድ መስኮት አገልግሎት መስጫ ማዕከል 71 ሴትና 3 ወንድ ህጻናት እንዲሁም በደሴ ሴፍ ሀውስ 31 ህጻናት፤ በደብረብርሀን የአንድ መስኮት አገልግሎት መስጫ ማዕከል 15 ህጻናት፤ በአጋር ኢትዮጵያ 70 ህጻናት፤ በድምሩ 218(ወንድ.3) ህጻናት በየማዕከላቱ የተለያዩ አገልግሎቶችን አግኝተዋል፡፡ ከነዚህ መካከልም 131ዱ የማህበራዊና ስነ-ልቦናዊ ድጋፍና 216 የጤና፤16 የህግ አገልግሎት አግኝተዋል፡፡ በባህር ዳር፤ ደ/ብርሀን እና ደሴ ከተሞች ለሚገኙ የአንድ መስኮት አገልግሎት መስጫ ማዕከላት የአልባሳት፤ የሴቶች ንጽህና መጠበቂያ ቁሳቁሶችና የቢሮ ቁሳቁሶች ድጋፍ ተደርጎላቸዋል፡፡ ጥቃት ለሚደርስባቸው ሴቶች ሁለንተናዊ ድጋፍ አግኝተው ወደ መደበኛ ህይወታቸው እንዲመለሱ የአንድ ማዕከል እና የማገፊያ ቤት ማዕከላትን ማቋቋምና ማጠናከር ተችሏል፡፡ በመሆኑም በበጀት ዓመቱ ደብረ ብርሀን፣ ወልዲያ፣ በዋግኽምራ፣ በኮምበልቻ፣ ደብረ-ማርቆስና ጎንደር ስድስት አዲስ ማዕከላት ተቋቁሟል፡፡ እንዲሁም አራት የአንድ ማዕከል አገልግሎቶች መሰጫ ተቋቋማትን ለማጠናከር ታቅዶ ስድስት ማዕከላትን የማጠናከር ስራ ተሰርቷል፡፡




በህልውና ዘመቻ ባለቤታውን ላጡሴቶች ድጋፍ ሲደረግ-ባህርዳር

## ለሴቶች የተደረገ ድጋፍ

4228 ሴቶች ቤታቸው የተቃጠለባቸው፣ 127,263 ለተለያዩ ችግሮችና ጉዳቶች ተዳርገው ድጋፍ የተደረገላቸው እና 732,767 ሴቶች የበነ ፈቃድ አገልግሎት በመስጠት ለወገን ደራሽነታቸውን አሳይተዋል፡፡ በአሁኑ ሰዓት 242,761 በላይ ሴቶች የተፈናቀሉ ሲሆን 40,010 ሴቶች በጊዜያዊ ማቆያዎች፣ 202751 ደግሞ በማኅበረሰቡ ውስጥ የሚገኙ ሲሆን ከእነዚህም ውስጥ 12,614 የሚያጠቡና 6,133 ነፍሰ ጡር ሴቶች ናቸው፡፡

የተለያዩ ድርጅቶችን በማስተባበር ለ86,364 ሴቶች 314,626,046 የብር ድጋፍ ፣1200 ነፍሰ ጡር እና አጥቢ እናቶች 4,271,385 ብር የቢሮው ድጋፍ 24,801 በላይ ሴቶች 50,079,960 የዓይነት ድጋፍ፣ 67,248 ህፃናት 230,265,350 ብር ድጋፍ እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ ከነዚህም መካከል (1,515 ህፃናት 8,864,415) ቢሮው በተለያዩ መንገዶች ካገኘው ሀብት ድጋፍ አድርጓል፡፡ 24,073 በላይ ህፃናት 49,487,152 ግምት ያለው የዓይነት ድጋፍ፣ ለ2,230 አካል ጉዳተኞችና 25,263 አረጋዊያን 25,159,198 ብር ድጋፍ፣ 9,383 በላይ አካል ጉዳተኞችና አረጋውያን 5,623,540 ግምት ያለው የዓይነት ድጋፍ አግኝተዋል፡፡

## ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀን

ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀን በሀገራችን ለ46ኛ ጊዜ፣ በክልላችን ለ27ኛ ጊዜ "እኔ የእህቴ ጠባቂ ነኝ" በሚል ሀገራዊ መሪ ቃል የተከበረ ሲሆን ይህን ምክንያት በማድረግ በርካታ የንቅናቄ ስራዎች ተሰርተዋል፡፡ በዓሉ በክልል፣ በሁሉም ዞኖች፣ በ165 ወረዳዎችና 2036 ቀበሌዎች ላይ የተከበረ ሲሆን ከቀበሌ እስከ ክልል በየደረጃው 623,189(ወንድ 257,995 ሴት 361,794 ተሳትፈዋል፡፡ ለበዓሉ ማስፈጸሚያ ከተለያዩ አካላት ከ9.7ሚሊዮን በላይ ብር በማሰባሰብ ጥቅም ላይ ውሏል፡፡




**ነጭ ሪባን ቀን በአደባባይ ሰልፍ ሲከበር-ባህርዳር**

## የህፃናትን መብትና ደህንነት ማስጠበቅ

የአፍሪካ ህፃናትን መብትና ደህንነት ከማስጠበቅ አኳያ ኩነቶችን በመጠቀም 615,214(ወንድ 310,524 ሴት 304,609) ህጻናትን እና 519,624 (ወንድ 271,896 ሴት 247,728) የህብረተሰብ ክፍሎች በተገኙበት በተለያዩ ፕሮግራሞች ለማክበር ዕቅድ ተይዞ 52,291 (ወንድ.26,053 ሴት.26,238) ህጻናትንና 22,819(ወንድ.10,908 ሴት.11,911) የህብረተሰብ ክፍሎች በተገኙበት የህጻናት መብቶችና ድንጋጌዎቻቸው ከህጻናት መብት ጥሰትና ብዝበዛዎች አኳያ በሚሉና መሰል ርዕሰ ጉዳዮች ዙሪያ የህጻናት ፓርላማ አመራሮችና ስራ አስፈጻሚዎች፤ ባለሙያዎችና ጥሪ የተደረገላቸው የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች በተገኙበት በየደረጃዉ የውይይት መድረክ በማዘጋጀት ተከብሯል፡፡ በተመሳሳይ 602,882 (ወንድ. 304,386 ሴት. 298,496) ህጻናትንና 564,384 (ወንድ. 292,384 ሴት. 272,000) የህብረተሰብ ክፍሎች በተገኙበት የአፍሪካ የህጻናት ቀንን በተለያዩ ፕሮግራሞች ለማክበር በተያዘው ዕቅድ መሰረት 373,728 (ወንድ. 188,409 ሴት .185,319) ህጻናትንና 328,648 (ወንድ. 178,492 ሴት. 152,156) የህብረተሰብ ክፍሎች በተገኙበት ዕለቱ እንደ ሀገር የተቀመጠውን ሀገራዊ መሪ ቃልን መሰረት በማድረግ ከክልል ጀምሮ በተዋረድ እስከ ወረዳ ተከብሯል፡፡

በክልል ደረጃ በተከበረበት ዕለትም “ኑ ትውልድ እንቅረጽ ሀገርን እንገንባ” በሚል ከክልሉ ወቅታዊ ሁኔታ አንጻር ህጻናት ያሉበትን ነባራዊ ሁኔታ የሚያሳይና የህጻናትን መብትና ድህነት ለማስጠበቅ ተቋሙ እያከናወናቸው ባሉ ተግባራት ላይ ያተኮረ ውይይት ተደርገዓል፡፡



**የአብክመ የመንግስት ኮሙዩኒኬሽን ቢሮ**

## የህፃናት ወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ

ዓለም አቀፍ የአካል ጉዳተኞችን መብትና ደህንነት ከማስከበር አኳያ ኩነቶችን መሰረት በማድረግ ለ148 (ወንድ118፣ ሴት 30) ተሳታፊዎች በተገኙበት ዓለም አቀፍ የሥጋ ደዌ ቀን ተከብሯል፡፡ የህፃናትን መብት ከማስጠበቅ አኳያ በበጀት ዓመቱ 599,738 (ወንድ. 299.869 ሴት. 299.869) የህብረተሰብ ክፍሎች በህጻናት ኩነቶች ምዝገባ፤ አላማና አስፈላጊነት ዙሪያ ግንዛቤ በመፍጠር ህፃናት የልደት ሰርተፊኬት እንዲያገኙ ለማድረግ በዕቅድ ተይዞ 513,328 (ወንድ. 264,777 ሴት. 248,551)የሚሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ግንዛቤ እንዲያገኙ ተደርጓል፣ የግንዛቤ ፈጠራ አፈፃፀሙም 85% ነው፡፡

ግንዛቤ ከተፈጠረላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች መካከልም 211,362 (ወንድ.106,343 ሴት.105,019) እንዲመዘገቡ የተደረገና ከነዚህ መካከል 162,452/32%/ (ወንድ.82,089 ሴት.80,363) ህፃናት የልደት ሰርተፍኬት እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ ከተመዘገቡት ህጻናት መካከልም 1,979ቱ (ወንድ.993 ሴት.986) የልደት ሰርተፍኬት ያገኙ አካል ጉዳተኛ ህፃናት ናቸው፡፡ የህፃናት መብት ከሚጠበቅባቸው መካከል አንዱ የአባትነት መብት ማወቅ ሲሆን 60 (ወንድ 30 ሴት 30) በህግ የአባትነትን የማወቅ መብት ጋር ተያይዞ የቀረቡ ሲሆን ለ47 (ወንድ. 27 ሴት.20) ህጻናት በህግ የአባትን የማወቅ መብታቸው እንዲረጋገጥላቸው የማድረግ ስራ ተሰርቷል፣ አፈፃጸሙም 78% ነው፡፡ በሌላ በኩል ህፃናት በህግ ፊት ቀርበው ሀሳባቸውን በነፃነት እንዲያቀርቡ ከማድረግ አኳያ 24 የህፃናት ተስማሚ ችሎቶችን ለማጠናከር በዕቅድ ተይዞ 9 ችሎቶችን ማጠናከር የተቻለ ሲሆን በዚህም 344(ወንድ. 169 ሴት.175) ህጻናት በነዚህ ምቹ የህፃናት ችሎቶች አገልግሎት እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ የመብት ጥሰት ለደረሰባቸው አካል ጉዳተኞች የህግ ጥበቃ እንዲያገኙ እንደ አመጣጡ የድጋፍና ክትትል አገልግሎት ለመስጠት በተያዘው ዕቅድ መሠረት 221 (ወንድ 99 ሴት 122) አካል ጉዳተኞች ባቀረቡት ቅሬታ መሠረት የሁሉንም ችግሮች መፍታት ተችሏል፡፡ የመብት ጥሰት ለደረሰባቸው 209 (ወንድ 114 ሴት95) አረጋዊያን የሕግ ጥበቃ እንዲያገኙ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን መብታቸውን ለማስከበር ታቅዶ 286 (ወንድ 146 ሴት 140) በተሰራው ስራ መብታቸው ተከብሯል፡፡

# ባህልና ቱሪዝም

## የቅርስ ጥበቃና እንክብካቤ ማሳደግ

በበጀት ዓመቱ 1200 መድረኮችን በማዘጋጀት ለ1,000,002 የህብረተሰብ ክፍሎች በቅርስ ጥበቃና እንክብካቤ ዙሪያ የግንዛቤ ትምህርት ለመስጠት ታቅዶ በ892 መድረኮች ለ295,868

ወንድ እና 252,118 ሴቶች በድምሩ ለ547,986 የህብረተሰብ ክፍሎች የግንዛቤ ትምህርት ተሰጥቷል፡፡ በሁሉም ዞኖችና ከተማ አስተዳደሮች በ295 ቅርሶች ላይ የጉዳት መጠን ልየታ ለማካሄድ ታቅዶ በ240 ቅርሶች ላይ የጉዳት ልየታ ተከናዉኗል፡፡ በተጨማሪም ለ30 ቋሚ ቅርሶች የጥገና ስራ ለመስራት ታቅዶ ለ37 ቅርሶች መፈፀም ተችሏል፡፡ እንዲሁም 530 ለሚሆኑ ተንቀሳቃሽ ቅርሶች የጥገና ስራ ለመስራት ታቅዶ ለ471 ተንቀሳቃሽ ቅርሶች የጥገና ሰራ ማከናወን ተችሏል፡፡ አፈጻጸሙም ከተያዘው ዕቅድ አንጻር በጉዳት ልየታ 82% ማከናወን ሲቻል ከቅርስ ጥገና አንጻር ከእቅድ በላይ እና ከተንቀሳቃሽ ቅርስ አንጻር 89% ተከናውኗል፡፡ በተመሳሳይ በሁሉም ዞኖች እና ከተማ አስተዳደሮች ለ1300 ቋሚና ለ11,806 ተንቀሳቃሽ ቅርሶች የእንክብካቤ እና የጽዳት ስራ ለመስራት ታቅዶ ለ891 (74%) ቋሚ እና ለ18,514 (ከእቅድ በላይ) ተንቀሳቃሽ ቅርሶች የጽዳት እና የእንክብካቤ ሥራ ተሰርቷል፡፡ ለ184 ቋሚ ቅርሶች የይዞታ ማረጋገጫ እና 289 ቋሚ ቅርሶች የወሰን ክለላ እንዲያገኙ የድጋፍና ክትትል ስራ ለመስራት ታቅዶ በተደረገው ድጋፍና ክትትል 358 ቋሚ ቅርሶች የይዞታ ማረጋገጫ እና 70 ቅርሶች የወሰን ክለላ እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡

የቋሚና የተንቀሳቃሽ ቅርሶችን የምዝገባ ሽፋን 50% ለማከናወን በእቅድ ተይዞ የቋሚ ቅርሶች 55% እና የተንቀሳቃሽ ቅርሶች 45% ምዝገባ ማከናወን ተችሏል፡፡ በተጨማሪም 32 የማይዳሰሱ ባህላዊ ቅርሶችን ለመመዝገብ ታቅዶ 40(ከእቅድ በላይ) የማይዳሰስ ቅርስ የምዝገባ ስራ ተከናውኗል፡፡

በክልሉ በ4 ሄክታር መሬት ላይ ለቅርስ ጥገናና እንክብካቤ ግብዓት የሚሆኑ የአገር በቀል እፅዋትን ለማልማት ታቅዶ በ5100 ካሬ ሜትር መሬት የአገር በቀል እፅዋትን የመትከል ስራ በጎንደር ከተማ አስተዳደር ባህልና ቱሪዝም መምሪያ ተሰርቷል፡፡ የክልሉን ባህልና ቋንቋዎች ልማትና አጠቃቀምን በማሳደግ በኩል የአዊኛ ቋንቋ ልማት አተገባበር ጥናትን አስመልክቶ ለጥናት ግብዓት የሚሆኑ መረጃዎችን የማጥራት፣ የማደራጀትና የመተንተን ሥራ ተከናውኗል፡፡ በ173 ዝግጅቶች ከክልል እስከ ወረዳ ድረስ ዓለም አቀፍ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ቀን ለማክበር ታቅዶ በ92 የተለያዩ ዝግጅቶች ቀኑ ተከብሯል፡፡ የአፍ መፍቻ ቋንቋ የመናገር ቀን በዓል አከባበር መነሻ ሰነድ ተዘጋጅቶ ለዞኖችና ከተማ አስተዳደሮች ተልኳል፡፡ የአፍ መፍቻ ቋንቋ የመናገር ቀን በዓል አከባበር መነሻ ሰነድ ተዘጋጅቶ ለዞኖችና ከተማ አስተዳደሮች ተልኳል፡፡ በመሆኑም ልሳነብዙህነት ለአገራዊ "መግባባት" በሚል መሪ ቃል በዓሉን በስነጽሁፍ ዝግጅት፣ የቋንቋ ፖሊሲ ይዘቶችን በማስተዋወቅ፣ በጥያቄና መልስ ውድድር ወዘተ እንዲያከብሩ መነሻ ሰነድ ተዘጋጅቶ በተላከው መሰረት በከተማ አስተዳደሮች፤ በዞኖች እና በወረዳዎች ተሳትፈዋል፡፡ በእነዚህ መድረኮች ወንድ 15,227 እና ሴት 1 11,182 በድምሩ 26,409

**የአብክመ የመንግስት ኮሙዩኒኬሽን ቢሮ**

የህብረተሰብ ባህላዊ ተምሳሌቶች /Icons/ ለመለየት የሚያስችል መነሻ ሰነድ ለማዘጋጀት ታቅዶ በዕቅዱ መሰረት ተከናውኗል፡፡ በተጨማሪም አገር አቀፍ የግዕዝ ጉባዔን ከፌደራልና ከደ/ጎንደር ዩንቨርስቲ ጋር በጋራ ለማካሄድ በታቀደው መሰረት ጉባዔው ተካሂዷል፡፡

## በክልሉ የሚከበሩ ነባር ባህላዊ ክብረ-በአላት

በክልሉ የሚከበሩ ነባር ባህላዊ ክብረ-በዓላት በማልማት ለማክበር በታቀደው መሰረት የመስቀል በዓል፣ ግሸን፣ ገና/ላሊበላ፣ የቡሄ፣ ዘመንመለወጫ፣ መውሊድ፣ የጥምቀት በአላትን በበተለይ የባህል አልባሳት ተጠቃሚነት እንዲያድግ ግንዛቤ የመፍጠር ስራ ከመሰራቱ ባሻገር ባህላዊ ስርዓቱን በጠበቀ መልኩ እንዲከበር የማድረግ ስራ ተከናውኗል፡፡ በሌላ በኩል በጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች እና አስተሳሰቦች ዙሪያ በ4500 የውይይት መድረኮች ለ900,000 የህብረተሰብ ክፍሎች የግንዛቤ ትምህርት ለመስጠት ታቅዶ በ1426 መድረኮች ለ287467 ወንድ እና ለ274826 ሴት በድምሩ ለ562293 የህብረተሰብ ክፍሎች ግንዛቤ መፍጠር ተችሏል፡፡

## የስነ-ጥበብና የኪነ-ጥበብ ስራዎችን ማጎልበት

የክልሉን የስነ-ጥበብና የኪነ-ጥበብ ለማጎልበት በሁሉም ዞኖች እና ከተማአስተዳደሮች 588 ነባር የባህል ቡድኖችን በድግግሞሽ በሙያ፣ በስልጠና በቁሳቁስ ለመደገፍ እና 135 አዳዲስ የኪነጥበብ ክበባትን ለማቋቋም ታቅዶ 427 ነባር የባህል ቡድኖችን በድግግሞሽ በመደገፍ እና 90 አዳዲስ ክበባትን ማቋቋም በመቻሉ አፈጻጸሙን ከነባር ቡድኖች ድጋፍ አንጻር 73% እና አዲስ ክበባትን ከማቋቋም አንጻር 81% ማድረስ ተችሏል፡፡ በተጨማሪም ከክልል እስከ ወረዳ የሚካሄዱ ዓመታዊ የኪነ-ጥበብ ውድድሮችን ለማካሄድ በታቀደው መሰረት የቀረቡ የውድድር ስራዎች ማለትም 9 የተውኔት የድርስት ስራዎች፣14 የስዕልና 6 የቅርጻቅርጽ ስራዎች፣ 29 የግጥምና 11 የአጭር ልብ-ወለድ ስራዎች እና 12 የሙዚቃ ስራዎች በየዘርፉ ባለሙያዎች የማወዳዳር ስራ ተሰርቷል፡፡ በተመሳሳይ 666 የስነጽሁፍ ምሽቶችን በማካሄድ 200,000 የህብረተሰብ ክፍሎችን ታዳሚ ለማድረግ ታቅዶ 598 የስነ ጽሁፍ ምሽቶችን በማካሄድ 183,736 ታዳሚዎች ተሳትፈዋል፡፡ በተጨማሪም ለ2213 አማተርከያንያን በስነ-ጽሑፍ፣ በቲያትር፣ በሙዚቃ፣ በባህል ሙዚቃ መሣሪያ አጨዋወት፣ በስዕልና ቅርጻቅርጽ ሙያ ዙሪያ ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ ለ2613 ከያንያን በመስጠት ከእቅድ በላይ ማከናወን ተችሏል፡፡ በሌላ በኩል በባህል እሴቶች ልማት እና በማህበራዊ እድገት ውስጥ ፋይዳቸው ጉልህ የሆኑ 48 ሀገር በቀል ዕውቀቶችንና ባህላዊ እሴቶችን ለማልማት እና ለመጠበቅ በዕቅድ ተይዞ 77 የአገር በቀል ዕውቀቶችን(2 ጎንደር፣ 1 ደሴ፣ 11 አዊ፣ 5 ኦሮሞ /ብ/ስ/ዞን፣ 8 በማ/ጎንደር፣ 1 በምዕ/ጎንደር፣ 5

ሰ/ጎደር ዞን፣ 2 ደቡ/ጎንደር፣ 8 ደቡ/ወሎ፣ 24 በሰሜ/ሸዋ ፣ 4 በምስ/ጎጃም እና 6 በምዕ/ጎጃም) ማልማት እና መጠበቅ ተችሏል፡፡



ባህላዊ የሸክላ ጥበብ- ጎንደር (ወለቃ)

## የእውቀት አስተዳደር እና የመረጃ ማህበረሰብ መፍጠር

የእውቀት አስተዳደር እና የመረጃ ማህበረሰብ ለመፍጠር በተሰራው ስራ 102,500 የተለያዩ መጻሕፍትን በድጋፍና በግዥ በማሰባሰብ ለህዝብ ቤተመጻሕፍት ተደራሽ ለማድረግ ታቅዶ 41,013 መጽሀፍቶችን እና የተለያዩ ህትመቶችን በባህርዳር፣ በጎንደር፣ በደሴ፣ አዊ፣ ዋግህምራ፣ ማ/ጎንደር፣ ምዕ/ጎንደር፣ ሰሜ/ጎንደር፣ ደቡ/ጎንደር፣ ሰሜ/ወሎ፣ ደቡ/ወሎ ፣ ሰሜ/ሸዋ፣ ምስ/ ጎጃም እና ምዕ/ጎጃምባሉ የህዝብ ቤተ-መፃህፍት ተደራሽ ማድረግ ተችሏል፣ አፈጻጸሙም የዕቅዱን 40% ነው፡፡ በተጨማሪም በክልሉ የንባብ ባህልን ለማሳደግ በንቅናቄ 156 የንባብብ ሳምንቶችን በማካሄድ 82,500 የህብረተሰብ ክፍሎችን ለማሳተፍ ታቅዶ 99 የንቅናቄ ሳምንቶችን በማካሄድ 37,655 ማሳተፍ በመቻሉ አፈጻጸሙን ከዝግጅት አንጻር 42 በመቶ እንዲሁም ከተሳታፊ አንጻር 45.6% ማድረስ ተችሏል፡፡

## የቱሪዝም መሰረተ ልማት አቅርቦት ማስፋፋት

በበጀት ዓመቱ የቱሪዝም መሰረተ ልማት አቅርቦትን ለማስፋፋት በተሰራው ስራ በ30 መስህብ ሃብቶች 359 ኪሎ ሜትር ወደ መስህብ ስፍራዎች የሚወስድ የጥርጊያ መንገድ ከተባባሪ ተቋማት ጋር ማሰራት፣ ለ10 መስህብ ሃብቶች የመጠጥ ውሃ ግንባታ፣ለ8 መስህብ ሃብቶች የመጸዳጃ ቤት ግንባታ ለማካሄድ ታቅዶ በ88 መስህብ ስፍራዎች 193 ኪሎ ሜትር የጥርጊያ መንገድ፣ ለ15 መስህብ ስፍራዎች የንጹህ መጠጥ ውሃ አቅርቦት እንዲሁም ለ18 መስህብ ስፍራዎች መጸዳጃ ቤቶችን ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት መስራት ተችሏል፡፡ አፈጻጸሙም

ከጥርጊያ መንገድ ግንባታ አንጻር 54 በመቶ እንዲሁም ከመስህብ ሀብቶች እና ከመጸዳጃ ቤት ግንባታ አንጻር ከዕቅድ በላይ ማከናወን ተችሏል፡፡

## የሀገር ውስጥ ቱሪዝም ልማት ማስፋፋት

የሀገር ውስጥ ቱሪዝም ልማት ለማስፋፋት 1993 መድረኮች በማዘጋጀት 498,250 የህብረተሰብ ክፍሎች በቱሪዝም ማህበራዊ፣ ባህላዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና አካባቢያዊ ጠቀሜታዎች ዙሪያ ግንዛቤ ለመፍጠር ታቅዶ 382 መድረኮች በማዘጋጀት ለ90,055 ወንዶች እና ለ85,552 ሴቶች በድምሩ ለ175,607 የህብረተሰብ ክፍሎች ግንዛቤ መፍጠር ተችሏል፡፡ አፈጻጸሙም ከመድረክ ዝግጅት አንጻር 19 በመቶ እና ከተሳታፊ አንጻር 35 በመቶ ነው፡፡

## አዲስ አገርክን እወቅ ክበባትን ማቋቋም

በበጀት ዓመቱ 1000 አዲስ የአገርክን እወቅ ክበባትን በማቋቋም 123,000 የህብረተሰብ ክፍሎችን ወደ ጉዞ ለማስገባት ታቅዶ 170 አዳዲስ ክበባትን በማቋቋም 28,811 የህብረተሰብ ክፍሎችን ወደ ጉዞ ማስገባት ተችሏል፡፡ በተጨማሪም 957 ነባር የአገርክን እወቅ ክበባትን ለማጠናከር እና 146 የአገርክን እወቅ ክበባትን ወደ የጉዞ ማህበራት ለማሸጋገር ታቅዶ 971 ክበባትን ማጠናከር እና 118 ክበባትን ወደ ጉዞ ማህበራት ማሸጋገር ተችሏል፡፡

## የቱሪስት ፍሰት

በበጀት ዓመቱ ጠቅላላ የቱሪስት ፍሰትን 12,737,437 ለማድረስ ታቅዶ 10,103,558 ማድረስ የተቻለ ሲሆን አፈጻጸሙ 79.3% ደርሷል፡፡ ከዚህ ውስጥ 10,082,755 የአገር ውስጥ ቱሪስቶች ሲሆኑ ቀሪ 20,803 የውጭ አገር ቱሪስቶች ናቸው፡፡ የቱሪስቶች ፍሰትን በሚመለከት አፈፃፀሙ ያነሰበት ምክንያት በኮረና ቫይረስ እና በክልሉ ባለው የጸጥታ ችግር ምክንያት የጎብኝዎች ቁጥር በመቀነሱ ነው፡፡

## ከቱሪዝም ዘርፍ የሚገኘውን ገቢ ማሳደግ

በበጀት ዓመቱ በአጠቃላይ ክልሉን ከሚጎበኙ የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር ቱሪስቶች **3,949,958,980** ብር ገቢ ለማግኘት ታቅዶ 2,363,006,765 ብር ገቢ ማግኘት በመቻሉ አፈጻጸሙ ከዕቅድ አንጻር 59.8% ሆኗል፡፡ ከተገኘው ገቢ ውስጥ 2,**286,305,032** ብር ከአገር ውስጥ ቱሪስቶች ሲሆን ቀሪው 76,701,733 ብር ከውጭ አገር ቱሪስቶች የተገኘ ነው፡፡

## የሆቴልና ቱሪዝም አገልግሎት

በበጀት ዓመቱ የሆቴልና ቱሪዝም አገልግሎቶችን መጠን፣ አይነት እና ደረጃ ለማሻሻል በተሰራው ስራ ለ6,876 አገልግሎት ሰጭ ተቋማት አገልግሎት አሰጣጣቸውን እንዲያሻሽሉ የሙያ ድጋፍና ክትትል ለማድረግ ታቅዶ ለ3,491(51%) በተደረገላቸው ድጋፍ አገልግሎት

አሰጣጣቸውን እንዲያሻሽሉ ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም ለ1,422 የቱሪስት አገልግሎት ሰጭ ተቋማት የብቃት ማረጋገጫ ለመስጠት ታቅዶ ለ570 (21%) ተቋማት የብቃት ማረጋገጫ ተሰጥቷል፡፡ በተመሳሳይ ለ15 ክልላዊ አስጎብኝ ድርጅቶች የአገልግሎት ብቃት ማረጋገጫ ተሰቷቸው ወደ አገልግሎት እንዲገቡ ለማድረግ ታቀዶ ለ4 ክልላዊ አስጎብኝ ድርጅቶች የአገልግሎት ብቃት ማረጋገጫ ተሰጥቷቸው ወደ አገልግሎት እንዲገቡ ተደርጓል፡፡



አቫንቲ ወይም ብሉ ናይል ሪዞርት-ባህርዳር

## የህብረተሰብ ተሳትፎ እና ተጠቃሚነት ማሳደግ

በአጠቃላይ በባህል፣ በተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ቅርስ ጥበቃ እንክብካቤ፣ በቤተ-መጽሀፍትና ሙዜዬም ግንባታ 734,904 የህብረተሰብ ክፍሎችን በማሳትፍ 16.2 ሚሊዮን ብር ለማሰባሰብ ታቅዶ 166,736 ወንድና 111,386 ሴት በድምሩ **278,122** የህብረተሰብ ክፍሎችን በማሳተፍ 42.5 ሚሊዮን ብር ማሰባሰብ ተችሏል፡፡ በባህልና ቱሪዝም ዘርፍ **የህበረተሰቡን ተጠቃሚነት** ለማረጋገጥ በርካታ ተግባራት ተከናውነዋል፡፡ ከዚህ ውስጥ በዘርፉ በአገልግሎት ሰጭ ተቋማት፣ በቅርስ ጥገናና እንክብካቤ፣ በባህል እንዱስትሪ ዘርፍ በሚሰሩ ስራዎች ለዜጎች የስራ ዕድል መፍጠር የተቻለ ሲሆን በበጀት ዓመቱ በአጠቃላይ ለ28,988 ሴቶች እና ለ28,988 ወንዶች በድምሩ ለ57,976 ለሚሆኑ ዜጎች ቋሚና ጊዜያዊ የሥራ ዕድል ለመፍጠር ታቅዶ ለ15,369 ሴቶች እና ለ13,570 ወንዶች በድምሩ 28,939(50%)ዜጎች የሥራ ዕድል ተፈጥሯል፡፡ ከተፈጠረው የስራ እድል ውስጥ 10375 ቋሚ ሲሆን 18564 ደግሞ ጊዜያዊ ነው፡፡

**የአብክመ የመንግስት ኮሙዩኒኬሽን ቢሮ**

## ሲቪል ሰርቪስና የሰው ሀብት አስተዳደር

### የሰው ሃብት ልማት ስርአቱን ማሻሻል

በ2014 ዓ.ም በሰው ሀብት ልማት ዙሪያ የሚታዩ ክፍተቶችን ለመለየት የሚያስችል የዳሰሳ ጥናት ለማካሄድ በተያዘ ዕቅድ መሰረት ለጥናቱ የሚያግዙ የቅድመ ዝግጅት ስራዎች ተጠናቀው መረጃ በመሰባሰብ ስልጠናዎች በተማከለ እና በዕቅድ እንዲመሩ ለማድረግ ይቻል ዘንድ ከ23 የክልል ተቋማት የመጣውን መረጃ በማደራጀት ላይ ቢሆንም የላኩ ተቋማት ቁጥር አነስተኛ በመሆኑ መረጃ የላኩ ተቋማት የስልጠና ፍላጎት ተደራጅቶ በአጭር እና በረጅም ጊዜ ሊሰጡ የታሰቡ የትምህርት መስኮች ተለይተዋል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ከሰራተኞች የስራ አፈፃፀም ምዘና፣ ከለውጥ አመራር አደረጃጀትና አሰራር፣ ከቴክኖሎጂ አጠቃቀም፣ ከኮረናና ኤች.አይ.ቪ.ኤድስ መከላከልና መቆጣጠር፣ ከህፃናት ድጋፍና እንክብካቤ ከመሳሰሉት ጉዳዮች ጋር በተያያዘ ለበርካታ አመራሮችና ሰራተኞች አጫጭር ስልጠና 578 (448 ወንድና 130 ሴት) የፖሊስ፣ የፍርድ ቤት፣ የማዘጋጃ ቤት እና የሆስፒታል ሃላፊዎች እንዲሁም የዞን ሲቪል ሰርቪስ መምሪያ የማኔጅመንት አባላትና የወረዳ የሪፎርም ክትትልና ግምገማ ቡድን መሪዎች ተሳትፈዋል፡፡ ይሁን እንጅ የአቅም ክፍተት የመለየትና ከሙያ ጋር የተያያዘ ስልጠና የመስጠቱ ተግባር በአግባቡ እየተከናወነ ስላልሆነ በየደረጃው ያለ አካል የሚጠበቅበትን ሃላፊነት ሊወጣ ይገባል፡፡



የሰው ሀብት ልማት ስርዓትን ለማሻሻል የተሰጠ ስልጠና-ባህርዳር

**የአብክመ የመንግስት ኮሙዩኒኬሽን ቢሮ**

## የተቋማትን ውጤታማነት በአደረጃጀት ማጎልበት

በክልል ደረጃ ከነበሩ 55(4በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ እንዲሁም 51 በሲቪል ሰርቪስ አዋጅ የሚተዳደሩ) ተቋማት መካከል ጠቅላይ ፍርድ ቤትን እና ክልል ምክር ቤትን ሳይጨምር 53ቱ በክልሉ መንግስት ውሳኔ እንደገና ሲደራጁ በ37 ተቋማት ላይ የአደረጃጀትና የስያሜ ለውጥ ተደርጓል፡፡ በዚህም መሰረት የታጠፉና ተግባራቱ ወደ ሌላ ተቋም እንዲሄድ የተደረጉ ከ3 ነባር ተቋማት ተግባርና ሃላፊነት ተወስዶ እንደ አዲስ የተደራጁ፣ 6የስያሜና የአደረጃጀት ለውጥ የተደረገባቸው፤ስያሜያቸው ሳይለወጥ የአደረጃጀት ለውጥ የተደረገባቸው 2ተቋማት ሲሆኑ፤14 ተቋማት የስያሜ ለውጥ በማድረግ የነበረውን አደረጃጀት ይዘው እንዲቀጠሉ ተደርጓል፡፡ ለእነዚህ ተቋማትም ኦርጋኖግራምና ፎርም ቁጥር 15 በመስራት ለየቢሮዎቹ እንዲደርስ ተደርጓል፡፡ ከስራ መደብ አኳያ ከ17 የክልል ተቋማት ጥያቄው ቀርቦ 1,112 ቋሚ እና ለ12 ተቋማት 39 ጊዜያዊ የስራ መደቦች የተፈቀዱ ሲሆን፤አለአግባብ ተፈቅደው የነበሩ ሁለት የስራ መደቦች እንዲሰረዙ ተደርጓል፡፡ በቋሚነት ከተፈቀዱ የስራ መደቦች ውስጥ 83.2% የጤና እና 9% የትምህርት ተቋማት ናቸው፡፡ ከስራ ምዘናና ከፍያ ጥናት ጋር በተያያዘ ከስምንት የክልል ተቋማት በቀረበ ጥያቄ መሰረት የጋራ የስራ መደቦችን ጨምሮ ለ36 የስራ መደቦች የደረጃ ማሻሻያ የተደረገ ሲሆን፤ከ10 ተቋማት 58 የሥራ መደቦች የስያሜና የደረጃ ለውጥ እና ከ2 ተቋማት 3 የሥራ መደቦች የስያሜ ለውጥ ይቀየርልን በሚል ለቀረቡ ጥያቄዎች ተገቢው ምላሽ ተሰጥቷል፡፡



የተቋማት ውጤታማነት በአሰረር ለማጎልበት የተሰጠ ስልጠና-ባህርዳር

## በይግባኝ ለቀረቡ ጉዳዮች ተገቢውን ውሳኔ መስጠት

በ2014 ዓ.ም በይግባኝ ለቀረቡ የስምሪት ጉዳዮች ተገቢውን ውሳኔ መስጠትጋር በተያያዘ 90% ውሳኔ ለመስጠት እቅድ የተያዘ ቢሆንም ለሶስቱ ምድብ ችሎቶች 3,309 ጉዳዮች ቀርበው ውሳኔ የተሰጠው በ2,267 (68.5%) ጉዳዮች ላይ ነው፡፡ በመሆኑም በይግባኝ ለቀረቡ ጉዳዮች ተገቢውን ውሳኔ በመስጠት በኩል የተሰራው ስራ አጥጋቢ ባለመሆኑ በቀጣይ በጀት አመት ትኩረት ሰጥቶ መስራት ያስፈልጋል፡፡

በአጠቃላይ ውሳኔ ከተሰጣቸው መዝገቦች መካከል የቅሬታ ጉዳዮች የሚበዙ ሲሆን፤ ምክንያታቸው ሲታይም በባህር ዳር ምድብ ችሎት 26.2% ከዝውውር፣ 13.3% ከደረጃ እድገት፣ 9% ከጥቅማ ጥቅም፣ 8.4% ከደመወዝ ማነስ እንዲሁም 5.9% ከሥራ መመለስ ጋር የተያያዙ መሆናቸውን ለመረዳት ሲቻል የተላለፈው የዲሲፕሊን ውሳኔ አይነት በደረጃ ሲቀመጥም 32.4% የሶስት ወር ደመወዝ ቅጣት፣ 31% ከደረጃና ደመወዝ ዝቅ ማለት እና 15.2% ከስራ ስንብት ጋር የተያያዙ ናቸው፡፡

በጠቅላይ ፍርድ ቤት የሚሻሩ ጉዳዮችን መጠን ለመቀነስ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ የተጠየቀባቸው ጉዳዮች የሚሻሩበትን መጠን በ5% ለመቀነስ በተያዘ እቅድ መሰረት የደሴ ምድብ ችሎት መረጃ የተሟላ ባይሆንም ከባህር ዳር ምድብ 561 (524 የቅሬታና 37 የዲሲፐሊን) ጉዳዮች ቀርበው 91(16.2%) ውሳኔ ያገኙ ሲሆን፤ ከእነዚህም ውስጥ 26(29%) በመጽናት እና 34(37%) በመሻር ውሳኔ አግኝተዋል፡፡ በጥቅሉ ለአስተዳደር ፍርድ ቤት የሚቀርቡ መዝገቦች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመሩ የመጡ ሲሆን፤ ጉዳዮች በአመዛኙ ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ባለጉዳዮችን የሚመለከቱ ናቸው፡፡

## የሰው ሃብት ስምሪት

የሰው ሃብት ስምሪት ስራዎችን አፈፃፀም ለማሻሻል ስምሪት እንዲፈፅሙ በተፈቀደላቸው የመንግስት ተቋማት የ452 ወንድና የ372 ሴት በድምሩ የ824 ሰራተኞች ቅጥር፣ 5,389 በደረጃ ዕድገት፤ በኬርየር 2,655፣ በምደባ 700 በዝውውር 633፣ በድልድል ቅጥርን ጨምሮ በድምሩ ለ11,685(6,814 ወንድና 4,871 ሴት )ሠራተኞች ስምሪት የተፈፀመ ሲሆን፤ በጡረታ118 (91 ወንድና 27 ሴት) ሠራተኞች፣ በህመም 9 (6 ወንድና 3 ሴት) ሰራተኞች፣ በዲሲፐሊን 9 ወንድ ሠራተኞች፣ በራሳቸው ፈቃድ 716 (454 ወንድና 262 ሴት) ሰራተኞች እና በሞት 77 (55 ወንድና 22 ሴት) በድምሩ 929 (615 ወንድና 314 ሴት) ሰራተኞች ተሰናብተዋል፡፡

# ጤና

## የክልሉ የጤና ተቋማት

በአማራ ክልል 1 የህበረተሰብ ጤና ኢንስቲቲዩት፣ 10 ደም ባንኮች፣ 5 ጤና ሳይንስ ኮሌጆች፣ 2 የኦክስጅን ፕላንት፣ 917 ጤና ጣቢያዎች፣ 98 ሆስፒታሎችና 3,725 ጤና ኬላዎች አገልግሎት እየሰጡ ይገኛል፡፡ በግሉ ዘርፍ 10 ሆስፒታሎች፣ ከ1,486 በላይ በተለያየ ደረጃ ያሉ ክሊኒኮችና ስፔሻሊቲ ማዕከላት እንዲሁም ከ1,109 በላይ የመድሃኒት መደብሮችና መድሃኒት ቤቶች አገልግሎት እየሰጡ ይገኛሉ፡፡

## የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት

በ2014 ዓ.ም የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት ተጠቃሚዎችን ምጣኔ 93% ለማድረስ ታቅዶ ለ3,059,081(66%) ተጠቃሚዎች ማድረስ ተችሏል፡፡ ከዚህም መካከል 22% የረጅምጊዜ መቆጣጠሪያ ተጠቃሚዎች ሲሆኑ 1.5% ከወሊድ በኋላ ወዲያውኑ በ48 ሰዓት ውስጥ የሚሰጥ (IPPFP) የቤተሰብ እቅድ አገልግሎት ተጠቃሚዎች ናቸው፡፡

## የእናቶች ጤና አገልግሎት

በበጀት ዓመቱ 85 በመቶ የሚሆኑ ነፍሰጡር እናቶችን በጤና ተቋማት የቅድመ ወሊድ ክትትል አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ ለ663,660/86 በመቶ/ የሚሆኑ ነፍሰጡር እናቶች ቢያንስ ለአንድ ጊዜ የቅድመ ወሊድ ክትትል ያገኙ ሲሆን 432,367(56%) የሚሆኑ እናቶች ቢያንስ ለ4 ጊዜ ክትትል አድርገዋል፡፡ በተጨማሪም በበጀት ዓመቱ 76 በመቶ የሚሆኑ ነፍሰጡር እናቶችን በሰለጠነ ባለሙያ የወሊድ አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ ለ395,928 (51%) የሚሆኑት እናቶች አገልግሎት ያገኙ ሲሆን በተመሳሳይ 86 በመቶ ለሚሆኑት እናቶች የድህረ ወሊድ አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ 512,740(67%) የሚሆኑት አገልግሎት አግኝተዋል፡፡ ከወሊድ ጋር በተያያዘ በጤና ተቋም 153 እንዲሁም በማህብረሰብ ውስጥ 169 በአጠቃላይ 322 የእናቶች ሞት መጠን ተመዝግቧል፡፡




የእናቶች ጤና እንክብካቤ- ምስ/ጎጃም(የጁቤ ጤና ጣቢያ)

## ኤች.አይ.ቪ ከእናት ወደ ልጅ እንዳይተላለፍ ማድረግ

በበጀት አመቱ ኤች.አይ.ቪ ከእናት ወደ ልጅ እንዳይተላለፍ ለማድረግ (90%) እናቶችን ለመመርመር ታቅዶ ለ606,991 (79%) ነፍሰጡር እና አጥቢ እናቶች ምርመራ የተደረገላቸው ሲሆን 3,893 እናቶች ኤች.አይ.ቪ በደማቸው ተገኝቷል። 90% ኤች.አይ.ቪ በደማቸው የሚገኝባቸው ነፍሰጡር፣ ወላድ እና የሚያጠቡ እናቶች የጸረ ኤች.አይ.ቪ. ህክምና አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ ለ4,180 እናቶች የተሰጠ ሲሆን በሽፋን 74% ነው። ኤች.አይ.ቪ በደማቸው ካለባቸው እናቶች ለተወለዱ ሕፃናት የቅድመ መከላከል (prophylaxis) ህክምና አገልግሎት 90% ለማድረስ ታቅዶ ለ3,808 (68%) ህጻናት አገልግሎቱን መስጠት ተችሏል።

## የጨቅላ ሕፃናት እና የሕፃናት ጤና አገልግሎትን ማሻሻል

በ2014 ዓ.ም ከሚጠበቁት 712,390 ህጻናት መካከል **98%** ለሚሆኑ ከ1 ዓመት በታች ለሆኑ ህጻናት የክትባት አገልገሎት ለመስጠት ታቅዶ ፔንታቫለንት-1 ክትባት 652,602(92%)፣ ፔንታቫለንት 3 ክትባት 619,453(87%) እንዲሁም የኩፍኝ አንድ ክትባት 614,306(86%) ለሚሆኑት ህጻናት አገልግሎቱን መስጠት ተችሏል። በአጠቃላይ በበጀት ዓመቱ 597,314 (84%) የሚሆኑት ህጻናት ሙሉ በሙሉ ክትባታቸውን ጨርሰዋል፡፡

**የአብክመ የመንግስት ኮሙዩኒኬሽን ቢሮ**



**የህፃናት ክትባት-ባህርዳር ከተማ**

## የስርዓተ ምግብ አገልግሎት

በ2014 ዓ.ም በአማካኝ 48% ከ2ዓመት በታች ያሉ ህፃናት የእድገት ክትትል የተሰራላቸው ሲሆን በጠቅላላ 313,540(5.4%) የሚሆኑት በመካከለኛና 49060(1%) በከፍተኛ ደረጃ ከስታንዳርድ ክብደት በታች የምግብ እጥረትና አለመመጣጠን ችግር በመጋለጣቸው አስፈላጊውን የጤና አገልግሎት በየደረጃው እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም 42% ከ5 ዓመት በታች ህፃናት የምግብ እጥረት ልየታ የተሰራላቸው ሲሆን ከነዚህ መካከል መካከለኛ የምግብ እጥረት የተገኘባቸው 1,097,317(7%) ሲሆኑ ከፍተኛ የምግብ እጥረት ያለባቸው 112,343(1%) ናቸው፡፡ የምግብ እጥረት ተገኝቶባቸው ወደ ህክምና የገቡ ህጻናት ድነው የወጡ ሲሆን በዚህም በምግብ እጥረትና አለመመጣጠን ምክንያት በህጻናት ላይ ሊደርስ የሚችለውን የጤና ችግር መቀነስ ተችሏል፡፡ በሌላ በኩል የጨቅላ ህጻናት ህክምና 47% ለማድረስ ታቅዶ 24,856(42%) ጨቅላ ህጻናት ህክምና አግኝተዋል። ለጨቅላ ህፃናት ሞት ዋነኛ ምክንያት የሆነው የመታፈን ችግር ሲሆን ህክምናውን ያገኛሉ ተብሎ ከታቀዱት 80% መካከል 6,081 (74%) ታክመዋል። በተጨማሪም ከ5ዓመት በታች የሳምባ ምች ህክምና ማግኘት ከሚጠበቅባቸው 52% መካከል 420,693 (51%) ህፃናት የሳምባ ምች ህክምና አገልግሎት ያገኙ ሲሆን የተቅማጥ ህክምና አገልግሎት ያገኛሉ ተብለው ከሚጠበቁ 21% ከአምስት ዓመት በታች የሆናቸው ህጻናት ውስጥ 515,335 (17%) የሚሆኑ ህፃናት ህክምና አግኝተዋል፡፡

## ኤች አይቪ/ኤድስ መከላከል እና መቆጣጠር

በ2014 ዓ.ም ለ1,508,871 ሰዎች የኤች አይ ቪ ምክርና ምርመራ አገልግሎት ለማድረግ ታቅዶ ለ1,357,166 (69%) ሰዎች የምክር አገልግሎት እና ምርመራ በማድረግ 8,164 ሰዎች ኤች አይቪ ቫይረስ በደማቸው ውስጥ መኖሩ የተረጋገጠ ሲሆን ፖዚቲቪቲ ምጣኔው 0.8 ደርሷል፡፡ የፀረ ኤች አይ ቪ መድሃኒት በመጠቀም ላይ ያሉ ህሙማን መጠን (currently on ART) በበጀት ዓመቱ መጨረሻ 161,616 ለማድረስ ታቅዶ 145,222 (72.1%) ሰዎችን የፀረ ኤች አይ ቪ መድሃኒት ተጠቃሚ ማድረግ የተቻለ ሲሆን ከእነዚህ መካከል 3,787 ህጻናት ናቸው፡፡

## የቲቢ በሽታ መከላከል እና መቆጣጠርን

የቲቢ በሽታ መከላከል እና መቆጣጠርን በሚመለከት የሁሉም ዓይነት ቲቢ ተጠርጣሪ ልየታ ከሚጠበቀው 18,202(75%) ለማድረስ ታቅዶ 18,904(59%) የደረሰ ሲሆን በቲቢ ህክምና ሙሉ በሙሉ የዳኑ ህሙማን (TB cure rate) መጠን 90% ለማድረስ ታቅዶ 3,766(85%) ማድረስ ተችሏል፡፡ በተጨማሪም የቲቢ ህክምናቸውን ያጠናቀቁ ሰዎች 96% ለማድረስ ታቅዶ 4257(96%) ማድረስ ተችሏል፡፡ በሌላ በኩል 732 የሥጋ ደዌ ህሙማንን ለይቶ ህክምና ለማስጀመር ታቅዶ 696 (95%)ተለይተው ህክምና እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ ከዚህም ውስጥ የ2ኛ ደረጃ የአካል ጉዳት የደረሰባቸው 68(10%) ሰዎች ናቸው፡፡

## የወባ በሽታን መከላከል እና መቆጣጠር

በበጀት አመቱ የወባ በሽታ ምርመራና ህክምና ስራ ለመስራት በተደረገው ጥረት ለ2,720,141 የወባ ተጠርጣሪዎች በየደረጃው ባሉ ጤና ተቋማት የላብራቶሪ ምርመራ ተደርጎላቸው 617,350 (22.9%) ወባ የተገኘባቸው ሲሆን የህክምና መመሪያው በሚያዘው መሠረት የወባ መድሃኒት እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም የላቦራቶሪ ምርመራ አገልግሎት ጥራቱን ለማስጠበቅ በተመረጡ 70 የጤና ተቋማት የወባ ምርመራ ውጫዊ የጥራት ቁጥጥር ስራ እየተሰራ ይገኛል፡፡ የክልሉ የወባ ስርጭት ከጠቅላላ ህሙማን አንፃር ያለው ድርሻ 3.5% የነበረ ሲሆን ምእራብ ጎንደር እና ማእከላዊ ጎንደር ከፍተኛውን ድርሻ ይዘዋል፡፡



የወባ ህክምና-ምስራቅ ጎጃም ዞን

## ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች

በዋና ዋና ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች ዙሪያ በጤና ተቋማት የሚሰጡ አገልግሎቶችን በተመለከተ በጀት ዓመቱ የደም ግፊት ልየታ ያሰራሉ ተብሎ ከሚጠበቀው እድሜያቸው ከ30 አመት በላይ ከሆኑ 4,117,860 ሰዎች ውስጥ ለ2,914,978 (65.3%) ተሰርቶ 101,374(3.5%) ሰዎች የደም ግፊት ልኬታቸው ከፍ ብሎ የተገኘ ሲሆን 45,725(45%) ሰዎች ህክምና እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ በተመሳሳይ የስኳር መጠን ልኬታ እድሜያቸው 40 ዓመት እና ከዚያ በላይ ለሆኑ 759,736 ሰዎች የተሰራ ሲሆን ከነዚህ መካከል 22,222(3%) ሰዎች የስኳር መጠናቸው ከፍ ያለ ሲሆን 11,223(51%) ህክምና እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ የማህጸን ጫፍ ካንሰር ልየታ 55,955 ሴቶች ስክሪን ተደረገው 4,576(2.2%) የማህፀን ጫፍ ካንሰር ምልክት የተገኘባቸው ሲሆን ህክምና ያገኙት ቁጥር 2,428(53%) ነው፡፡

## የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም

በ2014 ዓ.ም 2,576,559 የተሻሻለ መጸዳጃ ቤት ለማስገንባት ዕቅድ ተይዞ 1,434,507 በማከናወን ሽፋኑን 55.7% ማድረስ የተቻለ ሲሆን 455 ቀበሌዎችም ከአይነምድር ነጻ

እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡ በበጀት አመቱ መጨረሻ ሞዴል ሆነው የቀጠሉ አባዎራዎች /እማዎራዎች ቁጥር 2,242,566(41%) ነው፡፡

## የሳንባ ቆልፍ (COVID-19)

በ2014 ዓ.ም የ35,443 ሰዎች የሳንባ ቆልፍ (Covid -190 ናሙና ተሰብስቦ የተመረመሩ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ 4,617 (13.7%) ሰዎች የኮቪድ-19 ታማሚ ሆነው የተገኙ ሲሆን 491 ሰዎች በበሽታው ህወታቸውን አጥተዋል፡፡ ከባለፈው አመት ጋር ሲነፃር ቫይረሱ የመገኘት ዕድሉ በከፍተኛ ሁኔታ ጨምሯል ይሁን እንጅ ለወረርሽኙ እየተሰጠ ያለው ምላሽ በእጅጉ መቀዛቀዝ ታይቶበታል፡፡

## የሙያ ብቃት ምዘናና ማረጋገጫ ኤጀንሲ

የሙያ ብቃት ምዘናና ማረጋገጫ ኤጀንሲ የተሰጠውን አገራዊ ተልዕኮ ለማሳካት በመካከለኛና በዝቅተኛ ደረጃ የተሰማራውን የሰው ሃይል ብቃት በምዘና በማረጋገጥ ለኢንዱስትሪው በማቅረብ አገሪቱ መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገሮች ተርታ ለመሰለፍ በምታደርገው እንቅስቃሴ ላይ የበኩልን ድርሻ ተወጧል፡፡ በመሆኑም በያዝነዉ በጀት ዓመት ባለፉት ዓመታት የነበሩ ድክመቶችን በማረም& ማነቆዎችን በመለየትና በመፍታት ጥንካሬዎችን ደግሞ ይበልጥ በማጠናከር የህዝባችንን ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት ማረጋገጥ ስለሚገባ ምንም እንኳዋን በክልላችን የተከሰተዉ ጦርነት በእቅድ አፈፃፀሙ ላይ ተዕፅኖ ቢኖረዉም የእቅድ ክለሳ በማካሄድ በልዩ ትኩረት በዕቅድ አፈፃፀሙ ውጤታማ ሆኗል ፡፡

### የምዘና ማዕከላትን ማስፋት

በበጀት ዓመቱ ከመካከለኛና ከፍተኛ ኢንዱስትሪ27፣ ከጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች 139 በድምሩ 166 የምዘና ማዕከላትን አዲስ ዕውቅና ለመስጠት ታቅዶ ከመካከለኛ እና ከከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች 15(55.56%) እና ከጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች 51 (36.69%) በድምሩ ለ66(39.76%) የምዘና ማእከላት እወቅና ተሰጥቷል፡፡ እንዲሁም ለ67 ነባር የምዘና ማእከላት በ274 ሙያወች ተጨማሪ ፈቃድ ተሰጥቷል፡፡ የምዘና ማእከላት አዲስ ፈቃድም ሆነ የእድሳት ጥያቄ ሲያቀርቡ የተቀመጠውን መስፈርት ያሟሉ በአካል ተረጋግጦ ተሰጥቷል፡፡ አዲስ የምዘና ማዕከላት እውቅና ሲሰጣቸው ለቀጣይ ስራቸው አስፈላጊ የሆኑ ቅፃቅፆችና መመሪያዎችን በተሟላ ሁኔታ እንዲያገኙ በጥራዝ መልኩ ተዘጋጅቶ ለምዘና ማዕከላት ደርሷል፡፡ እንዲሁም በክልላችን አዲስ እውቅና የሚሰጣቸውንም ሆነ እውቅናቸውን የሚያሳድሱ የምዘና ማዕከላት ሊያሟሉ የሚገባቸው መስፈርቶች ተዘጋጅቶ ለሁሉም የክልል መ/ቤቶች፣ የሙያ

ብቃት ምዘናና ማረጋገጫ ክላስተር ማዕከላት፣ የዞን ቴ/ሙ/ያ ኢ/ል/መምሪያዎችና የዞን ጤና መምሪያዎች ደርሷቸዋል፡፡

## የኢንዱስትሪና የኢንተርፐራይዞች የእውቅና አፈጻጸም

| ተ.ቁ | የተቋሙ ስም | ከመካከለኛ እና ከከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች | | | ከጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፐራይዞች | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | የአመት ዕቅድ | ክንውን | አፈፃፀም በ% | የአመት ዕቅድ | ክንውን | አፈፃፀም በ% |
| 1 | ባ/ዳር | 7 | 2 | 28.57 | 32 | 6 | 18.75 |
| 2 | ጎንደር | 6 | 5 | 83.33 | 32 | 2 | 6.25 |
| 3 | ወልደያ | 1 | 0 | 0 | 5 | 3 | 60.0 |
| 4 | ደሴ | 4 | 0 | 0 | 18 | 6 | 33.33 |
| 5 | ደ/ብረሃን | 3 | 2 | 66.67 | 20 | 1 | 5.0 |
| 6 | ደ/ማርቆስ | 6 | 6 | 100.0 | 32 | 33 | 103.13 |
| ድምር | | 27 | 15 | 55.56 | 139 | 51 | 36.69 |

### የኢንዱስትሪ ምዘና ማዕከላትን እውቅና ማደስ

በበጀት አመቱ በተቋም ደረጃ 135 በሙያ ደረጃ 171 የኢንዱስትሪ ምዘና ማዕከላትን እውቅና ለማደስ ታቀዶ ክንውን በተቋም ደረጃ 123 በሙያ ደረጃ 688 የምዘና ማእከላት እውቅናቸውን ያሳደሱ ሲሆን አፈፃፀሙም በተቋም ደረጃ 91.11% ሲሆን በሙያ ደረጃ 402.34% ሆኗል፡፡ የተጣለውን ግብ ለማሳከት እውቅናቸውን የሚያሳድሱ የምዘና ማዕከላት እንዲያሟሉ የሚጠብቅባቸው መስፈርቶች ተዘጋጅተው ለሁሉም የክልል መ/ቤቶች፣ የሙያ ብቃት ምዘናና ማረጋገጫ ክላስተር ማዕከላት፣ የዞን ቴ/ሙ/ያ ኢ/ል/መምሪያዎችና የዞን ጤና መምሪያዎች እንዲደርሳቸው የተለያዩ አማራጮችን ማለትም በማህበራዊ ሚዲያም እንዲለቀቅ ማድረግ፣ ደብዳቤ አባሪ አድረጎ የመላክና ምዘና ማዕከላት አውቅናቸውን እንዲያሳድሱ በተደጋጋሚ ጊዜ በደብዳቤ ማሳሰቢያ የመስጠት፣ የምዘና ማዕከለት ያቀረቡት ጥያቄ በአግባቡ እንዲደራጅ የማድረግ እና በምዘና ማዕከላት በአካል በመገኘት ግምገማ በማድረግ መስፈርቱን ለሚያሟሉ የእውቅና ደብዳቤ እንዲደርሳቸው ሲደረግ ላላሟሉ ደግሞ ግብረ መልስ ተሰጧል፡፡

## የኢንዱስትሪ ምዘና ማዕከላት የእውቅና ማደስ እቅድ አፈጻፀም

| ተ.ቁ | የተቋሙ/ ስም | የአመት ዕቅድ | | ክንዉን | | አፈፃፀም | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በተቋም | በሙያ | በተቋም | በሙያ | በተቋም | በሙያ |
| 1 | ባ/ዳር | 37 | 40 | 40 | 195 | 108.11 | 487.50 |
| 2 | ጎንደር | 33 | 40 | 20 | 162 | 60.61 | 405.0 |
| 3 | ወልደያ | 3 | 7 | 6 | 50 | 200 | 714.29 |
| 4 | ደሴ | 16 | 16 | 11 | 30 | 68.75 | 187.50 |
| 5 | ደ/ብረሃን | 12 | 28 | 7 | 36 | 58.33 | 128.57 |
| 6 | ደ/ማርቆስ | 34 | 40 | 39 | 215 | 114.71 | 537.50 |
| ድምር | | 135 | 171 | 123 | 688 | 91.11 | 402.34 |




የምዘና ማዕከላት እውቅና ሲሰጥ

## የኢዱስትሪ መዛኞችን ማፍራት

በበጀት አመቱ ከመካከለኛ እና ከከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች 184 ከጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች 33 በድምሩ 217 የኢንዱስትሪ መዛኞችን ለማፍራት ታቅዶ ከመካከለኛ እና ከከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች 277 አፈፃፀም 150.54% ከጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች 67 አፈፃፀም 203.03% በድምሩ 344 የኢዱስትሪ መዛኞችን ማፍራት የተቻለ ሲሆን አፈፃፀሙም 158.53% ነው፡፡



መዛኝ ማፍራት-ባህርዳር

## መዛኞች ከዘርፉና ከሙያ አንጻር

ከትኩረት ዘርፎች አኳያ ግብርና ከመካከለኛ እና ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች ወንድ 32 ሴት6 ድምር 38 እና ከጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ወንድ 1 ሴት 0 ድምር 1 በጥቅሉ ወንድ 33 ሴት 6 ድምር 39፣ ኢኮኖሚክ መሰረተ ልማት ከመካከለኛ እና ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች ወንድ155 ሴት21 ድምር 176 እና ከጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ወንድ 45 ሴት 5 ድምር 50 በጥቅሉ ወንድ 200 ሴት 26 ድምር 226፣ ኢንዱስትሪ ልማት ከመካከለኛ እና ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች ወንድ 20 ሴት 2 ድምር 22 እና ከጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ወንድ4 ሴት6 ድምር 10 በጥቅሉ ወንድ 26 ሴት 6 ድምር 32፣ ጤና ከመካከለኛ እና ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች ወንድ 26 ሴት7 ድምር 33 እና ከጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ወንድ 1 ሴት0 ድምር 1 በጥቅሉ ወንድ 27 ሴት 7 ድምር 34 መዛኞችን ማፍራት ተችሏል፡፡

## የባለሙያዎች ምዘና

በበበጀት አመቱ 17,949 በመንግስትና በግል ድርጅቶች በመካከለኛና ዝቅተኛ ደረጃ ባለሙያወችን ብቃት በምዘና ለማረጋገት ታቅዶ ለምዘና የተቀመጡ ወንድ **4,669** ሴት **5,698** ድምር **10,367** ሲሆኑ አፈፃፀሙም **57.8**% ነው፡፡ ከነዚህ ውስጥ ተመዝነው ብቁ የሆኑ ወንድ **2,903** ሴት **2,398** ድምር **5,301** አፈፃፀሙም **51.1** % ነው፡፡

**የአብክመ የመንግስት ኮሙዩኒኬሽን ቢሮ**

| በመካከለኛ ና ከፍተኛ | | የዓመት ዕቅድ | የተመዘኑ ብዛት | | | % | የበቁ ተመዛኞች | | | % |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ተ.ቁ | የተቋም ስም | | ወንድ | ሴት | ድምር | | ወንድ | ሴት | ድምር | |
| 1 | ጎንደር | 3,213 | 674 | 852 | 1526 | 47.5 | 410 | 355 | 765 | 50.1 |
| 2 | ወልደያ | 786 | 90 | 39 | 129 | 16.4 | 65 | 23 | 88 | 68.2 |
| 3 | ደሴ | 2084 | 428 | 387 | 815 | 39.1 | 266 | 224 | 490 | 60.1 |
| 4 | ደ/ብረሃን | 1866 | 208 | 278 | 486 | 26.0 | 166 | 94 | 260 | 53.5 |
| 5 | ደ/ማርቆስ | 4,445 | 2196 | 2401 | 4597 | 103.4 | 1321 | 912 | 2233 | 48.6 |
| 6 | ባ/ዳር | 5,555 | 1073 | 1741 | 2814 | 50.7 | 675 | 790 | 1465 | 52.1 |
| ድምር | | 17,949 | 4,669 | 5,698 | 10,367 | 57.8 | 2,903 | 2,398 | 5,301 | 51.1 |



**ምዘና ሲሰጥ**

## የመደበኛ ፕሮግራም ስልጠና

በበጀት አመቱ ለ112,173 ሰልጣኞች ምዘና ለመስጠት ታቅዶ ለምዘና የተቀመጡ ወንድ **46,693**

ሴት **89,238** ድምር **135,931** ሲሆኑ አፈፃፀሙም **121.2%** ነው፡፡ ከነዚህ ውስጥ ተመዝነው ብቁ የሆኑ ወንድ **27,048** ሴት **37,597** ድምር **64,645** ሲሆኑ አፈፃፀሙም **47.6%** ነው፡፡

### የሙያ ብቃት ምዘና

በበጀት አመቱ 25% (104,279) የገበያ-ተኮር አጫጭር ስልጠና አጠናቃቂዎች ብቃታቸውን በምዘና ለማረጋገጥ ታቅዶ ለምዘና የተቀመጡ ወንድ 5,848 ሴት 10,856 ድምር 16,704 ሲሆን አፈፃፀሙም 16.0% ነው፡፡ ተመዝነው ብቁ የሆኑ ወንድ 4,414 ሴት 7,173 ድምር 11,587 ሲሆን አፈፃፀሙም 69.4% ነው፡፡

### የተቋማት የሙያ ብቃት ምዘና

ለ6,576 ተመዛኞች ክልላዊ የብቃት ማረጋገጫ ሰርቲፊኬት፣ በደረጃ 1 እና 2 ተመዝነው ብቁ ለሆኑ 41,180፣ በደረጃ 3 እና በላይ ተመዝነው ብቁ ለሆኑ 50,445 በድምሩ ለ98,201 ተመዛኞች ብሔራዊ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ማስረጃ ተሰጥቷል፡፡ ከተሰጣቸው ዉስጥ 87,301 (98.1%) ወደየምዘና ማእከሉ ተሰራጭቷል፡፡ የድጋሜ ማስረጃ እና ዕድሳት አገልግሎት ፈልገው ጥያቄ ላቀረቡ ተገልጋዮች በብቃት አሃድ ደረጃ ለ559፣ በደረጃ 1 እና 2 ለ23,523፣ለደረጃ 3 እና በላይ ለ17,523 ሰርቲፊኬት በማዘጋጀት ተሰጥቷቸዋል፡፡ 100% የተዘጋጁ ሰርቲፊኬቶችን ለማሰራጨት በታቀደዉ መሰረት ከተዘጋጀው 98,201 ውስጥ 87,301 ((98.1%)ወደ የምዘና ማዕከሉ ተሰራጭቷል፡፡ 100% ከደረጃ 1-5 በደረጃ ተኮር ተመዝነዉ ብቁ ለሆኑ ተመዛኞች ማስረጃቸዉ በድረ-ገፅ ለመልቀቅ ታቅዶ የወልድያ ክላስተርን ሳይጨምር ለ83,938 (93.5%) ተለቋል፡፡ **100%** በአዲስ መልክ ለተጠየቁ የብቃት አሃድ የምዘና መሳሪያዎችን ለማዘጋጀት ታቅዶ በ27 የሙያ ዓይነቶችና በ58 ዓይነት የብቃት አሃድ የምዘና መሳሪያዎች ተጠይቆ በ58ቱም ተዘጋጅቶ አገልግሎት ላይ ውለዋል፡፡

## የአማራ ክልል ህዝቦች ሰማዕታት መታሰቢያ

### የአገልግሎት ሽፋንን ማሳደግ

በ2014 ዓ.ም የተሟላ የትምህርት የመረጃ አገልግሉት ለማቅርብ በታቀደው መሰረት ለ100,000 የሀገር ውስጥ ጎብኝዎች የጉብኝት አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ 34,482 የጉብኝትና የትምርት አገልግሎት ተሰጥቷል፣ አፈፃፀሙም 34.4 % ነው፡፡ ከዚህ ውስጥ 2,482 በደብዳቤ ጥሪ የጎበኙ ናቸው፡፡ በተመሳሳይ ለ500 የውጭ ሀገር ጎብኝ የጉብኝት አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ ክንውን 58 ሲሆን አፈጻጸሙ11.6% ነው፡፡ በመሆኑም አፈጻጸሙ ዝቅተኛ የሆነበትን ምክንያት በማየት ትኩረት ተሰጥቶት ሊሰራበት ይገባል፡፡ በ2014 ዓም የመረጃ አቅርቦት አሰጣጥን በማሻሻል

የመደበኛ ቤተ-መጽሃፍት አንባቢ ብዛት 80,000 ለማድረስ ታቅዶ ከንውን ወንድ 32846 ሴት 16008 ድምር 48854 (61%) ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡ በሌላ በኩል የመረጃ አቅርቦት አግልግሉት በማሻሻል ዲጅታል ቤተ-መጽሃፍት አንባቢ ቁጥር 30,000 ለማድረስ ታቅዶ ወንድ 5,479 ሴት 2,399 ድምር7,878 ተጠቃሚዎችን ዲጅታል ቤተ-መጽሃፍት ንባብ አገልግሉት እንዲያገኙ ተደርጓል፣ አፈጻጸሙ 26.2% ነው፡፡ እዲሆም ለ19,500 በክፍያ የኢንተርኔት ንባብ አገልግሎት ተጠቃሚዎች ለማስጠቀም ታቅዶ ወንድ 53,555 ሴት 2,906 ድምር 56,461 ተጠቃሚ ማድረስ የተቻለ ሲሆን አፈጻጸሙ ከ100% በላይ ነው፡፡ ለሁለተኛ ጌዜ በተካሄደው ነጻ ንባብ ሳምንት በማንዋል፤ በዲጅታልና በኢንተርኔት 15,000 የንባብ አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ ወንድ 5,495 ሴት 1,009 ድምር 6,504 ደንበኞች ተጠቃሚ ማድረግ የተቻለ ሲሆን አፈጻጸሙ 43.3% ነው፡፡ በአጠቃላይ በማንዋል፤ በዲጅታልና በኢንተርኔት ንባብ እና ነጻ ንባብ ሳምንት 144,500 ታቅዶ ወንድ **97,375** ሴት **22,322** ድምር ጠቅላላ ድምር **119,679** አንባቢ ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡ አፈጻጸሙ **82.8**% ነው፡፡

## ገቢን ማሳደግ

በበጀት አመቱ በአገልግሎት መስጫ ቦታዎች ላይ የአትክልት ልማቱንና ነባር አገልግሎታቸው እንዳይቆራረጥና የውስጥ ገቢ እንዳይቀንስ የክትትል ስራ በመስራት ቀጣይነት እንዲኖረው ለማድረግ በማስብ ነባርና አዳዲስ ፕሮጀክቶችን በተቋሙ ውስጥ በማስፋፋት የተቋሙን ገቢ ለማሳደግ በተሰራው ስራ ብር 432,199 ገቢ ማድረግ ተችሏል፡፡

## የስራ ዕድል ፈጠራ

በ2014 ዓ.ም የተለያዩ ዜጎችን የስራ ዕድል ተጠቃሚ ለማድረግ በተሰራው ስራ 12,000 ዜጎች ጊዚያዊ የስራ እድል ለመፍጠር ታቅዶ ለ7,729 ወንድና ለ3,567 ሴቶች በድምሩ ለ11,296 ባለሞያዎች እና የቀን ሰራተኞች የስራ እድል መፍጠር ተችሏል፡፡

# IV. መልካም አስተዳደር ዘርፍ

## ርዕሰ-መስተዳድር

የርዕሰ መስተዳድር ጽህፈት ቤት በክልሉ ውስጥ የተቋቋሙ የተለያዩ አስፈፃሚ አካላት በሁለገብ ልማት ፈጣን የዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ በመዘርጋት ዘላቂ የመልካም አስተዳደር ዘርፎች አተኩረው እንዲሠሩና በሕግ የተሠጣቸውን ተግባር እና ሀላፊነት ለማሣካት በተናጠል የሚያካሂዱት ጥረት በክልል ደረጃ ይበልጥ ተቀናጅቶ የሚመራበትና አፈፃፀማቸውም በየጊዜው እየተገመገመ ከስትራቴጅካዊ ግቦች አኳያ የሚቃኝበት ተቋም ነው፡፡

### የአገልግሎት አሰጣጥን ማሻሻል

የጽ/ቤቱን የቅሬታ የአሰራር ስርዓት ለማጠናከር ያስችል ዘንድ በደንብ ቁጥር 179/2011 መሰረት የቅሬታ ማስፈፀሚያ የሚሆን የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት ወደ ስራ ገብቷል፡፡ በመሆኑም በበጀት ዓመቱ አገልግሎት ለማግኘት ወደ ጽ/ቤቱ የመጡ ዜጎች ቁጥር 9080 ሲሆኑ ከዚህ መካከል ወንድ 7846 ሴት 1234 ናቸው፡፡ ከዚህ ውስጥ 14,135/ ወንድ 9,124 ሴት 5,011/ ባለጉዳዩችን ተቀብሎ በመመዝገብ ጉዳያቸውን በማጣራት ወደ ሚመለከታቸው አካላት መምራት ተችሏል፡፡

በበጀት አመቱ አጠቃላይ የቀረቡት አቤቱታዎች በፆታና በእድሜ ሲታይ የሴቶች ድርሻ 15,927 (32.72%) ሲሆን ወጣቶችን ከማስተናገድ አንፃር ደግሞ እድሜያቸው ከ29 ዓመት በታች የሆኑ 15,195/ ወንድ 10,000 ሴት 5,208/ አፈፃፀሙ 32.72% ነው፡፡ በመሆኑም ለአቤቱታቸው ውሳኔ ያገኙ ዜጎች ደግሞ 7,453 /ወንድ 4,767 ሴት 2,686 /ሲሆኑ አፈፃፀሙ (98.87%) ነው ፡፡

### በየደረጃው ይግባኝ የተባለ

| ሂደቱ | ለወረዳ አስተዳደር ይግባኝ የተባለ | ለዞን አስተዳደር ይግባኝ የተባለ | ለርዕሰ መስተዳድር ይግባኝ የተባለ | በድግ ግሞሽ | የውሳኔ ጥራት አፈፃፀሙ በ% |
|---|---|---|---|---|---|
| ይግባኝ የተባለ | 500 | 60 | 15 | 575 | |
| የፀደቀ | 388 | 56 | 14 | 458 | 81.49 |
| የተሻረ | 102 | 1 | 1 | 104 | 18.51 |
| በሂደት ላይ | 10 | 3 | - | 13 | 2.26 |

**የአብክመ የመንግስት ኮሙዩኒኬሽን ቢሮ**

## አቤቱታና ቅሬታ የቀረበባቸው የስራ ዘርፎች

| ተ.ቁ | የጉዳዮች ዝርዝር | ጠቅላላ የቀረበ ቅሬታ | ድርሻ በፐርሰንት |
|---|---|---|---|
| 1 | ሴፍቲኔት ምልመላና መረጣ | 11,499 | 23.50 |
| 2 | ጥቆማዎችና ሌሎች | 10,599 | 22.20 |
| 3 | አስተዳደራዊ ዘርፍ | 9,059 | 18.51 |
| 4 | ከተማ መሬትና ማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት | 8,339 | 17.04 |
| 5 | ጥቃቅንና ስራ እድል ፈጠረ ፈጠራ | 2,570 | 5.25 |
| 6 | ገጠር መሬትና ግብርና | 1,365 | 2.79 |
| 7 | ንግድና ገባያ ልማት | 1,028 | 2.10 |
| 8 | የሰው ሃይል ስምሪት | 803 | 1.64 |
| 9 | ፍትህና ፍርድ ቤት | 722 | 1.47 |
| 10 | ፖሊስና ሚሊሻ | 577 | 1.17 |
| | ድምር | 48,663 | |

## ከፍተኛ አቤቱታ የቀረበባቸው ወረዳዎች

| ተ.ቁ | ዞኖች | ጠቅላላ የቀረበ | አቤቱታ የቀረበባቸዉ አካባቢና ወረዳዎች | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 1ኛደረጃ | | 2ኛ ደረጃ | | 3ኛ ደረጃ | | 4ኛ ደረጃ | |
| | | | ወረዳ | ብዛት | ወረዳ | ብዛት | ወረዳ | ብዛት | ወረዳ | ብዛት |
| 1 | ምዕራብ ጎንደር | 1449 | ምዕራብ አርማጭሆ | 574 | አዳኝ አገር | 289 | ምደረ ገነት | 187 | ገንዳ ዉኃ | 112 |
| 2 | ሰሜን ጎንደር | 6507 | ዳባት | 3987 | ደባርቅ | 934 | ጃናሞራ | 735 | ዳባት ከተማ | 330 |
| 3 | ማዕከላዊ ጎንደር | 10,046 | ምዕራብ በለሳ | 1913 | ኪንፋንዝ | 1122 | ታች አርማጭሆ | 963 | 0 | 0 |
| 4 | ደቡብ ጎንደር | 1603 | ታች ጋይንት | 279 | ፎገራ | 148 | ላይ ጋይነት | 133 | ጉና በጌምድር | 120 |
| 5 | ሰሜን ወሎ | 314 | ጉባ ላፍቶ | 152 | ሀብሩ | 41 | መቄት ወረዳ | 35 | ራያቆቦ | 27 |

**የአብክመ የመንግስት ኮሙዩኒኬሽን ቢሮ**

## አቅም ግንባታ

በበጀት ዓመቱ በማህበራዊ ሚዲያ ጽንሰ ሀሳብና በካይዘን ፍልስፍና መሰረታዊ መርሆዎች ዙሪያ ለጽ/ቤቱ አመራሮችና ሠራተኞች ለወንድ 79 ሴት 75 በድምሩ 154 ሰልጣኞች የአጭር ጊዜ ስልጠና መስጠት ተችሏል፡፡ በተመሳሳይ በህዝብ ቅሬታና አገልግሎት አሰጣጥ በተዘጋጁ ሁለት መድረኮች በአቤቱታ ቅበላና ምርመራ እንዲሁም በመረጃ አያያዝ ዙሪያ ለወንድ 361፣ ሴት 172 በድምሩ ለ543 ሰልጣኞች የአጭር ጊዜ ስልጠና መስጠት ተችለሏል፡፡



ካይዘን ስልጠና-እንጅባራ ከተማ

## የአሰራር ስርዓትን ማጎልበት

የተጠያቂነትንና የአሰራር ስርዓትን ለማጎልበት በመስተዳድር ምክርቤቱ የተወሰኑ 143 መረጃዎችን በኤሌክትሮኒክስ ሚዲያ በመጫን 1 ሀተታና 5 በራሪ ጽሁፍ በማዘጋጀት ለሚመለከተው አካልና ለህብረተሰቡ ማድረስ ተችሏል፡፡

አጠቃላይ በህዝብ ቅሬታና አስተዳደራዊ ፍትህ ዘርፍ ዙሪያ በቅሬታ ማስተናገኛ ስርዓቱ ላይ በዞንና በወረዳ ደረጃ የአሰራር ህገ ደንብ መመሪያ መሰረት 1,252,355 ለሚሆኑ የህበረተሰብ ክፍሎች ገጽ ለገጽ ግንዛቤ ለመፍጠር ታቅዶ ወንድ 596,811 ሴት 389,716 ድምር 986,327 ሰልጣኞች የአቅም ግንባታ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

**የአብክመ የመንግስት ኮሙዩኒኬሽን ቢሮ**

## አማራ ሚዲያ ኮርፖሬሽ

### የቴክኖሎጂ አጠቃቀምን ማዘመን

በበጀት ዓመቱ የአሚኮን የቴክኖሎጅ አጠቃቀም ለማዘመን የተከናወኑ ዋነኛ ተግባራት የሬዲዮና የቴሌቪዥን፣ የበይነ መረብና የጋዜጦች ሕትመትና ስርጭት ጥራት፣ ፈጣንና ጊዚ ቆጣቢ እንዲሆኑ ተደርጎ ቴክኖሎጅዎቹን ጥቅም ላይ በማዋል ተደራሽ ማድረግ ተችሏል፡፡ የአሚኮን የስርጭት ተደራሽነት ለማሳደግ በተሰራው ስራ በሁመራ አካባቢ በጀኔሬተርና በማቀባባበያ ማሰራጫ የራዲዮ ስርጭት ተደራሽ ተደርጓል፡፡ አዲስ አበባ የኤፍ ኤም ጣቢያ ተከፍቷል፣ የደብረ ብረሃንና የደብረ ታቦር ከተሞች የስርጭት ተደራሽነት ችግር ተፈቷል፡፡ የራዲዮ፣ የጋዜጣ እና የቴሌቪዥን ስርጭት በበይነ መረብ እንዲደርስ መደረጉ ህብረተሰቡ በከፍተኛ ሁኔታ መረጃ በሚያስፈልገው ወቅት በቀላሉ እንዲያገኝ ማድረግ ተችሏል፡፡

የዘገባ ተደራሽነትን ለማስፋት ከሩቅም ከቅርብም፤ ከከተማም ከገጠርም የሚገኙ ታዳሚያን ትክክለኛ ተዓማኒና ሚዛናዊ ዘገባዎችን ለማድረስ 22 የቀጥታ ስርጭቶች በወቅቱ ተላልፈዋል፡፡ በዚህም የማቀባበያ ጣቢዎችን ጠግኖ ወደ ስራ በማስገባት በኩል አዳዲስ ቴክኖሎጅዎችን በማበልጸግና የሬዲዮ ተደራሽነትን ማስፋት ተችሏል፡፡ በተጨማሪም የዘገባ ስምሪትን በእቅድ እና በስምሪት ካርታ በመምራት ፍትሃዊ ለማድረግ ጥረት መደረጉ ህብረተሰቡን ለማገልገል የነበረው ድርሻ ከፍተኛ ነው፡፡

የአሚኮን ተደራሽነት ለማስፋት በአማራ ክልል ዞንና ወረዳዎች እስከ ገጠር ቀበሌዎች በመውረድ በቴሌቪዥን ከ17 ሺህ በላይ የቀረፃና ቅንብር ሥራዎች ተሰርተዋል፡፡ በሬዲዮ ዜናና ፕሮግራምም ከ18 ሽህ በላይ ዜናዎችና ወደ 60 ሽህ ደቂቃ የሚጠጋ ፕሮግራሞች ተላልፈዋል፡፡ የበይነ መረብ ተከታታዮችም ከ1ሚሊዮን በላይ ሆነዋል፡፡

ወቅቱ የቀውስ ጊዜ በመሆኑ የተለያዩ መድረኮች እና ሁነቶች የሚዘጋጁበት ስለነበር 1390 የይዘገቡልን ጥያቄዎች፣ ጥቆማዎች እና ቅሬታዎች ቀርበው አብዛኛዎቹ በዜና ጉባኤ ፀድቀው 1,245 ዜናዎች የዘገባ ሽፋን አግኝተዋል፡፡

### የታዳሚ ተጠቃሚነትን ማሳደግ

በበጀት አመቱ የታዳሚ ተጠቃሚነትን ለማሳካት የአማራ ሚዲያ ኮርፖሬሽን የዘገባ ሽፋንን ማሳደግና ሽፋን ላላገኙ የህብረተሰብ ክፍሎች ድምጽ በመሆን አሸባሪውና ወራሪው የህውሃት ቡድን በአማራ ህዝብ ላይ የደቀነውን የህልውና አደጋ ለመቀልበስ፣ ለህልውና ዘማቹም ሆነ በወረራው ለተፈናቀሉ ልዩ ልዩ የማህበረሰብ ክፍሎች ከደጀን እስከ ግንባር የሚደረገው ድጋፍ

እንዲያድግ፣ በህልውና ዘመቻው የሚሳተፉ ሚሊሻዎች ሰብል በበጎ ፈቃደኞች እንዲሰበሰብ ትኩረት ተሰጥቶ ተሰርቷል፡፡

የመከላከያ ሰራዊታችን ላይ የተፈጠረውን የተሳሳተ እይታ በማስተካከል የአማራ ወጣቶች ወደ መከላከያው እንዲቀላቀሉ ለማድረግ የማህበረሰቡን አስተሳሰብ ለመቀየር ሰፊ ስራ ተሰርቷል፤ ስኬታማ ውጤትም ተገኝቷል፡፡ በመከላከያ ውስጥ ያለፉ ባለማዕረግ ጀግኖችን አሸባሪው ወራሪ በተጨባጭ በእነሱ ላይ ይፈፅም የነበረውን እኩይ ሴራ ማጋለጥ ተችሏል፡፡ መሪዎች እና የዘርፉ ባለሙያዎችም አሁን ላይ የተፈጠረውን በመከላከያ ውስጥ የአማራ ድርሻ ለመሙላት ወጣቶች መሳተፍ እንዳለባቸው መልእክቶችን እንዲያስተላልፉ ተደርጓል፡፡

በህልውና ዘመቻው ወቅት ሁሉንም የአሚኮ ጣቢያዎች እና ጋዜጣዎች መደበኛ ስርጭት በማጠፍ የተሸጡ እና ስፖንሰር የተደረጉ ፕሮግራሞችን በማቋረጥ የህልውና ዘመቻ ላይ አጀንዳ በማድረግ ሕዝቡን የሚቀሰቅሱ መረጃዎች ቀርበውበታል፡፡ ሁሉንም ማህበራዊና ምጣኔ ሐብታዊ የአየር ሰዓት፣ የጋዜጣ አምዶችና የበይነ መረብ መረጃ ማስተላለፊያዎች ወደ ህልውና ዘመቻው በማድረግ የስፖርት መዝናኛ እና ሌሎች ዝግጅቶችን በማጠፍ አዳዲስ ፕሮግራሞችን እንደ ነጋሪት ሀገሬን አትንኳት ወደ ስርጭት ማምጣቱ የአመለካከት ለውጥ ለማምጣት አስተዋጽኦው ከፍተኛ ነበር፡፡

ህዝባችንን የሚያነቁ እና ስነ ልቦናውን መገንባት የሚችሉ አዳዲስ የዘገባ ፎርማቶችንና አሰራሮችን በመቅረጽ ሁሉም ቅድሚያ ትኩረት ለህልውና ዘመቻው እንዲያደርግ የተሰራው ስራ ታሪክ የሚዘከረው ነው፡፡ የአሚኮ ባለሙያዎች በጦርነት ቀጠና በመግባት የወገን ጦር ተጋድሎን ከስፍራው በቀጥታ በመቅረጽ እና በማቀናበር የፈጠሩት መነሳሳት እና የተወጡት ሙያዊ ሃላፊነት ትውልድ የሚያስታውሰው እና ለሌሎች ስራዎች እንደ ማነሳሻ የሚያገለግል በመሆኑ በጥንካሬ የሚገለፅ ነው፡፡

በተሰጠው ተከታታይ የዘገባ ሽፋን የአማራ ወጣቶች መከላከያውን በስፋት እንዲቀላቀሉ ማድረግ ተችሏል፡፡ ወራሪው ቡድን ለአማራ ብቻ ሳይሆን ለመላ ኢትዮጵያዊያን ጠላት መሆኑን ጉዳት የደረሰባቸው የህብረተሰብ ክፍሎችን ከባለሙያ ማብራሪያዎች ጋር ማሳየት ተችሏል፡፡

በግንባር በተሰማሩ ዘጋቢዎች አማካኝነት ወራሪው የፈፀማቸውን ሰብአዊ፣ ቁሳዊና ስነ-ልቦናዊ ግፍ የተፈፀመባቸው የማህበረሰብ ክፍሎች በአይን እማኞች በማቅረብ ለኢትዮጵያ ህዝብ ማጋለጥ ተችሏል፡፡ አሸባሪውን ወራሪ አንገት ላንገት ተናንቀው የተፈፀሙ ጀብዱዎችን ከቦታው አብነት ያላቸው ምስክርነቶችን እንዲሰጡ ማድረግ ተችሏል፡፡ ይህ መሆኑ ደግሞ የህዝባችንን ስነ-ልቦና ለመገንባትና ለመጠበቅ የሚደረገውን ጥረት በከፍተኛ ሁኔታ አግዟል፡፡

በበጀት አመቱ በጦርነቱ ሰበብ የተፈጠረውን የኑሮ ውድነት ለመቋቋም መንግስት መከተል

**የአብክመ የመንግስት ኮሙዩኒኬሽን ቢሮ**

ስለሚገባው የምጣኔ ሐብት ፖሊሲ፣ አሸባሪው ወራሪ በፈጠረው አሉታዊ የዲፕሎማሲ ጎዳና ምክንያት የተከሰተውን የምንዛሬ እጥረት በሀገር ውስጥ ምርት የመተካትን አስፈላጊነት፣ የኑሮ ውድነቱ በተጨባጭ በዜጎች የዕለት ተዕለት ህይወት ላይ እያሳደረ ስላለው ጫና ትኩረት ተሰጥቶት ተዘግቧል፡፡

አሸባሪው ወራሪ ህ.ወ.ሀ.ት በሰው ህይወት፣ በአካል ማጉደል፣ በንብረት ማውደም ያደረሰውን ግፍ በዘጋቢ ዘገባ /ዶክመንተሪ/፣ በዜና፣ በፕሮግራም ለመላው ዓለም ማድረስ ተችሏል፡፡ በተለይም ደግሞ በእንግሊዝኛ እና አረብኛ ቋንቋዎች በመጠቀም አጫጭር መልእክቶች እና ዶክመንታሪዎችን በማዘጋጀት ለዓለም አቀፍ ማህበረሰብ ለማድረስ ለሚሰሩ የሰብዓዊ መብት ተሟጋቾች፣ ዲፕሎማቶች እና በውጭ ሀገር ለሚገኙ ኢትዮጵያዊያን መረጃ እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡

የበይነ መረብ ማሰራጫ ዘዴዎችን በመጠቀም በተለይም በማህበራዊ ብዙኃን መገናኛ (ቲዊተር፣ ዩቱብ፣ቴሌግራም እና ፌስቡክ) አሸባሪው ህ.ወ.ሀ.ት ወራሪ ያደረሰውን ውድመት እና ቡድኑ በአማራ ህዝብ ላይ ያደረሰውን ህገ-ወጥ ወረራ እና ኢሰብዓዊ ድርጊት ለማጋለጥ ከፍተኛ ስራ ተከናውኗል፡፡

በአሸባሪው ወራሪ የደረሰውን ከፍተኛ ውድመት እንደገና መልሶ ለመገንባት የሚጠይቀው ከፍተኛ ጥረት መደገፍ የሚችሉ የምጣኔ ሃብት ዘገባዎች፣ የአማራ ክልል በጦርነት የወደመ ብቻ ሳይሆን እንደገና መነሳት የሚችል የጠንካራ እሴት ባለቤት መሆኑን በህዝባዊ በዓላት እና በሌሎች መሰናዶዎች የዘገባ ስራ ተሰርቷል፡፡ በክልሉ ውስጥ ያለው የኢንቨስትመንት አመራጭ የመልማት እድልን በዘጋቢ ዘገባ (ዶክመንታሪ) እና በዜና ዘገባዎች በመስራት የጦርነት ቀጠና ብቻ ሳይሆን በከፍተኛ ሁኔታ መልማት የሚችል ክልል እንደሆነ የሚያሳዩ ስራዎች በሁሉም የመገናኛ ብዙኃን አውታሮች እና በአስራ አንድ ቋንቋዎች ሽፋን አግኝተዋል፡፡

የአሸባሪውን ወረራ ለመቀልበስ መላ ኢትዮጵያዊያን በአንድ ላይ ያደረጉትን ተጋድሎ መሰረት በማድረግ ሀገራዊ አንድነትን የሚያፀኑ ፕሮግራሞች ተቀርጸው ተላልፈዋል፡፡ ወራሪው የህ.ወ.ሀ.ት ቡድን ግፍ የፈጸመባቸውን የመከላከያ ሰራዊት አባላት የአማራ ህዝብ ተቀብሎ ያስተናገደበትን ሁኔታ በልዩ ትኩረት ሽፋን ተሰጥቷል፡፡

ከህልውና ዘመቻው ማግስት ጀምሮ አብሮነት ላይ ያተኮሩ ፕሮግራሞች በሁሉም የሀገራችን መዓዘን የዘገባ ሽፋን አግኝተዋል፡፡ ከዋና ዋና ተግባራት መካከልም የኢድ በዓልን ከጅግጅጋ፣ ከአሶሳ፣ ከሰመራ፣ ከናዝሬት በቀጥታ በማሳተላለፍ አሚኮ ሁሉንም ኢትዮጵያዊያን የሚያገለግል የህዝብ መገናኛ ብዙኃን ለማድረግ ከፍተኛ ስራ ተከናውኗል፡፡ ከዚህ ተጨማሪ በኦሮሚያ፣ በአፋር፣በደቡብ፣ በሲዳማ እና ደቡብ ምዕራብ የኢትዮጵያ ክልሎች ሰምሪት በመስጠት ሀገራዊ

አንድነትን ለማጠናከር ከፍተኛ ስራ ተከናውኗል፡፡

ከህልውና ዘመቻ ማግስት የተከበሩ ህዝባዊ፣ መንግስታዊና ኃይማኖታዊ በዓላትን በቀጥታ ስርጭት ማስተላለፍ ተችሏል፡፡ ጥምቀትን ከስምንት የክልላችን አካባቢዎች፣ የአገው ፈረሰኞች በዓል፣ የገና በዓል በላሊበላ፣ የደብረታቦር ፈረሰኞች በዓል፣ የጳጥታ ተቋማት እውቅና ስነ ስረዓት፣ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ምርቃቶችን በቀጥታ የማስተላለፍ ስራ የተከናወነ ሲሆን ይህ ተግባር ክልሉ ላይ የልማት ስራ እና መደበኛ እንቅስቃሴ የሚከናወንበት መሆኑን ለማስረዳት ከፍተኛ ሚና ነበረው፡፡

ያለንን የኢንቨስትመንት እና የመልማት አቅም በጥልቅ ዶክመንታሪዎች (የዋግ የብረት ሃብት፣ የውሃ ሐብት፣ የሙዝ ሃብት ፣...) ከፍተኛ ወጭ ተደርጎባቸው የተከናወኑ ሲሆን፣ የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴዎች፣ የመሰረተ ልማት ግንባታዎች፣ ጉዳት የደረሰባቸው የኢኮኖሚ እና የማህበራዊ ተቋማት መልሶ ግንባታዎች፣ ወደ ስራ የገቡ ፋብሪካዎች ከፍተኛ የሆነ የዘገባ ሽፋን ካገኙ ተግባራት ዋና ዋናዎቹ ተጠቃሽ ተግባራት ናቸው፡፡

በቀጣይ ይበልጥ መጠናከር የሚገባው ቢሆንም በየዘርፉ ያለውን ብልሹ አሰራር እና የአገልግሎት አሰጣጥ ችግር በቀጥታ ውይይት እና በምርመራ ዘገባ መዘገብ ተችሏል፡፡ በዜና እና በልዩ ዝግጅቶች አጀንዳ ለማድረግ ጥረት ተደርጓል፡፡ የ12ኛ ክፍል ብሄራዊ ፈተና ውጤት፣ የኮቪድ ክትባት፣ የአርንጓዴ አሻራ ስራዎች የትኩረት ማዕከል ሆነዋል፡፡ በውጭ ሀገር የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን እና ትውልደ ኢትዮጵያዊያን ከሀገራቸው ጋር እንዲተሳሰሩ እና ሁሉ አቀፍ ድጋፍ እንዲያደርጉ የሚያስችሉ ተግባራት ተከናውነዋል፡፡

የአዲስ ምእራፍ የመንግስት ምስረታና ሊፈቱ ይገባቸዋል ተብለው የተለዩ የመንግስት የቤት ስራዎችን ሁነቱን ከባለሙያ ማብራሪያ ጋር በማጣመር በቀጥታ ተላልፈዋል፡፡ ከአማራ ህዝብ አንፃር አዲሱ መንግስት ትኩረት ሊያደርግባቸው የሚገቡ አጀንዳዎችንም መጠቀም ተችሏል፡፡

አሚኮ በወራሪው እና በአሸባሪው ህ.ወ.ሀ.ት የተዘረፈና የወደመበትን የአማራ ደሴ ኤፍ ኤም ሬዲዮ ጣቢያ፣ የወልድያና የቆቦ የስርጭት ማቀበያያዎችን መልሶ በመጠገን እና ጊዜያዊ ስቱድዮውን በቦታው በማድረግ የቀጥታ ሽፋን ማሰራጨት ችሏል፡፡ በዚህም አካባቢውን ተደራሽ ለማድረግ ከፍተኛ የሳተላይት ክፍያ በመክፈል ከደሴ፣ ከወልድያ፣ ከላል ይበላ፣ ከሰቆጣና እና ከጎንደር የቀጥታ ስርጭት ሽፋን ተሰጥቷል፡፡ በዚህም ታዳሚያን ተጠቃሚ እንዲሆኑ በመደረጉ የአመለካከት ለውጥ አምጥተዋል ለማለት ይቻላል፡፡

## የገቢ አቅምን ማሳደግ

አሚኮን ብራንድ ከማድረግ አኳያ የሁነት ዝግጅት ስራዎች በማዘጋጀት በኢድ አል አድሃ (አረፋ) በዓል፣በአዲስ ዓመት ክብረ በዓል፣ በእየሱሱ ክርስቶስ የልደት በዓል ኮርፖሬሽኑን

የማስተዋወቅ ስራ ሰርቷል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አሚኮ የተለያዩ የገቢ ማስገኛ ማለትም ከፕሮግራም ሽያጭ፣ ከማስታወቂያ ገቢ፣ ከዩቱዩብ (ከሳብስክራይበር) እና ከመሳሰሉት የአገልግሎት ሽያጮች 170,487,169.29 (አንድ መቶ ሰባ ሚሊዮን አራት መቶ ሰማንያ ሰባት ሽህ አንድ መቶ ስልሳ ዘጠኝ ከሃያ ዘጠኝ ሳንቲም) ብር ገቢ ለማግኘት ችሏል፣ አፈፃፀሙም 110% ነው፡፡

ከተገኘው ገቢ ውስጥ 95,443,706.25 (ዘጠና አምስት ሚሊዮን አራት መቶ አርባ ሶስት ሽህ ሰባት መቶ ስደስት ብር ከሃያ አምስት ሳንቲም) ወደ ካዝና ገቢ ሆኗል፡፡ በበጀት ዓመቱ በእቅድ ከተያዘው እና ከውዝፍ ጠቅላላ ብር 131,606,332.17 (አንድ መቶ ሰላሳ አንድ ሚሊዮን ስድስት መቶ ስደስት ሽህ ሶስት መቶ ሰለሳ ሁለት ከአስራ ሰባት ሳንቲም) ብር ወደ ካዝና ገብቷል፡፡ የ607,868 (ስድስት መቶ ሰባት ሽህ ስምንት መቶ ስልሳ ስምንት) ብር ነፃ አገልግሎት ተሰጥቷል፡፡ ይህ ውጤት መመዝገብ የተቻለው አሚኮ የአገልግሎት አሰጣጡን በማሻሻሉ ነው፡፡

## ተደራሽነትን ማስፋት

የአማራ ሚዲያ ኮርፖሬሽን በ2014 በጀት ዓመት በአስራ አንድ ቋንቋዎች፣ በአራት ጋዜጦች፣ በሰባት የራዲዮና የኤፍ ኤም ጣቢያዎች፣ በሁለት ቴሌቪዥን በአማርኛ እና ባለ ብዙ ቋንቋው አሚኮ ህብር በኢትዮ ሳት፣ በካናል ፕላስ፣ በዲ ኤስ ቲቪ፣ በአሚኮ ድረ ገፅ፣ በሞባይል አፕ እና ሌሎች የማህበራዊ ብዙኃን መገናኛ አማራጮች ተደራሽ እንዲሆን ተደርጓል፡፡ ከአንድ ሚሊዮን በላይ ተከታይ ባለው የፌስቡክ በማህበራዊ ትስስር ገጽ አስቀድሞ በማቀድና በአጀንዳ በመመራት እየተከታተሉ ለመፈጸም የተደረገው ጥረት ከፍተኛ ነበር፡፡ ዘገባዎቹን የተለዩ ግብዓቶችን በመጨመር እና በምሁራን በማስተንተን ለአንባቢዎች፣ ለተመልካቾችና ለአድማጮች አድርሷል፡፡

ወጣቱን እና በውጭ ዓለማት የሚኖረውን የህብረተሰብ ክፍል ተደራሽ ለማድረግ የበይነ መረብ አማራጭ (ዩቱዩብ፣ ቴሌግራም፣ ቲዊተር፣ ፌስክ፣ ዌብ ሳይት እና ሞባይል አፕ) በመጠቀም ተደራሺነትን ማስፋት የተቻለ ሲሆን አሚኮ የሚያሳትማቸውን አራት ጋዜጣዎች ማለትም (በበኩር፣ በቻርቤዋ፣ በኢርኮና በኽምጠ ዊከ) እንዲሁም ከህትመት ባሻገር በአዲሱ ሚዲያ ተደራሽ ለማድረግ ተሰርቷል፡፡ አሚኮ ዓለም አቀፍ ተደራሽነትን ለማስፋት እና ወጣቶችን እና ዲያስፖራዎችን በቅርበት ለማግኘት ማህበራዊ ብዙኃን መገናኛን በመጠቀም በበጀት አመቱ የአማርኛው የፌስቡክ ተከታታይ ብዛት 1,279,233 ማድረስ ተችሏል፡፡ የፌስቡክ ላይክ ብዛት 1,010,560 ሆኗል፡፡ የትዊተር ገጽ ተከታታዮች ብዛት 237,000 ናቸው፡፡ የቴሌግራም ተከታታዮችን ብዛት 80,121 ሲሆኑ፣ በዩቱዩብ በዓመቱ 192,785 ዶላር ገቢ ተገኝቷል፡፡ የሰብስክራይቨር ቁጥር 568,974 ነው፡፡ አብዛኛው የዩቱዩብ ገቢ ከአሜሪካ፣ እስራኤል፣ ካናዳ፣

ሳዑዲ አረቢያ እና የተባበሩት አረብ ኤሜሬትስ ሀገራት ነው፡፡ ይህም ዘገባዎችን በከፍተኛ ደረጃ የሚመለከቱ መሆናቸውን ያሳያል፡፡

አሚኮ በተለያዩ ቋንቋዎች ማለትም በአማርኛ፣ በአዊኛ ፣በኽምጠኛ፣ በአፋን ኦሮሞ፣ በትግርኛ፣ በእንግሊዝኛ፣ በአረበኛ፣ በግዕዝ እያሰራጨ ይገኛል፤ እንዲሁም በቀጣይ በሌሎች ቋንቋዎችም ተደራሽ ለመሆን እየሰራ ይገኛል፡፡

በአጠቃላይ በበጀት ዓመቱ በዘገባ ይዘት፣ በአጀንዳ በመመራት፣ በቀዳሚነት፣ ተከታታይነትን በማሳደግ፣ ተዓማኒ የመረጃ ምንጭ በመሆን፣ ሀገራዊ አንድነትን የሚገነቡ ዘገባዎችን ለማቅረብ ተችሏል፡፡ ዘገባን በእቅድ መምራት፣ አካባቢያዊ ስብጥርን ማስፋት፣ የክትትል ዘገባን በዕቅድ ማካተት እና ዘገባዎችን በምሁራን ሐሳብ አስተንትኖ ማዳበር የሚጠቀሱ ጥንካሬዎች ናቸው፡፡

# ዋና ኦዲተር

## የኦዲት ጥራት

የኦዲት ስራን እና ጥራትን ለማስጠበቅ 46 ቡድን ተቋቁሞ ከ2008 ዓ.ም  እስከ 2012 ዓ.ም ማለትም በ5 ዓመቱ የተሰሩ 505 የኦዲት ፋይሎችን በመከለስ የተገኙ የአሰራር ስህተቶችን እና ክፍተቶች እንዲሞሉ ሁሉም ኦዲተሮች በተገኙበት ውይይት በማድረግ አቅጣጫ ተሰጥቷል፡፡

የኦዲት ጥራትን ለማሳደግ በሪጉላሪቲ ኦዲት ማንዋል ቨርዥን 2015 እና በክዋኔ ኦዲት ማንዋል ቨርዥን ከ2016 እስከ 2019 የተሻሻሉ አሰራሮች ተለይተው ወደ ስራ እንዲገቡ ተደርጓል፡፡

በበጀት ዓመቱ የኦዲት ጥራትን በሚያሰጠብቅ መልኩ ሱፐርቪዥን እንዴት መካሄድ ይኖርበታል በሚል ከፌደራል ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት ጋር ግምገማዊ ውይይት ተደርጓል፡፡

## የፋይናንስ ህጋዊነትና የኦዲት ስራ

በበጀት ዓመቱ ከጥር 16/2014 ዓ.ም ጀምሮ የመስክ ስምሪት በማድረግ በ36 ዋና መስሪያ ቤት 57 የኦዲት ቡድኖችን በማደራጀትና ወቅታዊ የድርጊት መርሃ ግብር ክለሳ በማድረግ ስምሪት ተሰጥቷል፡፡

በ2014 ዓ.ም 232 መስሪያቤቶችን የኦዲት ስራ ለማከናወን በዕቅድ ተይዞ በኦዲት መሸፈን የተቻለው በአንጻራዊ ስሌት የ204 መስሪያ ቤቶችን ሲሆን አፈፃፀሙም 87.9% ነው፡፡  ካለፈው ዓመት ተመሳሳይ ጊዜ ጋር ሲነጻጸር በ92 መስሪያቤቶች ያነሰ መሆኑን ያሳያል፡፡  በ2014 በጀት ዓመት በፋይናንስ ሕጋዊነት የኦዲት ስራ በስትራቴጅያዊ ዕቅድ ቅድሚያ ከሚሰጣቸው ኦዲት ተደራጊዎች ቁጥር ሽፋን 776 ሲሆን ይህም 204 መስሪያቤቶችን በማከናወን የኦዲት ሽፋኑ 26% ደርሷል፡፡

**የአብክመ የመንግስት ኮሙዩኒኬሽን ቢሮ**

## የኦዲት ስራዎች ከበጀት ሽፋን አንጻር

በበጀት ዓመቱ በክልሉ መንግስት መስሪያ ቤቶች በ2013 በጀት ዓመት የተፈቀደውን አጠቃላይ በጀት በመውሰድና በበጀት ዓመቱ ኦዲት ሊደረጉ የሚችሉትን መስሪያ ቤቶች መለየት ተችሏል፡፡ እስከ ሰኔ 30/2014 ዓ.ም የወጪ በጀትን 15% ለማድረስ ታቅዶ የወጪ በጀቱን ብር 17,445,479,669/ (62,600,000,000.00 (27.8%) መፈጸም ተችሏል፡፡ እንዲሁም የገቢ በጀት እስከ ሰኔ 30/2014 ዓ.ም ድረስ 10% ለማድረስ ታቅዶ የገቢ በጀቱን ብር 5,069,964,534/ (24,600,000,000.00 (20.6%) መፈጸም ተችሏል፡፡

## በቅድመ ሪፖርት የተላለፉ ግኝቶች

የስጋት አካባቢ የሆኑ ጉዳዮችን በመለየት ወደ ኦዲቱ ለመግባት መነሻ ይሆን ዘንድ የጉድለቱና የማጭበርበር ባህሪውን ለመለየት ተሞክሯል እንዲሁም ዋና ዋና ግኝቶችም ገንዘብ ያገኙ ያንቀሳቀሱት ሂሳብ ሲመረመር የተገኘ የጥሬ ገንዘብ ጉድለት፣ የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኝ ጥራዝ ቅጠሎች ተነቅለው እንዲጠፉ በማድረግ እና በኦርጅናል የገቢ ደረሰኝ ቅጠል የተሰበሰበውን የገንዘብ መጠን በካርበን ኮፒው ሳያስቀምጡ ሁለተኛ ግለሰብ የከፈለውን ገንዘብ በማስፈር በኦርጅናል ደረሰኝ ቅጠል የተሰበሰበው ገንዘብ ለግል ጥቅም ማዋል ላልተሰራ የካናል ግንባታ ስራ አላግባብ በብልጫ የተከፈለና አላግባብ የተከፈለ የተጣራ ደመወዝ ሂሳብ ናቸው፡፡ በአጠቃላይ በበጀት አመቱ ወጪ ካደረጉ 31 መስሪያ ቤቶች ብር 3,470,498.80 ጉድለትና የማጭበርበር ድርጊት የተፈፀመ መሆኑን በተደረገው የኦዲት ስራ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

## የክዋኔ ኦዲት ስራ

በ2014 ዓ.ም የተጀመሩ ሰባት የመደበኛ ክዋኔ የኦዲት ስራ ማጠናቀቅ ተችሏል፡፡ እንዲሁም ከበጀት ዓመቱ ከሁለት ዓመታት በፊት የተሰሩ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርቶች ላይ በመመስረት ስድስት የክትትልና የኦዲት ስራ ለመስራት ታቅዶ ሰባት መደበኛ የክዋኔ ኦዲት ተከናውኗል፡፡ በጀት ዓመቱ የተጀመሩ ልዩ ኦዲቶች ያሉበት ደረጃ ሲታይ ደግሞ ሁለቱ የተጠናቀቁ ሲሆን ቀሪዎቹ ሶስቱ ደግሞ ከ5% እስከ 56% የተከናወኑ ናቸው፡፡ እንዲሁም የክትትልና የኦዲት ስራ ያለበት ደረጃ ሲታይ ሁለት ሪፖርታቸው ያለቀና አራቱ ደግሞ በቢሮ ደረጃ በመከለስ ላይ ያሉ ሲሆኑ አፈፃፀማቸው 95% ነው፡፡

በአጠቃላይ በበጀት አመቱ በመደበኛና የክትትል የክዋኔ ኦዲት ስራ የ13.64 መስሪያ ቤቶችን ኦዲት ለማድረግ እቅድ ተይዞ በአንፃራዊ ስሌት የ12.67 መስሪያቤቶችን የክዋኔ ኦዲት በማድረግ የእቅዱን 92.88% መፈጸም ተችሏል፡፡

**የአብክመ የመንግስት ኮሙዩኒኬሽን ቢሮ**

## የኦዲት ሪፖርት መልስ አሰጣጥ

በበጀት አመቱ ወጪ ከተደረጉ በሁለት መስሪያቤቶች ጉድለትና ማጭበርበር የተከሰተ ሲሆን ጉድለትና ማጭበርበር የተከሰተባቸው መስሪያቤቶችም በፋግታ ንዑስ ማዘጋጃ ቤት ብር 437,469.00 እና በደብረ ማርቆስ ከተማ ልማት ኮንስትራክሽን መምሪያ ብር 1,710,738.10 በድምሩ ብር 2,148,207.00 ጉድለት ተገኝቷል፡፡

# ክልል ምክር ቤት

የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት በዴሞክራሲያዊ ስርዓት ውስጥ የህዝቦችን ሁለንተናዊ ተሳትፎ ለማረጋገጥ የመንግስት አሰራርን ግልፀኝነት እና ተጠያቂነት በተላበሰ መልኩ ለመፈጸም በመንግስት አካላት መካከል የቁጥጥርና የክትትል ስርዓት ዘርግቷል፡፡ አስፈፃሚ አካላትም በህግ ተለይተው የታቀዱ ተግባራትን ለመፈፀም የተሰጣቸውን ተግባርና ሃላፊነት በአግባቡ እየተወጡ ስለመሆኑ፣ የዜጎች ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብት ስለመከበሩ፣ ህዝቡ በየደረጃው የሚያነሳቸውን የልማት እና የመልካም አስተዳደር ጥያቄዎች ስለመፍታታቸው ሊያረጋግጥ የሚያስችል በጋራ እና በተናጠል ክትትል እና ቁጥጥር በማድረግ ህዝባዊ ውክልናቸውን እንዲወጡ በማድረግ እየሰራ ነው፡፡




5ኛው ዙር ምክር ቤት የስራ ዘመኑን ጨርሶ ለስድስተኛው ዙር ምክር ቤት የስልጣን ርክክብ ሲያደርግ-ባህርዳር

## የአገልግሎት አሰጣጥን ማሳደግ

በ2014 ዓ.ም በተቋሙ አገልግሎት ፈልገው የመጡ የውስጥ ደንበኞች 244 (ወንድ 130፣ ሴት 114 )፤ የውጭ ደንበኞች 96 (ወንድ 39፣ ሴት 57 ) በድምሩ 340 (ወንድ 169፣ ሴት 171 ) ማስተናገድ ተችሏል፡፡ ከዚህ ውስጥ 50.3% የሴቶች ናቸው፡፡ ወንድ 99፣ ሴት 117 ድምር 216 (63.52%) የሚሆኑት ደግሞ ወጣቶች ናቸው፡፡

## ምክር ቤቱ የሚያወጣቸውን ህጎች ጥራት ማሻሻል

ምክር ቤቱ በተሰጠው ህግ፤ደንብና ስልጣን መሰረት የህጎችን ጥራት በማስጠበቅ 100% ለማሻሻል አቅዶ ለምክር ቤቱ የሚቀርቡ ረቂቅ ህጎች ላይ የህዝብ አስተያየት በማሰባሰብና የበሰለ የውሳኔ ሃሳቦችን በማቅረብ በምክር ቤቱ የአሰራርና የስነ-ምግባር ደንብ መሰረት በቂ ዝግጅት በማድረግ ለ5ኛ ዙር 18ኛው የመጨረሻው ጉባኤና የ6ኛው ዙር 1ኛው መስራችና መደበኛ ጉባኤ የፀደቁ ሶስት አዋጆችን በማዘጋጀት የእቅዱን 100% ማከናወን ተችሏል፡፡

በምክር ቤቱ የሚወጡ የተለያዩ ህጎች፣ ደንቦች እና ረቂቆች እንዲሁም አዋጆች ለምክር ቤቱ ቀርበው ከመፅደቃቸው በፊት ማሻሻያ የሚያስፈልጋቸውን ጉዳዮች በመለየት በጠቅላይ ፍርድ ቤት ማቋቋሚያ አዋጅና በዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ሙያዊ አስተያየት እንዲሰጥባቸዉ ተደርጓል፡፡ እንዲሁም የክልሉ አስፈፃሚ አካላት ማቋቋሚያ አዋጅ ረቂቁን በአግባቡ በማስተካከልና የትርጉም ስራውንም ኢዲት በማድረግ የአመራሩን ጥቅማ ጥቅም መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 172/2002 ዓ.ም በማሻሻል ረቂቅ አዋጅን በማዘጋጀት እና የክልሉን የአስፈፃሚ አካላት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር **280/2014** ዓ.ም ረቂቁን በአግባቡ በማስተካከል ታትሞ ሥራ ላይ ውሏል፡፡

## በምክር ቤቱ የሚወጡ ህጐችን ተደራሽነት ማሻሻል

ምክር ቤቱ በተሰጠው ህግ የማውጣት ስልጣን መሰረት የ2014 በጀት ዓመት ለማጽደቅ እና የበጀት አስተዳደሩን ለመወሰን የወጣ አዋጅ በ5ኛው ዙር የምክር ቤት የስራ ዘመን በተደረገው ጉባኤ የወጡ አዋጆችን በአንድ ጥራዝ አጠቃሎ በማሳተም እና እስካሁን በአጣሪ ጉባኤ የታዩና በህገ-መንግስቱ ተርጓሚ የፀደቁ ውሳኔዎችን እንዲሰራጩ ተደርጓል፣ አፈፃፀሙም 100% ነው፡፡

በምክር ቤቱ የሚወጡ የድጋሜ ህትመት ፍላጎት በመለየት 100% ለማሳተምና ሥራ ላይ ለማዋል ታቅዶ በየደረጃው ላሉ ምክር ቤቶች እና ለሚመለከታቸው አስፈፃሚ አካላት ተደራሽ ለማድረግ በተያዘው ዕቅድ መሰረት ደንብ ቁጥር 12/2003 ዓ/ም በድጋሜ ህትመት በማሳተም ለምክር ቤቱ አባላት ተደራሽ ተደርጓል፣ አፈፃፀሙ 100% ነው፡፡

በምክር ቤቱ የሚወጡ አዋጆችን በተቋሙ ደረ-ገጽ ላይ በመጫን 100% ለተጠቃሚ ተደራሽ ለማድረግ ታቅዶ 79% ተደራሽ ተደርጓል፡፡ በአጠቃላይ የሚወጡ ህጐችን ተደራሽ በማድረግ በኩል የእቅዱን 73% ተግባራዊ ተደርጓል፡፡

## የክትትልና ቁጥጥር አሰራርን ማሳደግ

የህዝብና የመንግስት ሀብት በአግባቡ ለልማት ተግባር እየዋለ መሆኑንና የመንግስት አገልግሎት አሰጣጥ የተሳለጠ እንዲሆን የክልሉ ምክር ቤትና የቋሚ ኮሚቴዎች የጋራና የተናጠል እቅድ በማቀድ ለአስፈፃሚ አካላት በመስጠት የጋራ ውይይት ተካሂዷል፡፡ በመሆኑም በበጀት ዓመቱ የ1ኛ እና የ3ኛ ሩብ ዓመት ሪፖርትና እቅድ ተገምግመው ለቋሚ ኮሚቴው በማቅረብ የእቅዱን 100% ማከናወን ተችሏል፡፡

## የህዝብ ቅሬታና አቤቱታ ማስተናገድ

በበጀት ዓመቱ በምክር ቤቱ በቋሚ ኮሚቴዎች የሚቀርቡ አቤቱታዎችን በአግባቡ ተቀብሎ በማስተናገድና በመፍታት በኩል በተናጠል ሰላሳ አቤቱታዎች ቀርበው አስራ ስድስቱ (53.33%) መፍትሄ ያገኙ ሲሆን በተጨማሪ በቡድን ከመጡ አስራ አንድ አቤቱታዎች ደግሞ አስሩ (90.9%) የመፍትሄ ውሳኔ ማግኘት ችለዋል፡፡

## የምክር ቤቶችን የጉባኤ አፈፃፀም ማሻሻል

በህገ-መንግስቱ እንደተደነገገው የምክር ቤት ጉባኤ በክልል ምክር ቤት በዓመት ሁለት ጊዜ የብሔረሰብ አስተዳደር ምክር ቤት ሶስት ጊዜ በወረዳና በከተማ ምክር ቤቶች አራት ጊዜ በቀበሌ ደረጃ አስራሁለት ጊዜ ጉባኤ መካሄድ እንዳለበት ተቀምጧል፡፡ በመሆኑም በየደረጃው የሚገኙ ምክር ቤቶች ይህንን ተልዕኳቸውን ለመወጣት በየወቅቱ እየተገናኙ ጉባኤቸውን በየአካባቢያቸው ባሉ የልማት፣ የመልካም አስተዳደርና ወቅታዊ ጉዳዮችን አጀንዳ በማድረግ ጉባኤ የሚካሄድበትን ሁኔታ መፍጠር ችለዋል፡፡ ምክር ቤቶች የወከላቸውን የህዝብ ጥያቄ በማንሳት በእቅድና በሪፖርቱ ውይይት በማድረግ የሚወጡ አዋጆችን፣ ህጎችን፣ በጀትና ሹመቶችን ያፀድቃሉ፡፡ በዚህም ምክር ቤቱ 6ኛ ዙር 1ኛ ዓመት የስራ ዘመን 2ኛውን መደበኛ ጉባኤ የማስፈጸሚያ እቅድ በማዘጋጀት፣ ወንድ 162፣ ሴት 92 ድምር 254 ለማሳተፍ ታቅዶ ወንድ 72 ሴት 87 ድምር 159 የተሳተፉ ሲሆን አፈፃፀሙም 62.59% ነው፡፡

ምክር ቤቶች በህገ-መንግስቱ በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት መደበኛ ጉባኤቸውን ማካሄድ የግድ ይላል፡፡ በመሆኑም የሚመለከተው አካል ትኩረት ሰጥቶ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ምክር ቤት ያላቋቋሙ ከተማ አስተዳደሮችም ምክር ቤታቸውን እንዲያቋቁሙና በወቅቱ ጉባኤያቸውን እንዲያካሄዱ የድጋፍና የክትትል ስራ መስራት ተችሏል፡፡

በአጠቃላይ በበጀት ዓመቱ የምክር ቤቶችን የጉባኤ አፈፃፀም 72.67% ማድረስ ተችሏል፡፡




የምክርቤት ጉባኤ-ባህርዳር

## የመልካም አስተዳደር ችግሮችንና ሙስናን ማዳከም

ተቋሙ የመልካም አስተዳደር ችግርንና የኪራይ ሰብሳቢነት አስተሳሰብ እና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል በርካታ ተግባራትን አቅዶ በመንቀሳቀስ የአገልጋይነትን ስሜት ተላብሶ ደንበኞቹን በማርካት ብልሹ የሆኑ አሰራሮችን እንዳይፈፀሙ የመከላከል ስራ ሰርቷል፡፡

# ጠቅላይ ፍርድ ቤት

ፍርድ ቤቶች የተቋቋሙበት ዋነኛ ዓላማ የዳኝነት አገልግሎት አሰጣጣቸውን ቀልጣፋ፣ ተደራሽ፣ ውጤታማ፣ ነፃ እና ተጠያቂነት በሰፈነበት የህግ የበላይነትን ማስፈን ነው፡፡ ይህን መሰረታዊ አላማ ከግምት ውስጥ በማስገባትም በ2014 በጀት ዓመት እቅዱን በውጤታማነት ለመፈፀም በቅድመ ዝግጅት ምዕራፍ ተቋሙ የተቋቋመበትን ዓላማ በማሳካት በተደራጀ መንገድ ተግባራትን ለመፈፀም እና የፍትህ ተደራሽነቱን ለማስፋፋት በክልሉ የሚገኙ ፍርድ ቤቶች ለዜጎቻቸው ተሚጋችና ታአማኒነት ያለው ፍርድ መስጠት እንዲችሉ ተደርጓል፡፡

## የሰራተኞችን አቅም ማሳደግ

የዳኝነት ስራ ውጤታማ የሚሆነው የአስተዳደር ሰራተኞችን በአመለካከትና በክህሎት የተሻለ አቅም እንዲኖራቸው በማድረግ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር በየደረጃው ለሚገኙ የፍርድ ቤት

**የአብክመ የመንግስት ኮሙዩኒኬሽን ቢሮ**

ሰራተኞችን አቅም በመገንባት የተሟላ ቁመና ያለው የሰው ሃብት ለመገንባት የአፈፃፀም ግምገማና የእቅድ ትውውቅ በማድረግ ክህሎታቸውን ለማሳደግ ጥረት ተደርጓል፡፡ በመሆኑም በበጀት ዓመቱ የብሄር ግጭት በሚስተዋልባቸው የሰሜን ሸዋ ዞን እና የኦሮሞ ብሄረሰብ አስተዳደር ዞን በከፍተኛ ፍርድ ቤቶች የሚገኙ አጎራባች ወረዳዎች ላይ በሰብዓዊ መብት ድንጋጌዎችና ለተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎች በፍትህ አገልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ ወንድ 58፣ ሴት 12፣ ድምር 70 ለሚሆኑ ዳኞችና የጉባዔ ተሿሚዎች የአጭር ጊዜ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

የዳኞችና የጉባኤ ተሿሚዎችን የአቅም ክፍተቶችን በጥናት በመለየት በየደረጃው ለሚገኙ ፍርድ ቤቶች በጠቅላላው 25% ለሚሆኑ ዳኞችና የጉባኤ ተሿሚዎች አጫጭር ስልጠናዎችን ለመስጠት በእቅድ ተይዞ ወደ ተግባር የተገባ ሲሆን ወንድ ለ842 ለሴት 346 በድምሩ ለ**1,188** ለሆኑ ዳኞችና የጉባኤ ተሿሚዎችን ማሰልጠን ተችሏል፡፡ በዚህም በአዲስ ለተሾሙ የወረዳ ፍርድ ቤቶች የሸሪያ ዳኞችን አቅም ለመገንባት በተሰጠው የአጭር ጊዜ ስልጠና የሰለጠኑ የዳኞች ቁጥር ወንድ 13 ሴት 0 በድምሩ ለ13 ዳኞችን ማሰልጠን ተችሏል፡፡

በአጠቃላይ በበጀት አመቱ ወንድ 855 ሴት 346 በድምሩ **1,201 (53.02%)** ዳኞችና የጉባኤ ተሿሚዎንች በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ዙሪያ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡



**የሰራተኛ አቅም ግንባታ -እንጅባራ**

## ተዘዋዋሪ ችሎት

በጠቅላይ ፍርድ ቤት በዘጠኝ ተዘዋዋሪ ችሎት ጣቢያዎች 3,942 መዝገቦች ቀርበው 3,625 ጉዳዮች እልባት አግኝተዋል፡፡ በዚህም በከፍተኛ ፍርድ ቤቶች በ39 ተዛዋዋሪ የችሎት ጣቢያዎች 5,908 መዝገብ ቀርበው ለ3,626 መዛግብት ውሳኔ መስጠት የተቻለ ሲሆን በወረዳ ፍርድ ቤቶች ደግሞ በ480 ተዛዋዋሪ የችሎት ጣቢያዎች ላይ 11,971 መዛግብት ቀርበው 7,933 መዛግብቶች ውሳኔ ማግኘት ችለዋል፡፡

በአጠቃላይ በበጀት አመቱ በ528 ቀጠናዎች ላይ የተዘዋዋሪ ችሎት አገልግሎት በመስጠት 21,821 መዛግብት ቀርበው 15,184 መዛግብት ውሳኔ ያገኙ ሲሆን ከፆታ ስብጥር አንፃር ወንድ 52,080 ሴት 28,720 በድምሩ 80,800 ባለጉዳዮች ውሳኔ አግኝተዋል፡፡

## የመዛግብትን የማጣራት አቅም ማሳደግ

ፍርድ ቤቶች በበጀት ዓመቱ የፍርድ ቤቶችን የስራ አፈጻጸም ምዘና ስርአትን በመተግበር ተጨማሪ ዳኞችን በማሾም እና የዳኞችን ውሳኔ የመስጠት አቅም በማጐልበት የመዛግብትን የማጣራት አቅም ከፍ ለማድረግ እቅድ ተይዞ በተሰራው ስራ የመዛግብት የማጥራት አቅም አፈፃፀም ስናይ በሰበር ሰሚ ችሎት 11,105 መዛግብት በአዲስ ከተከፈቱና ከመዝገብ ቤት ከተንቀሳቀሱት መዛግብት በላይ ከአለፈው በጀት ዓመት የተላለፉ መዛግብትን ጨምሮ 13,048 መዛግብት እልባት ያገኙ ሲሆን አፈጻጸሙም 117.50% ነው፡፡ በጠቅላይ ፍርድ ቤት ደግሞ 8,742 በአዲስ ከተከፈቱና ከመዝገብ ቤት ከተንቀሳቀሱት መዛግብት በላይ ከአለፈው በጀት ዓመት የተላለፉ መዛግብትን ጨምሮ 9,359 መዛግብት ውሳኔ ያገኙ ሲሆን አፈጻጸሙን 107.06% ማድረስ ተችሏል፡፡ በዚህም የከፍተኛ ፍርድ ቤት አፈጻጸም 98.14% ሲሆን በወረዳ ፍርድ ቤት ደግሞ 99.95% ማድረስ ተችሏል፡፡



ዳኞች በስራ ላይ-ባህርዳር

## የፋይሎችን የመጨናነቅ መጠን መቀነስ

በየደረጃው በሚገኙ ፍርድ ቤቶች የአደረጃጀትና የአሰራር ስርዓትን አጠናክሮ በማስቀጠል የፋይሎችን የመጨናነቅ መጠን የተመዘገበውን ውጤት ስንመለከት የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት 1.25፣ የጠቅላይ ፍርድ ቤቱ 1.28፣ የከፍተኛ ፍርድ ቤቶች 1.26 ፣የወረዳ ፍርድ ቤቶች 1.06 መዛግብት የመጨናነቅ መጠን ያሳያል፡፡

## የመጽናት ምጣኔን ማሳደግ

ፍርድ ቤቶች የዳኞችን አቅም እና ክህሎት ለማሳደግ በተሰራው ስራ በይግባኝ ቀርበው የሚፀኑ መዝገቦች ቁጥር ከአመት አመት እየጨመረ መጥቷል፡፡ በዚህ መሰረት በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ታይቶ በፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት የመፅናት ምጣኔው አፈፃፀም 95.10%፣ በጠቅላይ ፍርድ ቤት ታይቶ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የመፅናት ምጣኔ 80.14%፣ በከፍተኛ ፍርድ ቤት ታይቶ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የመፅናት ምጣኔ 75.67%፣ በወረዳ ፍርድ ቤት ታይቶ በከፍተኛ ፍርድ ቤት የመፅናት ምጣኔው 64.20% መሆኑን በየደረጃው በሚገኙ ፍርድ ቤቶች በተመዘገበው መረጃ ማወቅ ተችሏል፡፡

## የመሻር ምጣኔን መቀነስ

ፍርድ ቤቶች የዳኞችን አቅምና ክህሎት ለማሳደግ የተለያዩ ሥልጠናዎችን በመስጠት ክህሎታቸውንና ስነ-ምግባራቸውን በማሳደግ እንዲሁም የፍርድ ምርመራውን አጠናክሮ በማስቀጠል በይግባኝ ቀርበው የሚሻሩ መዝገቦችን የውሳኔ ጥራት በማሻሻል በይግባኝ ቀርበው የሚሻሩ መዝገቦችን ቁጥር ከአመት አመት እንዲቀንሱ ተደርገዋል፡፡ በበጀት ዓመቱ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ታይቶ በፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት የመሻር ምጣኔው አፈጻጸም 1.40%፣ በጠቅላይ ፍርድ ቤት ታይቶ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የመሻር ምጣኔ 12.30%፣ በከፍተኛ ፍርድ ቤት ታይቶ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የመሻር ምጣኔ 16.06%፣ በወረዳ ፍርድ ቤት ታይቶ በከፍተኛ ፍርድ ቤት የመሻር ምጣኔው 23.62% ማድረስ ተችሏል፡፡

## የመሻሻል ምጣኔ

በየደረጃው የሚገኙ ፍርድቤቶች የዳኞችን አቅምና ክህሎት በማሳደግ የውሳኔ ጥራትን ለማሻሻል በተሰራው ስራ በይግባኝ ቀርበው የሚሻሻሉ መዝገቦችን ቁጥር ከአመት አመት የቀነሰ መሆኑን ማየት ተችሏል፡፡ በሌላ በኩል በየደረጃው ለሚገኙ ዳኞች የተለያዩ ሥልጠናዎችን በመስጠት ክህሎታቸውንና ስነ-ምግባራቸውን በማሳደግ እንዲሁም የፍርድ ምርመራውን ስራ አጠናክሮ በማስቀጠል በይግባኝ ቀርበው የሚሻሻሉ መዛግብት አፈፃፀም ሲታይ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት

ታይቶ በፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት የመሻሻል ምጣኔው 3.48%፣ በጠቅላይ ፍርድ ቤት ታይቶ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የመሻሻል ምጣኔ 7.54%፣ በከፍተኛ ፍርድ ቤት ታይቶ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የመሻሻል ምጣኔ 8.27%፣ በወረዳ ፍርድ ቤት ታይቶ በከፍተኛ ፍርድ ቤት የመሻሻል ምጣኔው 12.18% ማድረስ ተችሏል፡፡

## የተገልጋዩችን የአገልግሎት እርካታ ማሳደግ

የተገልጋዮችን የአገልግሎት አሰጣጥ እርካታ ከማሳካት አንፃር ሲታይ የተገልጋዮችን ወጭ የሚቀንሱ የአቤቱታ ማቅረቢያ ፎርማቶችን እንደየ ጉዳዮቹ አይነት በስፋት በማቅረብ በመረጃ ዴስክ በኩል አገልግሎት ያገኙ ወንድ 264,843 ሴት 215,289 ድምር 480,132 ባለጉዳዮ ናቸው፡፡በዚህም ባለጉዳዮች የአቤቱታ ማቅረቢያ ፎርማቶችን እንዲጠቀሙ በማድረግ በአማካኝ ብር 43,**322,643** ወጪ እንዲቀርላቸው ተደርጓል፡፡

## የሙያ ስነ-ምግባርን ማሻሻል

በበጀት ዓመቱ በድንገተኛ ደራሽ ፍርድ ምርመራ የቀረበውን 100% በመደበኛ ምርመራ 1.49% ለማድረስ እቅድ ተይዞ በድንገተኛ ደራሽ የቀረበው ወንጀል 118፣ በፍትሃብሄር 463 በድምሩ 581 መዛግብት የተመረመሩ ሲሆን በመደበኛ ፍርድ ምርመራ ደግሞ በወንጀል 2,486፣ በፍትሐብሔር 4,169 በድምሩ 6,655 መዛግብት ተመርምረዋል አፈጻጸሙም 1.21% ነው፡፡በመደበኛና በድንገተኛ የፍርድ ምርመራ በሚቀርቡ አቤቱታዎች የስነ-ምግባር ጉድለት በተገኘባቸው ጊዜ የተጠያቂነት ስርዓት በመዘርጋት እንቅስቃሴ የተደረገ ሲሆን በዚህም መሰረት በዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ጽ/ቤት ክስ የቀረበባቸው ወንድ 85 ሴት 8 ድምር 93 ሲሆኑ ውሳኔ የተሰጣቸው ወንድ 57 ሴት 6 ድምር 63 ውሳኔ ከተሰጣቸው 63ቱ መካከል የተቀጡት 55 ሲሆኑ ነጻ የወጡ 8 በክርክር ላይ ያሉ ደግሞ 30 ናቸው፡፡

## ለአካል ጉዳተኞች፣ ለህፃናትና ለአረጋውያን የተደረገ ድጋፍ

| ተ/ቁ | የፍ/ቤቱ ስም | ለአካል ጉዳተኞች | | | ለአረጋዊያን የተደረገ ልዩ ድጋፍ | | | ለሕጻናት የተደረገ ልዩ ድጋፍ | | | ሴቶች |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ | |
| 1 | ጠቅላይ ፍ/ቤት | 190 | 122 | 312 | 2,439 | 1,490 | 3,929 | 0 | 0 | 0 | 1,731 |
| 2 | ከ/ፍ/ ቤቶች | 181 | 75 | 256 | 671 | 334 | 1,005 | 2 | 17 | 19 | 1,009 |
| 3 | ወረዳ ፍ/ቤቶች | 2,292 | 1,643 | 3,935 | 8,725 | 7,050 | 15,775 | 4,578 | 5,933 | 10,511 | 22,199 |
| ድምር | | 2,663 | 1,840 | 4,503 | 11,835 | 8,874 | 20,709 | 4,580 | 5,950 | 10,530 | 24,939 |

## ፍትህ ቢሮ

የአብክመ ፍትህ ቢሮ በክልሉ ውስጥ በመካሄድ ላይ የሚገኘውን የሠላም፤የልማትና የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ እንዲጎለብትና ህገ-መንግስታዊ ስርአቱን በማስከበር የህግ የበላይነትን ያረጋግጣል፡፡ እንዲሁም የዜጎች ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች በማስከበር ረገድ ሰፊ ድርሻ ያለው ተቋም ነው፡፡ በተለይም በክልሉ እየተገነባ ያለው የፍትህ ስርአት ከሁሉም በላይ የዜጎችን ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ተጠብቀው የህግ የበላይነት የሰፈነበት በማድረግ በትኩረት እየሰራ ይገኛል፡፡

### ለዐቃቤ ህግ የቀረበ ቀጥታ ክስ

በበጀት ዓመቱ የዜጎችን መብት በመጠበቅና ወንጀለኞችን በማስቀጣት የሕግ የበላይነትን በማስከበር ከክልል እስከ ወረዳ ባሉ ልዩ ልዩ የሙስና ወንጀል ጉዳዮች ላይ ከአለፈው ዓመት የዞረና በአዲስ ክስ የተመሰረቱ 31,675 መዛግብት ለዐቃቢ ህግ ቀርበው 31,212 መዛግብት በዐቃቤ ሕግ ውሳኔ ማግኘት ችለዋል፣ አፈፃፀሙም 98.54% ነው፡፡

### የፍርድ ቤት ክርክር

በ2014 ዓ.ም ከክልል እስከ ወረዳ በልዩ ልዩ እና በሙስና ወንጀል ጉዳዮች በዐቃቢ ህግ 30,171 መዛግብት ለፍርድ ቤት ቀርበዋል፡፡ ከእነዚህ ውስጥ 17,262 መዛግብት ውጤት የሚለኩ ውሳኔዎች ተሰጥተዋል በ15,773 መዛግብት ላይ ጥፋተኛነት ውሳኔ የተሰጠ ሲሆን በ1,489 መዛግብት ላይ ደግሞ ተከሳሾች በነጻ ተሰናብተዋል፣ አፈፃፀሙ ሲታይ 91.37% ነው፡፡

በበጀት ዓመቱ በሙስና ወንጀል ከተመዘበረው የመንግስት እና የህዝብ ሀብት ውስጥ 32,205.27 ካሬ ሜትር ቦታና ዘጠኝ ቤቶችን ጨምሮ በሙስና የመዘበሩ ወንጀለኞችን ለህግ በማቅረብ ያለ አግባብ የነጠቁትን መሬት ለመንግስት ማስመለስ ተችሏል፡፡በጥሬ ገንዘብ 8,177,362.21 ብር ለመንግስት በውርስና በመቀጫ ገቢ ማድረግ ተችሏል፡፡

በሙስና ወንጀል ተከሰው ጥፋተኛ የተባሉ ወንድ 300 ሴት 55 ድምር 355 ሲሆኑ ጥፋተኛ ከተባሉት መካከል 66 የቀበሌ፣ 161 የወረዳ፣ 36 የዞን፣ 13 የክልልና ሌሎች 62 በድምሩ 307 ባለሙያዎች እንዲሁም 12 የቀበሌ፣ 21 የወረዳ፣ 5 የዞንና ሌሎች 10 በድምሩ 48 አመራሮች ሲሆኑ በጠቅላላ 355 ባለሙያዎችና አመራሮች የጥፋተኝነት ውሳኔ ተሰጧቸዋል፡፡

### የዐቃቤ ሕግ ይግባኝ

በበጀት ዓመቱ በተላለፉ እና አዲስ በቀረቡ በድምሩ 1,102 መዛግብት ቀርበዋል፡፡ ከዚህም ውስጥ በ430 መዛግብት ላይ ፍርድ ቤት ውጤትን የሚለኩ ውሣኔ ተሰጥቷቸዋል፡፡ ከቀረቡት መዛግብት መካከል በ373 መዛግብት ላይ ማሸነፍ ሲቻል በ57 መዛግብት ላይ ደግሞ

ተሽናፊነትን ያሳያል፡፡ እንዲሁም 307 መዛግብት በቀጠሮ የዞሩ ናቸው፡፡ የማሸነፍ ምጣኔ ሲታይ 86.74% ነው፡፡

## የፍርደኞች ይግባኝ

በበጀት ዓመቱ 2,883 የፍርደኞች ይግባኝ መዝገብ ቀርቦ በ1,847 መዛግብት ውሳኔ ያገኙ ሲሆን ከነዚህ መካከል በ1,521 መዛግብት አሸናፊ ሲሆኑ የማሸነፍ ምጣኔውን 82.35% ማድረስ ተችሏል፡፡

## የዐቃቢ ህግ ሠበር አቤቱታ

በበጀት ዓመቱ በተለያዩ ወንጀል የዐቃቢ ህግ ሰበር አቤቱታ ክርክር 210 መዛግብት የቀረቡ ሲሆን ከቀረቡ መዛግብት መካከል በ53 መዛግብት ላይ አሸናፊ መሆን ሲቻል አፈፃፀሙ 84.91 % ነው፡፡

## የፍርደኞች ሠበር አቤቱታ

በ2014 ዓ.ም በሙስና ወንጀል ሰበር አቤቱታ 819 መዛግብት ቀርበው 527 መዛግብት ውሳኔ ያገኙ ሲሆን ከነዚህ መካከል በ442 መዛግብት ላይ አሸናፊ መሆን ተችሏል፣አፈፃፀሙ 83.87% ነው፡፡

## የእጅ ከፍንጅ ወንጀል

በበጀት ዓመቱ በዞንና በወረዳ 1,175 የእጅ ከፍንጅ ወንጀል ቀርቦ 1,122 መዛግብት ውሳኔ ያገኙ ሲሆን 53ቱ  መዛግብት ደግሞ በቀጠሮ የተላለፉ ናቸው፤ አፈፃፀም 95% ነው፡፡

## ያለ እድሜ ጋብቻ

በ2014 ዓ.ም በተለያዩ ወረዳዎች 3,305 ያለ እድሜ ጋብቻ ጉዳዮች ቀርበው ጋብቻቸው የተፈቀደላቸው 1,309 ሲሆኑ በምክር እንዲቋረጥ የተደረጉት ደግሞ 1,361 ናቸው፡፡ህግን ተላልፈው ጋብቻ በመፈፀማቸው ምክንያት ክስ የተመሰረተባቸው 184፣ በፍርድ የተቀጡ 29፣ ነፃ የወጡ 1፣ ለጊዜው የተቋረጡ 126 እና በክርክር ላይ ያሉ 29 ናቸው፡፡



የህፃናት ጋብቻ ለማስቀረት በተሰሩ ስራዎች ዙሪያ ውይይት ሲካሄድ-

## ከፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቢ ህግ በውክልና የተሰጡ የወንጀል ጉዳዮች

በ2014 በጀት ዓመት በተለያዩ የሙስና ወንጀል ጉዳዮች በክልልና በዞን ደረጃ 944 መዛግብት ለዐቃቤ ህግ ቀርቦ 907 መዛግብት ውሣኔ ያገኙ ሲሆን የማጥራት ምጣኔ 96.08% ሆኗል፡፡

## በፍርድ ቤት የቀረቡ ጉዳዮች

በበጀት ዓመቱ በልዩ ልዩ የሙስና ወንጀል ጉዳዮች በክልልና በዞን 643 መዝገብ ቀርበው በ240 መዛግብት ውሳኔ የተሰጠ ሲሆን በ208 መዛግብት ጥፋተኛ የሆኑ 32 መዝገብ በነፃ በማሰናበት የማስቀጣት አቅም ሲታይ 86.67% ነው፡፡

## ለዐቃቤ ህግ የቀረቡ የተለያዩ ወንጀሎች

በ2014 በጀት ዓ.ም ለዐቃቢ ህግ በቀጥታ ክስ 300 መዛግብት ቀርቦ በ275 መዛግብት ውሳኔ ያገኙ ሲሆን በዐቃቢ ህግ በምርመራ ላይ የሚገኙት መዛግብት ደግሞ 25 ናቸው፤የማጥራት ምጣኔ 91.67% ነው፡፡

## ለፍርድ ቤት የቀረቡ መዛግብት

በበጀት ዓመቱ በቀጥታ ክስ 137 መዛግብት ለፍርድ ቤቱ ቀርበው 36 መዛግብት ውሳኔ ማግኘት ችለዋል፡፡ ከእነዚህ መካከል 30ዎቹ መዛግብት የአሸናፊነት ውሳኔ ሲያገኙ  አፈፃፀሙ 83.3% ደርሷል፡፡

**የአብክመ የመንግስት ኮሙዩኒኬሽን ቢሮ**

## ይግባኝ

በበጀት ዓመቱ በጠቅላይ አቃቢ ህግ 470 መዛግብት በይግባኝ ቀርው በ163 መዛግብት ላይ በፍርድ ቤቱ ውሣኔ ተሰጥቶባቸዋል፡፡ ከነዚህም መዛግብት መካከል 148ቱ መዛግብት ላይ አሸናፊ መሆን ተችሏል፡፡ በ200 መዛግብት ደግሞ በቀጠሮ የዞሩ ሲሆን የአሸናፊነት ውሳኔ በማስወሰን የማስቀጣት ምጣኔውን 90.8% ማድረስ ተችሏል፡፡ የፍርደኛ ይግባኝን በተመለከተ በጠቅላይ አቃቢ ህግና በዞኖች ደረጃ በልዩ ልዩ በኢኮኖሚ ነክ እና በሙስና ወንጀል የቀረቡ 1,112 መዛግብት ሲሆኑ ከእነዚህ ውስጥ 640 መዛግብት ላይ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡ በ504 መዛግብት ላይ ደግሞ የአሸናፊነት ውሳኔ ተወስኗል፡፡ የማሸነፍና የማስቀጣት ምጣኔው ሲታይ 78.75% ነው፡፡

## አቤቱታና ዋስትናን በተመለከተ

ከጠቅላይ አቃቢ ህግ እስከ ንዑስ ወረዳ አቃቢ ህግ ጽ/ቤቶች ባሉ አደረጃጀቶች 240 ልዩ ልዩ አቤቱታዎች የቀረቡ ሲሆን 182 ውሳኔ ያገኙ፣30 ትዕዛዝ የተሰጠበት፣28 በቀጠሮ ያለ እና 16 በትዕዛዙ መሰረት ፍፃሜ ያገኙ ሲሆን 14ቱ ደግሞ ተፈፃሚነትን የሚጠብቁ ናቸው፡፡በተመሳሳይ 152 የዋስትና ጥያቄዎች ቀርበው 134ቱ ውሳኔ ያገኙ ሲሆን 6 ትዕዛዝ የተሰጠበት እና 12 በቀጠሮ ላይ ያሉ ናቸው፡፡ 6 በትዕዛዙ መሰረት ፍፃሜ ያገኙ ሲሆን 5 መዛግብት ደግሞ ተፈፃሚነት የሚጠብቁ ናቸው፡፡

## ለፍርድ ቤት የቀረቡ መዛግብት

በበጀት ዓመቱ በፍርድ ቤቱ 98 መዛግብት ቀርበው 36 መዛግብት ውሳኔ ያገኙ ሲሆን ውሳኔ ካገኙት መካከል 31 መዛግብት የአሸናፊነት ውሳኔ ማግኘት ችለዋል፤ አፈፃፀሙ ሲታይ 86.11% ነው፡፡

## የፍርደኛ ሰበር አቤቱታ

በበጀት ዓመቱ በሙስና ወንጀል ሰበር አቤቱታ 72 መዛግብት የቀረቡ ሲሆን ከእነዚህ ውስጥ በ43 መዛግብት ላይ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡ 39 መዛግብት ላይ ደግሞ አሸናፊነትን ያስመዘገቡ ናቸው፡፡ በዚህም የማሸነፍና የማስቀጣት ምጣኔው 90.69% ደርሷል፡፡

## አቤቱታና ዋስትና

በበጀት አመቱ ከጠቅላይ አቃቢ ህግ እስከ ንዑስ ወረዳ አቃቢ ህግ ባሉ ጽ/ቤቶችና አደረጃጀቶች 144 ልዩ ልዩ አቤቱታዎች ቀርበው 144 መዛግብት ውሳኔ አግኝተዋል፡፡ በዋስትና አሰጣጥ ዙሪያ በዐቃቢ ህግ የተያዙ 116 መዛግብት ላይ አስተያየት እንዲሰጥባቸው በማድረግ 116 መዛግብት ውሳኔ እንዲያገኙ ማድረግ ተችሏል፡፡

**የአብክመ የመንግስት ኮሙዩኒኬሽን ቢሮ**

## የመዛግብት የማጥራት አቅም

በ2014 ዓ.ም የነፃ የህግ ድጋፍ ያገኙና እንዲሁም በቀጥታ ከሣሽነትና፣ በተከሣሽ መልስ ሰጭነት፣ በይግባኝ ሰበር አቅራቢነት፣ በይግባኝ ወይም በሰበር መልስ ሰጭነት የቀረበ የመዛግብት ብዛት 534 ሲሆን የያዙት የገንዘብ መጠን ብር 337,524,824.0 ሲሆን ከእነዚህ ውስጥ ውሳኔ ያገኙት መዛግብት ብዛት 534 ሲሆኑ የያዙት የገንዘብ መጠን ደግሞ በብር ሲተመን 337,524,824.0 ነው፤ አፈፃፀሙም በመዝገብ 100.0%፣ በገንዘብ 100.00% ሲሆን የመዝገብ የማጥራት አቅምን 100% ማድረስ ተችሏል፡፡

## የህግ ክርክር ድጋፍ ያገኙ የህብረተሰብ ክፍሎች

| ተ.ቁ | የድጋፍ አገልግሎት ያገኙ የህብረተሰብ ክፍሎች | ብዛት | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ወንድ | ሴት | ድምር |
| 1 | አረጋውያን | 334 | 222 | 556 |
| 2 | ህፃን | 739 | 357 | 1,096 |
| 3 | ወጣቶች | 512 | 152 | 664 |
| 4 | ጎልማሶች | 83 | 330 | 413 |
| 5 | አካል ጉዳተኞች | 1,282 | 122 | 1,404 |
| 6 | ኤች.አይ.ቪ ህሙማን | 20 | 28 | 48 |
| 7 | የወንጀል ሰለባ የሆኑ | 29 | 31 | 60 |
| 8 | የድሃ ድሃ | 0 | 464 | 464 |
| ጠቅላላ ድምር | | 2999 | 1706 | 4705 |

## የአገልግሎት አሰጣጥን ማሻሻል

በበጀት ዓመቱ የፍትህ አገልግሎት አሰጣጡን ቀልጣፋና ውጤታማ ከማድረግ አንጻር የሚነሱ ጥያቄዎችን በመፍታት ተቋሙ ከአገልግሎት አሰጣጡ ጋር በተያያዘ ባደረገዉ የዳሰሳ ጥናት የተለያዩ የአገልግሎት አሰጣጥና የመልካም አስተዳደር ችግሮችን መሠረት ያደረጉ የማስተካከያ ስልጠናዎችን በመስጠት በተገልጋዮች ላይ ይነሱ የነበሩ ቅሬታዎችን መቀነስ ተችሏል፡፡

### የአቤቱታ አቀባበልና የመስተንግዶ ሥርዓትን ማሻሻል

ተቋሙ ከክልል እስከ ወረዳ ባሉ የዐቃቤ ህግ መስሪያ ቤቶች ውስጥ ከሚሰጣቸው አገልግሎቶች ጋር በተያያዘ 23,379 መዛግብት ለአቤቱታ ቀርበው 22,811 መዛግብት ውሳኔ አግኝተዋል፣ አፈፃፀሙም 97.57% ነው፡፡ በተመሳሳይ 23,726 መዛግብት የዋስትና ጥያቄዎች ቀርበው 23,378 መዛግብት ውሳኔ ያገኙ ሲሆን አፈፃፀሙ 98.53% ነው፡፡

### የሕዝብና  የመንግሥትን ጥቅም ማስጠበቅ

ከጠቅላይ ዐቃቤ ህግ እስከ ወረዳ ነፃ የሕግ ድጋፍ ለሚሹ አካላት ብር 5,901,321,446.00 ወጪ ሊያስወጡ የሚችሉ 10,778 መዛግብት ላይ ነፃ የህግ አገልግሎት ተሰጥቷል፡፡ ከቀረቡት መዛግብት መካከል 5,720 መዛግብት የገንዘብ መጠን ብር 1,105,722,517.00 ማሸነፍ ተችሏል፡፡ በሌሎች መዛግብት ደግሞ ልዩ ልዩ ውሳኔ የተሰጣቸው ሲሆን በፍርድ ቤቱ ክርክር የማሸነፍ ምጣኔው 91.0% ነው፡፡

## የመንግሥት  ኮሙዩኒኬሽን ቢሮ

የመንግሥት  ኮሙዩኒኬሽን ጉዳዮች ቢሮ የክልሉን መንግሥትና የተቋሙን የልማትና የመልካም አስተዳደር ዕቅድ መነሻ በማድረግ  የሰላም፣ የልማትና የመልካም አስተዳደር ተግባራትን በላቀ የአስተሳሰብ ከፍታ እንዲመራ በማድረግ  በዋና  ዋና ክልላዊና አገራዊ ጉዳዮች መግባባት ለመፍጠር እንዲሁም የክልሉን ሁለንተናዊ ገፅታ ለመገንባት የተቋቋመና በዋናነት ይህንኑ ሃላፊነት ለመወጣት እየሰራ የሚገኝ ተቋም ነው፡፡

### አቅም ግንባታ

በበጀት አመቱ በክልል ቢሮ ደረጃ ሁለት ጊዜ አጫጭር ስልጠናዎችን ለመስጠት እቅድ ተይዞ በሚያዝያ ወር ለዞን፣ ወረዳና ሪጅዮፖሊታንት ከተማ አስተዳደር ኮሙዩኒኬሽን ኃላፊዎች በኮሙዩኒኬሽን ጽንሰ ሃሳብ ዙሪያ የአቅም ግንባታ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡ በዚህ የስልጠና መድረክ ወንድ 140 ሴት 32 ድምር 172 ተሣታፊ ሆነዋል፡፡ በተጨማሪም ሰራተኛው በአጫጭር የግንዛቤ መድረኮች ከሌሎች ተቋማት ጋር በመቀናጀት ግንዛቤ እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ በተመሳሳይ በወቅታዊ የኮሙዩኒኬሽን ስራና በህልውና ዘመቻ ዙሪያ ሁሉም የክልል ቢሮ የኮሙኒኬሽን ሰራተኞች በተገኙበት ለግማሽ ቀን ግንዛቤ እንዲያገኝ ተደርጓል፡፡

በዞንና በከተማ አስተዳደር ደረጃ  400 ያህል ስልጠና መድረኮችን ለማመቻቸት ታቅዶ 399 የስልጠና መድረኮችን በማካሄድ 99% መፈጸም የተቻለ ሲሆን በስልጠናው ወንድ 1,661 ሴት 1,442 በድምሩ 3,103 ሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች ወንድ 1,816 ሴት 595 በድምሩ 2,411 ያህል ባለሙያ በስልጠናው ይሳተፋል ተብሎ ታቅዶ ወንድ 816 ሴት 577 በድምሩ 1,393

ሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች ወንድ 1,664 ሴት 817 በድምሩ 2,481 ባለሙያዎች በምርጥ ተሞክሮ አቀማመር፣ በህዝብ ግንኙነት ተግባርና ሃላፊነት ዙሪያ፣ በሚዲያ ጥቆማ አዘገጃጀት፣ የዜና አሰራር ምንነትና አይነቶች፣ ቲዩተር አካውንት፣ በወቅታዊ ጉዳይ የህዝብ ግንኙነት ፅንሰ ሃሳብ፣ የህዝብ ግንኙነት ሙያተኞች ሊያከብሯቸው የሚገቡ መርሆዎችና መመሪያዎች፣ በኮምፒውተር አጠቃቀም፣ ስለ ሚኒሚዲያ አጠቃቀምና አያያዝ፣ በኤች አይ ቪ መዘናጋት ዙሪያ፣ የቴሌግራም ምንነት፣ አስፈላጊነትና አጠቃቀምን አስመልክቶ፣ በሴቶች ላይ የሚደርስን ጥቃት እንዴት እንከላከል፣ የአቋም መግለጫ አዘገጃጀት፣ የፓናል ውይይት ምንነት፣ የዕቅድ አዘገጃጀትና አተገባበር፣ በማህበራዊ ሚዲያ ምንነት፣ የቀውስ ጊዜ ኮሙዩኒኬሽን፣ የህዝብ አስተያየት አሰባሰብ፣ የመረጃ ምንነት፣ የጋዜጠኝነት ሙያ፣ የዜና ምንነትና ባህሪያት ወዘተ ... ዙሪያ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡ በአጠቃላይ የአቅም ግንባታ እቅድ ወንድ- 3,477 ሴት- 2,037 በድምሩ- 5,514 ሲሆን ክንውን ወንድ- 2,480 ሴት-,1,394 በድምሩ- 3,874 ነው፤ የሴቶች ተሳትፎም 57% ሆኗል፡፡

## የኮሙዩኒኬሽን፣ የሚዲያና የሴክተር ሕዝብ ግንኙነቶች ፎረም

በ2014 ዓ.ም በክልሉ ኮሙዩኒኬሽን ቢሮ አስተባባሪነት በዕቅድ የሚመሩ አራት ዋና ዋና የኮሙዩኒኬሽንና የሚዲያ አመራር ፎረም፣ የሚዲያ ቴክኒክ ፎረም፣ የሴክተር ሕዝብ ግንኙነት ፎረም እና የአማተር የኪነ ጥበባት ዘርፍ ሙያተኞች ፎረም ሲሆኑ ፎረሞችም ወቅታዊ መረጃ ወደ ኅብረተሰቡ መድረሱን እና አጠቃላይ የተግባራትን ክንውን በመገምገም እያጋጠሙ ያሉ ችግሮችን፣ መፍትሄዎችንና የቀጣይ ትኩረት አቅጣጫዎችን እያስቀመጡ የኮሙኒኬተሩን አቅም ለመገንባት የሚያስችሉ ስራዎች ሰርተዋል፡፡

## የሚዲያና የኮሙዩኒኬሽን አመራሮች ፎረም

በ2014 ዓ.ም የሚዲያና የኮሙዩኒኬሽን ፎረም የህልውና ዘመቻውን በተመለከተ እንደ ክልል የአማካሪ ቡድን ተቋቁሞ በተደራጀ ሁኔታ እየተገመገመ በልዩ ሁኔታ የተመራ ሲሆን ከእቅድ በላይ በየቀኑ እየተገናኘ ለ3 ወራት መምራት ተችሏል፡፡

## የሚዲያ ቴክኒክ ፎረም

በበጀት አመቱ የሚዲያ ቴክኒክ ፎረም የዜና፣ የፕሮግራሞችንና የዶክመንተሪ ሥራዎችን አፈጻጸም 12 ጊዜ ተገናኝቶ በመወያየት ለመገምገም አቅዶ 11 ጊዜ በመወያየት የእቅዱን 92% መፈጸም ችሏል፡፡ በፎረሙ የተሳተፉ ወንድ -9 ሴት- 3 ድምር 12 ሲሆን የሴቶች ተሳትፎ 33% ነው፡፡

**የአብክመ የመንግስት ኮሙዩኒኬሽን ቢሮ**

## የሴክተር ህዝብ ግንኙነት ፎረም፡-

በበጀት አመቱ የሴክተር ህዝብ ግንኙነት ፎረም አራት ጊዜ ተገናኝቶ ለመወያየት አቅዶ በወቅታዊ ጉዳይ፣ በተፈናቃዮች ዙሪያ የመረጃ አሰጣጥና በተደረገ ድጋፍ፣ በሚዲያና የኮሙኒኬሽን ሚና እና በዲያስፖራ አቀባበል ዙሪያ አምስት ጊዜ በመወያየት አፈፃፀሙን ከ100% በላይ ማድረስ ችሏል፡፡ በዚህም ወንድ 118 ሴት 79 ድምር 197 የተሳተፉ ሲሆን የሴቶች ተሳትፎ 40% ነው፡፡

## የአማተር የኪነ-ጥበባት ዘርፍ ሙያተኞች ፎረም

በ2014 ዓ.ም በዞንና በከተማ አስተዳደር ደረጃ 744 ፎረሞችን ለማካሄድ ታቅዶ በወሳኝ ኩነት አመዘጋገብ፣በማህበረሰብ አቀፍ የጤና መድህን፣ በአገልግሎት አሰጣጥና በሰዓት አከባበር፣ በህልውና ዘመቻው የሃብት አሰባሰብ፣ የጋራ ስራ አፈፃፀም እንቅስቃሴ፣ በ2013 ዓመታዊ ስራ አፈፃፀምና በ2014 በጀት ዓመት እቅድ ዙሪያ፣ ጁንታው በክልላችን ላይ እያደረሰው ባለው ጉዳት፣ በመረጃ አያያዝና ማህበራዊ ሚዲያ አጠቃቀም፣ በየተቋማቱ እየተሰራ ያለው ስራ እና ወደፊት መደረግ በሚገባቸው ጉዳዮች፣ በህዝብ ግንኙነት ስራዎች ዙሪያ፣ በማህበራዊ ሚዲያ አጠቃቀም፣ የኮሮና ቫይረስን በመከላከል፣ የቀጣይ የትኩረት አቅጣጫዎች፣ የሚዲያ ሽፋን አቀራረብ፣ በ90 ቀን ዕቅድ አፈፃፀምና በሌሎች ወቅታዊ ጉዳዮች፣ በወሳኝ ኩነት፣ በሙያ ስነ ምግባርና በኮሙዩኒኬሽን ፎረም ዙሪያ 494 ፎረሞች በማከሄድ አፈፃፀሙን 66% ማድረስ ችሏል፡፡

## የደንበኛ የመረጃ ፍላጎት ጥናት

በበጀት አመቱ ደንበኞች የሚፈላጓቸውን መረጃዎች ሰብስቦ ለማደራጀት እንዲቻል 192 የደንበኛ መረጃ ፍላጎት ጥናቶችን ለማካሄድ ታቅዶ 154 ጥናቶችን በማካሄድ አፈፃፀሙን 80% ማድረስ ተችሏል፡፡

## የአካባቢ ሚዲያ

| ተ.ቁ | ዝርዝር ተግባር | እቅድ | ክንውን | አፈፃፀም % |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ሚኒ ሚዲያ ማስፋፋት | 30 | 18 | 60 |
| 2 | አዲስ ማስታወቂያ ሰሌዳ ማስፋፋት | 80 | 61 | 76 |
| 3 | አዲስ ቲቪ ፖርክ ማቋቋም | 18 | 14 | 78 |
| 4 | አዲስ መረጃ ማዕከል ማቋቋም | 60 | 44 | 73.3 |

**የአብክመ የመንግስት ኮሙዩኒኬሽን ቢሮ**

## የሙያ ምዝገባ ፈቃድና እድሣት

የኢንፎርሜሽንና የሚዲያ ዘርፉን ለማሳደግ ይቻል ዘንድ የኮሙዩኒኬሽን ግለሰቦችና ድርጅቶች በሚዲያው ዘርፍ አቅማቸው እንዲጠናከርና እንዲጎለብት ተቋሙ ድጋፍ ይሰጣል፡፡ በመሆኑም የማስታወቂያና የፕሮሞሽን የምስክር ወረቀት ለማውጣት የሚመጡ ግለሠቦችና ድርጅቶች በክልል ደረጃ የሙያ የምስክር ወረቀት ለማውጣት የሚያስፈልጉ መስፈርቶችን ላሟሉ ስምንት ደንበኞች የሙያ ምዝገባ ፈቃድና እድሣት ተሰጧል፡፡

## የአቋም መግለጫ ማዘጋጀት

በበጀት ዓመቱ የተለያዩ ወቅታዊ ጉዳያዮች ሲኖሩ እንደ ክልል 167 የአቋም መግለጫ ለማዘጋጀት ታቅዶ 130 መግለጫዎችን በማዘጋጀት አፈፃፀሙም 77.8% ደርሷል፡፡

## የፓናል ውይይት ማካሄድ

በበጀት ዓመቱ መንግስት ባስቀመጠው አቅጣጫ መሰረት በአማራ ክልል በወራሪው የትህነግ ቡድን ምክንያት ከቀያቸው ከተፈናቀሉት የህብረተሰብ ክፍሎች ጋር ውይይት በማድረግ የአሸባሪውን ቡድን ለማስወገድ የወጣቱ ሚና ምን መሆን አለበት በሚል ውይይት ተደርጓል፡፡ በመሆኑም በልዩ ልዩ አገራዊ፣ ክልላዊና አካባቢያዊ ጉዳዮች ዙሪያ ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገቡ የፓናል ውይይቶች የተካሄዱ ሲሆን በክልል ቢሮ ደረጃ አራት ታቅዶ ሁለት የፓናል ውይይት በማካሄድ አፈፃፀሙን 50% ማድረስ ተችሏል፡፡

## የመረጃ አቅርቦትና ጥራት

በክልሉ 2,220 የመረጃ መልዕክት ለመቅረፅ ታቅዶ 2,519 ማከናወን ተችሏል፣ አፈፃፀሙም 100% በላይ ነው፡፡ ከዚህ ውስጥ በቢሮ ደረጃ 16 መልዕክቶችን ለጋራ መግባባት ሥራ ለማዘጋጀት ታቅዶ 25 በማከናወን አፈፃፀሙን 100% ማድረስ ተችሏል፡፡

## የሚዲያ ጥቆማ ዘገባ

በክልል ደረጃ 2,232 የሚዲያ ጥቆማ ለማከናወን ታቅዶ 3,444 ጥቆማ በማድረግ የእቅዱን ከ100% በላይ መፈጸም ተችሏል፡፡ እንዲሁም በክልል ቢሮ ደረጃ በተለያዩ ወቅታዊ ጉዳዮች ለሁሉም ሚዲያዎች 32 የሚዲያ ጥቆማ በመስጠት እንዲዘግቡ በማድረግ ክንውኑ 80 አፈፃፀም ከ100% በላይ ሆኗል፡፡

## ሳምንታዊ መረጃ መሰብሰብ

የክልሉን የእለት ከእለት እንቅስቃሴ ለማወቅ በተቋሙ በየሣምንቱ በዞንና ከተማ አስተዳደሮች 52 ሣምንታዊ መረጃ ልውውጥ ለማድረግ ታቅዶ ክንውን 52 ሲሆን አፈፃፀሙም 100% ነው፡፡

**የአብክመ የመንግስት ኮሙዩኒኬሽን ቢሮ**

## መረጃ መሰብሰብ፣ ማደራጀት፣ መተንተን እና ማሰራጨት

| ተ.ቁ | ዝርዝር ተግባራት | እቅድ | ክንውን | አፈፃፀም |
|---|---|---|---|---|
| 1 | መረጃ መሰብሰብ | 132,613 | 118,420 | 89% |
| 2 | መረጃ ማደራጀት | 132,613 | 118,420 | 89% |
| 3 | መረጃ ማሰራጨት | 20,402 | 23,616 | 100%+ |
| 4 | ወቅታዊ መረጃ መተንተን | 728 | 650 | 89% |



የኮሙዩኒኬሽን ቢሮ መረጃ ማዕከል

## ማህበራዊ ሚዲያ አጠቃቀም

በክልል ደረጃ ሶሻል ሚዲያውን መሰረት በማድረግ የጋራ መግባባትና የገፅታ ግንባታ ስራን መስራት እንደ ኮሙዩኒኬሽን ዋነኛ ተግባር ነው፡፡ በመሆኑም በበጀት ዓመቱ በፌስቡክ፣ በዩቲውብ፣ በትዊተር፣ በጽሁፍና ምስል ዜናዎች መረጃዎችን ማሰራጨት ተችሏል፡፡

**የአብክመ የመንግስት ኮሙዩኒኬሽን ቢሮ**

## በማህበራዊ ሚዲያ ገፆች ላይ የተሰራጩ መረጃዎች አፈፃፀም፣

| ተ.ቁ | የተከናወኑ ተግባራት | እቅድ | ክንውን | አፈፃፀም በ% |
|---|---|---|---|---|
| 1 | በፌስቡክ መረጃዎችን መጫን | 288 | 577 | 100+ |
| 2 | በዩቲውብ መረጃዎችን መጫን | 72 | 19 | 26 |
| 3 | በትዊተር መረጃዎችን መጫን | 240 | 251 | 100+ |
| 4 | የጽሁፍ ዜናዎችን ማሰራጨት | 192 | 100% | 52% |
| 5 | የምስል ዜናዎችን ማዘጋጀት | 96 | 33 | 34% |

## የሚዲያ ዳሰሳ

በበጀት ዓመቱ ክልላችን አስመልክቶ በህትመትና በኤሌክትሮኒክስ ሚዲያ፣ በመንግስት እና በግል ሚዲያዎች ውስጥ የተዘገቡ መረጃዎች ከማህበራዊ ጉዳዮች ጋር በተያያዘ 644፣ በኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች 606፣ በፖለቲካዊ ጉዳዮች 1,976 ዘገባዎች ተዳሰዋል፡፡ በእነዚህም በአዎንታ 2,326፣ በአሉታ 900 የተዘገቡ ሲሆን በድምሩ 3,226 ዘገባዎች የተዘገበ ሲሆን የተጨመቀውን የሚዲያ ዳሰሳ ለበላይ አካል ማቅረብ ተችሏል፡፡

## መደበኛ የህዝብ አስተያየት

ህብረተሰቡ የሚያነሳቸውን የተለያዩ ጥያቄዎች በተደራጀ ሁኔታ መረጃዎችን በመሰብሰብ የህዝብ አስተያየት ለማጥናት 1,254 መደበኛ የሆነ የህዝብ አስተያየት ጥናት ለማካሄድ ታቅዶ 1,033 በማከናወን አፈፃፀሙን 82% ማድረስ ተችሏል፡፡ የተጠናውን ጥናት መሰረት ያደረጉ የህዝብ አስተያየቶችን ለሚመለከተው የመንግስት አካላት ማቅረብ ተችሏል፡፡

## ወቅታዊ የህዝብ አስተያየት ጥናት

ህብረተሰቡ በተለያየ ጊዜ በማህበራዊ፣ በኢኮኖሚና ፖለቲካዊ አጀንዳዎች ሲኖሩ የሚያነሷቸውን ወቅታዊ የህዝብ አስተያየት ጥናት ለማካሄድ እቅድ 16 ክንውን 16 አፈፃፀሙ 100% ማድረስ የተቻለ ሲሆን የተጠናውን ወቅታዊ የህዝብ አስተያየት ለሚመለከታቸው የመንግስት አመራሮች ማቅረብ ተችሏል፡፡

**የአብክመ የመንግስት ኮሙዩኒኬሽን ቢሮ**

## ሥነ- ምግባር እና ፀረ-ሙስና

የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ሙስና እና ብልሹ አሰራር የክልላች ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ እድገት የሚገታ ተግባር መሆኑን በመገንዘብ የህግ ስርዓት በመዘርጋት ሙስና እና ብልሹ አሰራርን ለማስወገድ ብርቱ ትግል በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡

### የፊት ለፊት ትምህርት እና ስልጠና

